# እንኳን ደህና መጡ!!

# ወደ ብሔረ መፃሕፍት ዘ-ኢትዮጵያ

# @ETHIO_PDF_BOOKS

አዳዲስ መፅሐፍትን በ
የሚያገኙበት ምርጥ የቴሌግራም ቻናል ነው።

እናም ቤተሰብ ካልሆኑ ቤተሰብ ይሁኑ! ብዙ መፅሐፍት
እየመለጠ ነው ይፍጠኑ!





Scanned with CamScanner

# በራስ መተማመን



ዴል ካርኔጊ

ትርጉም: ዳዊት መላኩ

Scanned with CamScanner

# በራስ መተማመን

## How to Develop Self-Confidence & Influence People by Public Speaking

በጊዜ የተፈተኑ ሰዎችን የማግባቢያና የማሳመኛ መንገዶችን «ሰዎች ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ጓደኛ ማፍራት» በሚል ርዕስ ደርሶ በርካታ ቅጂዎች ከተሸጡላቸው መፅሐፎች ተርታ እንዲመደብ ካስቻለው ዝነኛው ዴል ካርኒጌ የቀረበ።።

# ማስታወሻነቱ

- አቶ መላኩ ወ/ማርያም:- በሀገንነት እድሜያችን የማንበብ ፍቅርና ፍላጎ በውስጣችን እንዲሰርፅ ላደረገው::
- ለሚካኤል መላኩ፣ እስክንድር መላኩ፣ ተፈራ ፈጣ፣ አክሊል ፍሰሃ፣ ታከለ ወርቁ፣ ደረጀ ተሰማ:- በተለያዩ ሃሳቦች ዙሪያ በሚያደርጓቸው አሉታዊና ምክንያታዊ ውይይቶችና ክርክሮቻቸው ከእለት እለት ለማንበብና ለማወቅ ጥረት እንዳደርግ ለረዱኝ::
- ለአብዱልሐሊቅ ረሺድ:- ንግግር ሲያደርግ የአድማጮቹን ትኩረት ጠቅልሉ የሚወስድ፣ ይዞም የፈለገውን ያህል ማቆየት ሚችል፣ እንዲሁም ሃሳቡን ሊረሱ በማይችሉ ንግግሮች የማስተላለፍና የማሳመን ከፍተኛ የንግግር ችሎታ ላለው
- ለሐይሌ ታረቀኝ:- ሲናገር ማንም ሰው በምቾትና በመደሳደል እንዲያዳምጠው በሚያስገድዱ ቃላቶቹና አረፍተ ነገሮቹ የሚያቀርበው ጠርዝ ያለው ንግግር አራቱንም ዋነኛ የንግግር ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችል ማራኪ የንግግር ችሎታ እንዳለው ለሚያሳዩት
- ለመሣይ ሽመና:- ፈጣኑ አእምሮው በሚያመነጨው ሃሳብና ከመላ አንደበቱ በሚወጡት ቃላቶች መካከል ያለው ተግባቦት (synchronization) አሳማኝና ተፅዕኖ ፈጣሪ የንግግር ችሎታ ባለቤትነቱን ለሚመሰክሩለት...
- ለካሳሁን ኃ/ስላሴ (አባታችን) :- ባለው ከፍተኛ የሆነ አስቂኝ እና አዝናኝ የንግግር ችሎታ በየትኛውም ዓይነት ግንኙነት ውስጥ ተፅዕኖ መፍጠር ለሚችለው . . . .

# ማውጫ


**ክፍል አንድ**

በራስ መተማመንንና ድፍረትን ለማዳበር ........................................ 1

**ክፍል ሁለት**

የራስ መተማመንን በዝግጅት ለማግኘት ........................................ 14

**ክፍል ሶስት**

ዝነኛ ተናጋሪ የነበሩ ሰዎች ንግግራቸውን እንዴት ያዘጋጃሉ ........................................ 31

**ክፍል አራት**

የማስታወስ ችሎታን ለማዳበር ........................................ 47

**ክፍል አምስት**

ስኬታማ የሆነ ንግግር ለማድረግ የሚረዱ ጠቃሚ ነጥቦች ........................................ 60

**ክፍል ስድስት**

ምርጥ ንግግር የማቅረቢያ ሚስጢር ........................................ 66

**ክፍል ሰባት**

የመድረክ አቀራረብና የግል ስብዕና ........................................ 76

**ክፍል ስምንት**

ንግግራችንን እንዴት ማድረግ እንደምንጀምር ........................................ 90

**ክፍል ዘጠኝ**

ንግግራችንን እንዴት እንጨርስ ........................................ 104

**ክፍል አስር**

ሃሳብህን እንዴት ግልፅ አድርገህ መናገር ትችላለህ ........................................ 121

**ክፍል አስራ አንድ**

አድማጮችህ የማዳመጥ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ ........................................ 139

**ክፍል አስራ ሁለት**

የቃላት ችሎታህን እና ክምችትህን አሣድግ ........................................ 152


Scanned with CamScanner

ዴል ካርኒጌ የሚከተሉትን ነገሮች እንዴት ልናዳብራቸው እንደምንችል ያሳየናል፡-

- ❖ የንግግር አቋቋማችንን
- ❖ በራስ መተማመናችንን
- ❖ የማስታወስ ችሎታችንን
- ❖ የንግግር መክፈቻና መዝጊያችንን
- ❖ አድማጫችንን ለመማረክና በንግግራችን እንዲሳቡ ለማድረግ
- ❖ የአነጋገር ዘይቤያችንን
- ❖ ጠላት ሳናፈራ በክርክሮች የምናሸንፍበትን ዘዴ

## በተጨማሪም

ይህ መፅሐፍ በተግባር የተደገፉና በህይወታችን ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን፣ ጓደኞቻችንን፣ ደንበኞቻችንን የሥራ ባልደረቦቻችንን እንዲሁም በአለቆቻችን ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር የሚረዱንን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ነጥቦችን አካቷል፡፡

እነዚህ ጠቃሚ መረጃዎች በገነኛው ዴል ካርኒጌ «ውጤታማ ንግግርና ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት» በሚል ርዕስ ተዘጋጅተው እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት/በመስጠት ላይ ሲሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ውጤታማ በማድረግ የተፈተኑ ናቸው፡፡

ዴል ካርኒጌ

**አሳታሚ፡-** ኤች ኬ አሳታሚ ኃ/የተ/የግል ማህበ
**HK Publisher P.L.C**
አ.አ ለም ሆቴል አካባቢ
☏0118601464
0911-23-80-57

**ዋና አከፋፋይ፡-** ኤደን መጽሐፍት መደብር
አ.አ ለም ሆቴል አካባቢ
0911-23-80-57

**ወኪል አከፋፋይ**

| | |
|---|---|
| ጅጅጋ ሙሉጌታ ሆቴል ፊትለፊት | 025-775-41-61 |
| አርባ ምንጭ ሲቀላ የገበያ ማዕከል ውስጥ | 0913-00-05-19 |
| ባ/ዳር ጋምቢ ክሊኒክ አጠገብ | 0911-34-05-36 |
| ጎንደር ዮሐንስ ቤ/ክርስቲያን አጠገብ | 0911-82-42-01 |
| ሐረር መሬማ ሕንፃ 2ኛ ፎቅ | 0911-238057 |

# ክፍል አንድ

## በራስ መተማመንንና ድፍረትን ማዳበር

ከ1912 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ከ500 ሺህ በላይ የሆኑ ወንድና ሴቶች የእኔን ዘዴዎች በመጠቀም በብዙ ሠዎች ፊት በመቆም ንግግር ለማድረግ የተሠጡ ኮርሶች ለመከታተል ችለው ነበር:: በርከት ያሉትም ለምን በዚህ ስልጠና ለመሠልጠን እንደፈለጉና ምን ዓይነት ውጤትስ ሊያገኙ እንደሚችሉ በፅሑፍ አስፍረው ነበር:: «ልክ ተነስቼ ንግግር እንዳደርግ ሲጠሩኝ» ሃሣቤ ይበታተናል «በጣም እደነግጣለሁ፣ በዚህ ጊዜ ታዲያ በደንብ ትኩረት ለማድረግና ሃሣቤን ለመሠብሠብ ካለመቻሌም በላይ ምን ለመናገር እንዳሰብኩ በፍፁም ማስታወስ አልቻልኩም ነበር:: በራስ የመተማመን ስሜት እንዲኖረኝ፣ እንዳልርበተበትና ቀደም ተከተሉን በጠበቀ መልኩ በሥራ ቦታ፣ በክበብ ስብሰባ ወይም ብዙ ሕዝብ ባለበት ቦታ ላይ አሣማኝና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ሃሣቤን በትክክል መግለፅ እፈልጋለሁ» በማለት ብዙ ሰዎች የተፈጠረባቸው ችግሮች እንደዚህ በማለት ተናግረው ነበር::

አንድ ጉዳዩን ጠንክር አድርጐ ሊገልፀው የሚችል ገጠመኝ ልንገራችሁ:: ከአመታት በፊት ሚስተር ዲ ደብሊው ጌንት የተባለ ሠው ፊላደልፊያ ውስጥ በህዝብ ፊት ንግግር ስለማድረግ በምሠጠው ኮርስ ላይ ተገኝቶ ነበር:: የመግቢያውን ትምህርት እንደጨረስኩም በሠራተኞቹ ክበብ ውስጥ አብሬው ምሣ እንድሠገብ ጋበዘኝ:: ሚስተር ጌንት ጥሩ ኑሮ ያለው የራሱ የሆነን ፋብሪካ የሚያስተዳድር በበጐ ፈቃድ ሥራዎች ላይ በንቃት የሚሣተፍና የአንድ ቤተክርስቲያን መሪ የሆነ በመካከለኛዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ ሠው ነበር:: ምሣ እየተመገብን እያለ ወደ እኔ ጠጋ ብሎ እንዲህ አለኝ:: «በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ለብዙ ጊዜያት ንግግር እንዳደርግ ብጋበዝም እኔ ግን ፍፁም ሊሣካልኝ አልቻለም:: በጣም ብዥ ይልብኛል:: ጭንቅላቴም ቅንጣት ታህል ሃሣብ የሌለው ይመስል ባዶ ቀፎ ስለሚሆን ይህን ንግግር የማድረግ ሃሣቤን ወደጐን ስለው ኖሬያለሁ:: አሁን ግን የኮሌጆች ህብረት የቦርድ ሊቀመንበር ሆኛለሁ:: በስብሰባዎችም ላይ እየተገኘሁ የሆኑ ንግግሮችን ማድረግ ይጠበቅብኛል . . . ይህንን የንግግር ችሎታ በዚህ ዕድሜዬ በመማር ላሣካው የምችል ይመስልሃል?::» «እንዴ ሚስተር ጌንት ሊመስለኝ መቻሉ ወይም አለመቻሉ ብቻ አይደለም:: ከልብህ ከተከታተልክ እንደሚሣካልህ በደንብ አውቃለሁ» አልኩት:: ሊያምነኝ ቢፈልግም እሱን ለማነሣሣትና ተስፋ እንዳይቆርጥ ብቻ ለማድረግ አጉል ተስፋ እየሰጠሁት መሰለው:: «ለእኔ ደግ በመሆን ውለታ እየዋልክልኝ መሠለኝ» አለኝና «ምክንያቱም አደርገዋለሁ ብዬ እንድበረታታ ማድረግ ስለሚገባህ» ሲል አከለበት::

በመሃከል ለትንሽ ጊዜ ሣንገናኝ የቀረን ቢሆንም እሱ ግን ከዚያ በኋላ የንግግር ችሎታውን ለማዳበር ስልጠናና ትምህርት ወስዶ ነበር:: ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ በድጋሚ ተገናኝተን እዛው የሠራተኞቹ ክበብ ውስጥ ምሣ አብረን

የተመገብነው፡፡ የተቀመጥንበት ጥጋትም ሆነ የተመገብንበት ጠረጴዛና ወንበር በመጀመሪያ የተጠቀምንበት ነበር፡፡ ከዚያም ለመጀመሪያ ጊዜ እዚያ ቦታ ቁጭ ብለን የተነጋገርነውን ነገር አስታውሼ እውነት በዚያ ሠዓት አጉል ተስፋ ሰጥቺህ ይሆን ስል ጠየኩት፡፡ ጀርባዋ ቀይ የሆነች ትንሽ የማስታወሻ ደብተር አወጣና ንግግር ለማድረግ ቀጠሮ የያዘባቸውን ጉዳዮችና መቼ እንደሆኑ አሣየኝ፡፡ «ይህንን ነገር ማሣካት በመቻሌ የማገኘው ደስታ ከዚያም ለህብረተሰቡ ማበርከት የምችላቸውን ተጨማሪ አገልግሎቶች ሣስባቸው በአጠቃላይ እነዚህ ነገሮች በህይወቴ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ኩራት እንዲሰማኝ አድርገውኛል፡፡» ሲል አመነልኝ፡፡ ከዚህ ቀን ቀደም ብሎ አንድ በጦር መሣሪያ ቅነሣ ላይ የሚወያይ ጉባዔ በዋሽንግተን ይደረግ ነበር፡፡ የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትርም በጉባዔው ለመሣተፍ ይመጡ ነበር፡፡ ከዚህ በላይ በፊላደልፊያ በሚደረገው ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲገኙላቸውና ለህዝብ ንግግር እንዲያደርጉ ሊቃነ ጳጳሱን በመጋበዝ የጥሪ መልዕክት ይልኩባቸዋል፡፡ እናም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚመጡ ሠዓት ለህዝብ የማስተዋወቂያና የመግቢያ ንግግር ለማድረግ እዚያ ከሚገኙት አገልጋዮች መካከል ሚስተር ጌንት ለመመረጥ እንደቻለ ገለፀልኝ፡፡ ከዛሬ ሦስት ዓመት በፊት በዚሁ ተመሣሣይ ቦታ ላይ ቁጭ ብለን በህዝብ ፊት ንግግር ማድረግ መማር ይችል እንደሆነ አስተዛዝኖ የጠየቀኝ ሠው ይኸ ነበር፡፡ የንግግር ችሎታውን እንዲህ ለማዳበር የወሠደበት ጊዜ ባልተለመደ መልኩ የፈጠነ ይመስላችኋል? በፍፁም አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከመቶ በላይ የሆኑ ብዙ አይነት ተመሣሣይ ጉዳዮች አጋጥመውናል፡፡ ለምሣሌ አንድ ግልፅ ያለ ሁኔታ እንጥቀስ፡፡

ከዓመታት በፊት ዶ/ር ኮርቲስ ብለን የምንጠራው የብሩክሊን ሃኪም የክረምት የዕረፍት ጊዜውን ለማሣለፍ ፍሎሪዳ ውስጥ የሚገኝ ጃየንትስ የተባለ ቡድን በሚሠለጥንበት ኳስ ሜዳ አካባቢ መጥቶ ነበር፡፡ ቤዝ ቦል ጨዋታን በጣም ይወድ ስለነበርም አዘውትሮ ለማየት ይሄድ ነበር፡፡ እየቆየ ሲሄድም በጣም ከሚቀራረባቸው የቡድኑ አባላት ጋር ጓደኛ ይሆናል፡፡ አንድ ቀን ታዲያ ቡድኑ ድል በማድረጉ በተዘጋጀ ግብዣ ላይ ይጠሩታል፡፡ ሻይ ቡና የማለቱ ሂደት ቀጥሎ ብዙዎቹ ተጋባዥ እንግዶች «ጥቂት ንግግር አድርጉ» እየተባሉ ይጠሩ ጀመር፡፡

በድንገትም ባልተጠበቀ ፍንዳታና አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ የመስተንግዶ አስተናባሪው እንዲህ ሲል ሰማ «እዚህ በመሃከላችን አንድ ሃኪም ይገኛል፡፡ እናም ዶ/ር ከርቲስን የምጠይቀው የቤዝ ቦል ተጫዎቾች ጤንነታቸውን እንዴት ሊንከባከቡ እንደሚችሉ ቢያስረዳ» ቅድመ ዝግጅት ይኖረው ይሆን? በትክክል በሙያው በዓለም ላይ አለ የተባለ ሰው ሲሆን ከሦስት አስርተ ዓመታት በላይም ስለጤናና ተያያዥ የህክምና ዘርፎች ሲያጠና ጊዜውን አጥፍቷል፡፡ ይህንን ጉዳይ አቢሮው ወንበር ላይ ተዝናንቶ በመቀመጥ ከግራና ከቀኝ ለሚገኝ ሠው ሌሊቱን በሙሉ ማስረዳት ይችላል፡፡ ነገር ግን ተመሣሣዩን ነገር ተሠብስበው ለተቀመጡ ትንሽ ሠዎች ቆሞ ለማስረዳት ከሆነ ጉዳዩ የተገላቢጦሽ ይሆናል፡፡ ይህ ለእሱ ሠውነትን የሚያርድ ጥያቄ ነው፡፡ ገና ነገሩን በማሠብ ብቻ የልብ ምቱ በእጥፍ ይጨምርና ዝልል ዝልል ይልበታል፡፡ በህይወቱ አንድም ጊዜ እንኳን ቢሆን ለተሰበሰቡ ሠዎች ንግግር አድርጎ አያውቅም እና አሁንም የሚያውቃቸውና

የሚያስባቸው ነገሮች ክንፍ አውጥተው መብረር ጀምረዋል:: ምን ቢያደርግ ይሻለዋል? ተመልካቹ ያጨበጭባል፣ እያንዳንዱ ሠውም እሱ ላይ አይኑን ተክሏል:: በዚህ ጊዜ ጭንቅላቱን በእንቢታ ነቀነቀ፤ ነገር ግን ይህ የፈየደለት አንድ ነገር ቢኖር ጭብጨባው ጥያቄያቸው እንዲጋጋል ማድረግን ነው:: «ዶ/ር ከርቲስ ተናገር! ተናገር!» የሚሉ ጩኸቶች እጅግ እየበረከቱ መጡ:: እሱ ግን የማይችለው ስቃይ ውስጥ ገብቶ ስለነበር እሺ ይሁን ብሎ ለመናገር ቢነሣ እንደማይሆንለት አውቋል::

ግማሽ አረፍተ ነገር እንኳን ከአፉ ማውጣት አይችልም:: ስለዚህም ከመቀመጫው በመነሣት አንዲትም ቃል እንኳን ሣይናገር ጀርባውን በጓደኞቹ ላይ አዙሮ ታላቅ ውርደትና ሃፍረት እየተሰማው (ጭራውን ቆልፎ) ሹልክ በማለት ወጣ:: ወደ ብሩክሊን እንደተመለሰ ግን ምንም ተአምር መፍጠር ሣያስፈልገው ወዲያውኑ በህዝብ ፊት ንግግር ስለማድረግ የሚያስተምረውን ኮርስ ለመከታተል ተመዘገበ:: በሚቀጥለው ጊዜም በእንደዚህ አይነት አጋጣሚ ፊቱ የሚቀላበትና መናገር የተሣነው ዱዳ አልፈለገም:: ከልቡ ለመማር በመጓጓት መምህሩን የሚያስደስት አይነት ተማሪ ወጣው:: ንግግር ለመልመድ በጣም ፍላጐት ስላለው ምንም የማመንታት ወይም በግማሽ ልቡ የመከታተል ነገር አይታይበትም:: ንግግር ለማድረግ የሚረዱትን ርዕሶች በጥልቀት ያዘጋጃል፣ በተግባርም ይለማመዳል፤ እንደሁም በትምህርት ክፍለ ጊዜውም አንድም ቀን ቀርቶ አያውቅም:: በአጭር ጊዜ ውስጥ መሻሻል አሣዬ:: የተሠጡትን ጥቂት ከወሆደ ካጠናቀቀ በኋላ የመረበሽ ስሜቱ ከመጥፋቱም በላይ በራስ የመተማመን ስሜቱም በዚያው ልክ እየጨመረ መጣ:: በሁለት ወር ጊዜ ውስጥም በሱ ግሩፕ ውስጥ ካሉ ተማሪዎች መካከል ኮከብ ተናጋሪ ወጣው:: ከዚህ በኋላም በየትም ቦታ ንግግር እንዲያደርግ ግብዣ ሲቀርብለት የመገኘት ፍላጎቱ ጨመረ:: የደረሰበትን ከፍ ያለ ቦታ ሊያሣየው ከመቻሉ ሌላ በዚሁ ያፈራቸውን አዳዲስ ጓደኞቹን በጣም እንዲወዳቸውም አድርጎታል::

በኒውዮርክ የሪፐብሊካኖች ፓርቲ የምርጫ ዘመቻ ኮሚቴ አባል የሆነ ሠው ዶ/ር ከርቲስ ለህዝብ ንግግር ሲያደርግ ሠማውና ለእነሱ ፓርቲ በከተማው ቅስቀሣ እንዲያደርግላቸው ጋበዘው::

ይህ ቅስቀሣ እንዲያደርግ የተጋበዘ ሠው ከዓመት በፊት ብዙ ህዝብ ያለበትን የግብዣ አዳራሽ በመፍራቱ፣ ንግግር ለማድረግ ምላሱ በመተሣሠሩ፣ በሃፍረትና ግራ በመጋባት ስሜት ተነስቶ ሹልክ ብሎ መውጣቱን ይህ ፖለቲከኛ ሠው ቢያውቅ እንዴት ባደነቀው ነበር::

በራስ መተማመንንና ድፍረትን ለማግኘት በሚደረገው ጥረት እንዲሁም ረጋ ብሎ በማሠብ በግሩፕ ካሉ ሠዎች ጋር ግልፅ የሆነ ውይይት ማድረግ ችሎታ ብዙ ሠዎች እንደሚገምቱት አስቸጋሪ አይደለም:: ይህ ችሎታ ለጥቂት የተቸሩ ሠዎች ብቻ እንደ ህብስተ መና ከሠማይ የወረደ ገፀ-በረከት አይደለም:: ልክ እንደ ጎልፍ ጨዋታ ማንም ሠው ተዳፍኖ ያለውን ችሎታ ሊያሣድገውና ሊያዳብረው የሚችለው ጥልቅ የሆነ ፍላጐት ካለው ብቻ ነው::

ተቀምጠን በነበረ ጊዜ በግልፅ የሚመጡልንን ሃሣቦች አድማጭ ፊት ለመናገር በጭራሽ እንዳናስብ የሚያደርገን ምክንያት ምንድነው? በእርግጥ ለዚህ ምንም ምክንያት እንደሌለ እናውቃለን:: እንዲሁም በተሠበሰቡ ሠዎች ፊት ስንሆን የምንናገራቸውን ነገሮች የበለጠ ማሠብ ያስፈልጋል:: የእነሱ እዚያ መኖር ሊያነሣሣንና ሊያነቃቃን ይገባል:: ብዙ ድንቅ የንግግር ችሎታ ያላቸው ሠዎች እንደገለፁት በርካታ አድማጭ መኖሩ አዕምሮአቸው በጥራትና ከፍ ባለ ደረጃ እንዲሠራ የሚያስችል ቅመም ወይም አነሣሽ ሃይል መሆኑን ነው:: በዚህን ጊዜ እነሱ እንዳላቸው የማያውቋቸው ሃሣቦች፣ እውነታዎችና ግኝቶች፣ ሄነሪ ዋረደ ቤከር እንዳለው፣ «ልክ እንደጭስ እየተግተለተሉ ይወጣሉ::» እናም እነዚህ ነገሮች ከሠዎች ጋር ይደርሱና በሞቀ እጃቸው ይዳብሷቸዋል::

ይህ ልምድ የእናንተም ሊሆን ይገባል:: ምናልባትም ደግሞ በደንብ የተግባር ልምምድ በማድረግ ቀርባችሁ ለማስቀረት ከጣራችሁ የማትችሉበት ምክንያት የለም::

ይሁን እንጂ እስካሁን ድረስ ያደረጋችሁት ሥልጠናና የተግባር ልምምድ በራስ መተማመናችሁን፣ ማዳበር ነበረባቸው የብዙ ሠዎች ስብሰባ የመፍራት አባዜ ጠራርጐ እንደሚወስደው እርግጠኛ ልትሆኑ ትችላላችሁ:: የእኔ ሁኔታ የተለየ ነው ብላችሁ አትገምቱ:: ባለፉት ትውልዶች ውስጥ እጅግ አንደበተ ርቱዕ በመሆን ለውጤት የበቁ ሠዎች እንኳን እዚህ ስሜት ላይ ከመድረሣቸው በፊት በራስ እምነት ማጣት ስሜት የተጠቁ ነበሩ::

ዊልያም ጄኒንግስ ብራያን የተባለ ጡረታ የወጣ የጦር ሜዳ ጀብደኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ንግግር ለማድረግ ሲሞክር ጉልበቱ ተርበትብቶበት እንደነበር አምኗል::

ማርክ ትዌይን ለመጀመሪያ ጊዜ በህዝብ ፊት ቆሞ ያስተማረ ቀን ልክ አፉን በጥጥ እንደተጠቀጠቀ ሠው መናገር እንዳቃተውና የልብ ምቱም ለዋንጫ ሽሚያ እንደሚወዳደር ሠው ፈጥኖበት እንደነበር ተናግሯል::

ግራንት በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ያልነበረውን ጦር እየመራ ቪክስበርግን በማስመለስ ለድል የበቃ ቢሆንም በህዝብ ፊት ለመናገር ሲሞክር ግን እሮጌ ሞተር እንዳለው መኪና ቀጥ እንደሚል አምኗል:: ጂን ጀረስ ትልቁ ፈረንሣይ በጊዜው ካፈራቻቸው አንደበተ ርቱዕ ፖለቲከኞች መካከል እንደ ነበር ቢታወቅም በተወካዮች ምክር ቤት ወስጥ የመግቢያ ንግግሩን ለማድረግ ድፍረቱን እስኪያገኝ ድረስ ለአንድ ዓመት ያህል አፉን ለጉሞ ተቀምጦ ነበር::

«ለመጀመሪያ ጊዜ በህዝብ ፊት ለመናገር ስሞክር ከባድ ሥቃይ ውስጥ እንደነበርኩ ልንገራችሁ:: እውነት ለመናገር አንደበቴ መንቀሣቀስ የማይችልና የቃላት እጥረት የነበረበት ሲሆን ምላሴ ደግሞ ላንቃዬ ላይ ተለጥፎ አስቸግሮኝ ነበር» ሲል ሊዩድ ጆርጅ አምኗል::

በእንግሊዝ የእርስ በርስ ጦርነት ወቅት ለነፃነትና ለአንድነት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረገውና ሃገሩን የተከላከለው ጆን ብራይት የመጀመሪያ የሆነውንና ልምዱን ያገኘበትን ንግግር ያደረገው በአንድ ት/ቤት ህንፃ ውስጥ ተሰብስበው

ለነበሩ ከፋት አካባቢ ለመጡ ሠዎች ነበር። ወደ ስብሰባው በሚሄድበት ጊዜም በጣም ከመፍራቱና አይሳካልኝም ብሎ ከመስጋቱ የተነሳ ባልደረቦቹን ንግግር በሚያደርግበት ወቅት የመረበሽና የጭንቀት ስሜት ከተመለከቱበት ሞቅ ያለ ጭብጨባ በማድረግ እንዲያነሣሡትና ጭንቀቱን እንዲያባርሩለት አዟቸው ነበር።

ቻርለስ ስቲዎርት ፖርኔል የተባለው ታላቁ የአይሪሾች መሪ የንግግር ችሎታው ዝቅተኛ በነበረበት ወቅት በጣም ይጨነቅና ይረበሽ ስለነበር አዘውትሮ ንግግር በሚያደርግ ጊዜ እጆቹን በጣም ጭብጥ አድርጎ ከመያዙ የተነሣ ጥፍሮቹ ስጋውን ሰርስረው እየገቡ እጁን ያደሙት እንደነበር የገዛ ወንድሙ ምስክርነቱን ሰጥቷል።

ዴዚሬል ለመጀመሪያ ጊዜ በተወካዮች ምክር ቤት ንግግር ከማድረግ ይልቅ አንድ ሙሉ ተሽከርካሪ ብርጌድ መምራት ይቀለው እንደነበር አምኗል። እናም ለመጀመሪያ ጊዜ እሱም ሆነ ሸርዳን የተባለ ሠው ያደረጉት ንግግር እርባና ቢስ ነበር።

በእርግጥ አሁን አሁን በጣም ድንቅ ተናጋሪ የነበሩት እንግሊዛውያን በመጀመሪያ የንግግር ሙከራቸው ርባና የለሽ ስለነበሩ ከአንድ ጀማሪ ወጣት ተናጋሪ እጅግ የተሣካ ንግግር መጠበቅ የገደቢስነት ምልክት ሆኗል።

ሠዎቹ ደርዘን ቢሞሉ ባይሞሉ፣ ወንዶች ቢሆኑ ሴቶች በሃዘን ቢሆን በደስታ ወይም በችግር ጊዜ የምናደርገውን ንግግር የኃላፊነት ስሜት በአለው ሁኔታ ልናደርገው ይገባናል። ንግግሩ ህያው የሆነው ሲሰሮ ከ1000 ዓመታት በፊት እንደተናገረው ሁሉም በህዝብ ፊት የሚደረጉ ንግግሮች የሚያመሳስላቸው እውነተኛ መገለጫቸው ድንጋጤን የሚፈጥሩ መሆናቸው ነው። ይህ አይነቱ ስሜት በሬዲዮ ለመናገር በሚሞክሩ ሠዎች ላይም ይንፀባረቃል። ይህም «የድምፅ ማጉሊያ» ፍራቻ በመባል ይታወቃል። ቻርልስ ቻፕሊን በህዝብ ፊት መቆምን የለመደውና የሚያውቀው ቢሆንም በሬዲዮ በቀጥታ ሲናገር ግን ከመፍራቱ የተነሣ ሁሉንም ንግግሩን በወረቀት ፅፎ ነበር የመጣው። ከ1912 (እ.ኤ.አ) በመላው አሜሪካ «አንድ ምሽት በሙዚቃ አዳራሽ›› የሚባል ትርዒቱን ዞሮ የሠራ ሲሆን ከዚህ በፊት ደግሞ በእንግሊዝ ውስጥ ህጋዊ የሆነ የመድረክ ዝግጅቶችን እያቀረበ ነበር።» እዚያች ጠባብ ክፍል ገብቶ ድምፅ ማጉሊያ ፊት ሲቀመጥ ማዕበል በበዛበት የካቲት ወር ላይ አትላንቲክ ውቅያኖስን በመርከብ የሚሻገር ሠው እንደሚሰማው ሆድ የሚያንዘፈዝፍ ስሜት ለእራሱም እንደሚሠማው ተናግሯል።

ጀምስ ከርክውድ የተባለው ዝነኛ የፊልም ተዋናይና ዳይሬክተር ይህ ተመሣሣይ ስሜት እንደነበረበት ገልጿል። በመድረኮች ላይ ኮከብ የሆነ ተናጋሪ ቢሆንም ከማያያቸው አድማጮቹ ጋር በሬዲዮ የሚያደርገውን የቀጥታ ንግግር ጨርሶ ሲወጣ ከፍራቻው የተነሣ ግንባሩ ላይ ችፍ ያለበትን ላብ እየጠረገ ነበር። ‹‹ብብሮድ ዌይ የመክፈቻ ዝግጅት ምሽት ላይ በመገኘት በሬዲዮ በቀጥታ ከመናገር ጋር ሲነፃፀር ምንም ማለት አይደለም ብሏል።

አንዳንድ ሠዎች ምንም ያህል የንግግር ችሎታቸው ጥሩ ቢሆንም ንግግራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ባሉት ደቂቃዎች ውስጥ ሁልጊዜ የፍራቻ ስሜት እንደሚከሰትባቸውና በጀመሩ በሰከንዶች ጊዜ ውስጥ ግን ሁሉም ነገር እንደሚያስተካክልላቸው ይገልፃሉ::

አብርሃም ሊንከንም ቢሆን በንግግሮቹ መጀመሪያ ላይ የማፈር ስሜት ነበረበት:: «በመጀመሪያ ላይ በጣም እንግዳ የሆነ ስሜት ይሠማዋል» ይላል ሄራንዱን የተባለው የህግ አማካሪ በዙሪያው ካሉት ነገሮች ጋር እራሱን ማለማመድ በጣም ከባድ ሥራ ይሆንበታል፤ ለትንሽ ጊዜም ግልፅ ከሆነ በራስ ያለመተማመን ስሜት ጋር ይታገላል:: ይሄ ታዲያ ግራ መጋባቱን ጭራሽ ያባብሰዋል:: አዘውትሬም ይሄን ጉዳይ ስለማይ ከሚሰተር ሊንከን ጋር ነገሩን አንስተን ለመነጋገርና ለመረዳዳት ሞክረናል:: ልክ ንግግሩን ሲጀምር ድምጹ ጆሮ የሚበጥስ ሰቅጣጭና ደስ የማይል ይሆንበታል፣ ባህሪውና አመለካከቱ የተለየ ይሆናል፣ ጠቆር ያለ ግራጫ ፊቱ ይጨማደድና ይደርቃል፣ እሱን ለየት ከሚያደርጉት መካከል ንግግሩን ቆም እያደረገ ስለሚቀጥልና በራስ የመተማመን ስሜቱን ስለሚያጣ ሁሉም ነገሮች የርሱ ተቃራኒ ሆኖ ይቆማል:: ነገር ግን ይህ ሁሉ የሚፈጠረው ለጥቂት ጊዜዎች ብቻ ነበር::» ያቺ ጊዜ ስታልፍ ማንነቱን፣ ለዛውንና ጥልቅ ስሜቱን መልሶ ያገኘውና እውነተኛ የሆነውን ንግግሩን ይጀምራል:: የእናንተም የሕይወት ልምድ ተመሣሣይ ሊሆን ይችላል:: የተቻላችሁን ያህል ጥረት አድርጋችሁ ጥሩ ንግግር አዋቂዎች ለመሆን እንዲሁም ያልተቆራረጠና ያልተንዛዛ ንግግር ለማድረግ አራት ነገሮች ያስፈልጓችኋል::

**አንደኛ፡- በጠንካራና ቀጣይ በሆነ የፍላጐት ስሜት መጀመር**

የዚህ ጉዳይ ጠቃሚነቱ ምናልባትም እናንተ ከምታስቡት በላይ ሣይሆን አይቀርም:: አስተማሪያችሁ የምታስቡትን ወይም የልባችሁን ስሜት ማየት ቢችል እንዲሁም የፍላጐታችሁን ጥልቀት ቢመረምር እያደረባችሁ ያለውን የመሻሻል ሂደት በትክክል ሊተነብየው ይችላል:: ፍላጐታችሁ የፈዘዘና ደካማ ከሆነ የምታገኙት ውጤትና ስኬትም እንደዛው ደካማና ፈዛዛ ሆኖ ይቀጥላል:: ትልቅ ውሻ አንዲት ድመትን ለመያዝ ሲያባርር እንደሚጠቀመው ጉልበት እናንተም ያላችሁን ሃይል አውጥታችሁ ትምህርታችሁን አጥብቃችሁ ከተከታተላችሁ ከሠማይ በታች ያለ ነገር ሊያሸንፋችሁ አይቻለውም::

ልታገኙ የምትችሉትን ከፍተኛ የሆነ በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሁም በአሣማኝ ሁኔታ የመናገር ችሎታ ያለውን ትርጉምና ጠቀሜታ ምን ያህል እንደሆነ አስቡት በገንዘብ ወይም በብር ቢተመን ምን ያህል ዋጋ ያለው ነገር እንደሚያመጣ ገምቱ::

የመሪነትን ሚና ለማግኘት ከምታስቧቸው፣ከምትገምቷቸውና ከምታደርጓቸው ሌሎች እንቅስቃሴዎች በፈጠነ ሁኔታ የንግግር ችሎታችሁ ሊያሣካው ይችላል::

ቻውንሲ ኤም-ዴር የተባለ ሰው በአጭሩ እንደገለፀው «ሰዎችን በሚማርክ መልኩ ንግግር አዋቂ መሆንን የመሠለ ለአንድ ሠው የሥራ ዕድልን የሚፈጥርና

ዕውትና እርካብ ላይ የሚያደላድል ከቶ ምንም ዓይነት ነገር የለም።» ሬሲፓ ዲ-አርመር የተባለ ሰው በንግድ ዘርፍ ተሠማርቶ ሚሊዮኖችን ካካበተ በኋላ እንዲህ ብሏል «ታላቅ ካፒታሊስት (ከበርቴ) ከመሆን ይልቅ ታላቅ ተናጋሪ ብሆን እመርጥ ነበር ብሏል።

ሁሉም በትምህርት ዓለም ውስጥ ያለፈ ሰው ሊያሣካው የሚመኘው ነገር ይህ ነው። እንድረው ካርኒጌ ከሞተ በኋላ ከተገኙት መረጃዎች መካከል የ33 ዓመት ዕድሜ በነበረ ጊዜ ያሰላው የህይወት ዕቅድን የሚያሣይ አንድ ወረቀት ነበር። በዚያን ጊዜ ሥራዎቹን ሁሉ መልክ መልክ አስይዞ ገቢውን በዓመት ወደ 50 ሺህ ዶላር በማድረግ ከሁለት ዓመት በኋላ ማለትም በ35 ዓመቱ ትምህርቱ «በተለይም በህዝብ ፊት ንግግር ስለማድረግ ልዩ ትኩረት መስጠት» በሚለው ዙሪያ ለመከታተል አስቦ ነበር።

የዚህ መፅሐፍ ደራሲ ባሉበዙና የተለያዩ የህይወት ልምዶች ባለቤት የነበረና እንዲሁም በዓለም ላይ ያልረገጠባቸው ቦታዎች ጥቂት ቢሆኑም ሠዎችን በማራኪ ንግግር ማርኮ የእኛን ሃሣብ እየተከተሉ እንዲሄዱ በማድረግ ከሚገኝ ወደ ውስጥ ዘልቆ ከሚሠማ እርካታ ጋር የሚስተካከሉ ነገሮች ብዙ እንዳልሆኑ ተረድቷል። ማራኪ ንግግር የማድረግ ችሎታ ያላችሁ የጥንካሬ ምንጭና የታላቅ ስልጣን ባለቤት የመሆን ኩራት እንዲሠማችሁ ያደርጋችኋል። መሠል ጓደኞቻችሁ ካሉበት ቦታ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ያስቀምጧችሁና ወደ ላይ ምንጥቅ ያደርጋችኋል።ውስጡ ምትሃታዊ ሃይል ስላለው ፍፁም የማይረሱት ትዕይንት ይሆናል። አንድ ተናጋሪ ሰው እንዳለውም «መናገር ከመጀመሬ ሁለት ደቂቃዎች በፊት ብገረፍ እመርጣለሁ። ከመጨረሴ ሁለት ደቂቃ በፊት ደግሞ ንግግር ከማቆም በጥይት ብመታ እመርጣለሁ» ሰዎች ብዙ ነገሮችን በደከመ መንፈስ ለመሥራት ይነሣና ወደ ሥርቻ ውስጥ ተሸቀንጥረው ይወድቃሉ። ፍላጐታቸውና ይህን ክህሎት ለመቀዳጀት ያላቸው ስሜት እጅግ ጥልቅ እና የጋለ እስኪሆን ድረስ በደንብ ያስቡበት። ይህን የትምህርት ፕሮግራም መጀመር ያለባችሁ በታላቅ የደስታ ስሜት ተሞልታችሁ ከሆነ እስከመጨረሻው ያለውን ሂደት በድል አድራጊነት እንድትወጡት ያስችላችኋል። በሣምንት ውስጥ ካሉት ቀናት አንዱን ቀን ይህንን መፅሐፍ ለማንበብ፣ በአጭሩ ለመግለፅና ወደፊት ለመጓዝ ያለውን ሂደት ቀላል እናድርገው። ወይም ማፈግፈግን አስቸጋሪና ከባድ እናድርገው። ጁሊየስ ቄሣር ሠራዊቱን በመርከብ ጭኖ (ጓል) ከሚባል ቦታ በማንሳት አሁን እንግሊዝ ተብላ የምትጠራው ሃገር ሲደርስ የጦሩን ድል አስተማማኝ ለማድረግ የተጠቀመበት ዘዴ ምንድን ነው? የተጠቀመው ብልሃት ወታደሮቹን በዶቨር ኖራማ ዳገት ላይ ይዟቸው ይጠጣና ወደታች ሁለት መቶ ጫማ እማዕበሉ ውስጥ እያንዳንዱን ሃገር እያቆራረጠ በመጡባቸው መርከቦች በሃይለኛ የእሣት ነበልባል እየተበሉ ወደ ትቢያ ሲቀየሩ እንዲመለከቱ ማድረግ ነው።

ከሌላው ዓለም ጋር የሚያገናኛቸው መሣሪያ ጠፍቷል፣ መሸሽ፣ ቢያስፈልግ እንኳን ይጠቅሟቸው የነበሩት መርከቦች ተቃጥለዋል። በዚያ ላይ

ያሉት ደግሞ በጠላት ምድር ላይ ናቸው:: ነገር ግን አሁንም አንድ ተስፋ ይቀራቸዋል፤ ይህም ተስፋ በጀግንነት ገስግሶ አገሪቱን ድል አድርጎ መቆጣጠር ብቻ ነበር:: እናም ያደረጉት ያንን ነበር::

ይህ ህያው የሆነው የጁሊየስ ቄሣር መንፈስ ነበር:: እናንተስ ያለባችሁን አድማጭ የመፍራት ሞኛ ሞኝ የሆነ ነገር ለማስወገድ ይህን መንፈስ ለምን የራሳችሁ አታደርጉትም?

**ሁለተኛ፡- ስለምንናገረው ነገር ይዘት በደንብ ማወቅ**

በማሠብ፣ በማቀድና በመዘጋጀት

አንድ ሠው የሚናገረውን ነገር ቀድሞ በማሠብ፣ በማቀድና በመዘጋጀት ምንም ዓይነት ምቾት ሲሠማው የንግግሩን ይዘት ካላወቀ አድማጩ ጋር ሲገናኝ ምንም ዓይነት ምቾት ሲሠማው ለመምራት አይችልም:: እራሱ አይነ ሥውር ሆኖ ሌላውን ዓይነ ስውር ለመምራት እንደሚሞክር አይነት ሠው ይሆናል:: በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የተገኘ ንግግር አቅራቢ ሠው እራሱን ሲጠላ ሲፀፀት እንዲሁም በቻልተኛነቱ ሲያዝንና ሲያፍር ይገባዋል::

ቴዎደር ሩዝቬልት የራሳቸውን ታሪክ በፃፉበት መፅሐፍ ላይ እንዲህ ብለዋል:: በ1981 (እ.ኤ.አ) ክረምት አካባቢ ለሕግ መወሠኛ ምክር ቤት ስመረጥ እዚያ ከሚገኝ ማንኛውም ሠው መካከል በጣም ወጣቱ እኔ ነበርኩ ማንኛውም ልምድ የሌለው ወጣት እንደሚያጋጥመው አይነት ችግር እኔም ንግግር ለመለማመድ ከባድ የሆነ ችግር ገጥሞኝ ነበር:: አንድ ግትር የሆነ ሽማግሌ የገጠር ሠው ግን በደንብ ረዳኝ:: እሱ ራሱ ሌላውን አባል በንግግሩ ከማረም ወደኋላ የማይለውን የዌልንግተኑን መስፍን ሲያርመው ሣያውቀው እኔን በተዘዋዋሪ አስተማረኝ:: ምክሩ እንዲህ የሚል ነበር «ለመናገር ያሰብከው ነገር ከሌለ በስተቀር አትናገር! የምትናገረው ካለህም ምን እንደሆነ በደንብ እወቀው ከዚያ በኋላ ተናገረውና ተቀመጥ::» ይህ ግትር የሆነ የገጠር ሠው ሩዝቬልትን ሌላም ፍራቻን ለማስወገድ የሚረዳ ነገር ሣያስተምረው አልቀረም:: ምናልባትም እንዲህ ሣይለው አይቀርም «በሠዎች ፊት በምትናገርበት ጊዜ ፍራቻ የሚያጠቃህ ከሆንክ አንድ ነገር ስታገኝ ጥቁር ሠሌዳው ላይ ማስፈር፣ ካርታው ላይ አንድ ነጥብ ማመልከት፣ የጠረጴዛውን ቦታ መቀየር፣ መስኮት መክፈት፣ መፅሐፍቶችንና ወረቀቶችን ወዲያና ወዲህ ማገላበጥና ማንኛውንም ዓላማህን ሊያሣካ የሚችል አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ከሚያጋጥምህ ኃፍረት ሊገላግልህ ይችላል::

በእርግጥ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ለማድረግ ብዙ ጊዜ ሠበብ አይኖርህም:: ነገር ግን አንድ ምክር ልለግስህ:: ይኸውም በዚህ ዘዴ መጠቀም ትችላለህ:: ቢሆንም ግን ስትጠቀም በመጀመሪያ ከላይ ባሉት ጥቂት ጊዜያቶች ብቻ መሆን ይኖርበታል:: አንድ ህፃን መራመድ ከጀመረ በኋላ ተመልሶ ወንበሩን እየተመረኮዘ ለመራመድ አይሞክርምና::

## ሦስተኛ፡- እምነት እንዳለህ አድርገህ አስመስል

አሜሪካ ካፈራቻቸው ዝነኛ የስነ ልቦና ባለመያዎች መካከል ፕሮፌሠር ዊልያም ጀምስ የሚከተለውን ፅፏል:: ድርጊታችን ስሜታችንን የሚከተል ይመስላል:: እውነተኛው ነገር ግን ስሜታችንም ሆነ ድርጊታችን አብረው የሚሄዱ መሆናቸው ነው::

በራሱ ሠዓት እየመጣ የሚያፍነከንክ የደስታ ስሜት ከጠፋ ደስተኛ ለመሆን ያለን ሌላ ነፃ የሆነና በእኛ ፈቃድ ማምጣት የምንችልበት መንገድ ልክደስታ እንዳለው ሠው ብድግ ብላችሁ ቀድሞውኑም ሃቃችሁና ሃሴታችሁ እዚሁ ከእናንተ ጋር እንደነበሩ ማውራትና ማስመሰል ነው:: ይህ ድርጊታችሁ ደስ የሚል ስሜት ካልፈጠረባችሁ ምንም ዓይነት ነገር በዚያ ሁኔታ ላይ እያላችሁ ደስታ አይፈጥርባችሁም ማለት ነው:: ድፍረት እንደሚሰማን ልክ ደፋር እንደሆንን አድርገን ማስመሰል ከቻልንና ሁሉንም ፍላጐቶቻችንን አውጥተን ከተጠቀምን የፍራቻ ድባብ ጠፍቶ በምትኩ የድፍረት መንፈስ እንዲሠማን ያደርገናል::

የፕሮፌሠር ጀምስን ምክር እስቲ በተግባር እናውለው:: ህዝብ ፊት በምንቀርብበት ጊዜ ድፍረት እንዲሠማን መጀመሪያውኑም ያው ድፍረት ከእኛ ጋር እንደነበር አድርገን መያዝ ይኖርብናል:: በደንብ ካልተዘጋጀን በምድር ላይ ያሉ ማስመሰሎችን ሁሉ ብንጠቀምም ብዙም አይረዳንም:: ነገር ግን በቅድሚያ ምን ለመናገር እንዳሰብን በደንብ ካወቅን በፈጣን እርምጃ ራመድ ብለን በመውጣት በረጅሙ ትንፋሽ እንሣብ:: በትክክልም ህዝብ ፊት ቀርበን ከመናገራችን ከአንድ 30 ሰከንዶች በፊት አየር በጥልቀት እየሣቡ ማስወጣት ጥሩ ነው:: በተጨማሪ የምናገኘው ኦክስጅንም ዘና እንድንልና ብርታት እንዲኖረን ያደርገናል:: ታላቁ ድምፃዊ ዣን ዲ ሬዚክ አየር በምንወስድ ጊዜ «እሱም ላይ መመርኮዝ በመቻላችን» ፍርሃታችን ድራሹ ይጠፋል ብሏል::

በማንኛውም የአድማስ ክልል ብንሆንና ተመሣሣይ የሆነ አስተሳሰብ ባይኖረንም ወንዶች ሁልጊዜም ጀግንነትን ያደንቃሉ:: ስለዚህ ወደፊት በድፍረት ተንዝ፣ ከዚያም ቁም:: ምንም ሣትነቃነቅ ድርጊቶችህን እንደምትወዳቸው አድርገህ መውሠድ በቁመትህሙሉ ቀጥ ብለህ በመቆም አድማጮችህ ፊት ለፊት አይናቸውን በማየትና ሙሉ በሙሉ በራስ የመተማመን ስሜት እንዳለህ ሆነህ ሁሉም ሠው ላንተ ያልከፈሉት ብድር እንዳለባቸው አድርገህ በማሠብ ንግግርህን ጀምር:: ልክ እንደዚህ ስታስብና ሁሉም እዚያ ተሠብስቦ አንተን የሚጠብቀው ያንን የተበደሩህን ገንዘብ ለመክፈል ተጨማሪ ጊዜ እንድትሠጣቸው ለማግባባት እንደሆነ ስትገምት ስነ-ልቦናዊ ውጤቱ አንተን በጣም ተጠቃሚ ያደርግሃል::

በፍርሃት አስር ጊዜ የኮትህን ቁልፎች መቆላለፍና መክፈት በጌጥህ መጫወት ወይም ደግሞ በእጆችህ ዕቃ መፈለግን አቁም! በተረፈ ግን እንደዚህ ዓይነት የፍራቻ እንቅስቃሴዎች ለማድረግ ከተገደድክ እጆችህን ወደኋላ



Scanned with CamScanner

በማቆላለፍ ከጀርባህ በኩል ማንም ማያስተውልህ ጣቶችህን መሬት ወይም ማሽከርከር ትችላለህ! አሊያም ደግሞ የእግርህን ጣቶች ማነቃነት ትችላለህ:: ጠቅለል ባለ «መመሪያ ለአንድ ንግግር አድራጊ ሰው ከቁሣቁስ ጀርባ እንዲደበቅ ማድረግ ጥሩ አይደለም:: ነገር ግን መጀመሪያ አካባቢ ላሉ ጥቂት ጊዜያቶች ከጠረጴዛ ጀርባ ወይም ከወንበሮች ኋላ ሆኖ እነሱን ጥብቅ አድርጎ በመያዝ ወይም ደግሞ በውስጥ እጆችን ማንቲም ግጥም አድርጎ መያዝ የተወሠነም ቢሆን ድፍረት ሊሠጠን ይችላል::»

ቴዎድር ሩዝቬልት ተለይቶ የሚታወቅበትን ድፍረትና በራስ መተማመን እንዴት ሊያገኘው ቻለ? ከማያወላውልና ደፋር ከሆነ መንፈስ ጋር አብይ ችሎታ በተፈጥሮ ተለግሶት ይሆን እንዴ? በፍፁም አይደለም:: የራሱን ታሪክ ሲፅፈው እንደገለፀው «በሽታ የሚያጠቃኝና ግራ የሚገባኝ አይነት የልጅነት ሕይወት በማሣለፌ በወጣትነት ጊዜዬ ፈሪና ማንንም የማላምን ስለነበርኩ ብዙ ስቃይና ልፋት በሚጠይቅ ሁኔታ እራሴን በአካልም ብቻ ሣይሆን በመንፈስም ማሠልጠን ነበረብኝ::

እንደ ዕድል ሆኖ እሱ እራሱን እንዴት ሊቀይር እንደቻለ እንዲህ በማለት ፅፎታል «ልጅ እያለሁ በእጅጉ ያስደነቀኝ አንቀጽ ከማረየት መፅሐፍ ላይ አንብቤ ነበር:: በዚህ መፅሐፍ ላይ የእንግሊዝን የጦር ሠራዊት የሚመራ አንድ ሻምበል ከጀግና ወታደሮቹ መካከል ፍርሃት አልባነትን እንዴት ለመቀዳጀት እንደሚቻል ሲገልፅለት ይተርካል:: ማንኛውም ሠው በመጀመሪያ ለግዳጅ ሲላክ መፍራቱ የተለመደ ነው:: ጥንካሬህን ካንተ ጋር ጠብቀህ ለማቆየት የሚረዳህ ዘዴ መጀመሪያውኑ ምንም አይነት ፍርሃት እንደሌለብህ አድርገህ ማስመሰል መጀመር ነው:: ይህ ድርጊትህም ካንተ ጋር እየቆየ ሲመጣ ይዋሃድህና ከማስመሰል እውነት ወደመሆን ይለወጣል:: በዚህ የተነሣ ይህ ሠው ይህን ድርጊት በመለማመድና ደጋግሞ በመሞከር ፍርሃት አልባነትን ሊጐናፀፍና ይህም የፍራቻ ስሜት በሚሠማው ቅፅበት የነገሩን አቅጣጫ በማስቀየር ደፋር እንዲሆን አስችሎታል::

ከላይ ሩዝቬልት የተጠቀመ የማርየት ሣይሆን የራሱን ማስመሰል ነው:: «ይህ ንድፈ ሃሣብ እኔ የተቀበልኩትና መንገዴንም የቀየስኩበት ነበር:: ከዚህ በፊት ብዙ የምፈራቸው ነገሮች ነበሩብኝ:: ከግራጫ ድብ ጀምሮ ያልተገራ ፈረስና በመሣሪያ የሚታገዙ ሠዎችን ሣይ ሁሉ ፍርሃት ይለቅብኛል:: ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በሚያጋጥሙኝ ጊዜ እራሴን እንዳልፈራሁ አድርጌ በማሰብና በማስመሰል በጊዜ ሂደትና ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላስወግደው ችያለሁ:: ይህን ልምድ ብዙ ወንዶች ለውጥ ለማምጣት ይረዳናል ብለው ከመረጡት ይሆንላቸዋል:: እናንተም ይህንን ዘዴ እና ልምድ ምርጫችሁ ልታደርጉት ትችላላችሁ» ማርሻል ፎክ እንዳለው «ምርጥ የሆነው የመከላከል ዘዴ ማጥቃት ነው::» እናም በፍራቻችሁ ላይ ጥቃት ሰንዝሩበት:: ውጡና ተጋፈጡት፣ ተዋጉት፣ በእያንዳንዷ አጋጣሚም ፍፁም በሆነ ቆራጥነት በቁጥጥራችሁ ሥር አድርጉት::



Scanned with CamScanner

የሚመጣላችሁ መልዕክት አለ:: እናም እራሳችሁን ዊስተርን ዩኒየን የሚሠራና እንዲያደርስ የተሰጠው መልዕክት በዕጅ የያዘ ትንሽ ልጅ አድርጋችሁ አስቡ:: የተላከውን ቴሌግራም በጣም ስለምንፈልገው ለልጁ የምንሰጠው ትኩረት አናሳ ነው:: መልዕክቱን ግን እንደ ንጉስ ነው የምናየው እናም አዕምሮአችሁንና ልባችሁን መልዕክቱ ላይ አሣርፉት:: ልክ እንደ እጃችሁ መዳፍ በደንብ አጥኑት፣ በእውነተኛ ስሜትም እመኑበት፣ ከዚያም ለማለት የፈለጋችሁትን ነገር ቁርጠኛ እንደሆናችሁ አድርጉና ተናገሩት:: ይህን ካደረጋችሁ በኋላ ብዙም የማይፈጅባችሁ የገጠመኞቻችሁና የራሳችሁ አዛዥና ታዛዥ የመሆን ዕድላችሁ አስር ለአንድ ይሆንላችኋል::

## አራተኛ:- ተለማመድ! ተለማመድ !ተለማመድ

የመጨረሻውን ነጥብ እጅግ አፅንኦት ሠጥተን ልናየው ይገባል እስካሁን ያነበባችኋቸውን ነገሮች በሙሉ ብትረሷቸው እንኳን ቀጥሎ ያለውን ነገር ግን እንዳትረሱት:: በንግግር ጊዜ በራስ መተማመናችንን ለማሣደግ የመጀመሪያው፣ የመጨረሻውና በፍፁም ቸል ልንለው የማይገባው መንገድ በደንብ መናገር መለማመዳችን ነው:: በመጨረሻም ሁሉም ነገር ወደ አንድ ነጠላ ወደሆነ ነገር ግን በጣም አስፈላጊ ወደሆነ ጉዳይ ይጠቃለላል:: መለማመድ፣ መለማመድ፣ መለማመድ:: ይህም የሁሉም ነገር መደምደሚያ ይሆናል «እሱ ከሌለ ምንም የለም» የሚባልበት ነው::

ሩዝቬልት ጥንቃቄ ማድረግ ያለብንን ነገር ሲነግረን እንዲህ ይላል «ማንኛ ውም ጀማሪ ተናጋሪ የአጋዘን ፍራቻ የሚባለው ይይዘዋል:: ይህ የአጋዘን ፍራቻ ጥልቅ የሆነ ጭንቀትና ውጥረት የነገሰበት ሁኔታ ውስጥ መገኘት ማለት ሲሆን በአብዛኛው ድንጉጥና ፈሪ ከመሆን የሚመነጭ አይደለም:: አንድ ሠው ለመጀመሪያ ጊዜ በብዙ ሠዎች ፊት ቆሞ ሲናገር ይህ ነገር ሲያጋጥመው ይችላል:: ይህም ልክ ለመጀመሪያ ጊዜ አጋዘን ሲመለከት ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ ጦር ሜዳ ሲሄድ የሚፈጠርበትን አይነት ስሜት ነው:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ሠው የሚያስፈልገው ጀግንነት ሣይሆን ረጋ ብሎ ማሠብና ነርቩን መቆጣጠር ነው:: ይህንንም ሊያሣካው የሚችለው በተግባር ልምምድ በማድረግ ብቻ ይሆናል:: ራስን ለማሸነፍ የሚያስችል ቀጣይነት ያለው ተደጋጋሚ ልምምድ በማድረግም ነገሮችን በደንብ አድርጐ ለመቆጣጠር ይችላል:: ይህ በአበዛኛው እንደ ልማድ አድርጐ የመያዝ ጉዳይ ሲሆን በተደጋጋሚ ጥረት በማድረግ ለመለማመድ ካለን ፍላጐትና ስሜትም ወሣኝነት አለው::

«አንድ ሠው እነዚህን ነገሮች ካሟላ በእያንዳንዱ ልምምድ እየጎለበተና እያደገ ይመጣል::» አድማጭ ፊት መቆምን ትፈራላችሁ አይደል? እስቲ በመጀመሪያ ይህ ፍራቻ በምን ምክንያት እንደተከሰተባችሁ እንመልከት:: ፕሮፌሠር ሮቢንሰን «የአዕምሮ ተግባር» በሚለው መፅሐፋቸው «ፍራቻ እርግጠኛ ካለመሆን ስሜትና ከድንቁርና ይመነጫል::» ብለዋል:: በሌላ አነጋገር በራስ መተማመን ስሜት አለመኖር ወይም መጥፋት ማለት ነው:: የዚህ መንስዔ ምንድነው? ይህ ደግሞ በእርግጠኝነት ምን መስራት እንደምንችል ካለመገንዘብ ይመነጫል:: ምን መስራት እንደምንችል አለማወቅ ደግሞ በተራው ወደ ልምድ



Scanned with CamScanner

የተሣካ የሥራ ልምድ እንዳ
አልባነት ይመራናል:: ከጀርባ ያለ ሪከርዳችሁ ብን ብሎ ይጠፋል:: ልክ ጭጋጋማውን
ላችሁ የሚያሣይ ከሆነ ይህ ፍርሃታችሁ እሱም ይቀልጣል::
የሃምሌ ምሽት የጠዋት ፀሃይ እንደሚያሞቀው ተቀባይነት ያለው መንገድ

አንድ ነገር እርግጠኛ ሁኑ:: ዋና ለመለማመድ መፅሐፍም እስካሁን ድረስ
መጀመሪያ ውሃ ውስጥ መጥለቅ ነው:: ይህን ዞር አድርጋችሁት በእጃችሁ
ስታነቡት ቆይታችኋል:: አሁን ደግሞ ወደ ጐን ምረጡ:: በተለይ በጉዳዩ ላይ በቂ
ወዳለው አጣዳፊ ሥራ አትገቡም? አንድ ርዕስ ደቂቃ የምትሆን ንግግር
እውቀት ያላችሁ ቢሆን ይመረጣል:: ከዚያ ለሦስት ንግግሩን ልታቀርቡት
አዘጋጁ:: ደግማችሁ ደግማችሁ በደንብ ተለማመዱ:: ከዚያ ሰብስባችሁ በእነሱ
ወዳሰባችሁት ግሩፕ ሄዳችሁ ወይም ከዚያ በፊት ጓደኞቻችሁን አቅርቡ::
ፊት ለፊት የተቻላችሁን ያህል ጥረታችሁንና ኃይላችሁን ተጠቅማችሁ

## ማጠቃለያ

በህዝብ ፊት ንግግር በማድረግ
ለደራሲው ተማሪዎች የሚሹትን ነገር ጠቅሰው ፅፈዋል::

1. በጥቂት ሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎች ሲያሣኩት የሚሹትን ነገር ጠቅሰው ፅፈዋል::
ላይ መሰልጠን እንደሚፈልጉና ሲያሣኩት ስሜታቸውን በቁጥጥር ሥር
ሁሉም በዋናነት የጠቀሱት ጉዳይ የመረበሽ ስሜታቸውን በቁጥጥር ሥር
ለማድረግ፣ ሃሣባቸውን ለመሰብሰብ እንዲችሉ በራስ የመተማመን ስሜት
ንግግር ለማድረግና በማንኛውም የቡድን ስብሰባ ፊት ቀለል ያለ ስሜት
እንዲሠማቸው ነው፣
2. ይህን የመፈፀም ችሎታም ለመቀዳጀት አስቸጋሪ አይደለም:: ለጥቂትና
ለተመረጡ ሠዎች ብቻም የሚሰጥ ገፀ-በረከት አይደለም፣ ልክ እንደጐልፍ
ጨዋታ ወንድ ሆነ ሴት ሣይል ማንኛውም ሠው በውስጡ ችሎታና ፍላጎት
እስካለው ድረስ አውጥቶ ሲያዳብረውና ሲያሣድገው ይችላል::
3. ብዙ ልምድ ያካበቱ ተናጋሪዎች ከግለሰብ ጋር ከሚነጋገሩ ይልቅ ብዙ ህዝብ
ባለበት ቦታ ሲሆን በደንብ ለማሠብና በደንብ ለመናገር ይችላሉ:: ብዙ ሰው
መኖሩ እነሱን ሲያነቃቃና ሲያነሣሣቸው ይችላል:: በሙሉ ዕምነት እዚህ
መፅሐፍ ላይ የተሰጡትን ምክሮች ብትከተሉ እናንተም የዚህ ልምድ ባለቤት
የምትሆኑበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም:: እናም የንግግር ማድረግ አጋጣሚዎች
ሲፈጠሩ በደስታ መንፈስ ትቀበሉታላችሁ::
4. የእኔ ጉዳይ ለየት ያለና ያልተለመደ ነው ብላችሁ አታስቡ:: ታላላቅ የሚባሉ
ብዙ ንግግር አዋቂዎች እንኳን በመጀመሪያ ሙከራቸው አድማጮቻቸውን
ከመፍራት የተነሣ በመርበድበድ ሽባ የሚያደርግ ስሜት እንደተሠማቸው
ገልፀዋል:: ከነዚህም መካከል ብርያን፣ ጂን ጃወረስ፣ ለዮድ ጆርጅ፣ ቻርለስ
ስቲዋርት ፓርኔል፣ ጂን ብራይት ፣ ጼዜራል ሼርዲንና ሌሎች ብዙዎች
ይገኙበታል::
5. ምንም እንኳን አዘውትረን የምንናገር ቢሆንም መጀመሪያ አካባቢ ላይ በዚህ
አይነቱ የፍራቻ ስሜት ውስጥ ማለፋችን አይቀርም:: ነገር ግን ለመናገር
በተነሣን በጥቂት ሰኮንዶች ውስጥ ሙሉ በሙሉ ብን ብሎ ይጠፋል፣
6. የመፅሐፉን ዋና ይዘት በፍጥነትና በጥልቀት ለመረዳት እነዚህን አራት
ነገሮች አስተውሉ፣

ሀ/ ጠንካራና ቀጣይነት ባለው የፍላጐት ስሜት መጀመር፤ እራሳችሁን የዚህ ችሎታ ባለቤት ማድረግ የሚያስገኝላችሁን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጠቀሜታቸው ማሠብ ስሜታችሁን ሲያነሣሣላችሁ ይችላል:: በገንዘብ ረገድ፣ በማህበራዊ ህይወታችሁና መሪ በመሆን ያላችሁን ተፅዕኖ በመጨመር ደረጃ ምን ትርጉም እንዳለው አስቡት:: የፍላጐታችሁን ጥልቀት ለመሻሻላችሁ ያለውን አስተዋፅኦ አስተውሉት

ለ/ ዝግጅት በማድረግ ምን እንደምትናገሩ በቅድሚያ ካላወቃችሁ በምንም ዓይነት በራስ መተማመን ስሜት አይኖራችሁም::

ሐ/ በራስ መተማመን ያለን አድርገን ማስመሰል የፕሮፌሰር ዊልያም ጀምስን ምክር በመጠቀም «ድፍረት እንዲሠማን ያለንን ፍላጐት ሁሉ እስከመጨረሻው አሟጠን በመጠቀም ድፍረት እንዳለን አድርገን ማስመሠል ነው:: እናም የጀግንነት ስሜት የፍራቻን ስሜት ገልብጦ ይቀመጣል:: ቴዲ ሩዝቬልትም በዚህ ተመሣሣይ ዘዴ የልባቸውን የግራ መደብ ያልተገራ ፈረስና ጥይት የሚታከሱ ሠዎች ፍራቻቸውን እንዳስወገዱበት አምነዋል:: እናንተም የአድማጭ ፍራቻችሁን ስነ-ልቦናዊ እውነት የሆነውን ይህን ዘዴ በመጠቀም ልትቆጣጠሩትና ልታስገዙት ትችላላችሁ::

መ/ መለማመድ፣ ይህ ከሁሉም በጣም ጠቃሚ የሆነው ነጥብ ነው:: ፍራቻ የእምነት ማጣት ውጤት ነው:: እምነት ማጣትን ደግሞ ምን ማድረግ እንደምንችል ያለማወቅ ሲሆን ይህም የሚከሰተው ከልምድ ማጣት ነው:: ስለዚህ ከጀርባችሁ ስኬታማ ልምዶችን እያስመዘገባችሁ ስትመጡ ፍርሃታችሁ ይወገዳል::

# ክፍል ሁለት

## በራስ መተማመንን ለማግኘት በቂ የሆነ ዝግጅት ማድረግ

ከ1912 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ባሉት ግዜያቶች በየዓመቱ ወደ ስድስት ሺህ የሚጠጉ ንግግሮችን መስማትና በእነሱም ላይ ሙያዊ አስተያየቱን መስጠት የዚህ መፅሐፍ ደራሲ ሥራው ያደረገውና በጣምም የሚያስደስተው ነገር ነበር።

እነኝህ ንግግሮች የሚዘጋጁት በሳል በሆኑ የንግድ ሠዎችና ባለሙያዎች ነበር እና ይህ ልምዱ አንድ ነገርን ከሁሉ በበለጠ ሁኔታ በጭንቅላቱ ላይ ተከትቦ እንዲቀር አድርጎታል። ይህም የቅድመ ንግግር ዝግጅት እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘብ እንዲሁም ሣይነገር መታለፍ የሌለበትን ነገር ማስደመጥ፣ ሊያስደንቀን የሚችል ነገርን መናገርና ግልፅና ነገሩን በትክክል ሊገልፅልን የሚችሉ ቃላትን መጠቀም ናቸው።

አንድ ሠው እየተናገረ እያለ መልዕክቱን በግልፅ እየተረዳንና እሱ በልቡ የሚያስበውና በአዕምሮው ወስጥ ያለው ነገር ከእኛ ጋር በቀና መንፈስ ልብ ለልብ እንዲገናኝ እንደፈለገ አይነት ስሜት ተሰምቶአችሁ አያውቅም? ይህ ንግግር የማወቅ ሚስጥር ከፊል ገፅታው ነው። ተናጋሪው እንደዚህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ልብ የሚደረግ ንግግር አድራጊ ከሆነ እውነተኛው ነገር ይገኛል። ማለትም ተፈላጊውን መልዕክት በንግግሩ ያስፈፅማል። ንግግሩም ቀንበሩ የላላ እና ሸክሙም የማይከብድ ይሆናል። በደንብ ዝግጅት የተደረገበት ንግግርም ከአስር እጅ ዘጠኙ መልዕክቱ ቀድሞ እንደተላለፈ ይቆጠራል።

በክፍል አንድ ላይ እንደተገለፀው ብዙ ሠዎች ስለንግግር ችሎታ ማዳበር ላይ ስልጠና መውሠድ የሚፈልጉት በራስ መተማመንን፣ ድፍረትንና በራስ መመካትን ለማግኘት እንደሆነ ሲገልፁ ብዙዎቹ በሚሠሩት ስህተት ደግሞ በንግግራቸው ላይ በቂ የሆነ ዝግጅት የማድረግን አስፈላጊነት በቸልታ ማለፋቸው ነው። የፍርሃትና የጭንቀት ብረት ለበስ ጦር፣ እርጥብ የሆነ የጥይት ፓውደር (ዱቄት) ባዶ ጥይቶችን ወይም ደግሞ ጥይቶችን ሣይዙ ወደ ጦር ሜዳ በመግባት እንዴት ሊያሸንፉና በቁጥጥር ሥር ሊያውሉ ይችላሉ። በእንደነዚህ አይነት ሁኔታዎች አድማጭ ፊት ሣይሆኑ እቤታቸው እያሉ ምርምር ለማድረግ ይረዳቸኋል።

አብርሃም ሊንከን ኋይት ሃውስ ውስጥ እያለ እንደተናገረው «ሳልሸመግል በፊት ምንም የምናገረው ነገር ሣይኖርና ሣልዘጋጅ እንዲሁም ምንም ውርደት ሣይገጥመኝ በትክክል መናገር እንደምችል አምናለሁ።»

በራስ የመተማመን ስሜትን ለማምጣት ለዚሁ የሚረዱ አሰፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ለምን በሥራ ላይ አታውሏቸውም? ሃዋርያው ዮሐንስ «ፍፁም ትክክለኛ የሆነ ፍቅር ፍርሃትን አሽቀንጥሮ ይጥላል» ብሎ እንደፃፈው ትክክለኛ የሆነ የንግግር ቅድመ ዝግጅት ማድረግ እንደዚያው ፍርሃትን አሽቀንጥሮ ይጥላል።

ዌብስተር በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገር « ሙሉ በሙሉ ሳይዘጋጁ ወደ አድማጭ ንግግር መቅረብ ግማሽ አካልን አራቁቶ ወደ ህዝብ ብቅ እንደማለት ይቆጠራል ይላል::»

ንግግሮቻችንን ለምን በከፍተኛ ጥንቃቄ አናደራጃቸውም? አንዳንዶቻችን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ምን ማለት እንደሆነና እንዴትስ ሊከናወን እንደሚችል የጠራ ግንዛቤ እንኳን የለንም:: ሌሎቻችን ደግሞ በጊዜ ማጣት እንዳልተዘጋጀንበት እንናገራለን:: ስለዚህ በቀጣዩ ክፍል ይህን ጉዳይ በስፋት እንዳስሰዋለን::

## ንግግር ለማድረግ መዘጋጀት ማለት ምን ማለት ነው?

መፅሐፍ ማንበብ ማለት ነው? ይህ አንዱ መንገድ ቢሆንም በጣም ምርጡ ዘዴ ግን አይደለም:: አንብቦ መዘጋጀት ሊረዳን ቢችልም ለምሳሌ አንድ ሰው ከመፅሐፍ ውስጥ የታጨቁ ሃሣቦችን መዞ በማውጣት ወዲያውኑ ልክ የራሱ ሃሣብ እንደሆነ አድርጎ ለሠዎች ቢናገር ይህ የሚያሣየው ጠቀሳላ ዝግጅታችንና አካሄዳችን አንድ የሚጎድለው ነገር እንዳለው ነው:: አድማጩ ምን እንዳጎደለ በግልፅ ማወቅ ባይችልም ተናጋሪውን ሠው በሞቀ ስሜት ሊከታተለው አይቻለውም:: ጉዳዩን በምሣሌ ለማሣየት ልሞክር፤ ከጥቂት ጊዜያቶች በፊት የዚህ መፅሐፍ ደራሲ በኒውዮርክ ለሚገኙ ባንኮች ለሚሠሩ የበላይ ኃላፊዎች በህዝብ ፊት ንግግር ስለማድረግ አንዳንድ ኮርሶችን ሰጥቶ ነበር::

እነዚሁ ሰዎች ንግግር ለማድረግ በቂ ዝግጅት አደረግን ብለው እንደሚያስቡት ለመሆን የሥራቸው ባህሪ አይፈቅድላቸውም:: ዕድሜያቸውን በሙሉ የግላቸው በሆኑ ሃሣቦች ተወጥረው፣ የራሳቸውን ፅኑ እምነት እየተንከባከቡ፣ ነገሮችንም በራሳቸው ለየት ያለ አመለካከት ብቻ እየተመለከቱ፣ ያልተበረዙና ያልተከለሱ የሚሏቸውን ልምዶች ለራሳቸው ብቻ ይዘው ይኖሩ ነበር:: በዚህ ዓይነት መልኩ ለአርባ ዓመታት ያህል ለንግግር የሚረዱ ግብዓቶችን በውስጣቸው ሲያከማቹ ቆይተዋል::

ነገር ግን ብዙዎቹ ይህን ጉዳይ ለመረዳትና ለመገንዘብ ከባድ ሆኖባቸው ነበር:: በጫካው ውስጥ ተደብቆ ያለውን የሚያንኮሻኩሸውን የፅድ ዛፍና መርዘኛ ቅጠል ማየት አልቻሉም:: ይኸው ቡድን አርብ አርብ በየሣምንቱ ከአስራ አንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ አንድ ሠዓት ድረስ ስብሰባ ይቀመጣል::

በአንዱ አርብ ምሽት አንድ በከተማው በሚገኝ ባንክ ውስጥ የሚሠራ ለዚህ መፅሐፍ ስንል ሚስተር ጃክስን ብለን የምንጠራው ሠው አስር ተኩል አካባቢ ሲሆን እዚህ ደርሷል:: ይህ ሠው ምን አይነት ንግግር ያደርግልን ይሆን?

ከቢሮው እንደወጣ ቡድኑ ለስብሰባ ወደተቀመጠበት የፌደራል ሪዘርቭ ባንክ ሲመጣ እግረ መንገዱን ከመተላለፊያው አካባቢ የፎርብስ መፅሔትን አንድ ቅጅ ገዝቶ መጥቷል:: ከዚህ መፅሔት ላይ አንድ «ለስኬት ለመብቃት አስር ዓመታት ብቻ ይቀሩሃል» የሚል አንቀፅ በማወጣት የርዕሱን ሃሣብ ስለወደደው ሣይሆን በአንድ ነገር ላይ ንግግር ማድረግና የራሱን ተራ ማሣለፍ ስላለበት ብቻ እያነበበ ለመዘጋጀት ይሞክር ጀመር:: ከአንድ ሠዓት በኋላም የእሱ ተራ ደረሰና ተነስቶ

በመቆም በሚስብና አሣማኝ በሚመስል መልኩ በዚሁ ሃሳብ ላይ ንግግር ማድረግ ጀመረ:::

ይህን ተከትሎ የሚመጣው ውጤት ምን ይመስላችኋል?

ለመናገር የሚሞክረው ነገር በደንብ አድርጎ አስኪዋሃደው ድረስ አላብላላውም ነበር:: «ለመናገር የሚሞክረውን» ይህ አባባል ነገሩን በተለየ ሁኔታ ይገልፀዋል:: ምክንያቱም ከውስጡ የሚወጣና ማብራሪያ የሚፈልግ እውነተኛ መልዕክት አልነበረውም:: ስለዚህም አጠቃላይ የሆነ የንግግርፀባይ እንዲሁም የድምፁ ቃና ያለምንም ስህተት ይህን ያሳብቁበት ነበር:: የእራሱን እውነተኛ ስሜት በንግግሩ ለማሣየት ሣይችል አድማጮቹ በእሱ ንግግር እንዲደነቁ እንዴት ሊያደርግ ይችላል?

የፎርብስ መፅሔትን አንቀጽ ደግሞ ደጋግሞ እየጠቀሠና ፀሃፊውን በስም እየጠራ እንዲህ እና እንዲያ ሲል ይቆያል:: ነገር ግን በዚህ ሃሳብ ውስጥ የመፅሔቱ አስተያየት ከመጠን በላይ ተንፀባረቀበት እንጂ ሚስተር ጃክሰን በፍፁም በቦታው አልነበረም::

እናም የዚህ መፅሐፍ ደራሲ እንዲህ በማለት ችግሩን ሊያሣየው ሞከረ «ሚስተር ጃክሰን እኛ እኮ ይህንን የምትናገረውን ፅሑፍ ስለፃፈው ሠው ስብዕና በግርድፉ መስማት ሊያስደስተን አይችልም:: እሱ እዚህ ባለመኖሩም ልናገኘው አንችልም:: ነገር ግን ያንተ የሆኑ ሃሳቦችንና በራስህ ዙሪያ የምትናገራቸውን ነገሮች ለመስማት እንፈልጋለን:: የሌላ ሠው ሃሳብ ያልሆኑትና አንተ በግልህ የሚሰማህን ነገር ንገረን:: ሚስተር ጃክሰንንም በደንብ በጉዳዩ ላይ አሣትፈው! እንደውም ይህንን ርዕስ ለምን በሚቀጥለው ሣምንት አንወያይበትም? ለምንስ ጉዳዩን ካነበብከውና በደንብ ካጠናኸው በኋላ ከፅሑፉ ደራሲ ጋር መስማማት አለመስማማትህን ለማወቅ ለምን እራስህን አትጠይቅም? የምትስማማበት ሃሳብ ካለው የሱን አስተያየት ከራስህ ልምድ አንፃር ለማየትና ለመገምገም ሞክር:: በሃሳቡ የማትስማማም ከሆነ ለምን ልትስማማበት እንዳልቻልክ ንገረን:: ይህን ርዕስም በመንተራስ ለመጀመሪያ ጊዜ የራስህን ንግግር ለማዘጋጀት እንደ መነሻ ነጥብ ተጠቀምበት::»

ሚስተር ጀክሠን ይህን አስተያየት በመቀበል አስፈላጊውን ምርመራ በየአንቀጹ ላይ ካደረገ በኋላ በፍፁም ከፀሃፊው ጋር እንደማይስማማ ተረዳ:: ቀጣይ ንግግሩን ለማድረግም እንደቀድሞው በመተላለፊያው ላይ ቁጭ ብሎ እያነበበ ለመዘጋጀት አልሞከረም:: በደንብ እንዲዳብርና እንዲያብብ አደረገው:: ከአዕምሮው የተወለደ ልጅ ሆነ:: ሃሳቡ እያደገና እየዳበረም ልክ ከአብራኩ የሚፈጠር ልጅ እንደሚያድገው ሆነ:: ልክ ሴት ልጅም ሣናስተውላት እድገቷ እንደሚጨምር በየቀኑና በየምሽቱ ይጨምር ጀመር አንድ ጋዜጣ ላይ የተፃፈ አስተያየት ሲያነብ የሆነ ሃሳብ አዕምሮው ወስጥ ዘው ብሎ ይገባል:: ከጓደኞቹ ጋር በዚሁ ርዕስ ላይ እየተጨዋወተ እያለ ደግሞ ባልጠበቀው ሁኔታ የጉዳዩን ሥዕላዊ መግለጫ ያገኘዋል::

በቀሩት የሣምንቱ ቀናቶችም ነገሩን እያመላለሠ ሲያጤነው በይዘት እየጠለቀ ፣ እያደገ፣ እየተለጠጠና እያበጠ ይሄድ ጀመር:: ታዲያ በሚቀጥለው ጊዜ ሚስተር ጃክሰን በጉዳዩ ላይ ንግግር ሲያደርግ ከአዕምሮው ማዕድን ማውጫ

ተቀፍሮ እንደወጣ ብረት ፤ ለራሱ የገንዘብ ማምረቻ ተጠፍጥፎ እንደተሠራ ማንቲም የራሱ የሚለው ነገር ነበረው:: ከፀሃፊው ሃሣብ ጋር ባለመስማማትም በደንብም አድርጐ ሲተነትነውና ሲያብራራው ችሏል:: አንድን ሠው ለንግግር በማነሣሣትና በስሜት ውስጥ እንዲገባ በማድረግ በኩልም የዚህኛው ወገን የተቀናቃኝነት መንፈስ መኖሩን የሚያክል ነገር የለም:: እጅግ በማይታመን መልኩ ከአንድ ሠው አቀራረብ የተደመጠ ተፃራሪና ተቃራኒ የሆኑ ሁለት ንግግሮችን ተመሣሣይ በሆኑ ሃሣቦችና ርዕሶች በተመሣሣይ አይነት ከ15ቀን በኋላ ባለው የስብሰባ ምሽት ልናዳምጥ ችለናል:: ከዚህ በሁለት ሠዎች የቀረበ እስኪመስል ድረስ መለያየት ከታየበት ንግግር መገንዘብ የምንችለው በትክክለኛ መልኩ መዘጋጀት ያለውን ከፍተኛ ጥቅም መሆኑን ነው::

እስቲ አሁን ደግሞ ይህን ችሎታ ለመከወን ሲያስችሉን ወይም ደግሞ ሲከለክሉን የሚችሉ ነገሮችን የሚያሣይ አንድ ምሣሌ እንመልከት::

ለዚህ ፅሑፍ ሚስተር ፍላይን ብለን የጠራነው ግለሰብ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ውስጥ የንግግር ችሎታን በማዳበር በሚሰጠው ኮርስ ተማሪ ነበር:: አንድ ቀን ከቀትር በኋላ የአሜሪካን ዋና ከተማ በጣም በሚያሞግስ መልኩ ንግግር አድርጐ ነበር:: ንግግሩን በችኮላና ጥልቀት በሌለው ሁኔታ የቀዳው አንድ ጋዜጣ ከሚያስራጫቸው አጫጭር መጣጥፎችና በራሪ ወረቀቶች ነው:: ስለዚህ ድርቅ ያሉ የተበታተኑ ሃሣቦች የሞሉበትና ያልተብላሉ ሆነውበት ነበር:: በጉዳዩ ዙሪያም ጊዜውን መስዋዕት አድርጐ እንዳላሰበበት ያስታውቃል:: የራሱን ጥልቅ የሆነ ስሜት ለማሣየት ካለመቻሉም በላይ የሚናገረውን ነገር እራሱ እንደሚያምንበት አድርጐ ማብራሪያ ለመስጠትና ለመግለፅ አልቻለም::

ስለዚህም አጠቃላይ ንግግሩ ፍሬ ነገር የሌለው፣ አሰልቺና ጣዕም አልባ የሆነና ውጤቱም በኪሣራ የተጠናቀቀ ነበር::

## ሊሠናከል ያልቻለው ንግግር

ይህ ከሆነ ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ሚስተር ፍላይንን ከልቡ ያሣዘነው አንድ ነገር ተከሰተ:: ይኸውም መኪናው ከጋራዥ የመሰረቋ ጉዳይ ነበር:: ወዲያውም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ ጉዳዩን ካመለከተ በኋላ መኪናውን ላገኘለት ሠው ወሮታውን እንደሚከፍል ገለጠ:: ነገር ግን ምንም ፋይዳ አልነበረውም:: ፖሊሶችም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያለው የወንጀል መበራከት ከአቅማቸው በላይ እንደሆነና ሊቆጣጠሩት እንዳልቻሉ በማመን ገለፁለት::

ይሁን እንጂ ከዚህ ክስተት አንድ ሣምንት በፊት መኪናውን ከተፈቀደው ሠዓት ከአስራ አምስት ደቂቃ በላይ አቁመሃል በማለት ቦታው ላይ በጠመኔ ምልክት በማድረግ አስቀጥተውት ነበር:: እነዚህ «ባለ ጠመኔ ፖሊሶች» በጣም ሥራ ስለሚበዛብን ወንጀለኞቹን ለመቆጣጠር አልቻልንም:: ማለታቸው በጣም እንዲቆጣ አደረገው:: ፍትህ በማጣቱም በጣም ተበሣጨ:: በዚህ ጊዜ ታዲያ የሚናገረው ነገር አገኘ:: እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ አንድ ጋዜጣ ካሠራጨው ፅሑፍ የተነሣ የተወሠደ ሣይሆን በራሱ ላይ ከደረሠውና በጣም ካናደደው ነገር

የመነጨ ነበር:: የእውነተኛ ማንነቱ ከውስጡ እየተንቀለቀለ ከሚወጣ ቁጭት የመነጨ ነበር:: የእውነተኛ ማንነቱ ከውስጡ እየተንቀለቀለ ከሚወጣ ቁጭት አካል የሆነ ስሜቱ እንዲነሣሣና ዕኑ እምነቱ እንዲታይበት ያደረገው ንግግር በዚህ ሁኔታ ነበር የተገኘው::

የዋሽንግተን ዲ.ሲ. ከተማን በጣም እያወደሰ የተናገረበት ንግግሩ ዓረፍተ ነገሮችን የሚያወጣቸው ተራ በተራ እያማጠ ነበር:: አሁን ግን ማድረግ ያስፈለገው ነገር ቢኖር ተነስቶ በመቆም ለንግግር አፉን መክፈት ብቻ ነው:: የፖሊሶቹን ድርጊት በማማረር የጀመረው ንግግር እየጠነከረ እንደ እሳተ ጐመራ ሲንተከተክ ችሏል::

እንዲህ ዓይነት ንግግር ማስረጃና ትንታኔ ሲቀርብበት የሚችልና ሲሰናከል የማይችል ነው:: ያለፈው ጊዜ ተሞክሮአችንና ከጥልቅ ሃሣባችን የመነጨ አስተያየት ድምር ውጤት ነውና::

## መዘጋጀት ማለት ምን ማለት ነው?

ለንግግር ዝግጅት ማድረግ ማለት በቃል ያጠናናቸውን ወይም ተፅፈው የተቀመጡ የቃላት ስብስቦችን ሣይሣሣቱ እያዳበሩ መናገር ማለት ነውን? አይደለም:: ከፊል በሆነ መልኩ የማንቀበላቸው ሃሣቦችና በድንገት የሚመጡልንን አስተያየቶች አሰባስቦ ማጥናት ማለት ነው? ይህም ፍፁም አይደለም:: ምክንያቱም ዝግጅት ማድረግ ማለት ከውስጥ ካለ ስሜት የሚመነጩ አስተያየቶችን ሃሣቦችንና ውጥረት ውስጥ ከከተቱን ድርጊቶች የሚመጡ ልምዶችን ባጠቃላይ ሠብስቦ መያዝ ማለት ነው::

ልንናገራቸው የምንፈልጋቸው አጣዳፊ የሆኑ ሃሣቦችና ጉዳዩች ሁሉ በየዕለቱ እየመጡ ያስቃዩናል:: አጠቃላይ የሆነው አኗኗራችን በገጠመኞችና በስሜታዊ ሁኔታዎች የተሞሉ ናቸው::

እነዚህ ሁሉ ነገሮች ንቁ ባልሆነው የአዕምሮአችን ክፍል ውስጥ ትንንሽ ጠጠሮች በወንዝ ዳርቻዎች ተከብረው እንደሚኖሩ ሁሉ አበረውን ያሉ ናቸው :: ዝግጅት ማድረግ ማለት እነዚህን ሃሣቦች ፈልፍሎ ማውጣት፣ ማስታወስ፣ በፈለግናቸው ሠዓትም የሚጠቀሙንን መለየት፣ ማስታወስ፣ መልክ እየሰጡ ማዘጋጀትና እራሳችን እንደሣልነው የግድግዳ ስዕል በደንበ ማወቅ ማለት ነው:: ይህ መቼም አስቸጋሪ አይመስለኝም ያስቸግራል እንዴ? ቀላል ነው:: ማድረግ የሚጠበቅብን ነገር ቢኖር ትንሽ ትኩረት ሰጥቶ ማሰብና ዓላማ አድርጐ መያዙ ነው::

ድዋይት ኤል ሙዲ በህዝብ ፊት ያደረጋቸውን ንግግሮች በመሠብሠብና በማዘጋጀት እንዴት መንፈሣዊ ታሪክ ሊያደርጋቸው ቻለ? በጉዳዩ ላይ ሲጠየቅም የሠጠው መልስ «ምንም ሚስጥር የለውም» ብሏል:: የሚል ነበር::

አንድ ርዕስ ለንግግሬ ስመረጥ በትልቅ የደብዳቤ ማሸጊያ ፖስታ ጀርባው ላይ የመረጥኩትን ርዕስ እፅፍበታለሁ:: እንደዚህ አይነት የደብዳቤ ፖስታ ብዙ ስላሉኝም በማንኛውም ጊዜ ሣነብ የማገኛቸውን ነገሮችና እኔ ንግግር ለማድረግ ከመረጥኩት አርዕስት ጋር የሚገናኙትን ሃሣቦች እመዘግብና በተዘጋጁት

ጋሴታ ዎን ውስጥ በማስገባት፡፡ እዚያው ይቀመጣሉ፡፡ ሁል ጊዜ ማስታወሻ ደብተር አይለየኝም እናም ስብከት በማዘጋጅ ጊዜ የምሰማቸውን ከርዕሱ ጋር የሚሄዱትን ሃሳቦች ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ነገሮችን አመዝግቤ በተዘጋጀው ጋሴታ ውስጥ እጨምራቸዋለሁ፡፡ ምናልባትም አንዳንዶቹ ከዓመታት በላይ እዚያው ይቀመጣሉ፡፡ አዲስ የስብከት ፕሮግራም ሲኖርም እዚያ ከተቀመጡት ካሉት ጋር የእራሴ ጥናት የሆኑና አዲስ የማገኛቸውን ነገሮች ጨምሬ ይዤ እሄዳለሁ፡፡ በዚህ መሠረት ብዙ የመረጃ ክምችቶች ሲኖሩን ትሰጣለች፡፡ ሁል ጊዜ ሩሴ ወደማዘጋጀው የስብከት ፕሮግራሞች ስሄድ የማጨምረውን በመጨመር የሚቀንሰውን በመቀነስ አስተካክለዋለሁ፡፡ በዚህም መንገድ ሁሉም ከጊዜው ጋር የሚሄዱ፣ የማያረጁና አዲሶች ይሆናሉ፡፡

## የያሌው ዲን ብራውን ጥበባዊ ምክሮች

የያሌ መንፈሳዊ ት/ቤት የተመሠረተበት የመቶኛ ዓመት በዓል በሚከበርበት ወቅት የት/ቤቱ ዲን ዶ/ር ቻርለስ ሬይኖልድስ ብራውን ስለስብከት ጥበብ በሚመለከት ተከታታይ የሆኑ ትምርህታዊ ገለፃዎችን አድርጎ ነበር፡፡ እነዚህ ትምህርቶችም ነው ዮርክ በሚገኘው ማክሲሚለን ኩባንያ አማካኝነት በመፅሐፍ መልክ ታትመው ነበር፡፡

ዶ/ር ብራውን እራሱ ከሠላሣ ዓመታት በላይ ትምህርታዊ ንግግሮችን ሲያዘጋጅና ሌሎችን በዚህ ዘርፍ እንዲያዘጋጁ ሲያስለጥናቸው ቆይቷል፡፡ ስለዚህም ያለበት የኃላፊነት ቦታ ጥበባዊ ምክሩን በጉዳዩ ላይ እያስተላለፈ እንዲያስተምር አስችሎታል፡፡ ይህ ምክሩ ታዲያ በዘጠና አንደኛው የዳዊት መዝሙር ላይ ጥናታዊ ፅሑፍ ለሚያዘጋጅም ሆነ በአንድ የጫማ ፋብሪካ ውስጥ ለሚሠራና ለሠራተኛ ማህበሩ አባላት ንግግር ለማድረግ ለሚዘጋጅ ሠው እጅግ በጣም ጠቃሚ ነበር፡፡

ስለዚህም ቀጥሎ የዶ/ር ብራዉንን ትምህርቶች በነፃነት እጠቅሳለሁ፡፡ «የመረጣችሁትን አርዕስትና መፅሐፋችሁን በጥልቀ መርምሩ፡፡ መልስ እስኪሰጧችሁና እስኪበስሉ ድረስም ታቀፏቸው፡፡ ከዚህ በኋላም እጅግ በጣም የሚማርኩና ተስፋ ሰጪ የሆኑ ሃሣቦችን ልክ ጀርሞች በአንድ ቦታ ውስጥ ታሽገው በመቆየት ተፈልፍለው ወደ ሌላ ቦታ ተሰራጭተው እንደሚያድጉ ሁሉ በመንጋ ፈልፍላችሁ ታወጧቸዋላችሁ . . . ይህ ሂደት ለረጅም ጊዜ ዝም ብሎ የሚቀጥል ቢሆንና እሁድ የማቅረቢያ ጊዜ በመሆኑም የመጨረሻ ዝግጅታችሁን የምታደርጉትም እስከ ቅዳሜ ከሠዓት ብቻ ባለው ጊዜ ባይሆን እንዴት ጥሩ በሆነ ነበር፡፡ አንድ የቤተክህነት አገልጋይ የሆነ ሰው እውነታዎችን በአዕምሮው ይዞ ለአንድ ወር፣ ከስድስት ወራት፣ ምናልባትም ለዓመታት ቢቆይ ስብከቱን ከማድረጉ በፊት ያሣለፋቸው ጊዜዎች አዳዲስ ሃሣቦች እየፈለቁ በመውጣት በቂ የሆነ እድገት ሊያሣዩ ይችላሉ፡፡

በመንገድ ላይ እየተጓዘ ሊያብሰለስላቸው ወይም በባቡር ላይ ተሣፍሮ ሲጓዝ በሚያሣልፋቸው ሠዓታት አይኑ እስኪደክም ድረስ ሊያነባቸው ይችላል . . . አንድ አገልጋይ በተለምዶ የቤተክርስቲያን ትምህርቱን ወይም ስብከቱን ወደ አልጋው ይዞ መሄዱ የሚመከር ባይሆንም ማታ እቤቱ ቁጭ በሚልባቸው

ጊዜያት እየመረመረ ሊያያቸው ይችላል:: አውደ ምህረት ለሰበካ ትምህርት የሚመች ቢሆንም ጥሩ የመኝታ አጋር አይደለም:: ነገር ግን እንዲህም ሆኖ አልፎ አልፎ በእኩለ ለሊት ተነስቼ ድንገት የሚመጡልኝን ሃሣቦች ጠዋት ልረሣቸው እችላለሁ በማለት ሰፌ አስቀምጣቸዋለሁ:: ለአንድ የተለየ የስብከት ፕሮግራም መረጃዎችን ለማሰባሰብ ስትዘጋጁ የሚመጡላችሁን ሃሣቦች በሙሉ አርዕስቱንና ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ፃፏቸው:: መፅሐፉን ስትመርጡ በቅድሚያ ምን እናገኝበታለን ብላችሁ እንዳሰባችሁ ፃፉ:: አሁን የተከሰተላችሁንና ተያያዥ ሃሣቦችንም አስፍሯቸው:: ያለማንም ሰው እርዳታ አምጣችሁ የወሰዳችሁትን ሃሣብ በሙሉ ዘርዝራችሁ ፃፉት:: እነዚህ ሃሣቦች አዕምሮአችን ግልጋሎቱን ሃሣብ በመሉ ዘርዝራችሁ ፃፉት:: እነዚህ ሃሣቦች አዕምሮአችን ግልጋሎቱን

ሃሣብ በመሉ ዘርዝራችሁ ፃፉት:: እነዚህ ሃሣቦች አዕምሮአችን ግልጋሎቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያደርጉና ደማቅ ቀለም ካለው ዳይመንድ ጌጥ ወይም እጅግ ከከበሩ ወርቆች የተሻሉና ውድ ናቸው ባገኛችሁትና እጃችሁ በገባው ቁራጭ ወረቀት፣ የድሮ ደብዳቤ ጀርባ ላይ፣ የፖስታ ከረጢት ቅዳጅ የሽንት ቤት ወረቀቶች ላይ ሁሉ መፃፍ ትችላላችሁ:: ይህም የማይረባ ነገር በንፁህ በረጅምና ቆንጆ በሆነ ነገር ላይ ከመፃፍ አስር እጅ ይሻላል:: እንዲህ ያደረጋችሁት በገንዘብ ማጣት ስላልሆነ በኋላ ላይ ጊዜ ስታገኙና እንደዚህ በተበታተነ ሁኔታ ያስቀመጣችሁት መረጃዎች አደራጅታችሁና አቀናጅታችሁ ማሰባሰብ ትችላላችሁ::

በአዕምሮአችሁ የመጣውን ሃሣብ አንድም ሣታስቀሩ በፅሑፍ አስፍሩ እግረ መንገዳችሁንም በደንብ ታስቧቸዋላችሁ:: ይህን ሂደት ማቃኮል የለባችሁም:: ይህን ወሳኝ የሆነ አዕምሮአዊ የሽግግር ወቅት እራሳችሁ ብቻ ባለመብት የሆናችሁበት ድርጊት ነው:: ይኸው መንገድም አዕምሮአችሁ እንዲዳብርና ወደ እውነተኛ አምራች ኃይልነት እንዲለወጥ ያደርገዋል::. . .

ከሥጠሃቸው ስብከቶችና ትምህርቶች በመሉ እጅግ አድርገህ የተደሰትክባቸውና በሠዎች ዘንድ በጣም ጥሩ እንደሆኑ የተነገሩህ በአብዛኛው ከውስጥህ አንጠፍጥፊህ በወጣው ያስተማርካቸውና ያሰብካቸው ይሆናሉ:: ከአጥንትህ የተሠነጠሩ ከሥጋህ የተቆረጡ የአዕምሮህ አብራክ የፈጠራቸውና የራስህ የሆኑ የፈጠራ ውጤቶችህ ናቸው:: በአብዛኛው መረጥ መረጥ ተደርገው የመጡና የተገለበጡ ስብከቶች ጣዕማቸው የተበላሸ እና እጅ እጅ ያለ–ይሆናል::

በቤተ-መቅደስ ውስጥ እየጨፈሩና እየዘመሩ እንዲሁም ጌታን እያመሰገኑ የሚተላለፉት ስብከቶች ከሠዎች ልቦና ወስጥ ሰተት ብለው በመግባት እንደወፍ ብረሩ የሚያሰኛቸው በግዴታ ሣይሆን በገዛ ፈቃዳቸው የሚያራምዷቸው ናቸው:: ራሣቸውን ስተው እንዲዝለፈለፉ የሚያደርጉ ስብከቶች የሚመነጩት ታላቅ በሆነ ሃይል ተሞልቶ ከውስጥ በሚተነፍሷቸው ሠው አማካኝነት ነው::

## ቢንከን ንግግሩን እንዴት ነው ያዘጋጀው?

እንደ ዕድል ሆኖ ተጨባጭ የሆኑትን ነገሮች በማወቃችን እዚህ ሲንከን የሚጠቀምባቸው ቅድመ ሆኔታዎችና ዲን ብራይ በትምህርቱ የሚጠቀምባቸው መመሪያዎች ምንም እንኳን ሲንከን ከሦስት ምዕተ ዓመታት በፊት በሥራ ያዋላቸው ቢሆኑም ተመሣሣይ ነበሩ:: ሲንከንን ዝነኛ ካደረጉት ንግግሮቹ መካከል ይህ እንደ ነብይ አይነት በሚመስለው መልኩ ያወጀው ይገኝበታል:: በአንድ



Scanned with CamScanner

«መንግሥት ውስጥ ግማሹ በባርነት ግማሹ በነፃነት የሚኖርበት ለዘለዓለም ፀንቶ ሊቆይ አይችልም፡፡ እርስ በእርሱ የተከፋፈለ ቤት ፀንቶ ሊቆም እንደማይችል የታወቀ ነውና፡፡

ይህን ንግግር ወደተለመደው ሥራው ሲሄድም ፣ በበረት ተቀምጦ ላም ሲያልብ፣ ወደ ሥጋ ቤት ሲያመራ፣ ምግቡን ሲመገብ፣ ለመግዛት ሲሄድ፣ መጠጥ ቤት ሲገባ፣ ረጅሙን የአንገት ልብሱን እያደረገ፣ የገበያ ቅርጫቱን በእጁ እንደያዘ፣ ትንሽ ልጁን ከኮት አድርጎም፣ ወደሰት ዕቃ ሆነ ጥያቄ ሲጠይቅ፣ ሲናደድና ረጃጅምና አጥንታም የሆኑ ጣቶቹን እያወናጨፈ አባቱ እንዲያናግረውጥረት በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ እያብሰለሰለው ነበር፡፡ ነገር ግን ሊንከን ሲያደባ ነበር፡፡ በራሱ ሃሳብ ውስጥም ንግግሩን ሲያስብ የልጁን መፈጠር እንኳን ረስቶት ነበር፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜም ይህን ሃሳቡን ታቅፎ እስኪፈለፍለው ድረስ አጫጭር ማስታወሻዎችን፡፡ ቁርጥራጮችንና አረፍተነገሮች እዚህም እዚያም በማያገኛቸው የፖስታ ከረጢት የወረቀት ቁርጥራጮች ከትልቅ የወረቀት ከረጢት በተቦጨቁ ቁራጮችና በአቅራቢያው ባገኛቸው ነገሮች ላይ ሁሉ ይፅፍ ነበር፡፡ እነዚህንም በከፍያው ቀዳዳ ውስጥ ይወሽቃቸውና ይሄቸው በመቦር ጊዜ ሲያገኝ ቁጭ ብሎ በሥርዓት እያዘጋጀ እየከላለሰና ቅርፅ እየሰጣቸው ለህትመትና ለሥርጭት እንዲበቁ ያስችላቸው ነበር፡፡

በ1885 በተካሄደው የሁለትዮሽ የምርጫ ክርክር ጊዜ ሴናተር ዳግላስ በየሄደበት ሲናገራቸው የነበሩ ንግግሮችን ደ'ሞ ሲመጣ ሊንከን ግን ቀለል ባለ ሁኔታ ማቅረብ እስከሚችል ድረስ ሲያጠና፣ ሲመረምርና መልሶ ሲናገራቸው ነበር፡፡ ይህም እንደተናገረው ሁልጊዜ ያለፈ ንግግርን ከመደጋገም ይልቅ አዲስ የሆነውን ንግግር በየቀኑ ማዘጋጀት የተሻለ መሆኑን ነው፡፡ በዚህም የታሠበው ርዕስ እየተለጠጠና እስከወደፊቱም በአዕምሮው ውስጥ እየሰፋ ይመጣ ነበር፡፡ በምርጫ አሸንፎ ወደ ኋይት ሃውስ ከመግባቱ በፊትም የህገ መንግስቱን ቅጂ እንዲሁም ከዚህ በፊት የተደረጉ ሦስቱን ንግግሮቹን ብቻ ለማስተያያ በመያዝ ስፕሪንግ ፊልድ በሚገኝ አንድ ቆሻሻና አቧራማ በሆነ የሱቅ ጓዳ ውስጥ ገባ እናም እዚያ ማንም ጣልቃ ሣይገባበትና ሣያቋርጠው የበዓል ሰዓቱን ንግግር ሊፅፈው ቻለ፡፡

ሊንከን የጌትስበርግ ንግግሩን እንዴት ነው ያዘጋጀው? እንዳለመታደል ሆኖ በዚህ ጉዳይ ላይ የሀሠት ዘገባዎች የተሠራጩ ቢሆንም እውነተኛው ታሪክ በጣም አስደናቂ ነበርና እስቲ እንመልከተው፡፡

የጌትስበርግ መካነ መቃብር ኃላፊዎች ለሠማዕታት የመታሠቢያ በዓል ለማድረግ በሚዘጋጁበት ጊዜ ኤድዋርድ ኤቨርትን ንግግር እንዲያደርግ ጋብዘውት ነበር፡፡ ኤቨርት የቦስተን ሚኒስቴር፣ የሃርቫርድ ፕሬዚዳንት፣ የማሳቹስቴስ አገር ገዢ፣ የአሜሪካን ሴናተር፣ በእንግሊዝ የአሜሪካን ልዑክ፣ የውጭ ጉዳይ ሚንስትርና በአሜሪካን ከታዩት ብቃት ካላቸው ንግግር አዋቂዎች መካከል እንደ አንዱ የሚቆጠር ነበር፡፡ የመታሰቢያው በዓል በመጀመሪያ ሊደረግ የነበረው በጥቅምት 23,1863 ነበር፡፡ ሚስተር ኤቨርት ግን ብልሃት በተሞላበት ሁኔታ በዚህ

አጭር ጊዜ ውስጥ ንግግር ለማዘጋጀት እንደማይቻለው ገልጾ እንቢታውን አሣየ:: ስለዚህም የመታሰቢያ በዓሉ ከአንድ ወር በኋላ ማለትም ለህዳር 19 እንዲተላለፍለት ተደረገ::

ከተጨመሩለት ጊዜያቶች መካከልም የመጨረሻዎቹን ጊዜያቶች ያሳለፈው እዚያ ቦታ ስለተካሄደው ነገር በመመራመር ከጉዳዩ ጋር ለመለማመድ በመሞከር ነበር:: በመሆኑም ጉዳዩን እየፈለፈለና እየመረመረ ማሰቡ እጅግ በጣም ጥሩው የመዘጋጃ መንገድ ነበር:: ልክ በጦር ሜዳው ላይ ያለም መሠለው:: ለኮንግረስ አባላት፣ ለፕሬዝዳንቱና ለካብኔዎቹ በበዓሉ ላይ እንዲገኙ የሚጋብዝ የጥሪ ካርድ ተበተነ:: አበዛኛው የግብዣ ጥሪ ተቀባይነት ባያገኝም ሊንከን ለመገኘት መስማማቱን ሲያሳውቅ የኮሚቴው አባላት ተገረሙ:: ንግግር እንዲያደርግላቸው መጋበዝ አለባቸው እንዴ? መጀመሪያ እንደዚህ ያለ ሃሣብ ፈፅሞ አልነበራቸውም:: በዚህ የተነሳ ብዙ ተቃውሞዎች ይመጡ ጀመር:: ገሚሶቹ የሚሉ ሲሆኑ ጊዜ ቢያገኝና ቢዘጋጅስ በጉዳዩ ለመዘጋጀት በቂ ጊዜ አይኖርም:: ላይ ንግግር ለማድረግ ችሎታው አለውን? በእርግጥም እውነት ነበራቸው:: ባርነትን በመቃወም ባደረጋቸው ንግግሮቹ ወይም ደግሞ የሱፐር ማህበራትን በተመለከተ ባደረገው ንግግር በብቃት መወጣት የቻለ ቢሆንም ማንም ሠው ቢሆን በዚህ የሠማዕታት መታሰቢያ ዝግጅትን በመሣሠሉት ላይ ንግግር ሲያደረግ ሰምተውት አያውቁም ነበር:: ይህ ጉዳይ ጠለቅ ያለ ሃዘንን የሚገልፁበት ለየት ያለ ጉዳይ ነበር:: ይህን ዕድል ለመጠቀም መወሰን ስላቃታቸው እንዲናገር እንጠይቀው ይሆን? በማለት አወጡ አወረዱ:: ነገር ግን የወደፊቱን ማየት ቢችሉ የዚህን ሠው ችሎታ እንደዚህ በጥያቄ ምልክት ያስቀመጡትና የተጠራጠሩት ምን አይነት አጠቃላይ ተቀባይነት ያለው፣ ከምንጊዜዎቹም ምርጥ በላይ የሆነ፣ ዘላለማዊ የሆነ የንግግር መልዕክቶች ሚች ከሆነ ሠው ከንፈሮች መካከል መውጣታቸውን ቢያውቁ እንዳሁኑ አንድ ሺህ ጊዜ ማሠብ ባላስፈለጋቸው ነበር::

በመጨረሻም ለበዓሉ አስራ አምስት ቀናት ሲቀሩት ለሊንከን «ጥቂት ተስማሚ የሆኑ አስተያየቶችን» በበዓሉ ላይ አሠማልን ሲሉ ዘገየ የሚባል መልዕክት ላኩለት:: የተጠቀሙበት ቃል በትክክልም «ጥቂት ተስማሚ የሆኑ አስተያየቶች» የሚለውን ነበር:: እስቲ አስቡት ለአንድ የአሜሪካን ፕሬዝዳንት ለሆነ ሠው እንደዚህ ዓይነት መልዕክት መፃፍ:: ሊንከን ግን ወዲያውኑ ነበር ዝግጅቱን የጀመረው:: ለኤቨርት ደብዳቤ በመፃፍም ይህ ታሪካዊ ተንኸ ሊያደርገው ያዘጋጀውን ንግግር ቅጅ አስመጣ:: ከአንድ ሁለት ቀን በኋላ ደግሞ ወደፎቶ ቤት በመሄድ ከእሱ ጋር ተነሣ:: የኤቨርትን ጽሁፍ በመያዝ በፎቶ ስቱዲዮ ተቀምጦ እረፍት ሲኖረው ያነበው ነበር:: ንግግሩንም በቀናት ያብላላው ጀመር:: ከኋይት ሃውስ ወደ ክፍለ ጦሩ ቢሮ ሲመላለስ በትልቁ የጦሩ ቢሮ ሶፋ ላይ ተቀምጦ የቴሌግራም መረጃዎችን በሚጠባበቅበት ጊዜ ሁሉ ያብሰለስል ነበር:: የንግግሩ አንኳር የሆኑ ሃሣቦችን ከትልቅ ወረቀት ላይ በቀደደው ቁራጭ ከፃፈ በኋላ ከረጅሙ የሃር ባርኔጣው ውስጥ በመክተት ይዞት መዞር ጀመረ:: ብዙም የተጨነቀ ሣይመስልና ሣያቋርጥ እያሰበበት ቅርፅና መልክ እያስያዘው ይመጣ ጀመር::

ለበዓሉ አንድ እሁድ ብቻ ሲቀረውም ኖሐ ለሚባል መፃህፍት አሣታሚ እንዲህ ከሚል ማስታወሻ ጋር ላከለት «በትክክል ተፅፏል ብዬ አላምንም። ለማንኛውም አልጨረስኩትም፤ ከአንዴም ሦስት ጊዜ በላይ ደጋጋሚ የፃፍኩት ቢሆንም እኔ የረካሁበት መሆኔን እስካውቅ ድረስ በድጋሚ ለብ ለብ ማድረግ ነበረብኝ።»

ከመታሰቢያ በአሉ አንድ ቀን ቀድሞ ጌትስበርግ ሲደርስ ትንሽዋ ከተማ በህዝብ ብዛት ተጥለቅልቃለች። የሌላ ጊዜ የህዝብ ቁጥር 1ሺህ 300 የነበረ ሲሆን በድንገትም ወደ 15ሺህ ያሻቅብ ጀመር። የእግረኛ መንገዶችም በሠዎች የተጨናነቁና ለማለፍ አስቸጋሪ ሆነዋል፣ ወንዱም ሆነ ሴቱም አደባባይ ወጥቷል፤ ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ የሙዚቃ ቡድኖችም ይዘፍናሉ። ህዝቡ ደግሞ «የጆን ብራውን ሬሣ» የሚለውን ዘፈን እየዘፈኑ ሲሆን ከሚስተር ሚልስ መኖሪያ ቤት ፊትለፊትም ሠዎች ተሠብስበው ሊንከን ያረፈው እዚህ ስለነበር! ንግግር እንዲያደርግላቸው መጠየቅ ሲጀምሩ ሊንከን በጥቂት ቃላትና በጣም ግልፅነት በታጀበበት ሁኔታ እስከ በዓሉ ዝግጅት ድረስ ለመናገር ፈቃደኛ አለመሆኑን ገለፀላቸው። እውነተኛው ነገር ግን የቀረውን ምሽት በሙሉ በንግግሩ ላይ በመዘጋጀት «ሌላ- ለብ ለብ» ለማድረግ ነበር። እንዲውም ዋና ፀሃፊ ሲዋርድ አረፈበት ክፍል በመሄድ ለእሱ ንግግሩን በማድረግ ለማስገምገም ሁሉ ፈልጎ ነበር። የበዓሉ ዕለትም ልክ ቁርስ እንደተጠናቀቀ «ተጨማሪ ማነብነብ» ለማካሄድ እየተንቀሣቀሠ ነበር። በኋላ ላይ ግን አስተናባሪው ወደ በሩ ተጠግቶ አሁን ቦታውን መያዝ ያለበት ሠዓት መድረሱን ነገረው። ኮሎኔል ካር ከፕሬዝዳንቱ ጀርባ በፈረስ እየተጓዘ በነበረበት ሠዓት ያየውን እንዲህ ሲል ተናግሯል «ሲጀመር ፕሬዝዳንቱ በፈረሡ ላይ ቀና ብሎ በመቀመጥ የጦር አዛዦቻቸውን በክፊል እየተመለከተ ነበር። ነገር ግን እየቀጠለ ሲሄድ ዘንበል አድርጎ ነበር። እጆቹን አጣጥፎ በጣም በሃሣብ የተዋጠም ይመስላል።» እኛ ግን መገመት የምንችለው ነገር በዚህም ቅፅበት እነዚህን ህያው እና ጊዜ የማይሽራቸው አድርጎ ስለተናገራቸው አስር መስመር ዓረፍተ ነገሮች የመጨረሻ የሆነውን ክለሳ በልቡ እያደረገ እንደነበር ነው። በእርግጥ ጥቂት የሆኑ የሊንከን ንግግሮች ብዙም የፍላጐት ስሜት ባልነበረው ሁኔታ ያደረጋቸውና ያለጥርጥርም ያልተሣኩለት ነበሩ። ነገር ግን ባርነትንና ማህበራቱን አስመልክቶ በተናገራቸው ንግግሮቹ እጅግ በጣም አስደናቂ ሃይል እንዳለቸው አሣይቷል። ለምን? ምክንያቱ እነዚህን ችግሮች ያለማቋረጥ ሲያብሰለስላቸው የነበሩና በጥልቀትም ልቡን የነኩት በመሆናቸው ነበር።

አንድ ጊዜ ከሊንከን ጋር ኢሊኖይስ በሚገኝ መዝናኛ ቦታ አንድ ክፍል የተጋራው ጓደኛው ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነሣ ሊንከንን አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ ብሎና ፊቱን ወደግድግዳው አዙሮ «ይህ መንግስት ግማሹ በነፃነት ግማሹ ደግሞ በባርነት የሚኖር ህዝብ ይዞ ለዘላለም ፀንቶ ሊቆም አይችልም።» በማለት ሲናገር እንዳገኘው ገልጿል።

እየሱስ ህዝቡን በሚያስተምርበት ጊዜ እንዴት ነበር ንግግሮቹን የሚያዘጋጀው? ከህዝቡ ተነጥሎ ይጠጣል፣ በጥልቀት ያስባል፣ ያብሰለስላል፣ ያወጣል ያወርዳል፣ ለብቻው ሆኖ ማንም ሠው በማይደርስበት ቦታ በመሄድም ለአርባ ቀንና ለሊት እየፆመና በተመስጦ እያሰላሰለ ተቀምጧል። ቅዱስ

ማቴዎስም እንደፃፈው «ልክ ከዚህ ጊዜ በኋላ እየሱስ መስበክና ማስተማርም ጀመረ::» ይህ ነገር ከተፈጠረ ከጥቂት ጊዜ በኋላም በዓለም ላይ እጅግ የተከበረውንና በተራራዉ ላይ ያደረገውን ስብከት አደረገ::

«ይህ በእርግጥ ደስ የሚልና የሚስብ ነገር ቢሆንም እኔ ግን እንደዚህ ያሉ አስደናቂና ህያው የሆኑ ንግግሮችን በማድረግ ታላቅ ተናጋሪ መሆንን ሣይሆን የምመኘው ቀለል ያሉ ንግግሮችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ ለማድረግ መማር ያሉብኝን ነገሮች ማወቅ ነው:: ኃሳቡን ልትቃወሙት ትችላላችሁ ትክክልም ናችሁ:: ፍላጐታችሁ ምን እንደሆነ ይገባኛል:: የዚህ መፅሐፍም ግልፅ ዓላማና ተግባር እናንተንና መሰሎቻችሁን በደንብ እንድትማሩ ማድረግና ማለማመድ ነው:: ምንም እንኳን ከላይ እንደገለፅኩት እናንተም ከልባችሁ ሣታስመስሉ ታዋቂ ተናጋሪዎች የደረሱበት ደረጃ መድረስ እንደምትፈልጉ ማረጋገጥ ባልችልም ያለፉትን ትውልዶች ዝነኛና ዕውቅ ተናጋሪ ሠዎችን ልምድና ተሞክሮዎች ማወቅ በእጅጉ ተጠቃሚ ያደርጋችኋል::

## ንግግርህን እንዴት ማዘጋጀት እንደምትችል!

በምን አይነት ርዕስ ላይ መናገር ትፈልጋለህ?

ለምታደርገው ልምምድ በምን አይነት ርዕስ ላይ መናገር ትፈልጋለህ? ለምታደርገው ልምምድ በምን አይነት ርዕስ ላይ ማድረግ ትችላለህ:: በዚህች አጭር በማንኛውም አንተን በሚስብህ ነገር ላይ ማድረግ ትችላለህ:: በዚህች አጭር ንግግርህም ብዙ ጉዳዮችን እዳስሳለሁ ብለህ በዓለም ላይ ያሉ ሠዎች ሁሉ የሚሠሩትን ስህተት እንዳትደግመው:: በርዕስህ ውስጥ ካሉት ነገሮች አንድ ሁለቱን ነቅሰህ አውጣና በእነሱ ላይ በደንብ አድርገህ ሽፋን ለመስጠት ሞክር:: ቀጥለህ ይህንንም በአጭር ንግግርህ ለማጠቃለል ከቻልክ እድለኛ ነህ ማለት ነው:: ቀጥለህ ርዕስህን ሠፋ ለማድረግ ወስንና ሥራ በማይኖርህ ጊዜ ሁሉ በጉዳዩ ላይ አስብበት፤ ለሰባት ቀናት አስበው፤ ለሰባት ለሊትም አልመው፤ በጡረታህ ማግስት እንዳገኘሽው የመጨረሻ አስደሣች ነገር አድርገህ ውሰደው:: በሚቀጥለው ጠዋት ፂምህን ስትላጭ፤ ገላህን ስትታጠብ፤ ወደ ከተማ ስትጓጓዝ፤ ሊፍት ስትጠባበቅ፤ የምሣ ወይም የቀጠሮህ ሰዓት እስኪደርስ፤ ልብስ ስትተኩስና ምግብ ስታበስልም አስበው:: ከጓደኞችህ ጋር ተወያይበት:: እንዲውም የንግግራችሁ ሁሉ አርዕስት አድርገው:: ተያያዥ የሆኑና ሊጠየቁ የሚገባቸውን ነገሮችም እራስህን ጠይቀው:: ለምሣሌ የምትናገረው ነገር በፍቺ ጉዳይ ላይ ከሆነ ፍቺን የሚያስከትለው ምንድን ነው? ብለህ እራስህን ጠይቅ:: ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖውስ? ይህን መጥፎ ነገርስ እንዴት ማዳን ይቻላል? ፍቺን የሚመለከት ሕግ አለን እንዴ? ፍቺ እንዳይፈፀም መከልከል አይቻልም? በጣም ከባድ እንዲሆንስ ማድረግ አይቻልምን? ቀላል እንዲሆን ማድረግስ?

ንግግር ማድረግን መማር ለምን እንደፈለክ በመግለፅ ንግግር ለማድረግ እያጠናህ ነው እንበል፤ በዚህ ጊዜ ታዲያ እነዚህን ጥያቄዎች እራስህን መጠየቅ እንዳለብህ አስታውስ:: ችግሬ ምንድነው? ከትምህርቱስ ምን አገኛለሁ ብዬ ተስፋ ላድርግ:: በህዝብ ፊት ተናግሬ አውቃለሁ እንዴ? ከሆነ መቼ? የት? በምንስ ተፈጠረ? ይህ ስልጠናስ በንግድ ለተሠማሩ ሠዎች ጠቃሚ ነውን? በራስ መተማመን ባላቸው ቁርጥ አቋም፣ አሣማኝ በሆነ የንግግር ችሎታቸው በንግድም ሆነ በፖለቲካው መስክ በስኬት ወደፊት መውጣት የቻሉ ወንዶችና ሴቶች አውቃ ይሆን? እነዚህን ነገሮች ባለማሟላታቸው ይህን ከፍተኛ የሆነ የስኬት ደረጃ

አመቺ ፍጥነት የሌቶች ሌሎችን ዘመንስ እውቀት የለም፣ የእነዚህን ሠምሮ ታሪክ ለማቅረብ ባትጠቅስ በድንብ አድርጎ አስረዳ፡ እንደ ነዚ ቀመዘ በጣም ሁኔታ እያነሳክ ሁሌትንና ቀሽቶ ደቂቃ መናገር ከቻልክ በመቆጣጠርያዎቹ ጥቂት የንግግር የማጠቃለያን ነገር በሚገባ አጥብ ማለት ነው። ለምን ንግግር ለማድረግ መጨረሻ፤ እንደፈለክ የሚነገሩን ርዕስ በጣም ቀላል ነው። በግልፅም ይታጠቃል. ስለ ርዕስ ላይም መረጃዎችን በማዘጋጀትና በመመረቅ ትንሽ ነዚ ካስቀ ርዕስህን አመለካከት፣ ፍላጎቶችህንና ተሞክሮዎችህን የሚተናገር በመሆኑ ለማስተጠስ መቻልህን ልትጠራጠር አይገባም።

በሌላ በኩል ደግሞ በሥራህና በሙያህ ዙሪያ ለመናገር ወሰንሃል እንበል፣ የዐ አይነቱን ንግግር ለማድረግ እንዴት መጀመር ትችላለህ፣ በጉዳዩ ላይ ቀድሞውንም የመረጃ ሃብታም ስለሆንክ ያንተ ትግር የሚሆነው እነዚያን መምረጥና ማቀናጀት ነው። ስለሁሉም ነገር በሦስት ደቂቃ ውስጥ ለመናገር እንዳትሞክር፣ ሊሆን የማይችል ነገር በመሆኑ ሙከራህ ሁሉ ጥራዝ ነጠቅና የተቆራረጠ ታሪክ ይሆናል። የርዕስህን አንዱን ክፍል ብቻ መዝዘ አጠባና ያንን እያሞቅኸውና እያሳደከው ቀጥል። ለምሳሌ ወደዚህ ለየት ወዳለ ሥራ ወይም ሙያ እንዴት ልትገባ እንደቻልክ ንገረን በምርጫህ ነው ወይስ በአጋጣሚ፣ ቀደም ብለህ ያጋለፍኸውን ትግል፣ ውድቀትና ተስፋ ወይም ድል በተያያዥነት ጥቀሰው። ሰውን የሚማርክና ትረካ የሚመስል ከራስ በተገኘ ልምድ በመነሣት የተሣሌ እውነተኛ የህይወት ገፅታ ስጠው። የማንኛችንም እውነተኛና ድብቅ ታሪክ በትህትና እንዲሁም ሠዎችን በግል በማያስቀይም ሁኔታ ከተነገረ እጅግ በጣም አዝናኝ የሆነ ትረካ ይወጣዋል። እንዲያውም ልክ በእሣት እንደተፈተነ ወርቅ ቆንጆ ንግግር ይወጣዋል። እስቲ ሌላውን የሥራ ክፍላችንን እንውሠድና እንጠይቅ ችግሩ ከምን መጣ? ወደሥራ ለሚገቡ ወጣቶችስ ምን ትመክራቸዋለህ? ወይም ደግሞ በሥራ አጋጣሚህ ከተዋወቅካቸው ሠዎች ውስጥ ሃቀኛ የሆኑትንና ያልሆኑትን መግለፅ ትችላለህን? ያንተን ችግርንም በማከል ስራህ ያስተማረህና በዓለም ላይ በጣም አስደሣቹ የምትለው ነገር ምንድ ነው? ስለ ሠው ተፈጥሮ? ስለስራህ ዝርዝር የሆኑና ቴክኒካዊ ነገሮችን ማውራት ንግግርህን ሌሎች ሲሠሙት የማይፈልጉት አይነት ያደርገዋል።

ነገር ግን ስለ ታዋቂ ሠዎች፣ ስለማንነታቸው፣ ስለሠሩት ታላቅ ሥራ ብትናገር እንደማንኛውም ግለሠብ በዚህ ጉዳይ ስህተት ልትሠራ አትችልም። ከሁሉ በላይ ግን ንግግርህ ድርቅ ያለና የስብከት አይነት አታድርገው፣ ምክንያቱም አሰልቺ ይሆናልና ነው።

ደረጃ በደረጃ እንደሚቀረስ ኬክ ንግግርህ ጠቅለል ባለ ይዘት እና ምሣሌዎች ይታጀብ። የተመለከትካቸው ጠንካራና ልብ የሚነኩ ጉዳዮች እስከ አሁንም አንተ የምታምንባቸው መሠረታዊ የሆኑ እውነታዎችና እነዚህንም በምሣሌ የሚያስረዱ አጋጣሚዎችን ተጠቅሞ በዚህ አጋጣሚም እነዚህ ጠንካራና ልብ የሚነኩ ጉዳዮች ውስብስብ ከሆኑት ይልቅ ለማስታወስና ለመዘርዘር ቀላል እንደሆኑ ትረዳለህ። በተጨማሪም የምታስተላልፈው መልዕክት ብሩህ እንዲሆን ያግዝሃል።

አንድ ደራሲ የተጠቀመበት እጅግ የሚስብ መንገድ ይኸውልህ። ይህ አንቀጽ ቢ.ኤ.ፍርብስ ኃላፊነትን ለሌሎች አጋር ሸርኮች ስለማስተላለፍ

አስፈላጊነት ለሥራ አስፈፃሚዎች ከፃፈው የተወሠደ ነው:: ምሣሌው ሠዎችን የሚያማ ነው:: በአሁኑ ጊዜ እጅግ ግዙፍ ለመሆን የበቁ የንግድ ድርጅቶች በአንድ ወቅት በአንድ ግለሰብ ቁጥጥር ሥር ብቻ የነበሩና ብዙዎቹም በዚህ መንገድ አልፈው የመጡ ነበሩ:: አሁን አሁን ግን ከዚህ ነገር እየተላቀቁ መጥተዋል:: ይህም እንደምክንያት የሚቀርበው በአንድ ሠው ጥላ ሥር ለረጅም ጊዜ የቆዩት ታላላቅ ድርጅቶች የንግድ ተቋማትና ፋብሪካዎች አሁን እጅግ የበቁ የሚባሉትን ጨምሮ ብሩህ ጭንቅላት ያላቸውን ሠዎች በማሣተፍ በአስተማማኝ ሁኔታ ሥራቸውን ማካሄድና እንቅስቃሴያቸዉን መቆጣጠር በመጀመራቸው ነው:: ውል ወርዝ እንደነገረኝ የእሱም ድርጅት በራሱ ተፅዕኖ ሥር ለረጅም ጊዜ መቆየቱንና በጤና መዛባትም ሆስፒታል ገብቶ ለብዙ ሣምንታት ከላካፈለ በስተቀር ሥራው እሱ ድረስ የኃላፊነቱን ቦታ ለሌሎች ሠዎች እንደማይችል አልተረዳም ነበር:: እንደሚመኘውና እንደሚያስበው ሲያድግለት እንደማይችል በአንድ ሠው ብቻ

ቤተልሄም የብረታ ብረታ ማምረቻም ለብዙ ዓመታት በአንድ ሠው ብቻ ከሚተዳደሩ ድርጅቶች መካከል አንዱ ነበር:: ሁሉም ሥራ የሚሠራው በቻርለስ ኤም ሽዌብ ነበር:: ከጊዜ በኋላ ግን የኢጄን ጂ ግሬስ የብረታ ብረት ማምረቻ ባደረጋቸው ተከታታይ የለውጥ ሂደቶች ከሽዌብ በተሻለ ቅርፅና ይዘት ጥሩ ብረታ ብረት አምራች ሊሆን በቅቷል:: ኢስት ማን ኮዳክ ሲመሠረት አካባቢ በጆርጅ ኢስት ማን ኃላፊነት ሥር ብቻ ነበር፤ ከዚያ ወዲህ ግን ብልህ በመሆኑ ብቃት ባለው አደረጃጀት መለወጥ እንዳለበት ሲረዳና ይህንንም በተግባር ሲያውለው ችሏል::

በቺካጎ የሚገኙ የታሸጉ ምግቦችን በማምረት ላይ የተሠማሩ ይገኙ ነበር በቺካጎ የሚገኙ የታሸጉ ምግቦችን በማምረት ላይ የተሠማሩ ይገኙ ነበር በተቃራኒው ድርጅቶችም የምስረታቸው ጊዜ በተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ:: በተቃራኒው ሁኔታ ስታንዳርድ ዘይት አምራች የሆነ አንድ ድርጅት ግን ከምስረታው ጀምሮም ቢሆን የአንድ ሠው አስተዳደር ተፅዕኖ ያረፈበት ሆኖ ስለማያውቅ ሊስፋፋና ሊያድግ ችሏል:: ጄ.ፒ.ሞርጋን ታላቅ የሆነ የግንባታ ድርጅት ባለቤት ቢሆንም ብቃት ያላቸው ሸርኮችን በመምረጥና ሸክሙን እንዲጋሩለት በማድረግ በኩል ፅኑ እምነት ያለው ሠው ነበር::

እንደዚህም ሆኖ ግን እጅግ ታታሪና ትጉህ በሆኑ ግለሠቦች የሚመሩና ራሳቸው ብቻ ሥራቸውን መምራትና መቆጣጠር እንዳለባቸው በሚያምኑ ሠዎች ቁጥጥር ሥር ያሉ ድርጅቶች አሉ፡ ነገር ግን ዞሮ ዞሮ ዘመናዊው የአሠራር ዘዴ ሃላፊነትን ለሌሎች ሠዎች እንዲያካፍሉና እንዲያጋሩ እያስገደዳቸው ይገኛል::

አንዳንድ ሠዎች ስለሥራቸው በሚናገሩበት ጊዜ እራሳቸውን ደስ ስለሚያሰኟቸው ጉዳዮች ብቻ በማውራት ይቅር የማይባል ስህተት ይፈጽማሉ:: አንድ የሚናገር ሰው ራሱን ሣይሆን አድማጩን የሚያስደስተው ነገር ላይ ማተኮር የለበትምን? ለራሱስ ግላዊ ፍላጐት መንበርከክ አለበት? ለምሣሌ ግለሠቡ በእሣት የተነሣ ለሚከሠቱ አደጋዎች መድህን (ካሣ/ በሚከፍል ድርጅት ውስጥ ቢሠራ እግረ መንገዱን ለደንበኞቹ በቅድሚያ እሣት እንዳይከሠትባቸው እንዴት ሊከላከሉ እንደሚችሉ ማስተማር የለበትም? በሌላ በኩል የባንክ ኃላፊ ቢሆን ደንበኞቹ ገንዘባቸውን እንዴት ለልማት ማዋል እንደሚችሉ ምክር መስጠት አይገባውምን? ተናጋሪያዋ የታዳጊ አገር የሴቶች ተቋም መሪ ብትሆን

በአካባቢዎ ለሚገኙ አድማጮቿ በሃገር አቀፍ እንቅስቃሴ ተሣታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚረዱ መንገዶችን በማሣየትና በዚያው በአካባቢያቸውም ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ምሣሌ መሆን እንደሚችሉ መግለፅ የለባትም?

ለንግግር ዝግጅት በምታደርጉበት ጊዜ የአድማጮችህን ፍላጐትና ምኞት ማጥናት የግጥሚያውን ግማሽ ክፍል ለማገባደድ ይረዳል:: በተለይ አንዳንድ ርዕሶች ላይ ለመዘጋጀት የሚሞክረው ነገር የተለያዩ ፅሑፎችን ማንበብ ያለውን ከፍተኛ ጥቅም ሲሆን ይህም ሠዎች በዚሁ ርዕሠ ጉዳይ ላይ ምን ሃሣብ እንዳላቸውና ምንስ ተናግረው እንደነበር ለማወቅ ይረዳሃል::

ነገር ግን በመጀመሪያ ራስህ በጉዳዩ ላይ በደንብ ካላሠብክበት በቀር ለማንበብ እንዳትሞክር፣ ይህ በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው:: ከዚህ በኋላ ግን ወደ ቤተ መፃህፍት በመሄድ ለኃላፊዋ በአንድ ርዕስ ላይ ንግግር ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆንህንና ለዚህም የሚረዳህን ፅሑፎች እንድታቀርብልህ ግልፅ በሆነ መንገድ ንገራት:: ከዚህ በፊት የጥናት ወረቀት ለማዘጋጀት ሞክረህ የማታውቅ ከሆነ በምታቀርብልህ መረጃ በጣም ልትገረም ትችላለህ:: እንደውም ስለምትፈልገው ጉዳይ በዝርዝር የሚያወራ አንድ ቅጅ፣ ለክርክሩ የሚረዱ ዝርዝሮችን የያዘ ፅሑፍ፣ በሁለቱም ጐን ሲነሡ ለሚችሉ ጥያቄዎች፣ ለማንኛውም አንባቢ መመሪያ የሆኑና ከምዕተ ዓመቱ ጀምሮ በቅደም ተከተል ተመዝግበው የተቀመጡ በተለያየ ርዕሶች ላይ የሚተነትኑ የመፅሔት አንቀጾች የወርልድ አልማናክ፣ የመረጃ አልማናክ ኢንሣይክሎፒድያና በደርዘን የሚቆጠሩ መጽሐፍት ልታቀርብልህ ትችላለች:: ለሥራህ የሚጠቅሙ መሣሪያዎች ናቸውና ተጠቀምባቸው::

## መጠባበቂያ ከምችት ማኖር ያለው ኃይልና ሚስጥር

ሉተር በርባንክ ከመሞቱ ጥቂት ጊዜያት በፊት እንዲህ ብሎ ነበር:: «በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የተክል ናሙናዎችን የፈጠርኩ ቢሆንም ከፍተኛ ውጤት መስጠት እንደሚችሉ የደረስኩባቸው ዝርያዎች ግን ከአንድና ሁለት አይበልጡም:: ስለዚህም እነዚህ ዝቅተኛ ወጤት የሚሰጡትን በመሉ ማጥፋት ነበረብኝ» ንግግርም ለማዘጋጀት እንደዚህ የተትረፈረፈና መርጠን ለመጣል የሚያስችል ከበቂ በላይ የሆነ መረጃ ሊኖረን ይገባል:: መቶ የሚሆኑ ሃሣቦችን መሰብሰብና ዘጠናውን ማስወገድ እርግጠኝነትን ስለሚጨምሩልን እንዲሁም ተጨማሪ የሆነ በራስ የመተማመን ስሜት ስለሚያመጡልን ባንጠቀምባቸውም እንኳን ብዙ መረጃዎችንና ብዙ ግብዓቶችን መሠብሠብ በንግግርህ ጊዜ ለሚኖርህ የአዕምሮና የልብ ፅናት ውጤታማነት ስትል ተጠቀምበት:: ይህ ለዝግጅት መሠረታዊና እጅግ ጠቃሚ የሆነ ነጥብ ቢሆንም በብዙ የግል እንዲሁም መንግስትን በመወከል ንግግር በሚያደርጉ ሠዎች ዘንድ ቸል ሲባልና ሲዘነጋ ይስተዋላል::

አርተር ዳን እንዲህ ሲል ተናግሮታል « በመቶዎች ለሚቆጠሩ ወንድና ሴት የሽያጭ ሰራተኞች መረጃ ሠብሣቢዎችና ምርቶችን ለሚያስተዋውቁ ሠዎች ስልጠናዎችንና ትምህርቶችን ሰጥቻለሁ:: ካገኘኃቸው ድክመቶችም ዋነኛው የሆነው ስለምረቶቻቸው ማንኛውንም ዝርዝር ነገር ተንትነው ሣያዉቁ በፊት

ለገበያ ይዘዋቸው መውጣት እንደሌለባቸው ያለመረዳትና ጠቃሚ ነጥብም እንደሆኑ ያለማወቃቸው ነው።

ብዙ ወንድ የሽያጭ ሠራተኞች ከቢሮዬ ይመጡና ስለዕቃው አይነት የሚገልፅ ዝርዝር ነገር ከወሰዱና ስለሽያጭ ሥራም አንዳንድ ወሬዎችን ከተነጋገሩ በኋላ ወዲያውኑ ምርቱን ወስደው ለመሸጥ ይጓጓሉ። ብዙዎቹ ታዲያ አንድ ሣምንት እንኳን ሣይቆዩ ለውድቀት ይዳረጉ ነበር፤ ከዚህ የባሰው ደግሞ 48 ሰዓት እንኳን ለመቆየት አይችሉም።

እነዚህኑ መረጃ ሠብሣቢና የሽያጭ ሠራተኞች በተለይ በምግብ ምርቶች ሽያጭ ላይ ስልጠናና ትምህርት በምሠጣቸው ጊዜ የምግብ ምርቶችን በዝርዝር ጠንቅቀው የሚያውቁ ኤክስፐርቶች እንዲሆኑ አልሜና አቅጄ ነበር። የአሜሪካ የግብርና ሚኒስቴር የሚያወጣቸውን የምግብ ዝርዝሮችን የሚያሣይ ሠንጠረዥ እንዲያጠኑ አስገደድኳቸው። በእያንዳንዱ ምግብ ውስጥ መኖር የሚገባውን የውሃ፣ የስብ፣ የፕሮቲን፣ የካርቦሃይድሬት፣ መጠን እንዲያውቁ አስጠናኋቸው። እነሱ ለሽያጭ የሚያዞሯቸው ምግቦች ከምን አይነት ንጥረ ነገር እንደተሰሩ ማወቅም እንዳለባቸው ነገርኳቸው። ለብዙ ቀናትም ወደ ትምህርት ቤት ልኬ እንዲማሩና የሚሰጣቸውን ፈተና እንዲወስዱ አደረኳቸው። ከዚህ በኋላ የእነሱን ዕቃዎች ለሌላ የሽያጭ ሰራተኞች እንዲሸጡ አዘዝኩአቸው። ብዙ ለሸጠው ሰውም ሽልማት አዘጋጀሁ። አንዳንድ የሽያጭ ሠራተኞች የሚሸጡትን ዕቃ ለማጥናት የሚወስደውን ጊዜ በማየት ትዕግስት የማይኖራቸው እንዳሉበት አይቻለሁ። እንዲህም ያሉ ነበሩ «ይህንን ሁሉ ዝርዝር ነገር በችርቻሮ ንግድ ለተሠማሩ ሠዎች ለመንገር ጊዜ ሊኖረን አይችልም፣ እነሱም ስራ ሊበዛባቸው ይችላልና ስለፕሮቲንና ካርቦኃይድሬት ስንነግራቸው አይሰሙንም። ካልሰሙን ደግሞ እያስረዳናቸው ስላለው ነገር ሊያውቁ አይችሉም» የእኔ መልስ ግን ይህንን እውቀት መያዝ ያለባችሁ ለደንበኞቻችሁ ጥቅም ብላችሁ ሣይሆን ለራሳችሁ መሆን ይኖርበታል። የምትይዟቸውን ዕቃዎች ምንነትም ከሀ እስከ ፐ ማወቅ ለመግለፅ የማትችሉት ስሜት ያሣድርባችኋል። በመሉ መንፈስ ትነቃቃላችሁ። የአመለካከትና የአስተሳሰብ አድማሣችሁ ጠንካራና የማይገረሠሥ ስለሚሆን ማንም ሊፎካከራችሁና ሊቋቋማችሁ የማይችል ያደርጋችኋል።»

ሚስ አይዳ ኤም ታርቤል የተባለች የስታንዳርድ ነዳጅ ዘይት ኩባንያ ታዋቂ የታሪክ አጥኚ ለዚህ መፅሐፍ ደራሲ ከዓመታት በፊት እንደነገሯቸው ፓሪስ እያለች ሚስተር ኤስ ማክሴር የተባለው የማክሴር መፅሔት መሥራችና ባለቤት የሆነ ሰው በቴሌግራም መልዕክት ስለ አትላንቲክ የቴሌግራም ኩባንያ አንድ አጠር ያለ ፅሑፍ እንድታዘጋጅለት ይነግራታል። ከዚህ በኋላ ወዲያው ወደ ለንደን ታመራና የአውሮፓ ዋና ቴሌግራም ተቆጣጣሪ የሆነውን ሠው ቃለ መጠይቅ አድርጋ ለሥራዋ በቂ የሆኑ ዳታዎችን ታገኛለች። ነገር ግን በዚህ ብቻ ሣታቆም በተጨማሪ ሊረዷት የሚችሉ እውነታዎችን ለማግኘት በእንግሊዝ ቤተመዘክር የሚገኘውን ቴሌግራም አጠቃላይ የአሠራር ፀባዩን አጠናች። ስለስልክ አመሠራረት የሚተርኩ መፅሐፍትን ካነበበች በኋላ በእንግሊዝ ጠረፍ የሚገኘውን የማምረቻ ቦታ ጎብኝታ ቴሌግራሞች እንዴት እንደሚዘረጉና አጠቃላይ ሂደቱን ተመለከተች። ለፅሑፍ ሊረዳት ከሚችለው መረጃ አስር እጥፍ በላይ መሰብሰቧ ለምን አስፈለጋት? ይህን ያደረገችው መጠባበቂያ የሚሆን መረጃ! ማኖር



Scanned with CamScanner

ተጨማሪ ሃይል እንደሚሆናት ስላመነች ነው:: ምክንያቱም በሚኖራት ትንሽ ጊዜ ልትገልፃቸው የማትችላቸውና የማታውቃቸው ብዙ ነገሮች በገለፃዋ ወቅት ለምትናገራት ትንሽ ነገር ሃይልና ልዩ ቀለም ሲሰጧት እንደሚችሉ ስለተሰማት ነው::

ኤዲዊን ጀምስ ካቴል በግምት ከ30 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ሠዎች ንግግር ያደረገ ሲሆን ሁልጊዜም በንግግሩ ወቅት ሣይገልፃቸው ለሚያልፉት በጉ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮች ሲል ራሱን እንደሚቀጣ ገልጿል:: ለምን? ምክንያቱም ከረጅም ጊዜ ተሞክሮው በመነሣት ሠዎች በተለየ ሁኔታ ሲያስተውሏቸው የሚችሉት ንግግሮች ከበቂ በላይ በመረጃ የታጀቡ፣ የተትረፈረፉና ተናጋሪው ካለው የመናገሪያ ጊዜ በላይ ሲያስኬዱት የሚችሉ ሲሆን ብቻ እንደሆነ ያውቃልና ነው::

## አጭር ክለሣ

1. አንድ ንግግር የሚያደርግ ሠው በአዕምሮውና በልቡ ትክክለኛና እውነተኛ የሆነ መልዕክት ከያዘና ለመናገርም ጉጉ ከሆነ ለራሱ አንድ ውለታ እንደዋለ እርግጠኛ መሆን አለበት:: ጥሩ ዝግጅት የተደረገበት ንግግር ቀድሞውንም ከአሥር እጅ ዘጠኙ እንደተሣካ ይቆጠራል፣

2. ዝግጅት ማድርግ ራሱ ምንድን ነው? ወይስ መካኒካዊ የሆኑ ዓረፍተነገሮች በወረቀት ላይ ማስፈር ነው? የተወሰኑ ሃረጉችን ማስታወስ ነው? በፍፁም አይደለም! ትክክለኛ ዝግጅት ማድረግ ማለት የራሳችን የሆነን ሃሣብ ቆፍሮ በማውጣት ማሠባሰብና ማቀናጀት እንዲሁም የራሳችን የሆኑ እምነቶችን በማሣደግና ተንከባክበን ሕይወት በመስጠት ማዘጋጀት ማለት ነው:: ለምሣሌ የኒውዮርኩ ሚስተር ጃክሰን ከፎረብስ መጽሔት ላይ ያገኘውን አንቀጽ እንደራሱ ሃሣብ ለማቅረብ ሲሞክር እንዴት ሊሣካለት እንዳልቻለና ያንኑ አንቀጽ ግን እንደመነሻ ሃሣብ ብቻ በመጠቀም የራሱ የሆኑ ሃሣቦችን አክሎበትና የራሱን ምሣሌዎች በመጠቀም ሲያቀርበው እንዴት ስኬታማ ሲሆን እንደቻለ አይተናል::

3. በሠላሣ ደቂቃ ውስጥ አንድ ንግግር ፈብርኮ ለማውጣት አለሙከር፣ ንግግርን እንደ ሥጋ ጥብስ ልናዘጋጀውና አዘን ልናስመጣው አንችልም:: እያሣደግነው እናመጣዋለን እንጅ! በሣምንቱ መጀመሪያ ርዕስ እንመርጣለን፣ ሥራ በማይኖረን ጊዜያቶች ሁሉ እናስብበታለን፣ እንታቀፈዋለን፣ ይዘነውም እንተኛለን፣ እናልመዋለን፣ ከጓደኞቻችን ጋር እንነጋገርበታለን፤ የንግግራችንም አጀንዳ እናደርገዋለን፤ እራሳችንንም ሲጠይቁ የሚገባቸውን ጥያቄዎች እንጠይቅበታለን:: የሚመጡልን ምሣሌዎችና ሃሣቦች በወረቀት እናሰፍርና ለሌሎች ሃሣቦች ደግሞ እንዘጋጃለን:: ሃሣቦች አስተያየቶች ምሣሌዎች ሳናስበው ግር ብለው የሚመጡልን፤ ስንታጠብ፣ ስንጓጓዝ፤ እራት እስኪቀርብ ስንጠብቅ ባልገመትነው በድንገተኛ ሁኔታ ነው:: ይህ ሊንከንን ጨምሮ የብዙ ስኬታማ የሆኑ ሠዎች ዘዴ ሊባል የሚችል ነው::

4. ለብቻችን ሆነን ሃሣባችንን ካወጣንና ካወረድን በኋላ ጊዜ ሲፈቅድ ቤተ መጻሕፍት ሄደን ከጉዳያችን ጋር የሚያያዙ መፅሐፍትን ማንበብ ለቤተመፅሐፍቱ ኃላፊም የምንፈልገውን መግለፅ በጣም ትልቅ እገዛ ያደርግልናል::

5. እጠቀምበታለሁ ብለን ከምናስበው በላይ ብዙ መረጃ ማሠባሰብ፤ ሉተር በርባክን እንውሠድ ከሚሊዮን በላይ የሆኑ የተክሎች ናሙና ቢፈጥርም ውጤታማ ሆነው ያገኛቸው ከአንድ ወይም ሁለት አይበልጡም ነበር መቶ ሃሣቦችን ማሰባሰብ ዘጠናውን ማስወገድ::

6. መጠባበቂያ ሃይል የሚሆን ክምችት ማዳበር ማለት መንገዱ ልንጠቀምበትና ከምንችለው በላይ የመረጃ ሙላት ማኖር ማለት መሆኑን እንረዳ:: ንግግር በምናዘጋጅበት ጊዜም አርተር ዲን የሽያጭ ሰራተኞችን በቁርስ ሽቀጦች ሽያጭ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሥልጠና በመስጠት የተጠቀመውን ዘዴ እንውሠደው:: በአይዳ ተርቤል ፅሑፏን ለማዘጋጀት በአትላንቲክ የቴሌግራም ኩባንያ ላይ የተጠቀመችባቸውን ዘዴዎች እንውሠድ::

# ክፍል ሦስት

## ዝነኛ ተናጋሪ የነበሩ ሰዎች ንግግሮቻቸውን እንዴት እንዳዘጋጁ

የኒውዮርክ ሮታሪ ክለብ ባዘጋጀው የምሣ ግበዣ ላይ ተገኝቼ ነበር:: ንግግር እንዲያደርግ የሚጠበቀው ዋና እንግዳ አንድ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ነው:: ያለበት ከፍተኛ የሆነ የኃላፊነት ቦታም ክብር የሚያሰጠው በመሆኑ ሁላችንም በደስታ ልናዳምጠው ተቀምጠናል:: እርሱ ራሱም ስለሚመራው ክፍል የስራ እንቅስቃሴ ሊነግረንም ቃል ገብቶልን ነበር:: የኒውዮርክ የንግድ ማህበረሠብም ጠቅለል ሁኔታ ሊሰማው የሚፈልገው ይህን ዓይነት ተሞክሮዎችን ነበር:: የሚናገረውን ርዕስ ይዘትም በደንብ የሚያስረዳለት ለንግግሩ ሊጠቀምበት ከሚችለው በላይ ማስረጃና ዕውቀት ቢኖረውም ምንም ዝግጅት አላደረገበትም፤ መረጃዎቹንም መርጦ አላወጣቸውም:: እንዲሁም ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መልኩ አላቀናጃቸውም፤ ይሁን እንጂ ከልምድ አልባነት በሚመጣ ድፍረት ምንም ሳያቅማማና ሳያመነታ በዕውር ድንብሩ ወደ ንግግሩ ገባ:: ወዴት እያመራ እንደሆነ አላወቀውም፤ መንገዱን ግን ጀምሮታል:: በአጭሩ ለመግለፅ የሚያስበው ነገር ድብልቅልቅ ከማለቱ የተነሣ ከአዕምሮው ፈልቆ የቀረበልን ድግስም እንደዚያው የተደበላለቀና ግሣንግሥ የበዛበት ነበር:: በመጀመሪያ ክሬም ኬክ አቀረበልን:: ከዚያ ቀጥሎ ሾርባውን ከፊት ለፊታችን አስቀመጠልን:: ከዚያ አንደገና አሣና ለውዝ አስከተለ::

ከዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ በአናቱ ላይ የሾርባ፣ የኬክና ጥሩ የሆነ ቀይ የባህር አሣ ደብልቅ የሚመስል ነገር አከለበት:: ከዚህ በፊት የትም ቦታ መቼም ቢሆን አንድ ተናጋሪ በጣም ግራ የተጋባ ነገር ሲናገር አይቼም ሠምቼም አላውቅም:: ምንም ቅድመ ዝግጅት የሌለው ንግግሩን አሁንም ማቅረብ ቀጥሏል:: በመሀከሉ ግን ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ከኪሱ ውስጥ ማስታወሻ የሰፈረባቸው ብዙ ወረቀቶችን አወጣ:: የራሱ ፀሃፊም እንዲህ አብዝታ ወረቀቶቹን በማዘጋጀቷም ግራ ተጋባ:: እስካሁን ድረስ ግን በእርግጠኛነት በትክክለኛ መንገድ መናገር እንደሚችል ሊያጠራጥርና ጥያቄ ሊያስነሣ የሚችል መሆኑን የገመተ አልነበረም:: ማስታወሻዎቹ ራሳቸው በግልፅ ሁኔታ ቅደም ተከተላቸውን ባለመጠበቃቸው አንድ የጭነት መኪና ሙሉ የብረት ቁርጥራጮችን እንደመለየት አስቸጋሪ ሆነዋል:: ጭንቀት በሞላበት ሁኔታም ከአንድ ገፅ ወደ ሌላው ገፅ እያገላበጠ ያያቸው ጀመር:: እራሱን ለማረጋጋትና አንድ የሆነ ማምለጫ መንገድ በሚፈልግ ሁኔታ ጥረት እያደረገ በተመሣሣይ ሆኔታም ለመናገር ሙከራ ያደርግ ነበር:: ነገር ግን የማይቻል ነገር ሆነበት:: ይቅርታ ካለ በኋላ ውሃ እንዲያቀርቡለት ጠየቀና በሚንቀጠቀጥ እጁ ተቀበለ:: ጥቂት የተበታተኑ ዓረፍተ ነገሮችን እየተንተባተበ ተነፈሣቸው:: እንደገናም ደገማቸውና ማስታወሻዎቹንም ያገለባብጥ ጀመር:: ደቂቃዎቹ እየጨመሩ ሲመጡም በጣም መረበሹና በጣም ግራ መጋባቱም እንደዚሁ ይጨምር ጀመር:: በሃፍረት ውስጥም ሰጠመ መሃረቡን ከኪሱ አውጥቶ ከመደንገጡና ከመረበሹ የተነሣ ግንባሩ በላብ ወረዛ፣



Scanned with CamScanner

ለመጠራረግ ሲሞክርም እየተንቀጠቀጠ ነበር:: እኛ አድማጮቹም ጠቅላላውን አሣዛኝና የውድቀት ትዕይንት በሃፍረትና በሃዘኔታ ስሜት ጭንቀላታችንን በመነቅነቅ ተመለከትነው:: የእሱ ስቃይ እኛ ላይ በተዘዋዋሪ በመድረሱ የሃፍረት ስሜት አደረብን:: ነገር ግን እኔ አውቃለሁ በሚል እንዲሁም ችክ ባለ ስሜት እየተፍጨረጨረ ማስታወሻውን እያገላበጠ፣ ይቅርታ እየጠየቀና ውሃውን እየተጐነጨ ንግግሩን ቀጠለ::

ትዕይንቱ ጠቅላላ ወደሚያመራበት ፍፃሜው እየተቃረበ እንደሆነ ከእሱ በስተቀር ሁሉም ታዳሚ አውቆት ነበር:: በድንገት ግን የሚያደርገውን የሞት ሽረት የንግግር ትግል አቁሞ ሲቀመጥ ሁላችንም እፎይታን አገኘን:: እጅግ በጣም ምቾት በማይሰጥ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ ከአድማጭ ጋር የተቀመጥኩበትና እጅግ በጣም በሚያሣፍርና በሚያዋርድ ሁኔታ አንድ ሠው ንግግር ሲያደርግ የተመለከትኩበት የዚህ አይነት ሁኔታ በህይወቴ ገጥሞኝ አያውቅም::በተለይ ንግግሩን ያደረገበት ሁኔታ ደግሞ ልክ ራሱ የፍቅር ደብዳቤ መፃፍ ይኖርበታል በሚለው መልኩ ነበር:: ይህም ምን መናገር እንዳለበት ሳያውቅ ንግግሩን ጀመረ፣ምን እንደተናገረ ሣያውቅ ደግሞ ንግግሩን ጨረሰ:: የታሪኩ ፍሬ ነገር ደግሞ ልክ ኸርበርት ስፔንሰር እንደተናገረው «የአንድ ሠው እውቀት በቅደም ተከተል ያልተያዘና እጅግ ብዙ ከሆነ የአስተሣሠብ ግራ መጋባትና መምታታትም የዚያኑ ያህል እጅግ ብዙ ይሆናሉ::» የሚል ይዘት ነበረው:: ማንም ጤነኛ የሆነ ሰው መቼም የሆነ ፕላን ሣይኖረው ቤት ለመሥራት አይሞክርም:: ታዲያ እሱ መጀመሪያውኑም የጠራና የተብራራ ፕሮግራም ሣይኖረው ንግግር ለማድረግ ለምን ፈለገ?

ንግግር ልክ የባህር ጉዞ እንደማድረግ ሁሉ መድረሻና ግብ ያለው ነውና በዝርዝር መመሪያ ሊደገፍ ይገባዋል::ስለዚህም አንድ ሰው ከየትኛውም ቦታ ጉዞውን ቢጀምር በመጨረሻ ላይ ያሰበው ቦታ መድረሱ አይቀርም:: ቀጥሎ ያሉ ናፖሊዮን የተናገረውን ጥቅስ በደማቅ ቀይ ቀለም ፅፈው በዓለም ላይ ባሉና በህዝብ ፊት ንግግር ስለማድረግ የሚማሩ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል በር ላይ በአንድ ጫማ ከፍታ ብንለጥፈው ብዩ የምመኘው ነው:: «የጦርነት ጥበብ ሣይንስ ነው፤ በደንብ ሳይታሰብበትና በዕቅድ ዝግጅት ሣይደረግበት የሚገኝ አንዳችም ውጤት አይኖርም::»

ይህ ለመታኮስ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ለንግግርም እንደዚሁ ይሠራል::ግን ንግግር የሚያደርጉ ሰዎችስ ልብ ይሉታል? ልብ ካሉትስ ሁልጊዜ ይጠቀሙበታል? አይጠቀሙበትም! በድጋሚ አስረግጬ እናገራለሁ አይጠቀሙበትም:: ብዙዎቹ ንግግሮች እንደዉም አንድ የአሣ ሾርባ ለማዘጋጀት ከሚደረግ ቅድመ ዝግጅት ትንሽ ሻል ያሉ ቢሆን ነው::

የያዝነውን ሃሣብ የምናደራጅበት በጣም የተሻለውና መልካም የሆነው መንገድ የትኛው ነው? ማንም ሰው ቢሆን በመጀመሪያ በደንብ ካላጠናቸው በስተቀር እንዲህ ነው ለማለት አይችልም:: አንድ ተናጋሪም ሲጠይቃቸው ደግሞ ደጋግሞ ሲመልሳቸው የሚገቡ ሁሌም አዲስ የሆኑትን ነገሮች ግድ ልናስቀምጥለት ባንችልም በማንኛውም ሁኔታ ምሣሌ እየሰጠን በቅደም ተከተል

ማቀናጀት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በበቂ ማስረጃ አስደግፈን ማብራራት እንችላለን::

## ሸለማት ያስገኘውን ንግግር እንዴት ነበር ያዘጋጀው?

በብሔራዊ የቤት ልማት ማህበር የቦርድ ሠብሣቢዎች ፊት ከጥቂት ዓመታት በፊት የቀረበ ንግግር ይኸውላችሁ:: ይህ ንግግር በ27 የተለያዩ ከተሞች ተደርገው ከነበሩት ንግግሮች ጋር ተወዳድሮ የአንደኝነት ደረጃን ሲያገኝ የቻለ ነው:: ሙሉ በሙሉ እውነታዎችን በማካተትና በመግለፅ በሚስብና በማያሻማ ሁኔታ በደንብ የተገነባና የተዘጋጀ ስለነበር ህይወት ያለውና ሳይቆራረጥ የሚፈስ ታሪክ ያለው በመሆኑ ጥናት ለማድረግና ለማንበብ የሚጠቅም ነው::

## ክቡር ሊቀመንበርና ወዳጆች

ከዛሬ 144 ዓመታት በፊት ይህች ታላቋ ሃገራችን በተባበሩት አሜሪካ የተፈጠረችው እዚሁ በምንኖርባት የፊላደልፊያ ከተማ ውስጥ ነበር:: ስለዚህም እንደዚህች አይነት ታሪካዊ አሻራ ያላት ከተማ የሃገሪቱ የማምረቻ ፋብሪካዎች ማዕከል እንድትሆን ያስቻላትን አሜሪካዊ መንፈስ እንድትይዝና በዓለም ላይ ካሉ እጅግ ትልቅና ወብ ከተሞች መካከል አንዷ መሆን መቻሏ ምንም የሚያስገርም አይሆንም:: የፊላደልፊያ ህዝብ ብዛት ሁለት ሚሊዮን አካባቢ ሲሆን የቆዳ ስፋቷ ደግሞ በስተንና ሚሊዋኪ፣ ፓሪስና በርሊን በጋራ ሆነው ያላቸውን ሥፋት እኩል ትሆናለች:: 130 ስኩዌር ማይልስ ከሚሆነው የግዛታችን መሬትና ወደ 8,000 ጋሻ የሚሆነውንና በጣም ምርጥ የሆነውን ክፍል ቆንጆ ለሆኑ መናፈሻዎች፣ አደባባዮችና፣ መንገዶች በማዋል ለመዝናኛና ለመደሰቻ ትክክለኛና ምርጥ ቦታ እንዲሆኑ በማድረግ ለማንኛውም ጨዋ የሆነ አሜሪካዊ የሚደሰትባቸንውና የሚዝናናባቸውን ምቹ አካባቢዎችን ለመፍጠር ችለናል::

ወደጀቼ ፊላደልፊያ በጣም ትልቅ ፅዱና ቆንጆ የሆነች ከተማ ብቻ ሣትሆን የዓለም ታላቋ የሥራ ማሣያ ከተማ ተደርጋ በየትኛውም ቦታ ትታወቃለች:: የዓለም የሥራ ፈጠራ ማሣያ ለመባል የበቃችውም በ9200 በሚሆኑት የማምረቻ ተቋማት ውስጥ ከ400,000 በላይ የሆኑ ሠዎች ተቀጥረው የሚሠሩ ሲሆን ይህም የሠው ኃይል በአንድ ቀን የሥራ ጊዜ ውስጥ ባሉ በእያንዳንዷ አስር ደቂቃዎች ወደ 100ሺህ ዶላር የሚጠጋ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች አምርቶ ያወጣል:: አንድ የስታትስቲክስ ባለሙያ እንዳቀረበው ዘገባ ደግሞ የትኛውም የአሜሪካን ከተማ ከሱፍ በሚሰሩ ምርቶች፣ በቆዳ ውጤቶች፣ በስፌት ዕቃዎች፣ በጨርቃጨርቆች፣ በባርኔጣዎች፣ በማምረቻ መሣሪያዎች፣ በወጥ ቤት ዕቃዎች ሃይል በሚሰጡ ባትሪዎች፣ ከብረት በሚሰሩ መርከቦችና ሌሎች ብዙ ነገሮች ፊላደልፊያን የሚወዳደራት እንደሌለ ገልጿል:: የባቡር ሃዲድ ተሽከርካሪዎችን በየሁለት ሠዓት ቀንና ማታ የምናመርት ሲሆን ከግማሽ በላይ የሆነው የዚህች ታላቅ ከተማ ነዋሪ ይጠቀማል:: ደግሞ በዚሁ ከተማ በተፈበረኩ ተሽከርሪካዎችና መኪኖች

በአንድ ደቂቃ ውስጥ 1000 ሲጋራ ስናመርት በ115 በሚሆኑት የውስጥ ልብሶችን በሚያመርቱ ፋብሪካዎቻችን ደግሞ ባለፈው ዓመት ብቻ ሁለት ጥንድ

ለእያንዳንዱ ወንድ ሴት ህፃን ካልሲና ስቶኪንጎችን በሃገር አቀፍ ደረጃ ለሚኖር በጋራ ሆነው ሲያመርቱት አምርተናል :: ታላቋ ብርታንያ እና አየርላንድ እናመርታለን:: እውነት ስጋጃዎችንም ከሚችሉት በላይ የወለል ምንጣፍና ፋበሪካዎቻችን የሚያስገኙት ለመናገር ከአጠቃላይ የንግድ እንቅስቃሴዎቻችንና ዓመት በባንኮች 38 ቢሊዮን ዶላር ገቢ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ባለፈው በመላው ሃገሪቱ የሚገኘውን የገንዘብ የተጣራ ትርፍ ያስቀመጥን ሲሆን ይህም ነገር ግን ወዳጆቼ በነዚህ የማምረቻ ደረሰኝ ለመተካተና ለመግዛት ያስችለን ነበር:: ያህል ·እንደዚሁም የታላቅ የህክምና ፋብሪካዎች ዕድገት በጣም የምንኮራውን በመሆናችንም በጣም እንኮራለን:: ከዚህ ዘርፎች የጥበብና የትምህርት ማዕከል ነገር ደግሞ በየትኛውም አለም በላይ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ ኩራት የሚያላብሰን መኖሪያ ቤቶች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር ከሚገኙ ከተሞች ውስጥ ካሉት የግለሰብ መኖሪያ ቤት ቁጥር የበለጠ መሆኑ ነው:: በፊላደልፊያ ከተማ የሚገኘው የግለሰብ መኖሪያዎች ያሉ.

በዚህች ከተማ 397.000 ተነጣጥለው የተሰሩ የግለሰብ መሬቶች ላይ ወደጐን ሲሆን እነዚህን ቤቶችም 25 ጫማ ስፋት ባላቸው የዚህ መስመር ርዝመት እየደረደርን አንድ መስመር ብናስቀምጣቸው አቋርጦ ወደ ካንሣስ ይደርስና ከፊላደልፊያ በመነሣት ይህን የስብሰባ አዳራሽ ዴንቨር ላይ ያቆም ነበር:: እንደገና አልፎ በመሄድ 1,881 ማይሎችን በመሸፈን እንድትሠጡኝ የምሻው ጉዳይ ነገር ግን አሁን ላነሣው የፈለኩትና ትኩረታችሁን በሠራተኛው ማህበረሰብ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩት ቤቶች በባለቤትነት የተያዙት ወለል እና ከበላዩ ክፍል በመሆኑና አንድ ሰው ደግሞ የሚያድርበትን ቤት በሽታዎች ያለውን ጣራ የራሱ የግሉ ያደረገ ጊዜ እነዚህ ከውጭ ሰርገው የሚገቡ የማያስነሳ ማለትም ሰፕሊዝምና በልሺሺዝም ተጠቂ መሆኑ የማይቀርና ክርክር የመሆኑ ጉዳዩ አሣሣቢነትና አንገብጋቢነት ነው::

የምትመኝ ፊላደልፊያ ለአውሮፓ ፈላጭ ቆራጭ መንግሥታት ግዙፎቹ አይደለችም:: ምክንያቱም መኖሪያዎቻችን፣ የትምህርት ተቋሞቻችንና እዚሁ የማምረቻ ፋብሪካዎቻችን ለፍሬ ሊበቁ የቻሉት በዚህ እውነተኛ በሆነና ክብሮች እከተማችን በተወለደው አሜሪካዊ መንፈስና ከአባቶቻችን በወረስናቸው ነፃነት ነው:: ፊላደልፊያ የዚህች ትልቅ ሃገር ወላጅ እናት የሆነችና የአሜሪካም ከተማ ከውሰጧ የፈለቀባት ወይም ለመገኘቷ ምንጭ የሆነች ከተማ ነች:: ይህች አዋጅ የመጀመሪያዋ የአሜሪካን ባንዲራ የተሠራባት፣ ይህች ከተማ የነፃነታችን ስብሰባ ሲታወጅ ስምምነቱ የተፈረመባት የመጀመሪያው የአሜሪካን ምክር ቤት ቦታ የተቀመጠባት፣ በአሜሪካ በጣም ተወዳጅ የሆነው ክቡር አስክሬን ያረፈት ህፃናት የሚገኙባት፣ በነፃነቱ ደወልም በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወንዶች ሴቶችና ለሥራ እንዲነሳሱ ያደረገች ከተማ ነች::

ይህም ስለዚህ አንድ ልንፈፅመው የሚገባን የተከበረ ግዳጅ ይጠብቀናል:: ከወርቅ የተሠራችውን ጥጃ ማምለክ አይደለም:: ነገር ግን የአሜሪካዊነትን ስሜትና መንፈሱን ለሌሎች ማዳረስ፣ የነፃነትን እሣት በውስጣችን እንዲንቀለቀል በማድረግ እግዚአብሔር ዋሽንግተን ባለው መንግስታችን፣ በሊንከንና በቴዎደር ሩዝቬልት ፈቃድ በአለም ላይ ለሚኖር የሠው ልጆች ሁሉ መድህን እንድንሆን ይርዳን:: እስቲ አሁን ይህን ንግግር በዝርዝር እንመልከተው:: እንዴት

እንደተደራጀና ተፈላጊውን መልዕክት ለማስተላለፍ እንደቻለ እንገምግመው:: በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ንግግር መግቢያ የተበጀለትና ጥሩ የሆነ መደምደሚያም ያለው ነው:: አልፎ አልፎ ከሚያጋጥሙና ልናስበው ከምንችለው በላይ ለየት ያለ አቀራረብ ያለው ንግግር ነው::

ከአንድ የሆነ ቦታ ይነሳል:: ወዲህና ወዲያ ሣይዘል ፣ ጊዜ ሳያባክንና ሳይንቀራፈፍ መድረስ ከፈለገበት ቦታ ልክ እንደምትበር ዝዬ ሠተት ብሎ ይገባል:: የእኔነት ስሜት የሚንፀባረቅበትና ሁሌም የማይሰለች አዲስ ንግግር ነው ያደረገው:: ተናጋሪው ንግግሩን የጀመረበት ዘዴ ሌሎች ተናጋሪዎች ባላደረጉት ሁኔታ ስለአራሱ ከተማ አንዳንድ ነጥቦችን ከማንሣት ጠቅላላ ሃገሪቷ እንደትፈጠር ምክንያት መሆኗን በመጥቀስ ነው::

በአለም ላይ ከሚገኙ እጅግ ትልቅና ወብ ከሆኑ ከተሞች መካከል አንዷ መሆኗንም ይጠቅሣል:: ይህ ግን በጥቅሉ የተቀመጠና በራሱ ነገሩን የሚገልጥ በመሆኑ ማንንም በጣም ሊያስደንቅ አይችልም:: ተናጋሪውም ይህን ነገር ያውቃል:: ስለዚህም የአድማጩን ትኩረት የበለጠ ወደ ፊላዳልፊያ የቆዳ ስፋት እንዲያደርግ ቦስተንና ሚሊዋኪ፣ ፓሪስና በርሊን በአንድ ላይ ቢሆኑ የሚኖራቸውን የቆዳ ስፋት እኩሌታ የሚሆን ስፋት እንዳላት በመናገር ተጠቀመበት:: ይህ እውነተኛና ትክክል የሆነ እውነታ ስለሆነ ለመስማት ይጋብዛል፣ ያስደንቀናል፣ እንድናስታውሠውም ምልክት ይሆናል፣ በሙሉ ገፅ የተሠሩ ስታስቲክሶች ሊሠጡ ከሚችሉት በላይ ግንዛቤን አስጨብጦ ይልከናል::

ቀጥሎ ደግሞ የተጠቀሠው ፊላደልፊያ «በየትኛውም ቦታ የዓለም የሥራ ፈጠራ ማሣያ ቦታ» ተብላ እንደምትጠራ ነው:: ልክ ፕሮፓጋንዳ በሚመስል መልኩ ለማመን ይከብዳል አይደል? ነገር ግን በቀጥታ ወደሌላ ርዕስ ቢሸጋገር ኖሮ ማንም ሊያምነው አይችልም ነበር:: እሱ ግን ይህን አላደረገም:: ከዚያ ይልቅ እረፍት በመውሠድ የጠቀሠው ፊላደልፊያ ዓለምን በሙሉ በመብለጥ የምታመርታቸውን «የሱፍ ልብሶች፣ የቆዳ ውጤቶች፣ የስፌት ዕቃዎች፣ ጨርቃ ጨርቆች፣ ባርኔጣዎች ፣ የወጥ ቤት ዕቃዎች የማምረቻ መሣሪያዎች፣ ሃይል ሰጪ ባትሪዎች ፣ የብረት መርከቦች » መጥቀስ ቀጠለ:: አሁን በአብዛኛው መልኩ ፕሮፓጋንዳ አይመስልም፣ ይመስላል እንዴ? ፊላደልፊያ በቀንና በማታም ጭምር በባቡር ሃዲድ ላይ የሚሽከረከሩ ተንቀሣቃሾችን በየሁለት ሠዓቱ እንደምታመርትና ከግማሽ በላይ የሚሆነው ነዋሪ ደግሞ የዚያው ከተማ ስራቶች በሆነ ተሽከርካሪዎችና መኪኖች እንደሚገለገል ገልጿል::

«ጥሩ ይሁን እኔ ፍፁም አላውቅም ነበር» ስንል ሁላችንም ተደንቀን «ምናልባትም ትላንት ከተማ ወጥቼ የነበረ ጊዜ በነዚህ መኪኖች ተጠቅሜ ይሆናል:: ነገር ግን እነዚህ ተሽከርካሪዎች ከየት እንደተገዙ አጣራለሁ::» «በደቂቃ አንድ ሺህ ሲጋራዎች. . . ለእያንዳንዱ ህዝቦች ሃገር ለሚኖር ወንድና ሴት እንዲሁም ህፃን ሁለት ጥንድ ካልሲዎች» አሁንም አግራሞታችን ቀጥሏል::......«ምናልባትም እኔ የምወደው ሲጋራ እዚህ ከተማ ይሆናል የተመረተው.........ይህ ያደረኩት ካልሲም እንደዛው»

ቀጥሎ ተናጋሪው ምን አደረገ? የፊላደልፊያን የቆዳ ስፋት በተመለከተ ዘው በማለት ቅድም ሣይጠቅስልን ያለፋቸው ነገሮች ስለነበሩት ወደኋላ ተመልሶ በደንብ ዘርዝሮ መናገር ጀመረ? በፍፁም እንዲህ አላደረገም የጀመረውን ነጥብ በማተኮር ወደኋላ ተመልሶ እስኪጨርስና እስኪደመድም እዛው ላይ ብቻ ያጠናቅቀዋል፡፡ ለዚህም ውድ ተናጋሪያችንን ማብራራት እንዳያስፈልገው አድርጐ በተገቢው ሁኔታ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

በጣም ግራ በተጋባና በሚያወዛግብ ሁኔታ ከአንዱ ርዕስ ወደሌላው እየዘለለ ከሚናገር ሰው የበለጠ ድንግዝግዝ ሲል ውር ውር እንደሚሉብን የሌሊት ወፎችን የመሠለ የሚያወራጨንና የሚረብሸን ድርጊት ከወዴት ይገኛል? ይሁን እንጂ ብዙ ተናጋሪ ሠዎች ይህን ሲፈፅሙት ይታያሉ፡፡ ሃሣቡን ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ 1.2.3.4.5. እያለ ከመዘርዘር ይልቅ አንድ የእግር ኳስ ቡድን አንበል 27.34.27.19.2.34.19 በማለት የተጫዎቾቹን የማልያ ቁጥር እንደሚጠራው ንግግሩን ያጠቃልላል፡፡

ይህኛው ተናጋሪያችን ግን ምንም ባልተዛነፈ ሁኔታ የተሠጠውን ሠዓት ሣያቆራርጥ ፣ ወደኋላ ሣይመለስ ጠብቆ ንግግሩን ወደፊት እያቀጣጠለ፣ ተሽከርካሪዎች ወደፊት ወደግራና ወደቀኝ ሣይዞር ልክ ሲጠቀሣቸው እንደነበሩት አንደ ድክመት ሊቆጠርበት መንዝ ችሏል፡፡ አሁን ግን ከጠቅላላ ንግግሩ ውስጥ የሚያስችለውን ዓረፍተ ነገር እንዲህ ብሎ ተናገረ፡፡

ፊላደልፊያ «ከዚህ ሃገር ከሚገኙት ሁሉ ታላቋ የጥበብ፣ የህክምና እንዲሁም የትምህርት ማዕከል ናት» ከአሥራ ሁለት በማይበልጡ ቃላቶች እውነታውን በደንብ ይገልፁልኛል፣ ብሩህ የሆነ መልኩም በሰዎች ህሊና ውስጥ ሊቀረፅና ሊታወስ ይችላል በሚል መንፈስ ይህችን ንግግር ወርወር አደረገና በቀጥታ ወደ ሌላ ርዕስ ዞረ፡፡ በአጠቃላይ ንግግሩ ካካተታቸው ወደ 65 የሚጠጉ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥም አስራ አንድ የሚሆኑት ቃላት ሊባክኑና ሊጠፉ ችለዋል፡፡ በእርግጥም ይህች በንግግሩ ልትሣካለት አልቻለችም፡፡ ምክንያቱ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የሰው ልጅ አዕምሮ ልክ በተከታታይ ሁኔታ እንዲያጠምዱ ተደርገው በተዘጋጁ የብረት ወጥመዶች ዓይነት ሊሠራ አይችልም፡፡ ለዚህ ነጥቡም ብዙ ጊዜውን ያልሠዋበት፣ ያላብራራዉና ጠቅለል አድርጐ ያቀረበው ስለነበረ አድማጩ ላይ ያመጣው ውጤት ዜሮ መሆኑን እንኳን አይቶ ምንም መደነቅ አልፈጠረበትም፡፡

ምን ቢያደርግ ሊያስተካክለው ይችል ነበር?

ይህን ሃሣብ ተመሣሣይ የሆኑ ቴክኒኮችና ዘዴዎችን በመጠቀም ልክ ፊላደልፊያ የዓለም ሥራ ፈጠራ ማሣያ መሆኗን እንዳስረዳበት አድርጐ ማቀናጀት ይችል እንደነበረ ያውቀዋል፡፡ በሌላ ጐኑ ደግሞ ለንግግሩ የተሠጠው ሰዓት ወደፊት እየነጐደበትና ከአምስት ደቂቃ በላይ አንዲትም ሰኮንድ እንደማይኖረው ተረድቷል፡፡ ስለዚህ ያለው ምርጫ ይህን ነጥብ አድበስብሶ ማለፍ ወይም ደግሞ ሌሎች ንግግሮቹን ቆራርጦ መጣል ብቻ ነበር፡፡

«በሌላው ዓለም ከሚገኙት ጋር ሲነፃፀር በፊላደልፊያ ያሉት የግል መኖሪያ ቤቶች ብዛት የበለጡ ናቸው፡፡» ይህን የርዕሱን አንድ ክፍል አስደናቂና

አሣማኝ አድረጎ ማቅረብ ቻለ? በመጀመሪያ የቤቶቹን ቁጥር ሰጠን (397,000) ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ እንዲህ በማለት በአዕምሮአችን ስዕሉን እንድንስለው አደረገን፡፡«እነዚህ ቤቶች 25 ጫማ ባላቸው የተከፋፈለ መሬቶች ላይ ጉን ለጉን ተደርገው በአንድ መስመር ቢደረደሩ ይህ መስመር ከፊላደልፊያ በመነሣት ይህን የስብሰባ አዳራሽ አቋርጦ ካንሣስን ያልፍና 1881 ማይሎችን በመሸፈን ዴንቨር ይደርስ ነበር፡፡» ምናልባት ንግግሩን ከመጨረሱ በፊት አድማጩ የተጠቀሠውን የቤቶች ቁጥር ሊረሣ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህን ስዕል ይረሣዋልን? ይህ መቼም ፍፁም ሊሆን የማይችሉ መረጃዎቹ የቀዘቀዙ እውነታዎችን የያዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ምርጡ ንግግር እነሱን ባለማካተቱና እነዚህንም ሳይጠቅስ የተዘጋጀ በመሆኑ ነበር፡፡ ይህ ተናጋሪ ልብን በመንካት ስሜትን በመጫርና ከፍተኛ የሆነ የስሜት ጡዘትን በመፍጠር ማነሳሳት ችሏል፡፡ ካሁን በኋላ ደግሞ ሲያስተላልፈው የፈለገው ዋናው ጉዳይ ቤቱን የተመለከተውን ሃሳብ በማንሳት ሊገባ ይችላል፡፡ የእነዚህ መኖሪያ ቤቶች ባለቤት መሆን በከተማው ለሚኖረው የህይወት እንቅስቃሴ ምን ማለት እንደሆነ ተናገረ፡፡ እንዲሁም ሶሻሊዝምና ቦልሸቪዝም ተብለው የሚጠሩት ከውጭ ሃገር የሚገቡ በሽታዎችን አወገዘ፣ ፊላደልፊያን ደግሞ «ለአሜሪካ ነፃነት መገኛት ዋና ምንጭ» በማድረግ አሞጋገሣት፡፡ ነፃነት ምትሃታዊ የሆነ ቃል፣ በስሜት የተሞላ ቃል፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሠዎችን ህይወታቸውን የሰውለት ቃል፡፡

ይህ ሀረግ በራሱ ጥሩ ቢሆንም ታሪካዊ ማጠቃሻዎችን በማስደገፍና መረጃዎችን በማካተት በአድማጮቹ ልብ ውስጥ ከአንድ ሺህ ጊዜ በላይ የተከበረና የተወደደ እንዲሆን አደርጎታል፡፡ «የመጀመሪያው የአሜሪካን ሰንደቅ ዓላማ (ባንዲራ) የተሠራባት ከተማ ናት የመጀመሪያው የአሜሪካን ምክር ቤት ስብሰባ የተደረገባት ከተማ ናት የነፃነት አዋጅ  ሠነድ የተፈረመባት. . .የነፃነት ደወል. . . . የተከበረ ግዳጅ የተወሰደበት አሜሪካዊ መንፈስን ማዳረስ. . .የነፃነትን እሣት በልባችን እያቀጣጠልን እግዚአብሔር፣ በዋሽንግተን ባለው መንግስታችን በሊንከን እንዲሁም በቴዎዶር ሩዝቬልት ፈቃድ ለሠው ልጆች ሁሉ መድህን ይሆን ዘንድ የበቃንበት» ይህ በእውነትም የመጨረሻውን ኢላማ የመታ ንግግር ነበር፡፡

የንግግሩን አወቃቀርም በተመለከተ የምንለው ነገር ተመሣሣይ ነው፡፡ ይዘቱንና አደረጃጀቱንም እናደንቃለን፡፡ ነገር ግን ይህ ንግግር የተደረገው ቀዝቀዝ ባለ ህይወት አልባ መንፈስ ቢሆን ኖሮ በአሳዛኝ ሁኔታ አስፈሪ ያልተሳካና አስቀያሚ ይሆን ነበር፡፡ ተናጋሪው ግን ቆንጆ አድርጎ እንዳቀናበረው ሁሉ ከውስጥ ፈንቅሎ በሚወጣ ጥልቅ የሆነ ስሜት ትህትናን ተላብሶ ሊያቀርበው ችሏል፡፡ ስለዚህም በውድድሩ አሸንፎ የአንደኝነትን ደረጃ ማግኘቱና የቺካጐን ዋንጫ መሸለሙ አያስገርምም፡፡

ዶ/ር ኮንዌል ንግግሩን ለማዘጋጀት ዕቅድ ያወጣበት መንገድ ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት በጣም ምርጥ የሆነ ንግግር ማቀናበርን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ምንም አይነት ህጐችና መመሪያዎች ሊያስቀምጡለት አልቻሉም፡፡     ማንኛውም አይነት ስዕላዊ መግለጫዎች፣ መመሪያ ዘዴዎችና ሰንጠረዦች ለሁሉም አይነት ንግግሮች እንዲስማሙ



Scanned with CamScanner

ተደርገው ሊቀረፁና ሊዘጋጁ ይቅርና በርከት ካሉትም ጋር እንኳን ማስማማት ይከብዳል፡፡ይሁን እንጂ ጥቂት የሆኑት የንግግር መመሪያዎች ለተወሠኑ ዓረፍተ ነገሮች ዝግጅት ሊረዱን ይችላሉ፡፡

ዶ/ር ሩሴል ኤች ኮንዌል የተባለው «የአልማዝ ጋሻዎች» የሚለውን መፅሐፍ የፃፈው ሰው አንድ ጊዜ እንዳጫወተኝ ከሆነ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ንግግሮቹን ቀጥሎ ባለው መሟፉያ መሠረት ለማዘጋጀት ችሏል፡፡

1. እውነታዎችን ጥቀስ
2. ከእነዚህ እውነታዎች በመነሣት አስረዳ
3. እርምጃ እንዲወሰዱ በማነሳሳት

ብዙ ሠዎች እነኚህን መመሪያዎች በጣም ጠቃሚና ለንግግር የሚያነቃቁ ሆነው አግኝተዋቸዋል፡፡

1. ስህተት የሆነውን ነገር አሣይ
2. እንዴት መስተካከል እንደሚችል ዘርዝር
3. ትብብር እንዲደረግልህ ጠይቅ

ወይም በሌላ መልኩ ለማስቀመጥ

1. ይህ አሣሣቢና አስቸኳይ መፍትሔ የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡
2. ጉዳዩን በተመለከተም እንዲህና .... እንዲህ ማድረግ ይጠበቅብናል
3. እናንተም በዚህ በዚህ ምክንያት እርዳታ ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡

ይህ መመሪያ እንደገና በተብራራ ሁኔታ ንግግራችንን ለማቀድ ይረዳል፡፡

1. ትኩረት ልትስብ መቻልህን አረጋግጥ
2. አሳማኝ ሁን
3. እውነት የምትላቸውን ዘርዝርና ያንተን ሃሣብ ተመረኩዘህ ሠዎችን ለማስተማር ጥረት አድርግ
4. ወንዶችን ለድርጊት የሚያነሳሱ ምክንያቶችን በመጥቀስ ጥያቄህን አቅርብ

ዝነኛ የሆኑ ወንዶች እንዴት ንግግሮቻቸውን እንዳዘጋጁ የቀድሞ ሴናተር የነበረው አልበርት ጂ ቢቨረጅ «በጣም አጭርና ሊተገበር የሚችል በህዝብ ፊት የመናገር ጥበብ» የሚል መፅሐፍ ፅፎ ነበር፡፡ ይህ የማይረሳ የፖለቲካ ሠው «አንድ ተናጋሪ የሚናገረው ርዕሰ ጉዳይ አዛዥ ወይም ጌታ መሆን ይኖርበታል» ብሎ ነበር፡፡ ይህም ማለት ሊካተቱ የሚገባቸው እውነታዎችን በሙሉ በመሰብሰብ መቀናበርና መጠናት አለባቸው፡፡ በአንድ ወገን ያሉትን መረጃዎች ብቻ ሣይሆን በሁለቱም ወገን እንዲሁም በአጠቃላይ ያሉት መረጃዎች ሁሉ መብላላት አለባቸው፡፡ ተራ ግምት ወይም ያልተረጋገጡ መረጃዎችን እንዳናካትታቸው መጠንቀቅና እርግጠኛ እስክንሆን መመርመር፡፡



Scanned with CamScanner

ስለዚህም ሁሉንም ዝርዝር ሃሣቦች መፈተሽና በግልፅ ለይቶ በማውጣት እርግጠኛ እስክንሆን ግምገማ ማድረግ::

ግን ምኑን እርግጠኛ እስክንሆን?

የራስህን ዜጐች ለመምከር መረጃ ለመስጠትና ለማስተማር አይደለም እንዴ የተነሣኸው? እራስህንስ ልክ እንደባለሥልጣን እያስቀመጥክ አይደለም እንዴ?

የማንኛውም ችግር እውነተኛ የሆኑ መረጃዎችን ከሰበሰብንና ካዘጋጀን በኋላ ለችግሩ መፍትሄ ነው የምንለውን ነገር ከውስጣችን ለማፍለቅ እንሞክር:: ከዚያ በኋላ ንግግራችሁ ጥራትና ኃይል ያለው ይሆናል:: የምትሉት ሃሣብም ይኖራችኋል:: በመጨረሻም ላይ ሃሣባችሁን ጥርት ባለና ስነ አመክሮያዊ በሆነ መንገድ ዓፉት::»

በሌላ አነጋገር በሁለቱም ወገን ሲኖሩ የሚችሉ እውነታዎችን ካቀረባችሁ በኋላ እነዚህንም እውነታዎች ሊያብራሩና ሊያጠሩልን የሚችሉ ማጠቃለያዎች በመዘርዘር ለማቅረብ ሞክሩ::

ፕሬዝዳንት ዊድሮው ዊልሰን በአንድ ወቅት ንግግሮቹን የሚያዘጋጅበትን ዘዴ ሲጠየቅ «ዝግጅት የምንጀምረው በንግግሬ ሽፋን ለመስጠት የምፈልጋቸውን ርዕሶች ዘርዝሬ በማውጣት በአዕምሮዬ እያብሰለሰልኩ ለማቀናጀትና ለማዋሃድ እየጣርኩ ነው:: ይህም የጉዳዩን ዋና ፍሬ ነገር ወይም ጠንካራ ክፍል ለመገጣጠም ስለሚረዳኝ በኋላ ላይ በአጭሩ እፅፈዋለሁ:: ሁልጊዜም ቢሆን በአጭር በአጭሩ መፃፍ ስለተለማመድኩ በጣም ጊዜ ቆጣቢ መሆኑን አውቀዋለሁ:: ይህ ከተጠናቀቀ በኋላ ኃረጐችን እየቀየርኩና ዓረፍተ ነገሩን እያስተካከልኩ እግረ መንገዴንም መረጃ እየጨማመርኩ በግል የመተየቢያ ማሽን እፅፈዋለሁ::»

ቴዎዶር ሩዝቬልት ንግግሮቹን የሚያዘጋጀው በሚታወቅበት ሩዝቬልታዊ ባህሪ ነው:: ይህም እውነታዎችን ቆፍሮ ያወጣል:: እየመላለሰ ይከልሳቸዋል፣ ከፍ ያለ ግምት ይሰጣቸዋል:: እንዲሁም ምንነታቸውን ይለይና ንቅንቅ በማይል የእርግጠኝነት ስሜት ወደ ማጠቃለያው ይደርሳል:: ከዚህ በኋላ ከፊት ለፊቱ ማስታወሻውን በማስቀመጥ እየተናገረ መለማመድ ይጀምራል:: ፍጥነት ባለው ሁኔታ ረገጥ እያደረገ ስለሚናገረው ጥድፊያ በተሞላበት ግምታዊ ሁኔታ ጋር ስለሚላመድ ንግግሩን ህይወት ባለው መንፈስ ለማስተላለፍ ያስችለዋል::

ከዚህ በኋላ ካመተየቢያ ማሽኑ ጋር በመሄድ ይከልሰዋል:: ይጨምርበታል፣ እየሰረዘ ይቀንሳል፣ በእርሳስ ምልክት ያደርግበታል፣ እንደገና ደግሞ ከመጀመሪያ ጀምሮ እየተናገረ ይለማመደዋል::

«ከፍተኛና አድካሚ ጥረት ሳላደርግ በምርጥ ውሳኔ ስጨነቴ ሳልጠቀም በጥንቃቄ ዕቅድ ሳላወጣና ስራዬንም እየቀደምኩ ሳልከውን ምንም ነገር አሸንፌ አላውቅም» ይላል:: ብዙ ጊዜ ፅፎ ያዘጋጀውን ንግግር እንዲያዩለት ወይም ሲናገር እያዳመጡ አስተያየት እንዲሰጡት ሠዎችን ይጋብዝ ነበር:: እሱ በብልሃት በሚናገራቸው ጭብጦች ላይ መከራከርን አይፈልግም፣ ምክንያቱም አዕምሮው በዚህ ነገር ላይ ቀደም ብሎ ያለማወላወል ውሣኔ ላይ ስለሚደርስ ነበር::

ስለዚህም ምን መናገር እንዳለበት ሳይሆን እንዴት መናገር እንዳለበት እንዲነግሩት ብቻ ነበር የሚፈልገው፡፡ ይህን ንግግሩን ደግሞ ደጋግሞ ወደ ታይፕ መተየቢያው እየሄደ ይገለብጠዋል፣ ቆርጦ በማውጣት ያስተካከለውና ያሻሸለው ነበር፡፡ በጋዜጦች ላይ የሚታተሙት ንግግሮቹ እነዚህ ነበሩ በእርግጥ ሁሉንም ንግግሮቹን ሊያስታውሣቸው አይችልም፡፡

በጋዜጣ ተቀባብተው

በንግግሩ ጊዜ የሚጠቀምባቸው ቃላቶች ነገር ግን በቃሉ ንግግሩን እየደጋገመ ከሚታተሙት ጋር ልዩነት ይኖራቸዋል፡፡ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነው ልምምድ የሚያደርግበትና የሚከልስበት መንገድ መረጃዎችና ከንግግሩ ቅደም የመዘጋጀት ዘዴው ነበር፡፡ ይህም ከሚያበቃባቸው በሌላ የተለየ ዘዴ ሊያገኝ ተከተል ጋር በጣም እንዲላመድ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ድምቀትን ይሰጡታል፡፡ የታሪክ ፍሰትና ው ከሚችለው በላይ እርግጠኛነት እየተናገረ በማጥናት

ሰር ኦሊቨር ሎጅ እንደነገረኝ ከሆነ ንግግሩን በቃሉ በፍጥነት መናገሩ ልክ እድማጩ ፊት እንደቀረበ ሆኖ ጮክ እያለ በመደጋገም ብዙ ንግግር ለማድረግ እጅግ በጣም ድንቅ የሆነ የዝግጅት መንገድ ሆኖለታል፡፡ ድምፃቸውን በንግግር መቅጃ የሚለማመዱ ተማሪዎች ጮክ ብለው እየተናገሩ ማዳመጥና መገምገሙ መሣሪያ ከቀረፁ በኋላ እንደገና መልሰው እራሳቸውን ተናግረዋል፡፡ አዎን፣ ትክክል ትምህርታቸውን ግልፅ ለማድረግ እንደጠቀማቸው አጥርተን ለማለፍ ብለዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ያልጠሩ ሃሣቦች ሲያጋጥሙን ይህም ዘዴ ብዙ ነገሮችን እንዲሁም በቀላሉ ንግግራችንንም ለመፃፍ ይረዳል፡፡ እንድትጠቀሙበት እመክራለሁ፡፡ ጠቅለል አድርጐ በመያዙ እናንተም በደንብ መለማመድን በግዴታ

ምን መናገር እንዳለብህ በፅሑፍ ካሠፈርክ ጥርት ያለ እንዲሆን በማድረግ በአዕምሮህ እንድታስበው ያደርግሃል፡፡ አስተሳሰብህ በጣም በመቀነስ ንግግርህን በጥሩና ለመቅረፅ ያስችልሃል፡፡ የሃሣብህን መዋዥቅ በተሻለ ሁኔታ እንድታደርገው ይረዳሃል፡፡

ቤንጃሚን ፍራንክሊን የራሱን የህይወት ታሪክ በፃፈበት መፅሐፍ እንዴት የመናገር ችሎታውን እንዳዳበረ፣ ሃሣቦቹን አቀናጅቶ ለማቅረብ ራሱን ያስተማረባቸውን ዘዴዎችና ቃላቶቹን ለመጠቀም ያለውን ዝግጁነት ክላሲክ ሲሆን እንደሌሎቹ ዘመናዊ ፅሑፎች በተለየ ሁኔታ የማይሰለች ለማንበብም የሚጋብዝና አስደሳች ይዘት ያለው ነበር፡፡ መናገር የፈለገውን መልዕክት በደንብ የሚገልፅና በብዙ መልኩም ሲጠራ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ምሳሌ መሆን የሚችል ነው፡፡ ማንኛውንም ንግግር ለማድረግና ፅሑፍ ለማዘጋጀት የሚፈልግ ሠው ይህን መፅሐፍ እንደ መመሪያ ደስ እያለው ሊጠቀምበትና ብዙ ጥቅምም ሊያገኝበት ይችላል፡፡

ቀጥሎ ከመፅሐፍ ላይ መርጬ ያቀረብኩትን ክፍል እንደምትወዱት እገምታለሁ፡፡ በአንድ ወቅት «ስፔክታተር» የሚባለውን መፅሐፍ ለየት ያለ ቅጅ አግኝቼ ነበር፡፡ ይህ ሦስተኛው ክፍል ሲሆን ከዚህ በፊትም ይህኛውን የመሠለ አይቼ አላውቅም ነበር፡፡ ገዛሁትና አነበብኩት፤ ደግሜ ደጋግሜ እያነበብኩት ስሄድ በጣም እየሳበኝና ደስ እያለኝ መጣ የአፃፃፍ ስልቱ በጣም ድንቅ ስለነበር ከቻልኩ አስመስዬ ለመፃፍ ተመኘሁ፡፡ ይህን ሃሣቤንም በጭንቅላቴ እያመላለስኩ ጥቂት

ወረቀቶችን አዘጋጀሁና በየአረፍተ ነገሩ ያሉትን ፍንጭ ሊሰጡ የሚችሉ ሃረጎችን በአጭር በአጭሩ እየገለበጥኩ በጥቂት ቀናት ውስጥ ጨረስኩ::

ከዚህ በኋላ መፅፉን ሳልመለከት እነዚህ ለመረጃ ያህል በአጭሩ የገለጥኳቸው አይነት ትርጉም እንዲኖራቸው እየሞከርኩ እንዲሁም የጐደለውን ቦታ የሚያሟሉ ቃላትን አስማምቼ በመጠቀም ለመፃፍና ለማነፃፀር ስሞክር ትንሽ የተሟሟትኳቸው ነገሮች አገኘሁበትና አስተካከልኳቸው:: በዚህ ጊዜ በርከት ያሉ አዳዲስ ቃላት አገኘሁና ልጠቀምባቸውና ልሰበስባቸው ፈለኩኝ:: እንደዚህ ያሉ ዓረፍተ ነገሮች እየሰራሁ ለመለማመድ ብሞክር ኖሮ ቀደም በማለት ይህን ዓይነት ብዙ የሆኑ ቃላትን የማወቁ ዕድል ይኖረኝ ነበር:: ብዬ አሰብኩኝ:: እነዚህን ቃላቶች ወደራሴ ሃሣብ ለማምጣት በሚደረግ ተደጋጋሚና የማይቋረጥ ሂደትም እየተከናወነ በተለያየ ርዝመት የተፃፉ የሚወጣውን መስፈርት ለማሟላት ወይም ከምፈልገው ዘይቤ ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ስል ያልተቋረጠ ፍለጋ በማድረግ የተለያዩ ይዘትና ትርጉም ያላቸውን ቃላት ወደማሰሱ ገባሁ:: እነዚህን የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ቃላትም በአዕምሮዬ ለማስተካከል እንዲገጥሙ ለማድረግ በመሞከሬም ችሎታዬን በማዳበር የተካንኩ እንድሆን አብቅቶኛል::

አንዳንድ ታሪካዊ የሆኑ ፅሑፎችን በመውሠድ መልሼ እየገለበጥኩ እፅፋቸዋለሁ:: አንዳንድ ጊዜ ምስቅልቅል ባለ ሁኔታ የሰበሰብኳቸው ፍንጭ የሚሰጡ ቃላት ትርምስምስ ይሉብኛል:: እነዚህን ፍንጮች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮቹን ሙሉ በማድረግ አስተካክዬ በመፃፌ አጠቃላይ ስራውን ለመጨረስና ምርጥ ወደ ሆነው አወቃቀራቸው ለማምጣት ለጥቂት ሳምንታት ያህል ጥረት ማድረግ ነበረብኝ:: ይህ ዘዴ ነበር ሃሣቦችን ለማቀናበር የረዳኝና ያስተማረኝ:: ቆየት ብዬ ደግሞ የእኔን ስራዎች ከዋናው ቅጅ ጋር ሳነፃፅረው ብዙ ስህተቶችን አገኘሁበትና እንደገና ጠጋግኜ አስተካከልኩት:: ለየት ባለ ሁኔታ የተፃፉ ቃላትን በማገኝበት ጊዜ ግን የቋንቋውን አወራረድ ለማሻሻል እሞክራለሁ:: ይህንን በማድረጌም ደስ የሚል ስሜት ስለሰጠኝ እራሴን ዕድለኛ አድርጌ ቆጠርኩት:: ከጊዜ በኋላም ተወዳዳሪ የማይገኝለት እንዲሁም የተዋጣለት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፀሃፊ እንደሚወጣኝ በመተማመኔ ከፍተኛ ብርታት ሰጠኝ:: እዚያም ቦታ ለመድረስ እጅግ በጣም ጓጓሁ::

## ከማስታወሻዎቻችሁ ጋር የሶሊታር ጨዋታ ተጫወቱ

ባለፈው ምዕራፍ ማስታወሻ መያዝ ያለውን ጥቅም ተመክራችኋል:: የተለያዩ ሃሣቦቻችሁን እና ምሣሌያዊ መግለጫዎቻችሁን በቁርጥራጭ ወረቀት ላይ ካሠፈራችኋቸው በኋላ ሶሊተር ተጫወቱበት:: በጨዋታው ላይ ተከታታይ የሆኑና አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ስብስቦችን እንደበታተናቸው ሁሉ ማስታወሻ የያዙትን ቁርጥራጮችም እንደዚያው እናድርጋቸው:: የማስታወሻው ክምር ዋና ክፍል የንግግራችሁን ፍሬ ነገር የያዙ አድርጉት:: ከዚህ በኋላ እንደገና ወደ ትንንሽ ቁርጥራጭ ከፋፍሏቸው:: ገለባው ከስንዴ እስከሚለይ ድረስም እናበጥራቸው:: በተቀማጭነት የሚቀሩ ይሆናሉ:: አንድ ሠው ስራውን በአግባቡ እያከናወነ የሚያገኘውን ገቢ ሙሉ በሙሉ ማጥፋት አይችልም:: የተወሠነውን

ክፍል ተቀማጭ ያደርጋል ስለዚህም የመለየቱና የማስቀመጡ ሂደት ይቀጥላል ማለት ነው::

አንድ ንግግር ለማድረግ የሚዘጋጅና የሚያጠና ሰው ንግግሩ እስከሚቀርብበት ዕለት ድረስ የሚያደርገውን ክለሣና ዝግጅት ማቋረጥ የለበትም:: ምክንያቱም ንግግሩን ከማቅረቡ በፊት ይቅርና ካቀረበ በኋላ እንኳን ሊሻሻልና ሊስተካከል የሚገባውና የቀረ ነገር እንደነበር ይታወሰዋል:: አንድ ጥሩ ተናጋሪም ሁል ጊዜ ንግግር አድርጎ በጨረሰ ማግስት ንግግሩ አራት ክፍሎች እንደነበሩት ተደርሶበታል:: እነሱም የመጀመሪያው እራሱ ያዘጋጀው፣ ሁለተኛው ለአድማጭ ያቀረበው:: ሦስተኛው በጋዜጦች ላይ እንዲህ እንዲህ አይነት ንግግር አደረገ ተብሎ የሚወጣው ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ ወደ ቤቱ እየሄደ እያለ እንዲህ እንዲህ አድርጌ ባቀረብኩት ኖሮ ብሎ የሚመኘው ናቸው::

## «በንግግሬ ጊዜ ማስታወሻዬን ብጠቀም ይሆን?»

ሊንከን ምንም እንኳን ያለምንም ማስታወሻ በቃሉ ንግግር በማድረግ የተካነ ቢሆንም ጌይት ሃውስ በደረሠ ማግሥት ግን ሃሣቡን በወረቀት ፅፎ ሣያዘጋጀው በፊት ምንም አይነት ይፋዊ የሆነም ያልሆነም ንግግር ለካቢኔው አላደረገም ነበር:: የበዓለ ሹመት ንግግሩም እንዲሁ እያነበበ እንዲናገር ተገደ ነበር:: ምክንያቱም የዚህ አይነት ታሪካዊ ይዘት ያላቸውን ንግግሮች ያለቅድመ ዝግጅት ማድረግ ዋጋ ሊያስከፍሉ ይችላሉና ለስህተት ሊጋለጡ አይገባቸውም:: ነገር ግን ሊንከን ኢሊኖስ እያለ አንድም ጊዜ ቢሆን ማስታወሻውን እያነበበ ንግግር አድርጎ አያውቅም ነበር:: «አድማጬን የማስልቸትና ግራ የመጋባት ስሜት ይፈጥሩበታል» ይላል:: ታዲያ ማንኛችን ነን ልክ አይደለህም ለማለት የምንደፍረው? እንደዚህ አይነቶች ማስታወሻዎችን ይዞ ለመናገር መሞከር ስለመናገር ካለህ ፍላጎት ላይ ግማሹ ያህሉን አያሳጣህም? የአይን ግንኙነት በማድረግ ከአድማጭህ ጋር መቀራረብን በመፍጠር እጅግ ጠቃሚ የሆነውን አጋጣሚ እንድትፈጥር ጋሬጣ ሊሆኑብህና ሊከለክሉህ አይችሉምን? ንግግርህ ያንተ እንዳልሆነ አይነት ስሜት እንዲፈጠርብህስ አያደርጉህም? በአድማጮችህ ዘንድ እምቅ የሆነ የንግግር ችሎታና ኃይል እንዲሁም በራስህ እምነት የሌለህ ሰው አድርጎ አያሣይህም?

ስለዚህ እደግመዋለሁ ማስታወሻዎችህን በንግግርህ ዝግጅት ወቅት ብቻ ተጠቀምባቸው፣ አብራራቸው፣ አትረፍርፌህ ያዛቸው:: ለብቻህ ሆነህ ንግግርህን በምትለማመድበት ጊዜ ልታያቸው ማሰብህ አይቀርም:: ወይም ደግሞ ከአድማጭህ ጋር ለንግግር በምትቀርብበት ወቅት የሆነ ቦታ በኪስህ ውሽቅ አድርገህ ብትገባ ምቾት እንዲሠማህ ሊያደርጉህ እንደሚችሉ ትገምታለህ:: ነገር ግን በተጐታች ስረገላ ላይ የሚቀመጡትን እንደ መደሻ፣ መጋዝና መጥረቢያ ያሉ በአደጋ ጊዜ የሚረዱ መሣሪያዎች የምንጠቀምባቸው ውድመት ሊያደርስ ከሚችል አደጋ እንዲሁም ለሞት ከሚያደርስ ጥፋት ለመከላከል ብቻ እንደሆነ

ሁሉ ያንተንም ማስታወሻ መጠቀም ያለብህና የሚረዳህ በእንደዚህ አይነት የአደጋ ጊዜ ብቻ ነው::

ነገር ግን ማስታወሻ መጠቀምህ የግድ ከሆነ በትልቅ ወረቀት ላይ በአጫጭሩና ጉላ ጉላ ባሉ ፊደላት ከፃፍክ በኋላ ንግግርህን ከምታደርግበት ጠረጴዛ ላይ ቀደም ብለህ በመግባት ከመፅሐፎች ሥር ደብቀህ ማስቀመጥ ትችላለህ:: ከዚህ በኋላ አስፈላጊ በመሠለህ ጊዜ አድማጮችህ ይህን ሊያስተውሉት በማይችሉበት ሁኔታ መልከት ማድረግ ትችላለህ ይህን ድክመትህን በንግግር ጊዜ ማስታወሻ መጠቀም እንደብልሃት የሚወሠድበት ጊዜ አለ:: ለምሣሌ ጀማሪ ተናጋሪ የሆኑ ሠዎች በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ንግግሮቻቸው የመረበሽና የአይን አፋርነት ስሜት ስለሚያድርባቸው የተዘጋጁበትን ንግግራቸውን ሃሣብ በሙሉ ፍፁም አያስታውሱትም:: ታዲያ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሃሳባቸውን መስመር ይስታሉ፣ እንዲሁም በደንብ የተለማመዱበትና የተዘጋጁበትን መረጃ ሊያገኙ አይችሉምና ዋናውን የአስፋልት መንገድ በመሣት አረግረጉ ውስጥ ይዘፈቃሉ::

ታዲያ በእንዲህ አይነት የተቸገሩ ሠዎች ትንሽና አጥር ያለች ማስታወሻ በንግግራቸው ጊዜ ይዘው ቢገቡ ምን ችግር ይኖረዋል? አንድ ህፃን እንኳን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመራመድ የሚሞክረው ጠረጴዛና ወንበሮቹን እየተደገፈ ነው:: መራመድ ከጀመረ በኋላ ግን አያስፈልጉትም::

## ንግግርህን ቃል በቃል አታጥና

ንግግርህን ቃል በቃል እያነበብክና ቀርፀህ ለመያዝ እየሞከርክ አትዘጋጅ:: ይህ በአንተ ላይ ጥፋት ከማድረሱም በላይ ጊዜህን ያለአግባብ ያባክንብሃል:: እንዲህም ሆኖ ግን አንዳንድ ሠዎች ይህን ማስጠንቀቂያ እየሰሙ እንኳን ሊሞክሩት ይፈልጋሉ:: አንድ በዚህ መንገድ የተዘጋጀ ሰው ለንግግር በሚነሣ ጊዜ ምን እያሰበ ይመስላችኋል? የሚያስተላልፈውን መልዕክት ይሆን? አይደለም:: ያጠናውን የንግግር ሀረጎች እንዳሉ ለማስታወስ እየሞከረ እንጂ ወደፊት ከማሰብ ይልቅ ወደኋላው እየተመለከተ ነው:: የሰው ልጅ አዕምሮ ተፈጥሮአዊና ተለምዶአዊ አሠራሩን እንዲተው እያስገደደው የተገላቢጦሹን ለማድረግ ይሞክራል:: ታዲያ በዚህን ጊዜ ሁሉም ነገራችን ድርቅ ያለ፣ ቀዝቃዛ ምንም ቀለምና ህብር የሌለው፣ ከሠው ፍላጐትም ጋር ሊጣጣም የማይችል ይሆናል:: ስለዚህም ነው በዚህ አይነቱ እርባና ቢስ የሆነ ነገር ላይ ጊዜያችሁን እንዳታጠፋ የለመንኳችሁ::

አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ የሥራ መግባቢያ ቃለ መጠይቅ ቢኖርባችሁ ቁም ብላችሁ ምን መመለስ እንዳለባችሁ ቃል በቃል ለማጥናት ትዘጋጃላችሁ? እንደዚህ ታደርጋላችሁ እንዴ? በእርግጥ አታደርጉም:: በዚህ ፋንታ አንዳንድ ማስታወሻዎችን እየያዛችሁና ስለቃለ መጠይቅ የሚያስረዱ መረጃዎችን በማውጣት አስፈላጊ የምትሉትን ነጥብ በአዕምሮአችሁ ለመያዝ ጥረት ታደርጋላችሁ:: ለራሳችሁም «ይህኛው ወይንም ያኛው ነጥብ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ እይዘዋለሁ እነዚህ ነገሮች ደግሞ በዚህ በዚህ ምክንያት አስፈላጊ

ስለሆኑ..........» እያላችሁ ታጠናላችሁ:: ከዚያም አስፈላጊ ሆኖ ያገኛችሁትን ነጥብ በምሣሌና በተጨባጭ ማስረጃ በማስደገፍ ለመያዝና ለማጥናት ትሞክራላችሁ:: በዚህ መንገድ አይደለም እንዴ ለቃለ መጠይቅ የምትዘጋጁት? ይህን ተመሣሣይ ዘዴ ታዲያ ለምን ለንግግር ዝግጅት ማድረግ በምትፈልጉ ጊዜ አትጠቀሙበትም?

## ግራንት ስፓማቶክስ

ጄኔራል ፓርከር የተባለው ሰው የተባበሩት ጦር አዛዥ የነበረውን ጄኔራል ግራንትን የምርኮ ስምምነት እንዲደረግ የሚያዝ ሠነድ እንዲዘጋጅለት በጠየቀው ጊዜ ግራንት ደግሞ በተራው ጄኔራል ፓርከርን አንዳንድ ለመፃፍ የሚረዱ መረጃዎች እንዲሠጠው ጠይቆታል::

«ልክ ብዕሬን ከወረቀት ጋር ሳገናኝ ምን ብዬ መፃፍ እንዳለብኝ የመጀመሪያው ቃል እንኳን ሊመጣልኝ አልቻለም:: አንድ የማውቀው ነገር ቢኖር በጭንቅላቴ ውስጥ የያዝኩት ሃሣብ መኖሩን ነው:: ነገር ግን ይህን ሀሣቤን ሣልሣሣት በግልፅ ፅፌ ማስቀመጥ ብችል እያልኩ ደግሞ እመኛለሁ::»

እንደ ጄኔራል ግራንት የመጀመሪያውን ቃል ማወቁ የግድ አስፈላጊህ አይደለም:: ለመናገር የፈለከው ነገር እንዳለህና ሃሣቡ በደንብ አለህ:: አንድ ግልፅ አድርገህ ለመናገር የፈለከው ነገር እንዳለህና ሃሣቡ በደንብ አለህ:: ስለዚህም በውጤቱ ያለተጨማሪ ጥረት ያንንም ለማከናወን ቁርጠኝነቱ አለህ:: ስለዚህም በውጤቱ ያለተጨማሪ ጥረት ያንንም ለማከናወን ቁርጠኝነቱ እንዲመጡልህ ማድረግ በተለምዶአዊ የንግግር ችሎታህ ብቻ በመጠቀም ቃላቶቹ እንዲመጡልህ ማድረግ ትችላለህ ማለት ነው:: ይህ ለማንኛውም ሰው የሚሠራና በጣም የሚጠቅም ነገር ትችላለህ ማለት ነው:: ይህን ሞክሩት:: አንድን ሰው ገፍትራችሁ ነው:: ጥርጣሬ ካላችሁ እስቲ ይህን ሞክሩት:: አንድን ሰው ገፍትራችሁ ብትጥሉት ከወደቀበት ሲነሣ ንዴቱን የሚገልፅበት ቃል ለማግኘት ጥቂት ጊዜያትን እንኳን ሲቸገር አታዩትም::

*ሆራስ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት እንደተናገረው:-*

*ቃላትን ሣይሆን እውነታዎችንና ሃሣቦችን ፈልግ::*

ከዚያ በኋላ ቃላቶቹ ሣትፈልጋቸው እየተሳቡ ይመጣሉ:: ሃሣብን አጠንክረህ በአዕምሮህ ከያዝክ በኋላ ንግግርህን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እየተለማመድከው ማሻሻል ትችላለህ:: ይህንንም በፀጥታ ሆነህ በአዕምሮህ አስበው:: በሻይ ጀበና የጣድከው ሻይ እስኪፈላ፣ በመንገድ ስትጓጓዝ፣ አሣንሠርህ እስኪመጣም ድረስ አብሰልስለው:: አንድ ክፍል ውስጥም ለብቻህ ግባና ጮክ ብለህ በእንቅስቃሴ አጅበህ ሃይል ሰጥተህና ህይወት ዘርተህ ተናገረው:: የካንተርበሪ ነዋሪ የሆነው ካነን ኮክስ ሊትል እንዳለው አንድ የኃይማኖት ሠባኪ በትምህርቱ ማስተላለፍ የሚፈልገውን መልዕክት ከግማሽ ደርዘን በላይ ለሆነ ጊዜ ደጋግሞ እየተናገረ እስኪያስተምር ድረስ በብቃት ሊያስተላልፍ አይችልም:: ታዲያ አንተስ የንግግር ልምምድህን ይህን ያህል ጊዜ ሣትለማመድ በበቂ ሁኔታ መልዕክትህን የማስተላለፍ ብቃት ይኖረኛል ብለህ ተስፋ ታደርጋለህ? በልምምድህ ጊዜ ብዙ አድማጭ ከፊት ለፊትህ እንደተቀመጠ አድርገህ ተለማመድ፤ ይህንንም በደንብ በአዕምሮህ ቀርፀህና አፅንኦት ሰጥተህ ከተለማመድክ በኋላ የእውነት

ተመልካች ፊት ንግግርህን ይዘህ ስትቀርብ ልክ ከበፊት ጀምሮ ልምድ እንዳለው ሰው ይሆማኃል።

## ገዘፊዎቹ ሲንከንን በጣም ‹‹ሲበዛ ሰነፍ›› በማለት ለምን ሲተቹትና ሲገምቱት ቻሉ?

ይህን ከላይ የገለፅኩትን መንገድ በመከተል ልምምድህን የምታደርግ ከሆነ የብዙ ዝነኛ ሰዎችን ተሞክሮ በታማኝነት ተከተልክ ማለት ነው። ሲዮድ ጆርጅ ዊልስ በሚገኘው መኖሪያ ሰፈሩ ክርክር የሚያቀርቡ ሠዎች ያሉበት ማህበር አባል በነበረበት ጊዜ በጫካ ውስጥ እየዞረ ለአጥሩ ቋሚዎችና ለእፅዋቶቹ እንደሚናገር ሁሉ ያዋራቸው ነበር።

ሊንከን በጣም ወጣት እያለ ብርክኒጅን የመሣሠሉ ታዋቂ ተናጋሪዎች ለማዳመጥ ሲል ከ30-40 ማይሎችን በእግሩ እየተጓዘ አገር አቋርጦ ይሄድ ነበር። ከእንደዚህ አይነት ንግግሮች ሲመለስ በጣም በመነሣሣቱ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ቁርጠኛ ውሣኔ ላይ ለመድረስ ቻለና ከእሱ ጋር በጊዜው አብረው በእርሻ ላይ የሚሰሩ ሰዎችን እየሰበሰበ አንድ ጉቶ ላይ በመቆም የተለያዩ ተረቶችን እያወራላቸው ንግግሮቹን ይለማመድ ነበር። በዚህን ጊዜ ታዲያ አሠሪዎቹ በጣም ከመናደዳቸው የተነሣ ይህ የባላገር ተራኪ በጣም «ሲበዛ ሰነፍ» ከመሆኑም በላይ ሌሎች ሠራተኞች እንኳን ስራቸውን በትክክል እንዳያከናውኑ ተረቶችን እየነገራቸው ያስንፋቸዋል ብለው ገምተው ነበር። አስኩዊታ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቋሙን የከፈተው እስከ ፍርድ ቤት ድረስ ክርክር በሚያደርጉ ማህበራት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ነበር።

ዊድሮው ዊልሰንም ንግግር ማድረግን በሚገባ የተለማመደው በዚህ ክርክር በሚያደርገው ማህበር ውስጥ ታቅፎ ነው። ታላቁ በረክ አንቶኒዬ ብላክዌልና ሉሲ ስቶንም የማህበራቱ አባል ነበሩ። ኢሉ ሩት ደግሞ በኒው ዮርክ 23ኛው ጐዳና በሚገኘው ወ.ወ.ክ.ማ ውስጥ ለሚገኙ አባላት ንግግር በማድረግ ችሎታውን ሊያዳብር ችሏል።

የእነዚህን ዝነኛ ተናጋሪ ሠዎች የህይወት ታሪክ ስታጠና ሁሉንም ሊወክል የሚችል አንድ እውነታ ታገኛለህ። ይኸውም ሁሉም ንግግር ለመማር ለዚህ ብዙ ሰዓት አይኖረኝም ካላችሁ ዮሴፍ ቻውት ያደርግ የነበረውን ነገር አድርጉ። ይኸውም በጠዋት ጋዜጣ ይገዛና ሌሎች ተሳፋሪዎች እንዳይረብሹት የሚያነብ መስሎ አንገቱን ይቀብራል። ነገር ግን በጋዜጣው ላይ የወጣውን የዕለቱን የቅሌት፣ የሃሜት . . . የመሳሰሉትን ዜናዎች ከማንበብ ይልቅ ለንግግር እቅድ የሚያወጣበትን ፅሑፍ እያነበበ ነበር ጉዞ የሚያደርገው። ቻውንሲ ኤም .ዲፒ ደግሞ የባቡር አገለግሎት ሰጪ ማህበር ፕሬዝዳንት እንዲሁም የአሜሪካ ምክር ቤት ሴናተር በመሆን ንቁ ተሣትፎ ያደረገ ሰው ነበር። ይህም ሆኖ ግን በየዕለቱ ምሽት ላይ ንግግር ማድረግ ይጠበቅበት ነበርና «ከስራዬ ጋር እንዲጋጭብኝ አላደርግም ነበር ሁሉንም ንግግሮቼን የማዘጋጀው ከሰዓት በኋላ ከስራ ወደ ቤት

ተመልሼ በሚኖረኝ ሰዓት ነው» ይላል፡፡ ሁላችንም በቀን ውስጥ በርከት ያሉና የፈለግነውን ነገሮች የምንሰራባቸው ሰዓቶች አሉን፡፡

ዳርዊንም ጤናው በተዛባበት ጊዜ ዝነኛ ያደረጉትና ለሥራ ያዋላቸው እነዚህን ሠዓታቶች ነበር፡፡ ከ24 ሠዓቶች ውስጥም ይጠቀምና ይሠራባቸው የነበሩት ሦስት ሠዓቶችን ብቻ ነበር፡፡ ቴዎዶር ሩዝቬልት ኃይት ሐውስ እያለ ከቀትር በፊት ያሉትን ሠዓቶች በሙሉ በየአምስት ደቂቃ ለሚደረጉ ተከታታይ ቃለመጠይቆች አውሎት ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ግን በየመሃከሉ በሚኖሩ ሽርፍራፊ ሰከንዶች ለማንበብ ሲል መፅሐፍ ከእጁ አይለየውም፡፡

በጣም ሥራ የሚበዛብህና ጊዜ የሚያጥርህ ከሆነ አርኖልድ ቤኔት የፃፈውን በቀን ውስጥ ያሉንን 24 ሠዓቶች እንዴት እንጠቀም የሚለውን መፅሐፍ አንብብ፡፡ ልታነበው የፈለካቸውን ገጾች አውጥተህ በኪስህ በመያዝ በሥራህ መሃከል በሚኖሩህ እረፍቶች ማንበብ ትችላለህ፡፡ እኔ በዚህ መንገድ በሁለት ቀናት ውስጥ አንድ መጽሐፍ እጨርስ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ከተለመደ ሥራችን ውጭ አንድ ለየት ያለ ነገር ዘና ለማለትና ለመደሰት ብለን እንደምንሠራ ሁሉ እንዲሁም የንግግር ልምምዶችን ማካሄድ ያለብን በዚህ መንገድ መሆን ይኖርበታል፡፡ አንዱ ዘዴ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር እቤት ቁጭ ብላችሁ ለጨዋታ ያህል በንግግር እያደረጋችሁ ማትጨነቁ ጊዜያችሁን መጠቀም ነው፡፡

# ክፍል አራት

## የማስታወስ ችሎታህን ማዳበር

ታዋቂው የስነ ልቦና ባለሙያ ካረል ሲሾርበር ሲናገር አማካይ ዕድሜ ካላቸው ወንዶች ግማሽ በግማሽ የሚሆኑት በተፈጥሮ ከሚያገኙት የማስታወስ ችሎታ ውስጥ ከ10% በላይ መጠቀም አልቻሉም:: ቀሪውን 90% ደግሞ ለማስታወስ ችሎታ የሚጠቀመውን ተፈጥሯዊ ህጎች ለመጣስ ያውሉታል::

አንተስ? ከእነዚህ ሠዎች ምድብ ውስጥ አለህበት እንዴ? ካለህበት በማህበራዊ እንዲሁም በሥራ ህይወትህ ከፍተኛ በሆነ የአካልና ስነልቦናዊ ጉዳት የምትሰቃይ በመሆኑ ይህን ምዕራፍ ማንበብህ አፎይታና እርካታ ይሠጥሃል:: በዚህ ክፍል ሌላ ለማስታወስ ችሎታ የሚረዳ የተፈጥሮ ሕግጋትና እነሱንም በማህበራዊና በሥራ ህይወትህ እንዴት መጠቀም እንደምትችል የሚያሳይ፣ በተጨማሪም ለንግግር ብቃትህ መዳበር የሚረዱ የተብራሩ ሃሣቦች ታገኛለህ:: «ማስታወስ የሚያስችሉ የተፈጥሮ ሕግጋት» ተብለው የሚጠሩት ብዛታቸው ሦስት ሲሆኑ እነርሱም መቅረፅ፣ መደጋገምና ማያያዝ ናቸው:: አጠቃላይ የሆነው «የማስታወስ ዘዴ» የተገነባው በእነሱ ዙሪያ ነው::

ለማስታወስ የሚረዳው የመጀመሪያ ተግባር ጥልቅ በሆነ እና በተብራራ መንገድ ለማስታወስ የፈለከውን ነገር በአዕምሮህ ቀርፀህ ለማስቀረት ጥረት ማድረግ ነው:: እዚህ ላይ ትኩረት ማድረግ ለውጤቱ በጣም አስፈላጊ ነው:: ቴዎደር ሩዝቬልት የተባለው ነገሮችን የማስታወስ ችሎታ ያገኘውን ሰው ሁሉ በጣም ያስደንቅ ነበር:: ይህ አስገራሚ ችሎታ የተገኘው ግን በቀልድና በቀላሉ አይደለም:: ይህም አንድን ነገር በአዕምሮው ቀርጾ የሚያስቀርበት መንገድ በውሃ ላይ እንደሰፈረ ፅሑፍ ሣይሆን ልክ በብረት ላይ ተፈቅፍቆ እንደተሣለ ምስል ነው:: ለዚህም ያልተቋረጠ ልምምድ በማድረጉና እራሱን በማስተማሩ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ እንኳን ትኩረት ሰጥቶ ለማዳመጥ ይችል ነበር::

የ1912ቱ የቡል ሙስ ጉባዔ ሲዘጋጅ ዋና ጽ/ቤቱን ያደረገው በኮንግረስ ሆቴል ውስጥ ነበር:: እታች ከሆቴሉ ስር በርከት ያሉ ሠዎች መፈክሮችን በመያዝ እያውለበለቡ «ቴዲን ነው የምንፈልገው! ቴዲ ይምጣልን» እያሉ በታላቅ ደምፅ ይጮሃሉ፣ አደባባዩ በጡሩንባ እየተናጋ ነው፣ የሙዚቃ ቡድኑም የህብረት ማርሽ ያሰማል፣ ብዙ የስብሰባ ተሣታፊ ፖለቲከኞች ደግሞ በኮሪደሩ ላይ ወዲያ ወዲህ ይመላለሣሉ፣ አጫጭር ቃለ መጠይቆችና መግለጫዎች ይሰጣሉ፣ ይከራከራሉ:: እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሌላ ተራ ሠውን ሊረብሹ ይችላሉ:: ነገር ግን በዚህ ሠዓት ትልቅ ወንበሩ ላይ በመቀመጥ የቢሮውን በር መለስ አድርጎ፣ ከውጭ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ቁብ ሣይሰጥ በታላቁ የግሪክ ደራሲ የተፃፈውን «ሄሮደተስ» የሚባለውን መፅሐፍ በትኩረት የሚያነበው ሠው ቴዎደር ሩዝቬልትን ብቻ አልረበሹትም ነበር:: በብራዚል ደኖች ውስጥ የሽርሽር ጉዞ ባደረገ ጊዜም አመሻሽ ላይ የሚያርፉበት ቦታ አዘጋጅተው ድንኳናቸውን እንደጣሉ እሱ አንድ በርጩማ በመያዝ ትልቅ ዋርካ ስር ባለች ደረቅ ቦታ አረፍ

ብሎ የጊቦንስን « የሮማ ኢምፓየር አነሣስና አወዳደቅ » የተሰኘ መፅሐፍ ማንበብ ጀመረ:: በጣም የሚገርመው ነገር በተመስጦ ንባቡ ላይ ከማተኮሩ የተነሣ የዝናቡ ማካፋት ፣ በካምፑ ዙሪያ ኳኳታና ጫጫታ ፣ በትሮፒካል ጫካው በሚፈጥረው ድምጽ ምንም ችግር አላስከተለበትም ነበር::

ትኩረታችንን ሰጥተን ለአምስት ደቂቃ ጥራት ባለው መልኩ ማንበብ ቀኑን ሙሉ ጭጋግ ውስጥ ባለና ባልተረጋጋ አዕምሮ ከማንበብ የተሻለ ውጤት ያስገኛል:: ሄነሪ ዋርድ ቤከር እንደጠቀሰው «አንዲት የጋለ ስሜት የምትፈጥርብን ሰዓት ከአመታት የቅገርት ጊዜያቶች የበለጠ ልታገለግለን ትችላለች»

የቤተልሄም ብረታ ብረት ማምረቻ ፕሬዝዳንት በመሆን በወር ከሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የሚያገኘው ኢግዊን ግሬስ «በህይወት ተሞክሮዬ እጅግ አስፈላጊ የሆነውና በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ሆኜ የምለማመደው ነገር በእጄ ለያዝኩት ማንኛውም አይነት ሥራ ትኩረት መስጠትን ነው» ብሏል:: ይህ የሃይላችን ምንጭ ሚስጥር ነው:: በተለይ ደግሞ የማስታወስ ሃይል:: ቶማስ ኤዲሰን ሃያ ስድስት የሚጠጉ ረዳቶቹ ለስድስት ወራት ያህል ተመሳሳይ በሆነው ጉዳና ብቻ እየተጠቀሙ ከአምፖል ማምረቻው በመነሣት ኒውጀርሲ ከሚገኘውና ማናሎፓርክ ከተባለው የሥራ ማዕከላቸው እንደሚመላለሱ ታዝቧል:: ታዲያ የሚገርመው ከእነኚህ 26 ሠዎች መካከል አንዱም እንኳን በመንገዱ ዳር ላይ የተተከለውን የቼሪ ዛፍ ልብ ብለው ሊያስተውሉት ይቅርና ይኖራል ብለው ገምተው እንደማያውቁ ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ችሏል::

በዚህም የተነሣ ሚስተር ኤዲሰን የደረሰበት ድምዳሜ «የአንድ አማካይ ዕድሜ ያለው ሰው አዕምሮ አይኑ ሊያየው የሚችላቸውን ከአንድ ሺህ በላይ ነገሮችን ሊያስተውልና ሊቀርፅ አለመቻሉን ነው ብሏል:: ይህም የአይናችንን የመመልከት ብቃት በማይታመን መልኩ እጅግ ደካማ መሆኑን ያሣያል ወይም ጥልቅ በሆነ ሁኔታ የማስታወስ ሃይል ይጎድለናል ማለት ነው፣

አማካይ ዕድሜ ያለውን ሠው ለሦስት ሠዎች አስተዋውቀው:: ከዚያ ወዲያውኑ ከሁለትና ሦስት ደቂቃዎች በኋላ መልሰህ ብትጠይቀው እንኳን የሦስቱን ይቅርና የአንዱን ሠው ስም እንኳን ለማስታወስ ያለው ዕድል አናሣ ነው፣ይህ ከምን የመጣ ይመስላችኋል? በመጀመሪያ ደረጃ በቂ ትኩረት አለመስጠቱና በትክክለኛ ሁኔታ ለማስታወስ ፍፁም ሙከራ አለማድረጉ ነው::

እሱ ምናልባት ደካማ የሆነ የማስታወስ ችሎታ እንዳለው ሊናገር ይችላል:: ይህ ግን ልክ አይደለም:: የሱ ችግር ደካማ የሆነ የማስተዋል ችሎታ ነው:: አንድ ሰው የፎቶ ግራፍ ማንሻ ካሜራውን በጭጋግና በደብዛዛ ብርሃን ውስጥ ጥራት ያለው የፎቶ ምስል ባለማንሣቱ ሊያማርረው አይችልም:: ነገር ግን አዕምሮውን በፈዘዘና ጭጋግ ባጠላበት መልኩ ያስተዋላቸውን ነገሮች ቀርጾ እንዲያስቀርለት ይፈልጋል:: ይህ በእርግጥም የማይቻል ነገር ነው:: ዮሴፍ ፑልትዘር የተባለው የኒው ዮርክ ወርልድ መፅሔት መስራች በእያንዳንዱ አርቲክል ሦስት ቃላትን ዕፎ እቢሮው ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጥላቸው ነበር:-

ትክክልነት

ትክክልነት

ትክክልነት

እኛም የምንፈልገው ይኸን ነው:: አንድ ሠው ስሙን ሲያስተዋውቅህ በተክክል አድምጠው፣ አብሰልስለው፣ እንዲደግምልህ ንገረው፣ የስሙን ፊደል እንዴት እንደሚፃፍ ጠይቅ:: በዚህ ጊዜ ታዲያ ግለሰቡ የሱን ስም ለማወቅ ባሣየኸው ፍላጎት ይደመማል:: አንተም ነገሩን አጥብቀህና ትኩረት ሰጥተህ በማሰብህ ለማስታወስ አትቸገርም:: እናም በማያሻማና ትክክል በሆነ ሁኔታ ለመቅረፅ ያስችልሃል::

## ሲንከን ጮክ ብሎ የሚያነበው ለምንድን ነው?

ሲንከን በልጅነቱ የተማረበት የገጠር ት/ቤት ወለሉ ከፍልጥ እንጨት የተሠራ፣ መስኮቱ በቅባት በታሹ የመፅሐፍ ገጾች የታሸጉና በመስታወት ምትክ ብርሃን እንዲያስተላልፉ ተደርገው የተሰሩ ነበሩ:: የሚማሩበት መፅሐፍ ደግሞ አንድ ብቻ በመሆኑ አስተማሪያቸው ጮክ እያለ በማንበብ ሁሉም እንዲያዳምጡ ከእርሱ ቀጥለው እንዲደግሙት በማድረግ ያስተምራቸው ነበር:: በዚህ ጊዜ ታዲያ ሁሉም ተማሪዎች አንድ ላይ ሲጮኹ የማያቋርጥና ድብልቅልቅ ያለ ሁካታ ስለሚፈጠር በአጉራባች የሚኖሩ ሰዎች «የልፍለፋው ት/ቤት» ብለው ይጠሩት ነበር::

ከዚህ «የልፍለፋ ት/ቤት» ነበር ሲንከን ህይወቱን በሙሉ እንደመመሪያ አድርጐ የያዘውን ይህን ልማድ ሲያዘወትረው የቻለው:: ከዚህ ጊዜ በኋላም ማናቸውንም ማስታወስ የሚፈልገውን ነገር ሲያገኝ ጮክ ብሎ እያነበበ ያጠናዋል:: ሁልጊዜም ጠዋት ጠዋት ስፕሪንግፊተን በሚገኘው የጥብቅና ቢሮው እንደደረሰ ትልቅ ወንበሩ ላይ ሆኖ ረጃጅም እግሮቹን ወደፊት ዘርግቶ በመቀመጥ የዕለቱን ጋዜጠኛ ሠው ሊሠማው በሚችል ሁኔታ እየጮኸ ማንበብ ይጀምራል::

አንድ የሥራ ባልደረባው ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር «በጣም ያበሳጨኝ ነበር:: እንደውም አንድ ጊዜ ከቁጥጥር ውጭ ሆኜ ለምን እንደዚህ እንደሚያነብ ጠይቄው ነበር» የእሱ መልስ ታዲያ « ጮክ ብዬ በማነብ ጊዜ ሁለት የስሜት ህዋሣቶቼ አንዱን ሃሳብ በጋራ ይይዙታል:: የመጀመሪያው የማነበውን እንድመለከተው ሲያደርግልኝ ሁለተኛው ደግሞ እንዳዳምጠው ያደርግልኛል:: ስለዚህም በተሻለ ሁኔታ እንዳስታውሰው ይረዳኛል::» የማስታወስ ብቃቱ እጅግ በጣም በሚገርም መልኩ ቀርጸ መያዝ ያስችለው ነበር «አዕምሮዬ ልክ እንደ ብረት ቁራጭ እላዩ ላይ ለመቅረፅና ለመፃፍ አስቸጋሪ ሲሆን አንዴ ከተቀረፀበት በኋላ ደግሞ ለማስለቀቅ እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል::»

እሱ ሁለቱን የስሜት ህዋሣቶቹን እየተጠቀመ በአዕምሮው ላይ ይቀርፅና ይመዘግብ ነበር፤ እናንተስ ታዲያ እንደዛው ... እዚህ ጋር ዋናው መሠረታዊ ነጥብ ማስታወስ የምንፈልገውን ነገር ማየትና መስማት ብቻ ሣይሆን መዳሰስ፣ ማሽተትና መቅመስ መቻላችንን ማረጋገጥ ነው::

የኛ አዕምሮ ነገሮችን የማስመሠል ችሎታ አለው:: የዐይናችንም የማስተዋል ችሎታ የዳበረ ነው:: ብዙ ጊዜ እንደውም የአንድን ሠው ስም ብንረሣ እንኳን መልኩ ግን አዲስ ሲሆንብን አይታይም:: ከአይናችን ወደ አዕምሮአችን መልዕክት የሚያስተላልፉ ነርቮች ከጆሮአችን ወደ አዕምሮ መልዕክት ከሚያስተላልፉት ነርቮች (25) እጥፍ በላይ የዳበሩና የበለጠ ናቸው:: ቻይናዎች አንድ አባባል አላቸው « አንድ ጊዜ ማየት ከአንድ ሺህ ጊዜ በላይ ከመስማት የበለጠ ዋጋ አለው::»

ስሞችን፣ የስልክ ቁጥሮችንና ለማስታወስ የምትፈልገውን የንግግር ረቂቅህን ፅፈህ አስቀምጣቸው፣ ተመልከታቸው:: ዐይንህንም በመጨፈን ልክ እንደሚንቀሳቀል የእሣት ነበልባል አድርገህ ፊደሎቹን በአዕምሮህ ሳላቸው::

## ማርክ ትዌይን ማስታወሻ ሣይዝ ንግግር ለማድረግ እንዴት ቻለ?

ማርክ ትዌይን የማየት ችሎታውን በመጠቀም እንዴት ለማስታወስ እንደሚቻል በመረዳቱ እነዚህ ለዓመታት የንግግር ችሎታውን ሲጨቁኑበት የነበሩትን ማስታወሻዎቹን ሊያስወግዳቸው በቅቷልና ለሃርፐር መፅሔት የተናገረው ታሪክ ይኸውላችሁ::

ቀናቶችን ለማስታወስ አስቸጋሪ የሚሆኑት የቁጥር አሃዞችን ብቻ በመያዛቸው ነው:: እነኚህ የቁጥር አሃዞች አሰልቺ በሆነ ሁኔታ ገፅታቸው ሲስብ የማይችል፣ ለማዛመድ አስቸጋሪ የሆኑና ስዕላዊ የሆነ መግለጫ የሌላቸው ናቸው:: ስለዚህም ዐይናችንን ለመሣብ የሚበቃ እይታን አይሰጡትም:: ስዕሎች ግን እነዚህን ቀናት እንድናስታውሣቸው ያስችሉናል:: ማናቸውንም ነገር ቀርፀን ለመያዝ እንደ ምስሎችን የሚስተካከል ነገር ከቶ አይገኝም:: ቀናትን እንድናስታውሣቸው ያስችሉናል:: በተለይ ምስሎቹ የተሣሉት በራሳችን ከሆነ በበለጠ ይታወሣሉ:: ይህን ነገር ልደርስበትና ልረዳ የቻልኩት ከብዙ ልምድ በመነሣት ነው::

ከሠላሣ ዓመታት በፊት ሁል ጊዜ ማታ ማታ አንድ ርዕስን በቃሉ በመያዝ ለተማሪዎች ገለፃ አድርግ ነበር:: ታዲያ የሃሣብ መደበላለቅና መዘለል እንዳይመጣ በማለት አንድ ገፅ ማስታወሻ ይገፍ እገባ ነበር::

ይህም የአሥራ አንድ ዓረፍተ ነገሮችን የመጀመሪያ መግቢያ ቃላትን በአንድ ገፅ ላይ በአጭር ሠፍረው ያሉበት ነበር:: ከእነሱ መካከልም፣

የክልሉ አየር ፀባይ ....................

ብዙ ጊዜ አንድ ባህል የሆነው ነገር ....................

አንድም በካሊፎርኒያ ነዋሪ የሆነ ሰው ............

እነዚህ አስራ አንዱ የትምህርት ርዕስ መግቢያ የሆኑትን ሃሣብ በአጭሩ የያዙ ስለሆነ የመጀመሪያውን ሣልጨርስ ወደሚቀጥለው እንዳላልፍ ያደርጉኝ ነበር:: ነገር ግን ምን ለማለት እንደሚፈልጉ በልቤ ባውቃቸውም ተራቸውን በጠበቀ መልኩ ለመሄድ አይመቹም ነበር::

ስለዚህም ሁልጊዜ ማስታወሻዬን ከጐኔ አድርጌ እየተመለከትኩኝ መመራት ነበረብኝ:: አንድ ጊዜ ታዲያ አንዱን ርዕስ በልዩ በድንገት ወደ ሌላ አዲስ ሃሣብ ገባሁኝ:: ምን አይነት አሳፋሪ ምሽት እንደገጠመኝ ገመትኩ:: በዚህ ጊዜ ታዲያ አንድ መላ ማበጀት እንዳለብኝ ተረዳሁና የአስራ አንዱንም አረፍተ ነገሮች የመጀመሪያ ፊደላት ተራቸውን ጠብቄ ከላይ ወደታች መሸምደድ ጀመርኩ:: ለምሣሌ ከላይ ከጠቀስኳቸው ሰስት ዓረፍተ ነገሮች የ፣ ብ፣ አ...... እና የመሣሠሉት እያልኩ አስሩን የመጀመሪያ ፊደላት በአስሩ የእጆቼ ጣቶች በእስክርቢቶ ፃፍኳቸውና ወደማስተምርበት ክፍል ገባሁ:: ነገር ግን ሊሆን አልቻለም:: የትኛው ጣቴ ላይ እንደደረስኩ ሁሉ ተምታታብኝ:: መቼም አንዱ ጣቴ ላይ ያለውን ምልክት ተጠቅሜበት ግዜ በምላሴ ልሼ ማጥፋት አልችልም:: ይህ በእርግጥ ችግሩን ቢያቃልለውም በአድማጭ ፊት የተለየ ግርምት መፍጠሩ አይቀርም:: ቀደም ብዬም በቂ የሆነ መረበሽን ስላሳለፍኩ ተጨማሪ ችግርና ረብሻ አልፈለኩም:: በመጨረሻ ግን ይህ ዘዴ ከማስተምረው ትምህርት ይልቅ የእጄን ጣቶች ማየት በማብዛቴ ትኩረቴን ያልሰጧቸው አይነት ስሜትን በአድማጭ ዘንድ አስከተለብኝ:: እንዲውም አንድ ሁለቴ ጣቴን ምን እንደሆንኩኝ ጠይቀውኝ ነበር::

ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው ስዕሎችን የመጠቀሙ ሃሣብ ሸው ያለብኝ:: በሁለት ደቂቃ ውስጥም ስድስት ስዕሎችን ሣልኩኝና አስራ አንዱንም የንግግሬን ዓረፍተ ነገሮች እንዲወክሉ በማድረግ ችግሬን ለመቅረፍ በቃሁ::

እነዚህን ስዕሎች ታዲያ ዐይኔን ጨፍኜ እንኳን እንደማልረሣቸው ሳውቅ ጣልኳቸው:: ይህ ከሆነ ሩብ ምዕተ አመት በፊት መሆኑና የትምህርቱን ይዘት ከዛሬ ሃያ ዓመታት በፊት ብዘነጋውም ይህ ስዕል ዛሬም በጭንቅላቴ ተቀርጾ ስለሚገኝ አስታውሼ ጽሑፉን መፃፍ እችላለሁ::

አንድ በማስታወስ ችሎታ ላይ ያተኮረ ንግግር ለማድረግ አስቢያለሁ እንበል:: ታዲያም ከዚህ መፅሐፍ ያገኘኋቸውን መረጃዎች በመጠቀም ለንግግሬ ዝግጅት ለማድረግ ፈለግኩኝ:: ነጥቦቹን በስዕል በመወከል ለማስታወስ እንዲረዳኝ ሩዝቬልት ያ ሁሉ ሰው እየጮኸበትና የሙዚቃ ባንድ እያንባረቀበት መፅሐፉን በተመስጦ ሲያነብ፣ ቶማስ ኤዲሰን የቼሪውን ዛፍ እየተመለከተ፣ ሊንከን ጮክ እያለ ጋዜጣ ሲያነብ ማርክ ትዌይን ደግሞ የጣቶቹን ቀለም ለማስለቀቅ ሲልሳቸው እያሰብኩ ለመቅረፅና ለማስታወስ ሞከርኩ::

ታዲያ እንዴት አድርጌ የዚህን ምስል ቅደም ተከተል ጠብቆ ማስታወስ እችላለሁ? አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት በማለት? እንደዚህ አይቻልም፣ ከዚያ ይልቅ እነዚያን ቁጥሮች ወደ ስዕል እቀይራቸዋለሁ::: እነዚህን ስዕሎች ሃሣብን ከያዙ ነጥቦች ጋር አቀናጃቸዋለሁ:: ለምሣሌ አንድ ቁጥር የውድድር ፈረስ ቢሆን የሳልኩት ሩዝቬልትን ክፍሉ ቁጭ ብሎ የፈረስ ውድድር ማስታወቂያ ሲያነብ እስበዋለሁ:: ለሁለት ቁጥር ደግሞ (በእግሊዝኛው ቱ የሚለውን ዙ በሚለው በመተካት) ስለዚህ የእንስሣት ዙ ውስጥ ቶማስ ኤድሰን የቼረው ዛፍ አጠገብ ቆሞ እንስሳቱን ሲመለከት አድርገዋለሁ:: ለሦስት ቁጥር ደግሞ (ትሪ የሚለውን ሊንከን የዛፍ ጫፍ ላይ ወጥቶ ጮክ ብሎ ወስጄ ዉደ (ዛፍ) ቆሞ (በመለወጥ)

ሲያነብ እስለዋለሁ፡፡ ለአራት ቁጥር (ፎር የሚለውን የእንግሊዝኛ ቁጥር ወደ ዶር (በር)) በማስጠጋት ማርክ ትዌይን ወደተከፈተ በር ይጠጋና ወደቅስቱ አንገቱን ስገግ በማድረግ ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ የጣቱን ቀለም ለማስለቀቅ ሲልሳቸው እስልዋለሁ፡፡

ብዙ ሠዎች ይህን ሲያነቡ በጣም የሚያስገርምና አስቂኝ የሆነ ዘዴ ነው ብለው ሲያስቡ ይችላሉ፡፡ በእርግጥም ነው፡፡ ስለዚህም ነው መጀመሪያ አስቸጋሪ በመሆኑ ለማስታወስ ቀላል የሚሆነው፡፡ በቁጥር ደርድሬ ከመፃፍና ከማስታወስ ይልቅ በዚህኛው ዘዴ ሦስት ቁጥር ምን እንደሆነ ለማስታወስ ስፈልግ (ትሬ-ዛፍ) ዛፍ ላይ ምን እንዳለ ስጠይቅ ሲንከንን ማየት እችላለሁ፡፡

## ከአዲስ ኪዳን በይዘቱ ትልቅ የሆነን መጽሐፍ በቃል ማስታወስ

በዓለም ላይ ከሚገኙት ታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ የካይሮው አል አዝር ዩንቨርስቲ ነው፡፡ በዚህ ማዕከል ከ21 ሺህ በላይ የሆኑ የመሃመድ ተከታዮች ይማሩበታል፡፡ የዚህ ት/ቤት የመግቢያ ፈተና ቅዱስ ቁራኑን በቃላቸው እንዲቀሩት ያስገድዳቸዋል፡፡ ይህ በይዘቱ ከአዲስ ኪዳን የበለጠ በመሆኑ በቃል ለመጨረስ ከሦስት ቀን በላይ ይፈጃል፡፡

የቻይና ተማሪዎች ወይም «የጥናት ልጆች» ተብለው የሚጠሩት ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ የሃይማኖትና ታሪካዊ ይዘት ያላቸውን መዕሐፎች በቃላቸው ማስታወስ ግድ ይላቸዋል፡፡

እነዚህ የዓረብና የቻይና ተማሪዎች እነዚህን እጅግ ብዙ የሆኑ ጽሑፎች እንዴት በቃላቸው ሊያስታወሱ ይችላሉ? መልሱ «ደጋግሞ እያነበነቡ ማጥናት፡፡ እንዲሁም የተፈጥሮ ማስተወስ ሕግን በመጠቀም እጅግ ብዙ የሆኑና ማለቂያ የሌላቸውን መረጃዎችና ፅሑፎች ደግመን ደጋግመን በማንበብ መሸምደድ ስንችል ነው፡፡» አንድ ለማስታወስ የፈለጋችሁት ነገር ካለ ይህን ዘዴ መጠቀም የሰው ወይም የጓደኛ ስም አድርጉ መያዝና ከጓደኞቻችሁ ጋር ስትጫዋወቱ እንደ መወያያ አጀንዳ በማድረግ ደጋግሞ መጠቀሙ ምንጊዜም ከአፋችን እንዳይጠፉ ያደርገዋል፡፡

## በጣም ጠቃሚው የመደጋገሚያ ዘዴ

አንድን ፅሑፍ በደፈናው፣ በግልቢያና በፍጥነት እየደጋገሙ ማንበብ ምንም ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ከአዕምሮአችን ባህሪ ጋር ተዛምዶ ባለው መልኩ ትልቅ ትኩረት በመስጠት ማንበብ እንደገና በመድገም ማንበብና ማቀናጀት ያስፈልጋል፡፡ ለምሣሌ ፕሮፌሰር ኢባንጋዝ ለተማሪዎቹ ምንም ጣዕምና ትርጉም የሌላቸውን አስቸጋሪ የሆኑ ቃላትን እንዲያስታውሱ ሰጥቷቸው ነበር፡፡ ተማሪዎቹም በሦስት ቀናት ውስጥ በየመሃሉ እረፍት እያደረጉ ለ38 ጊዜያት ከደጋገሟቸውና ካነበቧቸው በኋላ በቃል ሲይዟቸው ችለዋል፡፡

እነዚህን ቃላት ግን ያለምንም እረፍት ለ68 ጊዜያት እየደጋገሙ በማንበብ ማጥናት ያስፈልግ ነበር፡፡ ይህ ውጤት በሌሎች የስነ ልቡና ጠበበቶችም

የተረጋገጠና በአዕምሮ የማስታወስ ብቃት ላይ በተደረገ ለየት ያለ ጥናት የተገኘ ነው። ይህም ማለት አንድን ነገር እየደጋገሙ በማንበብ ያልተቋረጠና እረፍት በሌለው ጥናት በቃል ለመያዙ የሚወስድብን ሃይልና ጊዜ በየመሃሉ እረፍት እየወሰዱ በድግግሞሽ በማንበብ ተመሣሣዩን ውጤት ለማግኘት ከሚወስድብን ሃይልና ጊዜ በግማሽ ያህል ያነሰ መሆኑን ያሳያል። ይህን የአእምሮአችን ባህሪ ብለን ብንጠራው ሁለት ነገሮች ለዚህ ውጤት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

የመጀመሪያው ዘዴ እየደጋገምን ስናጠና በሚኖሩን እረፍቶች ድብቁ የአዕምሮአችን ክፍል እነዚያን አዲስ ሃሳቦች ከእራሴ ጋር ለማዋሃድ በሥራ ተወጥሮ ነበር። ልክ ፕሮፌሰር ጀምስ እንዳሉት «በክረምት በበረዶአማ ወቅት ዋና መለማመድ በበጋ ደረቅ ወቅት ደግሞ የበረዶ ሸርተቴ ልምምድ ማድረግ ማለት ነው»

በሁለተኛው ምክንያት እረፍት እየወሰድን ስንለማመድ በተከታታይ ሁኔታ ከሚሰጡ ልምምዶች የተነሣ ከሚመጡት ከባድ ድካምና ውጥረት ነፃ በመሆን አዕምሯችንን ለቀጣይ ልምምድ ዝግጁ ስለሚያደርግ ነው።

ሰር ሪቻርድ በርተን የተባለው «የአረቢያን ናይት» መፅሐፍ ተርጓሚ ሃያ ሰባት ቋንቋዎችን እንደተወላጅ አቀላጥፎ ቢናገርም ሁሉንም ቋንቋዎች ሲያጠና ግን ከሚጠቀመው ጊዜ ከአንድ ሠዓት ውስጥ አስራ አምስት ደቂቃዎችን ብቻ ነው። ከዚህ በላይ ለመግፋት ሲሞክር ግን አዕምሮው ብሩህነቱን እንደሚያጣ ገልጿል። እነዚህን እውነታዎች ከግምት በማስገባት አንድ ለንግግር ዝግጅት የሚያደርግ ሰው እስከሚያቀርብበት ቀን ድረስ ለማዘግየት በዚህ ዘዴ ይጠቀማል። አዕምሮውም ሳይደክምና ሣይዝል በግማሽ ኃይሉ ተጠቅሞ ተፈላጊ ውጤት ማምጣት ይችላል።

በስነ-ልቦና ባለሙያዎች እንደተረጋገጠው ከሆነ የተማርናቸውን አዳዲስ ነገሮች በ30 ቀናት ከእኛ ጋር እንዲቆዩ ከማድረግ ይልቅ ለ8 ሠዓታት ሣይረሱ እንዲቆዩ ማድረግ ይከብዳል። የሚገርም ልዩነት ነው አይደል?

ስለዚህም በአጭር ጊዜ ውስጥ የተዘጋጀንባቸውን ንግግሮች በጉባዔዎች በቅርብ ሰዓታት በመከለስ ማጥናት ያስፈልጋል።

ሊንከን የዚህ አይነቱን ልምምድ ጥቅሙን በመረዳቱ በተግባር አውሎት ነበር። ኤድዋርድ ኤቨርት በጌትስበርግ በሚደረገው ዝግጅት ላይ ከሊንከን በፊት ንግግር ያደርግ ነበር። ኤድዋርድ ንግግሩን እያገባደደ እንደሆነ ሊንከን ሲያውቅ ፍርሃት ወረረው። ሁልጊዜም ከሌላ ሰው ቀጥሎ ሲናገር እንዲህ አይነት ስሜት ያድርበት ነበር። ቀጥሎ ያደረገው ነገር በችኮላ እጁን ወደ ኪሱ በመስደድ ያዘጋጀውን ንግግር አውጥቶ ተራው እስኪደርስ ድረስ እየከለሰ ማጥናት ነበር።

## ፕሮፌሠር ዊሊያም ጀምስ ጥሩ የማስታወስ ችሎታን ሚስጥር ይነግረናል

እስካሁን ባየናቸው ሁለት የማስታወስ ችሎታ ህጎች ላይ የምንለውን እናቁምና ማያያዝ ወደሚባለው ሦስተኛ ሕግ እንለፍ:: ይህ ሕግ ለማስታወስ ለሚባለው ነገር ችሎታ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አለው:: እንደውም ማስታወስ ለሚባለው ነገር እንደፕሮፌሰሩ አመለካከት « አዕምሮአችን እንደመገለጫ ሁሉ ያገለግላል:: ለምሣሌ ዝም ብዬ በድንገት አስታውስ! አስብ! ነገሮችን የሚያያይዝ ማሽን ነው:: ብልህ የአንተ አዕምሮ የማስታወስ ክፍል ትዕዛዙን ብትቀበል የሆነ ምስል ያስቀምጥልሃል? ባዶ የሆነ ነገር ላይ ሲያፈጥ ይቆይና ምን አይነት ነገር ነው እንዳስታወስ የምትፈልገው ? የሚል ጥያቄ ያመጣብሃል እንጅ ምስል አያስቀምጥልህም:: ለማለት የፈለኩት ነገር በአጭሩ አንድ ፍንጭ ወይም ምልክት ይፈልጋል:: ይህም ፍንጭ በጠቅላላው በማስታወሻ ተቀማጩ ያለውን ሃሣብ ወደ አንድ ነጥብ ለማምጣት ይረዳዋል::

ይህ እንዴት እንደሚሆን ለማየት ማስታወስ የፈለግነው ነገር ከፍንጩ ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆኑን እናስተውል:: ለምሳሌ የልደት ቀኔ የሚለው ቃል በቀጥታ ወደምናውቀው ቀንና ዓመት ምህረት ሲመራን ቁርስ የሚለው ቃል ደግሞ እንቁላል፣ ዳቦ. . . የመሣሠሉትን ያስታውሠናል:: በሌላ መልኩ የሙዚቃ ስኬል የአዕምሮአችንን . . . ጉረቤት ዶ:ሬ:ሚ: ፋ: ሶ: ላ: ሲ: ዶ ያገናኙናል:: የማያያዝ ሕግ የአስተሳሰባችን ባቡር ከውጭ በሚመጡ የስሜት ውጥረቶች ሳይቆራረጥ እንዲፈስ የሚቆጣጠርና የሚመራ ነው:: ምንም አይነት አዲስ ነገር ቢገጥመው ቀድሞ ካለው ሃሳብ ጋር ያያይዘዋል::

የማስታወስ ትምህርት በተቀናጀ የማዛመድ ዘዴ ላይ የተመረከዘ ሲሆን ጥራቱን ደግሞ ሁለት ነገሮች ይወስኑታል:: አንደኛው ለማያያዝ ወይም ለማዛመድ የፈለግናቸው ነገሮች ያላቸው ትስስር የጠበቀ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ብዛታቸው ነው::

ስለዚህም የማስታወስ ሚስጥር የሚባለው ብዛት ያላቸውና የተያያዙ ሃሣቦችን መስርተን ልናስታውሣቸው ከምንፈልገው እውነታዎች ጋር እንዴት ማያያዝ እንደምንችል ማወቅ ማለት ነው::

ይህ ማለት ታዲያ እውነትን ከተያያዙ ሃሣቦች ጋር መመስረት ነው? እውነታዎቹን አቅም እስኪፈቀድ ድረስ ማሰብ ነው? በእርግጥም ነው:: ግን አሁንም ቢሆን ይህ አይነቱ ከፍተኛ ችሎታ ባላችሁ ሁለት ሠዎች መካከል ባለው ልምድ በጥልቀት በማሠብና በመመርመር እውነታዎቹን እርስ በርሳቸው እያስተሣሠረ አለታዊ በሆነ የማያያዝ መንገድ ማዋቀር የቻለ ሠው እጅግ ድንቅ የማስታወስ ችሎታ ባለቤት ይሆናል::

## ያሉህን እውነታዎች እንዴት ታያይዛቸዋለህ

በጣም ጥሩ! የሆኑ እውነታዎች አስታዊ በሆነ የማያያዝ ዘዴ እንዴት ማስተሳሰር እንችላለን? መልሱ ትርጉማቸውን እየፈለጉ ደግሞ ደጋግሞ ማሰብ ነው::

ለምሳሌ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች እራስህን እየጠየክ መልስ ለማግኘት ከጣርክ ሂደቱ አስታዊ የሆነ ማያያዝህን ከሌሎች እውነታዎች ጋር ለማስተሳሰር ይረዳሃል::

1/ ይህ ለምን ሆነ?

2/ እንዴት ሊሆን ቻለ?

3/ መቼ ነው የሆነው?

4/ የት ነው የሆነው?

5/እንዲህ ብሎ ያለው ማነው?

አዲስ ስም ሲያጋጥመን የተለመደ ስም ከሆነ ከምናውቀው የጓደኛ ወይም የዘመድ ስም ጋር እናያይዘዋለን:: ነገር ግን ያልተለመደና እንግዳ የሆነ ስም ከሆነ ይህ ጉዳይ ከሠዎቹ ጋር ጨዋታ ለመጀመር ጥሩ አጋጣሚ ይሆነናል::

ይህን ክፍል ስፅፍ አንድ ሚስስ ሱትሪ የምትባል ሴት ተዋውቄ ነበር:: ለየት ያለና እንግዳ የሆነ ስም እንዳላት ከነገርኳት በኋላ ለመያዙ እንዲመቸኝ በወረቀት ፅፋ እንድትሰጠኝ ጠየኳት:: እሷም «አዎን እንግዳ ቢሆንብህ አይገርምም:: ምክንያቱም የግሪክ ቃል በመሆኑ ነው:: ትርጉሙም አዳኞችን ማለት ነው» አለችኝ:: ቀጥላ የባሏ ቤተሰቦች በግሪክ የታወቁ ባለስልጣኖች እንደሆኑ በመንገር ብዙ ጨዋታ አጫወተችኝ:: ይህ መንገድ ሠዎችን ስለስማቸው በማወያየት በዚያውም እንዳንረሳው ያደርገናል::

ሌላው ነጥብ አዲስ ሰው ስትተዋወቁ ፊቱን በደንብ ማስተዋል የፀጉሩን ቀለም፣ የአይኑን፣ የፊቱን አቀማመጥ ገፅታ፣ አለባበሱን ፣ የንግግር ዘይቤውን፣ ስብዕናውን በተብራራ ሁኔታ በማጥናት ከስሙ ጋር ለማያያዝ እንዲሁም በአዕምሮአችሁ ለመቅረፅ ሞክሩ:: በሚቀጥለው ጊዜ ስትገናኙ እነኚህ የተቀረጹ ምስሎች ስሙን ለማስታወስ ይረዳችኋል::

አንድ ከዚህ በፊት የተዋወቅከው ሰው በድንገት ለሁለተኛ ወይም ለሦስተኛ ጊዜ ስታገኘው ስራውንና ሙያውን እያወቅከው ስሙ ግን በጭራሽ አልመጣልህ ብሎህ አያውቅም? ምክንያቱ ምን መሠለህ የአንድ ሰው ስራ ወይም ሙያ ማለት የሚታይና የሚጨበጥ ነገር ስለሆነ ነው:: ትርጉምም ይኖረዋል:: የሠውዬው ሥራ ወይም ሙያ ከእኛ ጋር ልክ እንደ ፍርድ ቤት? ፕላስተር ተጣብቆ ሲቀር ትርጉም አልባው ስም ግን የጋደለ ጣራ ላይ እንደሚዘንብ በረዶ እየተንከባለለ ይወድቃል:: ይህን ነገር ለማረጋገጥ ከፈለክ የግለሰቡን ሥራ ከስሙ ጋር ሊያያይዝልህ በሚችል አጭር ሃረግ ፈጥረህ ለማስታወስ ሞክር:: የዚህን ዘዴ ውጤታማነት ፍፁም ልትጠራጠረው አይገባም:: ምሳሌ ልስጣችሁ፡-

ወደ ሃያ የሚሆኑ እርስ በርስ የማይተዋወቁ ሰዎች ፊላደልፊያ በሚገኘው የፔን አትላንቲክ ክበብ ለስብሰባ ተገናኝተው ነበር:: ከዚያም እያንዳንዱ ግለሰብ

ተነስቶ ስሙንና ስራውን እንዲያስተዋውቅ ተደረገ:: ቀጥሎ የሁሉንም ስም ከሥራው ጋር የሚያያይዙ አጫጭር ሃረጎች ተፈበረኩ:: ከጥቂት ቆይታ በኋላ በክፍሉ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው የሌላውን ሰው ስም ያለስህተት ለማስታወስ ችሏል:: በሌላው ጊዜ ደግሞ ከብዙ ዓመት በኋላ እንደገና ለስብሰባ ሲገናኙ ስምና ሥራዎቻቸውን ከራሳቸው ጋር በጣም ከማዋሃዳቸውና ከማስታወሳቸው የተነሣ ሁሉንም አስታውሰው ለመናገር ችለዋል:: ከሃያዎቹ ሠዎች ውስጥ የተወሰኑትን ስምና ሥራ በአጭር ሃረግ ለማስታወስ እንዲመች የተደረገበት ዘዴ (መንገድ) ይኸውላችሁ::

ሚ/ር ጂ.ፒ ክራይት (የአሸዋ ንግድ) የአሸዋ ትርፍ ሁሉንም ያበራል (ብርሃን ይሰጣል)

ሚስተር ጂ ማይል ደብሊው (አስፓልት ሥራ) ቤ.ኤም ደብሊው በአስፓልት ይመቻል::

ሚስተር ኤች ኤም. ቤድል (የሱፍ ልብስ) ከሱፍ የአልጋ ልብስ ይመረታል

ሚስተር ቶማስ ዴቨር (ህትመት) ዴቨር ማሽን ለህትመት ጥሩ ነው

ሚስተር ኦ ዲየ ቢትል (መኪና ሻጭ ) ቢትል ዘመናዊ መኪና ነው

ሚስተር ቶማስ ፊሽ (ከሰል ማዕድን) ከሰል ማምረት ዓሣ ማጥመድ ነው

ሚስተር ፍራንክ ኤች ጉልድ (ጣውላ ሥራ) ከጣውላ ሥራ ወርቅ ይገኛል

ሚስተር ጂ ኤች ሃንከክ (ጋዜጣ) ሃንከክ ጉማ ለመግዛት በጋዜጣ ማሳወቅ::

## ቀናቶችን እንዴት ማስታወስ ይቻላል

ቀናቶችን በተሻለ ሁኔታ ለማስታወስ የሚረዳን ዘዴ ከዚህ ቀደም ከምናውቃቸው ወይም በአዕምሮአችን ቀርፀን ካያዝናቸው ቁጥሮች ጋር በማያያዝ ነው:: ይህ ብዙም አስቸጋሪ አይደለም:: ለምሣሌ ለአንድ አሜሪካዊ የስዊዝ ካናል የተከፈተበትን ቀን ለማስታወስ ከአሜሪካ የእርስ በርስ ጦርነት ከተደረገበት ቀንና ዓመት ማለትም 1869 ጋር በማያያዝ ማስታወስ ቀላል ሲሆን ከአራት ዓመታት በኋላ የመጀመሪያው መርከብ በዚሁ ካናል ማለፉን ለማስታወስ መሞከርም ይችላል:: አውስትራሊያ በሠፋሪዎች የተመሠረተችበትን 1788 ለአንድ አሜሪካዊ ለማስታወስ እንዲችል ቢነገረው ልክ ከአንድ መኪና ላይ የላላ ብሎን ወድቆ እንደሚጠፋው ሁሉ ቀኑንም ወዲያው ይረሳዋል:: ነገር ግን ይህንኑ ቀን አሜሪካ ነፃነቷን ከተቀዳጀችበት 1776 ላይ 12 ዓመታትን በመደመር አስተሳስሮ ሊያስታውሰው ቢሞክር ቅድም ያላላውን ብሎን አጥብቆ ማሰር ይችላል ማለት ነው::

የስልክ ቁጥሮችንም ለማስታወስ ይህን ዘዴ መጠቀም ይችላል:: ለምሣሌ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት የዚህ መፅሐፍ ደራሲ ስልክ ቁጥር 1776 ማለትም የአሜሪካ የነፃነት ቀንን በመወከሉ ለማስታወስ ቀላል ነበር:: በዚህ መልክ በዚያን ወቅት የስልክ ቁጥሩ 1492 የነበረ ሰው ለሌላ ሰው በሚሰጥ ጊዜ እንዲያስታውሱት ከፈለገ «የእኔ ስልክ ቁጥር አሜሪካ በኮሎምቦስ ከተገኘችበት ዓ.ም ጋር አንድ ነው:: አውስትራሊያዊ፣ ካናዳዊ ፣ ኒውዝላንዳዊ ወይም የማንኛ

ውም ሃገር ዜጋ ብትሆኑ ቀናቶችና ዓመታቶችን በሃገራችሁ ካለው ክብር በዓል፣ የነፃነት ቀን፣ ወይም ሌላ ታዋቂ የሆነ ቀን ጋር ብታያይዙት ለማስታወስ ይቀላችኋል።

እስቲ ቀጥሎ ያሉትን ዓመታት ለማስታወስ ይህን ዘዴ ተጠቀሙ

እስቲ ቀጥሎ ያሉትን ዓመታት ለማስታወስ ይህን ዘዴ ተጠቀሙ

ሀ/ 1564 የሼክስፒር ልደት
ለ/ 1602 እንግሊዛውያን ለመጀመሪያ ጊዜ በጀምስ ታውን የሰፈሩበት ቀን
ሐ/ 1819 የንግስት ቪክቶሪያ ልደት
መ/ 1867 የሮበረት ሰ. ልደት
ሠ/ 1789-የባስቲሌ ግንብ (ፈረንሳይ) የወደቀበት ቀን

በመደዳ እየደጋገሙ የማንበብ ዘዴ የመጀመሪያዎቹን ወደ አሜሪካ ውህደት የገቡትን 13 ሃገራት በቅደም ተከተላቸው ለመያዝ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን እነዚህን ሃገራት በታሪክ ውስጥ አካቶ በማጥናት ለማስታወስ ጥረት ማድረግ እጅግ ይረዳናል። እስቲ የሚቀጥለውን አንቀፅ አንድ ጊዜ ክልብ ሆናችሁ አንበቡት፤ በትኩረትም አስቡት። ከዚያ በኋላ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቃችሁ ለመያዝ ይከብዳችኋል?

አንድ ቅዳሜ ከሠዓት ላይ ከደልዌር የመጣች ወጣት ልጅ ከፔንስልቫኒያ ባቡር ጣቢያ ለጉዞ የሚሆናትን ትኬት ቆረጠች። ከኒው ጀርሲ የገዛችውን ሸሚዝ በሻንጣዋ አድርጋ ከያዘች በኋላ ጆርጂያ የምትባል ጓደኛዋን ከነክቲከት በሚገኘው ቤቷ ተቀምጣ አገኘቻት። በሚቀጥለው ጠዋት ከበረራ አስናጋጆቹ ጋር በመሆን በሜሪላንድ በሚገኝ አንድ ቤት ክርስትያን ጉባዔ ላይ ተሳተፈች። እራታቸውን ከቨርጂኒያ ታሽጐ የመጣ የአሣማ ስጋ ተመገቡ።

ከኒው ዮርክ የመጣ ነበር። በቀለማት ያሸበረቀው ተከታዩ ምግብ ደግሞ ከእራት በኋላ በኖርዝካርላ በመሳፈር ወደ አይስላንድ አመሩ

## የንግግራችንን ነጥብ እንዴት ማስታወስ እንችላለን

አንድን ሃሳብ በደንብ አውቀን እንድንይዝ የሚያደርጉን ነገሮች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው እንድናውቅ የሚረዳን ውጫዊ ሃይልና ስሜት ሲሆን ሁለተኛው ግን ቀድሞ በአእምሮአችን ውስጥ ከሚገኝ ሌላ ሃሳብ ጋር በማያያዝና በማዛመድ ነው። ውጫዊ ሃይል የሚባለው እንደ ማስታወሻ ደብተር ነው። . . . ግን አንድ ተናጋሪን ማስታወሻ ነገር ይዞ ማየት ማን ይፈልጋል? ሁለተኛው ከሁለተኛው በማያያዝ የምናውቅበት ዘዴ ነው። ከአንዱ ነጥብ ወደ ሁለተኛው ከሁለተኛው ወደ ሦስተኛ እያለ እንዲሄድ መቀናጀት አለበት፡ ይህ ዘዴ በእርግጥ ቀላል ቢመስልም ለጀማሪ ተናጋሪ ግን ሊከብድ ይችላል። ነገር ግን አንድ ቀላልና ፈጣን የሆነ ዘዴ አለ። ይኸውም ትርጉም አልባ የሆነ አረፍተ ነገር በመጠቀም ነው። ለምሳሌ በንግግርህ ላይ እንደ ማጣቀሻ የምትዘረዝራቸው እርስ በርስ የማይገናኙ የቃላት ስብስቦች ቢኖሩ ይህን ዘዴ መጠቀም ይቻላል። ላም፣ ሲጋራ፣ ሂይማኖት፣ ናፖሊዮን፣ ቤት የሚሉትን ቃላት በትርጉም አልባ አረፍተ ነገር ሰርተን በማያያዝ ለማስታወስ ይረዳናል «ላሟ ሲጋራ እያጨሰች ናፖሊዮንን በቀንዷ

ወግታ ስትጥለው ቤቱ በሃይማኖት እሳት ተቃጠለ» ቀጥሎ ያሉትን ጥቂዎች ለመመለስ አረፍተ ነገሩን አትመልከት!

መጀመሪያ ላይ የተጠቀምከው ቃል የትኛው ነው? ሁለተኛውና አራተኛው ቃልስ ምንድነው? እንዴት ነው ዘዴው ጥሩ ነው? በእርግጥም ጥሩ ሆኖ እንዳገኘኸውና ወደፊትም እንደምትጠቀምበት አያጠያይቅም:: በተለይ አረፍተ ነገሩ በጣም የሚገርም ከሆነ ለማስታወስም በጣም ቀላል ነው::

## በንግግራችን ወቅት ችግር ውስጥ ብንገባ ምን እናድርግ?

አንዲት ልጅ በቤተክርስትያን ለሚገኙ አባሎቿ ንግግር ለማድረግ ቅድሚያ ዝግጅቷን በጥንቃቄና በተገቢው መንገድ አድርጋለች ብለን እንገምት:: ነገር ግን በንግግሯ መሃከል ችግር ተፈጠረና ጠቅላላ በአእምሮዋ ያለው ሃሳብ ልክ በጨለማ እንደተዋጠ ሰው ድፍንፍን አለባት:: ዝም ብላም አድማጮቿን ትመለከት ጀመር . . . ቀጥሎ ስላለው የንግግሯ . . . በጣም አስደንጋጭ ሁኔታ ውስጥም ገባች:: በእነዚህ በዝምታ ባሳለፈቻቸው 15 እና 20 ነጥብ ለማስታወስ ሙከራ አደረገች:: በእነዚህ በዝምታ ባሳለፈቻቸው 15 እና 20 ሰከንዶች ውብ እና ደስ የሚሉ ነገሮችን ብትናገር ተመኘች:: ግን ምንም አልነበረም:: በአድማጭ ዘንድ ደግሞ በዝምታ ተውጦ መቆም እንደ ስህተት መቆጠሩ አይቀርም:: ታዲያ ምን ማድረግ ይሻላል? አንድ በጣም ታዋቂ የነበረ አሜሪካዊ ሴናተር በተመሳሳይ ሁኔታ ችግር ውስጥ በነበረ ጊዜ «መጨረሻ ባለው መቀመጫ ላይ የምትገኙ አድማጮቼ በደንብ ትሰሙኛላችሁ? ድምፄ ይሰማል?» በማለት ጠይቋል:: በእርግጥ እንደሚሰሙት ያውቀዋል:: ከእነሱ ማረጋገጫ ፈልጎ ሳይሆን ጊዜ ለመግዛት ሆን ብሎ ያደረገው ነበር:: እናም በዚያች ቅፅበት የንግግሩን ሃሳብ ሊያገኘውና ሊቀጥል በቅቷል:: ነገር ግን ከዚህ በተሻለ መልኩ በአእምሮ ላይ ከሚደርስ ሱናሚ የሚያወጣ መንገድ ልንገራችሁ:: ይኸውም ችግሩ በገጠማችሁ ቅፅበት ልትናገሩት ከነበረው ሃሳብ፣ ሃረግ ወይም ቃል በመነሳት ቀጣይ ለሆነው ንግግራችሁ እንደመጀመሪያነት መጠቀም ነው:: እስቲ በምሳሌ እንመልከተው:-

አንድ ሰው በስራችን ስኬታማ ለመሆን ምን ማድረግ እንዳለብን የሚገልጽ ንግግር ያደርግ ነበር:: «ግማሽ ያህል የሚሆነው ተቀጣሪ ሠራተኛ በስራው ወደፊት ጎልቶ ሊወጣ ወይም ሊታይ ያልቻለው በሚሰራው ሥራ ላይ ከልብ የሆነ ፍላጎትና ተነሳሽነት ስለሌለው ነው. . .» ካለ በኋላ ግን መቀጠል አልቻለም:: ከመጨረሻው ቃል በመነሳት ምን ሊል ይችላል? «ተነሳሽነት ማጣት» ምን በሉ ምን ብቻ በዝምታ ተውጦ ለሽንፈት ከመዳረግና ከመዋዠቅ የማይሻል ነገር የለም «ተነሳሽነት ማለት አለቃችንም ሆነ ሌላ ማንም ሰው እንዲህ አድጉ ሳይለን በእራሳችን ፍላጎት ሥራችንን ማከናወን መቻል ማለት ነው» በማለት ንግግሩን ቀጥሏል:: ይህ በእርግጥ አስደናቂ ትንታኔ ነው ማለት አይቻልም:: ነገር ግን ከከባድ ዝምታ ይሻላል. . . እስኪነገረን መጠበቅ ማለት ደግሞ ተከታታይ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግብን መጋበዝ ሲሆን በራሳችን ተነሳሽነት ፈጠራችንን ተጠቅመን ለመሻሻል ጥረት ስናደርግ አንታይም ማለት ነው» እንዲህ አድርገን እኛ ደግሞ በሱ ንግግር ላይ መቀጠል እንችላለን::



Scanned with CamScanner

አሁን ደግሞ ከራሳችን አንድ ቃል እንጨምር «ምናባዊ አይታ» ምናባዊ ዕይታ ይህ ማለት ሁላችን ሲኖረን የሚገባ ራዕይ ነው፡፡ ንጉስ ሰለሞን እንኳን ራዕይ የሌለው ህዝብ ይጠፋል! ብሏል፡፡ ከመጨረሻው ቃል ተነስተን እንቀጥል፡፡

ስራ በሚደረግ ትንቅንቅና ትግል በየአመቱ ብዙ ሰራተኞች ይጠፋሉ፡፡ ወይም ይወገዳሉ፡፡ ይህ በጣም አሳፋሪ ነው፡፡ አሳፋሪ ያልኩበት ምክንያት ትንሽ ታማኝነት ትንሽ ጥረት እንዲሁም ትንሽ ፍላጎት ቢታከልበት የትኛውም ሰራተኛ ሊሻሻልና ውድቀት ብቻ ሳይሆን ስኬት ከሚባለው ገደብ በማለፍ እራሳቸውን ከፍ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በየስራ ቦታ የሚታየው ውድቀት ይህን ስዕል አያሳየንም፡፡

በዚህ መንገድ እየተናገርን በተመሳሳይ ሰዓት ስለሚቀጥለው ነጥባችን ለማስታወስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡

ይህ መንገድ የአድማጮችን ትኩረት በምነግራችሁ ሃሳብ ላይ እንዲያደርጉ በማስገደድ በዝንጉነቱ ለተጎዳው አዕምሮአችን የመጀመሪያው እርዳታ በመስጠት ወደ መስመሩ ይመልሰዋል፡፡ በተግባርም በውድቀትና ሞት ላይ ነበሩ፡፡ ብዙ ንግግሮችን ነፍስ እየዘራ ሊያኖር የቻለ ግሩም ዘዴ ነው፡፡

## የማስታወስ ችሎታችንን ሁሉንም ነገር እንዲያስታውስ አድርገን ልናዘጋጀው አንችልም

እውነታዎችን ባገናዘበ መልኩ በአእምሮ በመቀረፅና፣ ደግሞ ደጋግሞ እያነበቡ በማጥናት የማስታወስ ችሎታችንን እንዴት ለማሻሻል እንደምንችል ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን ማስታወስ ማለት ነገሮችን የሚያያዝ ጉዳይ ስለሆነ ፕሮፌሰር ጀምስ እንደተናገሩት «አጠቃላይ ወይም ጀማሪ የሆነውን የማስታወስ ኃይል ያለበትን ክፍል ማሻሻል አይቻልም እና ማሻሻል የምንችለው የማስታወስ ኃይል ነገሮችን ልዩ በሆነ ዘዴ እርስ በእርስ እያገናኘንና እያያያዝን በማጥናት ያገናኘናቸውን ሃሳቦች ነው፡፡»

ከሼክስፔር ላይ የተወሰነ ጥቅስ ወስደን በማጥናት እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮችን በመያዝ አእምሮአችን በተሻለ ሁኔታ እንዲያስታውስ ማድረግ ብንችልም ከሮሚዮ እስከ ሃምሌት ያሉትን ጥቅሶች በሙሉ ማስታወስ መቻል ማንንም በጥጥ ገበያ ውስጥ ያሉትን እውነታዎች ለማስታወስ እንዲችል አያደርጉትም፡፡ በመከተል ልድገመውና በዚህ ክፍል (መፅሐፍ) የተማርናቸውን መመሪያዎች በዓይነቱ ለማሻሻል ተግባራዊ ለማድረግ በመጣር የማስታወስ ብቃታችንን ስለ ቤዝ ቦል እንችላለን፡፡ ነገር ግን እነዚህን መመሪያዎች ተግባራዊ ሳናደርግ ለስቶክ ገበያ የሚረዱ አንድ ሚሊዮን እውነታዎች ብናውቅና ብናስታውሳቸው የማይገናኙ መረጃዎች እውነታዎችን እንድናውቅ አይረዳንም፡፡ እንደዚህ አይነት ምክንያቱም «አእምሮአችን በአንድ ላይ አድርገው ቢያጠኗቸው አይመቹም፡፡ ነገሮችን የሚያይዝ ማሽን በመሆኑ ነው፡፡»

# ክፍል ስምንት

## ለስኬታማ ንግግር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

ይህን ምዕራፍ በምፅፍበት ጊዜ የሰር ሻክልተን የሙት ዓመት ማለትም ጥር 5 ቀን እየታሰበ ነበር:: የሞቱ ምክንያት ወደ አንታርክቲክ ኩዌስት በምትባለው መርከብ እየቀዘፈ በነበረበት ወቅት ባጋጠመው አደጋ ነበር:: በዚህች ኩዌስት መርከብ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳፈረ ሰው በነሃስ ላይ በተቀረጹ የግጥም ስንኞች መማረኩ አይቀርም::

ህልም ማለም ብትችልም የህልምህ ባሪያ እንዳትሆን፤
ሀሳብ ማሰብ ብትችልም ዓላማህ እንዳይሆን ብቻ ማጠንጠን፤
ከውድቀትም ሆነ ከድል ብትገናኝ በድንገት፤
በተመሳሳይ ዘዴ ማስተናገድ ይበጃል ለአንተ ህይወት፤
ልብህን፣ ነርቭህንና የሰውነትህን ጅማት፤
ዞረህ መግቢያህን ጊዜው ሳያልፍ ተጠቀምባቸው ለማግኘት፤
በእጅህ ምንም ባይኖር ተጠባበቅ ታገስ፤
የምኞትህን ደንቃራ ነው ሳይታገሱ መገርሰስ፤
ይቅር የማታውቅና ካለፈች አለፈች ነው እያንዳንዷ ደቂቃ፤
ውስጧን አምቃ ይዛለች ስልሳ ሰከንዶች ደብቃ፤
ያለህን ጊዜ አሟጥጠህ በትጋት ብትሰራበት፤
ምድር ያላት ነገር በሙሉ ያንተ እማይሆኑበት፤
ከቶ ምን ይገኛል ምንስ አለ ምክንያት፤
ከዚህስ በላይ ምን አለ ሁሉ ካለ በደጄ፤
ሰው መሆን ማለት ይኸው ነው በደንብ አድምጠኝ ልጄ፤

እነዚህን የግጥም ስንኞች ሻክልተን «የኩዌስት መንፈሶች» ብሎ ይጠራቸው ነበር:: በእርግጥም ናቸው:: አንድ ሰው የፈለገውን እንዲያደርግ የሚያነቃቁ ደቡብ ዋልታ ለመዝለቅም ሆነ በንግግራችን ጊዜ በራስ መተማመናችንን ለማሳደግ የሚረዱ አበረታችና አነቃቂ መንፈሶች ናቸው::

ይህም ሆኖ ግን ብዙ የንግግር ተማሪዎች ልምምዳቸውን ሲጀምሩ የሚያሳዩት የንግግራቸው መንፈስ ይህ እንዳልሆነ ስነግራችሁ እያዘንኩ ነው:: ከብዙ ዓመታት በፊት በማስተማር ስራ ላይ በነበርኩ ጊዜ እጅግ በጣም ያስደነቀኝ ነገር በማታው ፕሮግራም በተለያዩ ዘርፎች ተመዝግበው ትምህርታችውን መከታተል ከጀመሩ ተማሪዎች መካከል ያሰቡት ደረጃ ሳይደርሱ እያቋረጡ የሚወጡት በጣም መብዛታቸው ነበር:: ይህ በጣም ሊያሳፍረንና ግርምት ሊፈጥርብን የሚችል ጉዳይ ነው:: በተለይ ደግሞ በሰዎች ተፈጥሮአዊ ባህሪ ላይ የሚሰነዘር ትችት ስለሆነ ነው ነገሩን አሳዛኝ ያደርገው::

ይህን መጽሐፍ ለንግግሩ እንዲረዳው የሚያነብ ሰው አሁን ወደ ግማሽ አካባቢ በመጠጋታችን እስካሁን ባሳየው ለውጥ ደስተኛ ባለመሆን ወደ ተስፋ መቁረጥ ሊሄድ ይችላል:: ምክንያቱም የአድማጭ ፍራቻውን ገና ሊያስወግድ ስላልቻለና በሰዎች ፊት ለመናገር የሚያስችል በራስ የመተማመን ስሜትን ስላላገኘ ሊሆን ይችላል:: ለእነዚህ ሰዎች እያዘንኩ የምነግራቸው ነገር «ተስፋ

የሚቆርጡ በጣም አሳዛኝ ናቸው:: ምክንያቱም የትኛው ቁስል ባንድ ቀን ዳነ? ቀስ በቀስ እንጂ» በማለት ነው::

## በስቋም ፀንቶ የመቀጠል አስፈላጊነት

ማንኛውንም አዲስ ነገር ለማወቅ ስንማር እንደ ጎልፍ፣ ፈረንሳይኛ ቋንቋ ወይም ህዝብ ፊት ስለመናገር በምንለማመድ ወቅት ሁል ጊዜ የሚቀጥልና የማያቋርጥ ለውጥ ለማግምጣት በፍፁም አንችልም:: እየተሻሻልን የምንሄደው ቀስ በቀስም አይደለም:: ነገር ግን ለውጡንና መሻሻሉን የምናየው በድንገተኛ መመንጠቅና እልህ ባለው ጅማሬ ተነስተን ባንድ ጊዜ በመቀየር ነው:: ከዚህ በኋላ ደግሞ እንደገና እናዘግማለን ባለፈው የተማርናቸውን አንዳንድ ነገሮች ልናጣቸው የምንችልባቸው ሁንታዎች ይኖራሉ:: እንደነዚህ ያሉ መንገታገቶች ወይም የኋልዮሽ የመሄድ ነገር እንደሚያጋጥም የስነ-ልቦና ጠበብቶች ለማረጋገጥ ችለዋል:: ስያሜም ተሰጥቶአቸው «በመማር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ዳገቶች» ተብለው ይጠራሉ::

የንግግር ተማሪዎችን አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ዳገቶች አንቀው ይይዟቸዋል:: ለሳምንታትም ያቆዩዋቸዋል:: ምንም ያህል ቢፍጨረጨሩ እንኳን አይወጧቸውም በዚህ ጊዜ ታዲያ ቶሎ ተስፋ የሚቆርጡ ከሆነ እጅ ይሰጣሉ:: በብርታትና ፅናት የቀጠሉ ግን ሳያስቡት ድንገት በአንድ ምሽት ወይም ቀን ለምንና እንዴት እንደሆነ ሳያውቁት ታላቅ መሻሻል ያሳያሉ:: ልክ አውሮፕላን በድንገት ተፈናጥሮ እንደሚነሳ ሁሉ እነሱም ከዳገቱ ላይ ተመንጭቀው ይወጣሉ:: በድንገትም በራስ መተማመናቸውንና ለንግግራቸው የሚረዳቸውን ሃይል ያገኛሉ:: በሌሎች ሰዎች ላይ እንዳየነው ንግግር ሲጀመር አካባቢ ብዙዎች ፍራቻ ይኖርባቸዋል:: ነገር ግን ይህ ፍራቻ ከጥቂት አረፍተ ነገሮች በኋላ ይጠፋና ደስ በሚል ስሜት ንግግር ማድረግ ይጀምራሉ::

## ይህን ችሎታ ዘላቂ ስለማድረግ

በአንድ ወቅት ህግ ለማጥናት የፈለገ ሰው ምክሩን ይለግሰው ዘንድ በመማፀን ለሊንከን ደብዳቤ ጽፎለት ነበር:: ሊንከንም በመልሱ «በመጀመሪያ ህግ ለማጥናት ቁርጠኛ ውሳኔ እንዳለህ እራስህን ካሳመንከው የምኞትህ ግማሹ ክፍል ቀደም ብሎ ተሳካ ማለት ነው . . . ሁልጊዜም ቢሆን ስኬታማ ለመሆን ያለህ ፅኑ ፍላጎት ከሌሎች ነገሮች ሁሉ በላይ ወሳኝ መሆኑን ልብ አድርግ::»

ሊንከን በእዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ስላለፈ በደንብ ያውቀዋል:: ህይወቱን በሙሉ ከአንድ ዓመት በላይ በትምህርት ቤት ገብቶ አልተማረም:: መጽሐፎችን ግን? በአንድ ወቅት እንደተናገረው ከቤቱ በ50 ማይል ርቀት ላይ የሚገኙ መጽሐፍት ቤቶች በሙሉ እየሄደ ይዋስ ነበር:: እክፍሉ ውስጥ ሁልጊዜ ፍልጥ እንጨት እያነደደ ስለሚያድር አንዳንድ ጊዜ አልታይም ሲለው በፍሙ ተጠቅሞ መፅሐፉን እስኪጠፋ ድረስ ያነባል:: በእንጨቱ መካከል ባለው ስንጥቅ ውስጥም መፅሐፉን ያስቀምጠውና ጠዋት ደግሞ ብርሃን ፈንጠቅ ሲል አይኑን እያሸ መፅሐፉን አውጥቶ በጉጉት ንባቡን ይቀጥላል::



Scanned with CamScanner

ንግግር በሚኖርበት ጊዜም ዝግጅቱን በዕለቱ ርዕስ ላይ ልክ እናንተ አሁን እንደምታደርጉት ይለማመዳል:: ነገር ግን የበታችነት ስሜት በጣም ያጠቃው ነበር:: በተለይ ሴቶች በዙርያው ካሉ በሃፍረት የተነሳ ዱዳ ይሆናል:: አንድ ወቅት ሚሪ ቶድ የተባለች ሴት ተቀብለው ሲያነጋግር በእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ በሃፍረት ተሸብቦና በሀጥታ ሆኖ እሷ የምትለውን ብቻ ይሰማ ነበር:: በሌላ ገፅታው ግን በታላቅ ጥረት፣ ጥናትና ልምምድ እራሱን ወደ ዝነኛና ታላቅ ተናጋሪነት መለወጥ የቻለና ከእንከን የለሹ ሴናተር ደግላስ ጋር ክርክር ገጥሞ ያሸነፈ ሰው ነበር:: ይኸው ሰው በጌቲስበርግ እንዲሁም ለሁለተኛ ጊዜ ምርጫውን ሲያሸንፍ የበአለ ሲመቱን ንግግር በድንቅ የንግግር ችሎታው አጅቦ በማቅረብ በሌሎች ሰዎች ላይ አልፎ አልፎ እንኳን የማይታይ ታላቅ የብቃት ደረጃ ላይ መድረሱን አሳይቷል::

በእራሱ በኩል እንደዚህ ያሉ ችግሮች ቢኖሩበትም ለወጣቱ የህግ ተማሪ ግን ያን የመሰለ ምክር መለገሱ ምንም ሊደንቀን አይገባም:: ቴዎዶር ሩዝቬልት እንደተናገረውም «አንድ ፈተና የሆነና ለመወሰን አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ ሲከሰት እንዲሁም የፍላጎቶችና የመብት ጉዳይ ግጭት ሲፈጥሩብኝ በቢሮዬ ወደ ተሰቀለው የሊንከን ፎቶ ቀና ብዬ በማየት እሱ ቢሆን ምን ያደርግ ነበር ብዬ አስባለሁ:: እውነቱን ለመናገር ምንም ያህል ሊሆን የማይችል ነገር ቢመስላችሁም ለእኔ ችግሬን ወደ መፍትሄ በማምጣት ያቃልልኝ ነበር::»

እናንተስ የሩዝቬልትን መንገድ ለምን አትሞክሩትም? ልትሞክሩት ትችላላችሁ ተስፋ የሚያስቆርጥና ለመሻሻል አይቻለኝም የሚል ስሜት ሲፈታተናችሁ በአምስት ዶላር ላይ ያለውን የሊንከን ፎቶ ከኪሳችሁ በማውጣት በእናንተ ቦታ ችግሩ የደረሰው እሱ ላይ ቢሆን ምን ያደርግ እንደነበር ለማሰብ ሞክሩ:: ምን እንዳደረገም ታውቃላችሁ:: ምክንያቱም ለሴኔት መቀመጫ በሚወዳደር ጊዜ በስቴፋን ዳግላስ ክፉኛ ተደቁሶ ሲሸነፍ ለደጋፊዎቹ እንዲህ ብሎ የማሳሰቢያ መልዕክቱን አድርሶ ነበር:: «ለአንድ ጊዜ ሳይሆን ለመቶ ጊዜ ያህል እንኳን ብትሸነፉ ተስፋ አትቁረጡ»

## የእርግጠኝነት ስሜት ከፍተኛ ዋጋ አለው

ይህን መፅሐፍ ስታነቡ የምታገኙትን የዝነኛውን የሀርቫርድ የስነልቦና ፕሮፌሰር ዊሊያም ጀምስ ንግግር የተፃፈበትን ይህንን ክፍል ሁልጊዜ ጠዋት ለቁርስ ስትቀርቡ ጠረጴዛችሁ ላይ አደርጋችሁ በደንብ እስኪዋሃዳችሁ ድረስ ብታዩት ብዬ እመኛለሁ:: ማንኛውም ወጣት የትምህርት ውጤቱ እንዴት ይሆን? በማለት ጭንቀት ውስጥ መግባት የለበትም:: የተሰጠውን የሥራ ሰዓት በአግባቡ ተጠቅሞ በታማኝነት ከተገለገለበት በኋላ በመጨረሻ የሚመጣውን ውጤት ለእራሱ መተው አለበት:: ወደፊት አንዱን ቀን ከእንቅልፉ ሲነቃ በእሱ ትውልድ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከጨረሱት መካከል በተሰማሩበት በማንኛውም መስክ በብቁ ችሎታና ጉብዝና ስኬታማ ከሆኑት አንዱ እንደሚሆን በእርግጠኝነት ምንም ሳያመነታ መቀበል አለበት::

እኔም ታዲያ ከታዋቂው ፕሮፌሰር ምክር በመነሳት የምነግራችሁ የንግግር ጥናታችሁን በትጋትና በፅኑ ፍላጎት ከተለማመዳችሁ አንዱን ቀን በአካባቢያችሁ ወይም በከተሞች ከሚገኙት እጅግ ብቁና ጎበዝ ተናጋሪዎች መካከል አንዱ

እንደምትሆኑ ማመን ይኖርባችኋል፡፡ የበታችነት ስሜት የሚያጠቃውና በግል ስብዕናው ሰውን ዝቅ አድርጎ የሚያይ ሰው በተጨማሪ ምንም የንግግር ተሰጥኦ የሌለው ከሆነ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር እንደ ታዋቂው ዳንኤል ዌብስተር ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ተቀባይነት ያለውና በምክንያትም ሲረጋገጥ የቻለ ነገር ነው፡፡ በምሳሌ ለማሳየት የቀድሞው የኒውጀርሲ ገዥ የነበረው ስቶክ በንግግር ለተማሪዎች በተደረጉት የስብሰባ የመዝጊያ ስብሰባ ንግግሮች በዋሽንግተን ባለ የተወካዬች ምክር ቤት አባላት ከሚደረጉት እጅግ የተሻሉ ሆነው እንዳገኛቸው ገልጿል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ታዲያ ከጥቂት ወራት በፊት በአድማጭ ፍራቻ በመዋጣቸው ምንም ቃል ሊወጣቸው ያልቻሉ የንግዱ ማህበረሰብ ሰዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት አንዱን ቀን በከተማቸው ከሚከኙት ድንቅ ተናጋሪዎች መካከል ራሳቸውን ሲያገኙት ችለዋል፡፡

በዚህ ደረጃ ለስኬት ለመብቃት ሁለት ነገሮች ወሳኝ ናቸው፡፡ አንደኛው በተፈጥሮ የምናገኘው ተሰጥኦ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለመሻሻል ያለን ጥልቅና ጠንካራ ፍላጎት ነው፡፡ ፕሮፌሰር ጀምስ ሲያስረዱ «በማንኛውም የትምህርት ዓይነት ስኬታማ ውጤት ለማግኘት ያለን ዕድል ለትምህርቱ ባለን ዝንባሌ የተወሰነ ነው፡፡» ውጤት ለማግኘት ብንፈልግ እናገኛለን፤ ሃብታም ለመሆን ብንመኝ እንሆናለን፡፡ ነገር ግን ስንመኝ ብንመኝ እንሆናለን ጥሩ ሰው ለመሆን ብንመኝ እንሆናለን፡፡ ነገር ግን ስንመኝ በጥልቅ ፍላጎትና ከልብ ሆነን አንዱን ነገር ነጥለን በመያዝ እንጂ አብረው የሚሄዱ መቶ ነገሮች ደርበን መሆን የለበትም፡፡ እንደዚያው ሁሉ የበቃን ተናጋሪ ለመሆን ከልብ የሆነ ምኞትና ፍላጎት ካለን አስተማማኝ የሆነ የንግግር ችሎታ ባለቤቶች እንሆናለን፡፡»

በሺህ የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበርና በራስ መተማመናቸውን ለማግኘት ጥረት ሲያደርጉ ተመልክቻለሁ፡፡ ታዲያ በጥቂት አጋጣዎች ብቻ ነበር የተለየ ድንቅ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ስኬታማ ሲሆኑ ያጋጠመኝ፡፡ ሌላውን ጊዜ ግን እንደማንኛውም በአካባቢያችሁ እንደምታገኟቸው እጅግም ብልህ ያልሆኑ ሰዎች ነበሩ፡፡ በጣም ብልህ የምንላቸው ሰዎች ቶሎ ተስፋ ይቆርጣሉ ትኩረታቸውንም ገንዘብ በሚያስገኝ ነገር ላይ ብቻ ያደርጋሉ፡፡ ተራ የሆኑ ሰዎች ግን በከፍተኛ ፍላጎትና ለዓላማ ስለሚጥሩ በትምህርቱ ማብቂያ ላይ አንደኛ የሚሆኑት እነሱ ናቸው፡፡ ይህ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው፡፡ ይህ ነገር በተመሳሳይ ሁኔታ በንግድና በስራ ዓለም ባሉ ሰዎች ላይ ሲከሰት አይታችሁ አታውቁም?

ትልቁ ሮክፌለር በንግዱ ዓለም ለስኬት ለመብቃት በጣም አስፈላጊው ነገር ትዕግስት እንደሆነ ተናግሯል፡፡ ለእኛ ጉዳይም አስፈላጊው ነገር ይሄ ነው፡፡ ማርሻል ፎክ በአለማችን ከታዩት እጅግ ትልቅ የሆነውን የጦር ሃይል በማሸነፍ ለድል ለመብቃት ችሏል፡፡ እናም አንድ ታላቅ መርህ ነበረው፡፡ ይኸውም ፍጹም ተስፋ አለመቁረጥ ነው፡፡ የፈረንሳይ ጦር በ1914 ወደ ማርኔ ማፈግፈግ በጀመረበት ወቅት ጄኔራል ጆፍረ በእሱ ዕዝ ሥር የነበሩና ሁለት ሚሊዮን ወታደሮችን የሚመሩ ጄኔራሎቹን መሸሻቸውን በማቆም በመልሶ ማጥቃት አፀፋውን እንዲመልሱ ይነግራቸዋል፡፡ ይህ በአለማችን ታሪክ እጅግ ወሳኝ እንዲሁም አዲስ የሆነ ጦርነት ለሁለት ቀናት ተጧጡፎ በመቀጠል ላይ እንዳለ

የዕዝ ጣቢያው የበላይ አዛዥ የነበረው ጄኔራል ፎክ ለጀኔራል ጆፍሬ እንዲህ በማለት በወታደራዊ ማህደሮች ውስጥ እጅግ ድንቅ ሆኖ የተቀመጠውን መልዕክት ላከለት። «ዕዝ ማዕከሉ አደጋ ላይ ነው። ቀኝ ክንፌ፣ ላልቷል። ሁኔታው ግን እጅግ በጣም ጥሩ በመሆኑ አጠቃለሁ» ይህም የማጥቃት እርምጃ ፓሪስን ሊታደጋት ችሏል። እናንተም ውጊያው በጣም ከባድ ቢሆን፣ ተስፋ ብታጡ፣ ማዕከላችሁ ለጥቃት ቢጋለጥና ቀኛችሁ ቢላላ «ያለው ሁኔታ እጅግ አመርቂ ነው አጥቃ! አጥቃ! አጥቃ! በማለት ብትነሱ ምርጥ የሆነውን ማንነታችሁን፣ ድፍረታችሁንና እምነታችሁን ትታደጉበታላችሁ።»

## ዋይልድ ኬይዘርን መውጣት

ከብዙ ዓመታት በፊት በአውስትራሊያ አልፐስ የሚገኘውን «ዋይልድ ኬይዞር» ተብሎ የሚጠራውን ተራራ ለመውጣት ተንቀሳቀስኩ። ባዲከር የሚባል ሰው ወደላይ ለመውጣት ያለው ጉዞ አስቸጋሪ ነው። በተለይ ለጀማሪ ወጪዎች የሚመራ ሰው ያስፈልጋል አለ። እኔና ጓደኛዬ ምንም እንኳን ሁለታችንም ጀማሪዎች ብንሆንም ሊመራን የሚችል የሆነ ሰው አልነበረንም። እናም ሌሎች ሰዎች በውሳኔያችን ተገርመው «ይሳካልናል ብላችሁ ትገምታላችሁ?» ሲሉ ጠየቁን «በእርግጥም አዎን ይሳካልናል» ብለን መለስንላቸው እንዴት እንዲህ እርግጠኛ ልትሆኑ ቻላችሁ? ሲሉ በድጋሚ ጠየቁን «ከዚህ በፊት ሌሎች ሰዎች ምንም የሚመራቸው ሰው ሳይኖር ሊወጡ ችለዋል። ስለዚህ እኔም ከምክንያት ውጭ እንዳልሆንኩኝ አውቃለሁ። ሽንፈትን እያሰብኩም አንድን ነገር ጀምሬ አላውቅም።» ስል መለስኩላቸው።

እንደ ተራራ ወጭ ስታይ ጀማሪና ምንም የማላውቅ ብሆንም ነገር ግን ተሳክቶልኛል። ይህ ለማናቸውም እንደ ስነ-ፅሑፍ የንግግር ትምህርትም ሆነ የኤቨረስትን ተራራ ለመውጣት የሚረዳ ትክክለኛ የሆነ የሥነ-ልቦና ዘዴ ነው። ድል ስታደርጉ አስቡ፣ በአይነ ህሊናችሁም በህዝብ ፊት ቆማችሁ እራሳችሁን በሚገባ ተቆጣጥራችሁ ንግግር ስታደርጉ እዩት፣ ይህ በእናንተ ኃይልና ቁጥጥር ስር ያለ ነገር ነውና እንደሚሳካላችሁም እመኑበት። በእውነትም ከልብ ካመናችሁ ለስኬት የሚያበቃችሁን ማንኛውንም ነገር ማከናወን ትችላላችሁ። አድሚራል ዱፓንት ለምን የጦር ጀልባዎቹን ወደ ቻርልስ ደሴት ሊወስድ እንዳልቻለ የሚገልጹ ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ ድንቅ ምክንያቶችን አቅርቦ ነበር። አድሚራል ፍራውት ግን ዱፓንት በመደጋገም ሲናገር የነበረውን ነገር በጥሞና ካዳመጠ በኋላ «ነገር ግን አንድ ያልጠቀስከልን ምክንያት አለ» ሲል ነገረው ። «ይህን ማድረግ ትችል እንደነበረ በሙሉ ልብህ አምነህ ያለመቀበልህ» ሲል መለሰለታል።የንግግር ተማሪዎች ከትምህርታቸውና ከልምምዳቸው የሚቀስሙት እጅግ ጠቃሚው ነገር በራስ መተማመናቸው በእጅጉ በመጨመሩ ምንም ነገር ለመቀዳጀት እንደ ተጨማሪ መተማመኛ ማገልገሉ ነው። ከዚህ በላይ ለስኬት እጅግ አስፈላጊ የሆነና ማንኛውንም ነገር ለማከናወን የሚረዳ ነገርስ ከወዴት ይገኛል?

# ለማሸነፍ ያለን ፍላጎት

ይህ አንጋፋው አንጋፋው ኤልበርት ሁባርድ ልጠቅሰው የሚገባ ጠቢባዊ ምክር ነው፡፡ ማንኛው ወንድና ሴት በዚህ ምክር ውስጥ ያለውን ጥበብ በተግባር በማዋል ህይወታቸውን ቢመሩ እሱም ሆነ እሷ ደስተኛና ባለፀጋ ይሆናሉ፡፡ «ሁልጊዜ ከቤት ስትወጣ የራስህን አክሊል ከፍ አድርገህ በመያዝ ሳንባህን በአየር በደንብ ሞልተህ፣ ጓደኞችህንም በፈገግታ ተሞልተህና ከልብህ ሆነህ ሰላምታ ስጣቸው፡፡ ይህ ነገር በሌላ ይተረጉመብኛል ብለህ አትፍራ፡፡ ስለጠላቶችህም አታስብ፣ አእምሮህን ማከናወን በምትፈልገው ነገሮች ላይ እንዲያተኩር አድርገው፡፡ ከዚህ በኋላ አቅጣጫህን ሳታዛንፍ በትክክል ወደ ግብህ ተጓዝ፡፡ በአስደናቂና በታላላቅ ነገሮችም አዕምሮህን ሙላው እናም ቀናቶች እየገፉ ሲመጡ ምንም ሳታውቀው እነዚህን ፍላጎቶች የሚያሟሉልህ አጋጣሚዎች ልክ በወራጅ ውሃ ውስጥ የምትፈልገውን ምግብ እንደምታገኝ ወፍ ሲከሰቱ ታገኛለህ፡፡»

በአእምሮህ ላይ የተካንክና ሁሉንም ነገር ለማድረግ የምትችል ጠቃሚ ሰው መሆንክን ስለህ አስቀምጥ፡፡ ይህ እምነትህ ወደዚያ ልዩ አድርገህ ወደሳልከው ሰው ያሻግርሃል፡፡ ትክክለኛ አመለካከት ይኑርህ ግልፅ የሆነ፣ አመለካከትና ደስተኛ መንፈስ ይኑርህ በትክክል ማሰብ ማለት በትክክል መፍጠር ማለት ነው፡፡ ሁሉም ነገሮች በፍላጎቶችህ ውስጥ ናቸው፡፡ ከልብ የሆነ ፀሎት ምላሽ ያገኛልና ጭንቅላታችንንም ከፍ በማድረግ አክሊላችንን ቀና እናድርገው፡፡ ናፖሊዮን፣ ዌሊንግተን፣ ግራንት፣ ጄኔራል ፎክን የመሳሰሉ ወታደራዊ አመራሮች አንድ ሰራዊት ለማሸነፍ ያለው ፍላጎት እንዲሁም በራስ የመተማመን ስሜት ከሌሎች ነገሮች በላይ ለድል የሚያበቁ መሆናቸውን በደንብ ያውቁ ነበር፡፡ ማርሻል ፎክ «ዘጠና ሺህ የተሸነፉ ሰዎች ለሽንፈታቸው ምክንያትና ለድል ሊበቁ ያልቻሉት እንደሚያሸንፉ እምነተ ስለሌላቸውና ሞራላቸውም የላሸቀና ተሟጥጦ ጫፍ ላይ የደረሰ በመሆኑ ነው ብሏል፡፡ ፍሬዘር የተባለው የአሜሪካን ባህር ኃይል ከፍተኛ ባለማረግ የነበረ ሰው ባህር ኃይሉን ለማገልገል እንዲሁም ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን እንደሆኑ ሲጠየቅ በአራት ቃላት «ግርማ ሞገስ፣ ብልህነት፣ ብርታትና፣ ፅናት» በማለት መልሷል፡፡ በንግግርህ የዳበርክ ለመሆንም እነዚህን ነጥቦች ማሟላት አለብህ፡፡

# ክፍል ስድስት

## ጥሩ ትረካ የማቅረቢያ ሚስጥር

ልክ አንደኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ ሁለት ወንድማማቾችን ለንደን ውስጥ ተዋውቄ ነበር:: ሰር ሮዝ እና ሰር ኬይዝ ይባላሉ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከለንደን ወደ አውስትራሊያ የተደረገውን በረራ በማድረጋቸው ለእያንዳንዳቸው የ50 ሺህ ዶላር ሽልማት ከአውስትራሊያ መንግስት ሲበረከትላቸው በመላው እንግሊዝ ንጉስ የማዕረግ ስም ተሰጥቷቸዋል::

ካፒቴን ሃርሊ የተባለ ታዋቂ የሳይንስ ፎቶግራፍ ባለሙያ ይህን ጉዞ በተንቀሳቃሽ ምስል ቀርፆ ለማስቀረት አብሮ ተጉዞ ነበር:: እኔም ታዲያ ይህን የጉዞ ታሪክ ለማቅረብ የሚረዱትን ዝግጅቶች በማድረግና በመምራት እገዛ አድርጌ ነበር:: ለአራት ወራት ያህል በየቀኑ በፊል ሃርምኒክ አዳራሽ እየተገኙ አንደኛውን በቀን ሌላኛው በማታ ይለማመዱ ነበር:: አብረው ያሳለፉት ተሞክሮ አንድ አይነት በመሆኑና ጎን ለጎን ተቀምጠውም የዓለምን ግማሽ የበረሩ ስለሆነ ትረናቸው አንድ አይነት ንግግር እንደውም ቃል በቃል የተመሳሰለ አይነት ንግግር መሆን ነበረበት:: ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ትረካ ፈፅሞ አላዳመጥንም::

በንግግራቸው ውስጥ ተራ ከሆኑ ቃላት በላይ ውድ ዋጋ ያላቸው አባባሎች አሉ:: ይህም እነዚህ ቃላቶች የሚቀርቡበት ሁኔታ ለዛ ያለው፣ የጣፈጡና የሚስቡ ሲሆኑ ብቻ ነው:: «ዋናው ጉዳይ ምን እንደምትናገር ማወቅህ ሳይሆን እንዴት እንደምትናገረው ማወቅህ ነው» አንድ ጊዜ ከአንዲት ወጣት ልጅ አጠገብ ተቀምጬ የኮንሰርት ትርዒት እከታተል ነበር:: በቶፒሊን የተፃፈውን ሙዛራካ ማስታወሻ የሚለውን ጭውውት ልክ ፓድርውስኪ እንደተወነው አስመስላ ጮክ ብላ እያነበበችው ነበር:: የእሷ አነባበብ የተደናበረ በመሆኑ ምንም ሲገባን አልቻለም:: እሷ ያነበበችውን ክፍልም ተዋናዩ ራሱ በጣቱ እየተከተለ ሲለው የነበረው ክፍል ነው:: ነገር ግን የትወና አቀራረቧ ተራ በሆነ አነባበብ ነበር:: የእሱ ግን ድንቅና ውብ ነው ተብሎ ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን አድማጮቹን በአድናቆት እንዲሰሙና እንዲመሰጡ ያደረገ የትወና አቀራረብ ነበር:: ከማስታወሻው ላይ ያነበበውንና ያጠናውን ብቻ አላቀረበም የአገላለጹ መንገድ ጥበባዊ ስሜት በተላበሰ ስብዕና ማቅረብና መተረክ መቻሉ እንደነገሩ ተቀነባብሮ በሚዘጋጅና በምጡቅ አእምሮ እየፈለቀ ከሚቀርብ ተውኔት መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነበር:: ታላቁ የሩሲያ ሰዓሊ ቡርሌፍ የተማሪውን ስራ እያረመ በነበረበት ወቅት ተማሪው የተሞነጫጨረ የሚመስለውን ስእል እያየ በማጋነን እንዲህ ሲል ተናገረ «ትንሽ ቦታ ላይ ነው ጫር ያደረከው ታዲያ እንዴት ፍፁም ሌላ ስዕል ሲመስል ቻለ?» በማለት ሲጠይቀው

ቡርሌፍ የመለሰው «ጥበብ የሚጀምረውም በጭረት ነው» በማለት ነበር:: ይህ አባባሉ ለስዕሉም ሆነ ለፖድር ውስኪ ተውኔት ገላጭ የሆነ እውነታ ነው:: ስለ እንግሊዝ ፓርላማ የሚነገር አንድ የድሮ አባባል አለ:: ይህም ማንኛውም

ጉዳይ ውሳኔ ያገኘ የነበረው በተናጋሪው የአቀራረብ ባህሪ እንጂ ባቀረበው ጉዳይ ምንነት ላይ ተመርኩዞ አይደለም። ይህን ነገር ኬንትሲን የተናገረው እንግሊዝ ክሮም ሰሬ ቀኝ ግዛቶች አንዷ በነበረች ጊዜ ነበር። ጥሩ አቀራረብ የተላበሰ ንግግር ግን በጣም የሳሳ ይዘት ያለውን ጉዳይ ብዙ ርቀት እንዲሄድ ያስችለዋል። በኮሌጆች ውስጥ የሚደረጉ የንግግር ውድድሮችን ተከታትያለሁ። ሁልጊዜ ሲያሸንፍ የማየው በጥሩ መረጃ ተደግፎ ንግግሩን ያቀረበው ሰው ሳይሆን አቀራረቡን በማሳመር ጥሩ መረጃ የያዘ የሚያስመስለው ሰው ነው።

ሎርድ ሙሪ በአንድ ወቅት ንግግርን አስመልክተው በሰጡት ደስ የሚል ጥርጣሬያዊ ንግግር «በአንድ ንግግር ላይ ወሳኝ የሆኑ ሶስት ነገሮች አሉ ከእነዚህም መካከል የመጨረሻው ነጥብ ብዙም ዋጋ ሲሰጠው አይታይም ብለዋል። የተጋነነ ገለፃ ይመስላል አይደል? በእርግጥም ነው። ነገር ግን ላዩን ፋቅ ፋቅ ብታደርጉት እውነታውን ቁልጭ ብሎ ታገኙታላችሁ።»

ኤድመንድ ብሩክ ንግግሮቹን ድንቅ በሆነ ሁኔታ በስነአመክኖያዊና በምክንያት አብራርቶ መፃፍና ማቀናበር ስለሚችል የእሱን ፅሁፎች እንደ ሞዴል የሆኑ መማሪያዎች በማድረግ ብዙ ኮሌጆች አስከዛሬ ይጠቀሙበታል። ነገር ግን ብሩክ እንደተናገረው ለመሆን ሊሳካለት አልቻለም። ይህን እንቁ የሆነ ችሎታውን በንግግር በማቅረብና እንዴት ማራኪና ኃይል ያላቸው እንደሆኑ ለማሳየት አልተቻለውም። ስለዚህም የምክር ቤቱ «የእራት ደውል» የሚል ቅፅል ስም ወጥቶለት ነበር። ምክንያቱም እሱ ንግግር ማድረግ ሲጀምር የምክር ቤቱ አብዛኛው አባሎች ማሳል፣ መጎነታተልና ሹልክ እያሉ መውጣት ስለሚጀምሩ ነበር።

የጥይት አረርን በእጅህ የቻልከውን ያህል ወርውረህ በርቀት ያለን ሰው ልትጎዳ አትችልም። ነገር ገን የጥይቱን ዱቄት በቂጡ በኩል በሻማ ብታሞቀው ወፍራም ጣውላ በስቶ ሊወጣ የሚችል ሃይል ያገኛል። በሻማ የተለኮሰ ጥይት የሆነ ንግግር ማድረግ ሲቻል ታዲያ አብዛኛው ተናጋሪ ይዞ የሚመጣው ጥይቱን እንጂ ሻማውን ይዞ አለመሆኑን ስነግራችሁ በማዘን ስሜት ነው።»

## ንግግር ማቅረብ ራሱ ምን ማለት ነው?

ከአንድ ሱቅ የገዛችሁትን ዕቃ ባለቤቱ የሚልክላችሁ እንዴት ነው? የባለሱቁ ሹፌር እቃችሁን እግቢያችሁ ጓሮ ወርውሮት ነው የሚሄደው? ከአንድ ሰው እጅስ የሆነ ዕቃን ማግኘት ማለት ልክ እንደቀረበ ይቆጠራል? በቴሌግራም መልእክት የሚያስተላልፍ ሰው በቀጥታ መልእክቱን ለተፈለገው ግለሰብ እንደሚያስተላልፍ ሁሉ ብዙ ተናጋሪዎች ይህን ያደርጋሉ? ብዙ ሰዎች የሚናገሩበትን መንገድ የሚገልጽ ምሳሌ ልንገራችሁ አንድ ጊዜ በምስዊዙ የአልፓስ የበጋ መዝናኛ ተገኝቼ ነበር። ይህ መዝናኛ በእንግሊዝ ኩባንያ ባለቤትነት የተያዘ በመሆኑ በየሳምንቱ ከለንደን የተለያዩ ምሁራንን በመላክ ለእንግዶቹ ገለፃና ትምህርት ይሰጥ ነበር። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ታዲያ ታዋቂዋ የእንግሊዝ ልብ ወለድ ፀሃፊ ነበረችበት የምትናገረው ርዕስ «ልብ ወለድ እና የወደፊት ዕጣው» የሚል ነበር። ይህን ርዕስ እሷ ራሷ እንዳልመረጠችው በማመን ንግግር ጀመረች። ወጣም ወረደም ስለሃሳቡ ምንም የምትለው ነገር



Scanned with CamScanner

የሴላትና በገለፃዋ የያዘችውን ርዕስ በትክክል በሚያብራራ መልኩ አሳዘጋጀችም ነበር፡፡ ጥድፊያ በተሞላበት ሁኔታ የሆነ ማስታወሻ ጫር ጫር አድርጋ በእንግዶች ፊት ቆመች አድማጮቿን ረስታቸዋለች ማለት ይቻላል፡፡ እንደውም ፊት ለፊት ሁሉ አታያቸውም፡፡ አንድ ጊዜ ከእነሱ በላይ ጣሪያ ጣሪያውን ታያለች፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወደ መሬት እንዲሁም ወደ ማስታወሻዋ ታያለች፡፡

ከዚህ በኋላ ከርቀት ባለ ባዶ ቦታ ላይ አይኖቿን አሻግራ በመወርወር ከርቀት የሚመጣ በመሰለ ድምፅ ቃላቶቿን ማውጣት ጀመረች ይህ አይነቱ ነገር በጠቅላላ ንግግር ማቅረብ ተብሎ ሊጠራ አይችልም፤ ይህ ግለ ወግ ወይም ለራስ ንግግር እንደማድረግ ነው የሚቆጠረው፡፡ ምንም የመግባባት ስሜት የማይታይበት ሲሆን ይህ ስሜት ደግሞ ለአንድ ጥሩ ተናጋሪ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነጥብ ነው፡፡ አድማጩ ከተናጋሪው ሰው ልብ እና አዕምሮ ወደ እሱ ልቦና የሚተላለፍ መልዕክት እንዳለ ሊሰማው ይገባል፡፡ ከላይ የገለጽኩት ንግግር ግን በጎቢ በርሃ ላይ እንደ ተላለፈ መልእክት ይቆጠራል እንጂ በእውነ ሰብዓዊ ፍጡር ፊት የተደረገ አይመስልም፡፡

## ጥሩ ንግግር የማቅረቢያ ሚስጥር

ብዙ አሰስ ገሰስ የያዙ ፅሁፎች በንግግር አቀራረብ ላይ ተፅፈዋል፡፡ በህጎች፣ አባባሎችና ልምዶች የታጠሩና ሚስጥራዊ የሆኑ ናቸው «የመናገር ችሎታ» በአምላክ ዘንድ እንዲሁም በሰው ልጆች አመለካከት የተጠላና የተወገዘ የሚያደርጉ ኋላቀር አስተሳሰባቸውም አሰገራሚ ነው፡፡ ሰዎችም በቤተ መፃሐፍት የሚያገኙት እነዚህን ዋጋ የለሽ መጽሐፍት ነበር፡፡ ዘመናዊው አድማጭ ተናጋሪው ሰው ለአስራ አምስት ሰውም ሆነ ለሺህ ሰው የሚናገር ቢሆንንም ልክ ለእያንዳንዱ ሰው በቀጥታ የሚናገር በሚመስል መንገድ እራሱን ከአድማጩ ጋር አግባብቶ እንዲሄድ ይፈልጋል፡፡ ይህም ሲባል ለአንድ አድማጭ ሲናገር የሚጠቀመውን ሀይል ከአርባ በላይ ለሆኑ ሰዎች ንግግር ቢጠቀም ተደማጭ ያደርገዋል ማለት አይደለም የሚጠቀመው ኃይል ከአድማጩ ብዛት ጋር መመጣጠን ይኖርበታል፡፡

ማርክ ትዌን በኔቫዳ የማዕድን ማውጫ ካምፕ ውስጥ የመዝጊያ ንግግር ለማድረግ በተዘጋጀበት ወቅት አንድ የዱሮ አድማጩ ወደ እሱ በመቅረብ እንዲህ ሲል ጠይቆት ነበር «በተፈጥሮ ያለህን አንደበተ ርቱዕነትህን ትጠቀምበታለህ?» አድማጩም የሚፈልገው ይህን ተፈጥራዊ የሆነ አንደበተ ርዕቱነትህን ነው፡፡ ቅድም የልብ ወለድ ፀሃፊዋን የንግግር አቀራረብ አይተናል፡፡ እዚያው አዳራሽ ውስጥ ግን ከጥቂት ምሽቶች በኋላ ሰር ኦሊቨር ሎጅ ያቀረበውን ንግግር ሰምቼ ነበር፡፡ ያዘጋጀው ርዕስ «አቶሞችና ዐለማትን» የተሰኘ ነበር፡፡ ይህን ጉዳይ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ምርምር በማድረግ ሲያጠናውና ሲመረምረው የነበረ ጉዳይ ነበር፡፡ የእራሱ የሆነ ከልቡ የሚረዳው፣ በአእምሮው የሚያስበውና የህይወቱ ግማሽ የሆነ ነገር ነበር፡፡ ስለዚህ ለእኛ እየተናገረ መሆኑን እንኳን ረሳው . . . እኔም በረሳው ስል እግዚአብሄርን ለመንኩ . . . እሱን ያሰጋው ይኸው ጉዳይ ብቻ ነበር፡፡ ምክንያቱም ብዙ ትኩረቱን ያደርገው ለእኛ ለአድማጮቹ ስለ አቶም ምንነት በስሜትና በትክክል በመግለጽ ላይ ስለነበር ነው፡፡ ስለሆነም ጥረት ያደርግ



Scanned with CamScanner

የነበረው እሱ ያየውን ነገር እንድናየውና የተሰማው ስሜት እንዲሰማን በመሞከር ላይ ነበር:: እናስ ውጤቱ ምን የሆነ ይመስላችኋል? እጅግ ድንቅ የሆነ፣ ኃይልና ግርማ ያለው በተብራራ ሁኔታ ግልፅ ጥልቅና ስሜት ጨምድዶ የሚይዝ ንግግር አቀረበልን:: በእርግጥም እሱ የተለየ ችሎታ ካላቸው ጥቂት ሰዎች የሚመደብ ተናጋሪ ነበር:: እሱ እራሱን በዚያ መልክ እንደማይመድብ ግን በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ:: በዚያ የሚገኙ ብዙ ሰዎችም ንግግር በማድረግ በጣም ታዋቂ የሆነ ሰው መስሏቸው ነበር:: እናም ይህን መጽሀፍ አንብባችሁ በህዝብ ፊት በብቃት መናገር የቻላችሁ ሁሉ ደራሲው ዋጋዬን ክፈሉኝ ብሎ እንደማይጠይቃችሁ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ:: ጥሩ ተናጋሪ ማለትም እንደዚሁ ነው በጣም ተፈጥሮአዊ ክህሎት ስለሚመስልም አድማጩ የንግግሩን ባህሪ ሳይሆን የሚያስተውሰው የንግግሩን ፍሬ ነገር ይሆናል::

## የሄንር ፎርድ ምክር

«ሁሉም የፎርድ መኪኖች ተመሳሳይ ናቸው» ይባላል ፈጣሪ የሆነው ሰው «ነገር ግን ሁለት» ሰዎች በፍፁም አይመሳሰሉም እያንዳንዱ አዲስ ፍጡር ከጸሃይ በታች ያለ አዲስ ነገር ነው:: እንደሱ ያለ ነገር አልተፈጠረም ወደፊትም አይፈጠርም:: አንድ ወጣትም ይህን ነገር ማወቅ አለበት:: እናም እራሱን ከሌሎች መስሎቹ የሚለይበትን ጥቂት የሆነች ጭላንጭል ፈልጎ ማግኘት አለበት:: ሲያገኘውም በማሳደግና በመንከባከብ የራሱ አድርጎ ሊገለገልበት ይችላል:: ማህበረሰቡና ትምህርት ቤት ይህን እንዳያደርግ አጥር ሊያበጁለት መሞከራቸው አይቀርም:: ምክንያቱም የእነሱ ፍላጎት ሁላችንንም በአንድ አይነት ቅርፅ ማውጫ ጠፍጥፎ ለማውጣት ስለሆነ ነው ነገር ግን እኔ የምመክራችሁ ይህችን ጭላንጭል እንድትጠፋ አታድርጓት ያለቻችሁ የኔ የምትሏት ገፀ በረከታችሁ እሷ ናትና»

በህዝብ ፊትም ለመናገር ይህ እውነታ በእጥፍ ይሰራል፤ በእዚህ ምድር እንዳንተ ያለ ሌላ ሰው የለም፤ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሁለት ዓይን አንድ አፍንጫና አፍ አላቸው:: ነገር ግን ማናቸውም አንተን አይመስሉም:: ጥቂት የሆኑ እንዳንተ ሊናገሩና ሃሳባቸውን ሊገልፁ ይችላሉ:: ነገር ግን ያንተ አይነት ተሰጥኦና ዘዴ ሊኖራቸው አይችልም:: ሰር ኦሊቨር ሎጅ ከሌሎች ሰዎች በተለየ ሁኔታ ሊናገር የቻለው ከማንም ጋር ስለማይመሳሰል ብቻ ነው:: የአንድ ሰው የንግግር ባህሪ ልክ እንደ ፂሙና የጭንቅላቱ ቅርፅ የማንነቱ አንድ አካልና ገፅታ ነው ማለት ይቻላል:: ስለዚህ ሎጅን ለመሆንና ለማስመሰል መሞከር ውጤቱ ከባድ ውድቀት ይሆናል::

በአሜሪካ እጅግ ታዋቂ የሆነው ክርክር የተደረገው 1858 ነበር:: ይህም በስቴፋን ዳግላስና በአብርሃም ሊንከን መካከል ማለት ነው:: ሊንከን ረጅምና ጎታታ ነበር:: ዳግላስ ደግሞ አጭርና ግርማ ሞገስ ያለው ነበር:: እነዚህ ሰዎች በባህሪ፣ በአስተሳሰብ በአጠቃላይ ሰብእናቸውና የሰውነት ቅርፃቸው የተለያዩ አይነት ሰዎች ነበሩ:: ነገር ግን ሁለቱም በየራሳቸው የበቁ ተናጋሪዎች ነበሩ:: ምክንያቱ ደግሞ እራሳቸውን የመሆን ድፍረቱና በጎ ፍላጎት ስለነበራቸው ነው:: አንዳቸው እንዳቸውን ለመቅዳት ቢሞክሩ ኖሮ በአሳፋሪ ሁኔታ ለውድቀት ይዳረጉ ነበር:: ነገር ግን የየራሳቸው የሆነውን ልዩ ተሰጥኦ ተጠቅመው የተለዩና ተፅዕኖ

ፈጣሪ ሰዎች ለመሆን በቅተዋል፡፡ ይህ መንገድ ለማሳየት ቀላል የሆነ ለመከተል ግን የሚከብድ ነው፡፡ ማርሻል ፎክ ስለጦርነት እንዳለውም «ጦርነት በሃሳብ ደረጃ ቀላል ቢሆንም በተግባር ለሚሰራው ግን እጅግ አስቸጋሪ ነው» ሰዎችን ለንግግር ለማብቃትም የሚደረግ ትምህርትና ስልጠና ያለው ችግር ተጨማሪ ችሎታና ባህሪዎችን በላያቸው ላይ በመጫን ሣይሆን ጨምድዶ ከያዛቸው መሰናክሎች ነፃ ማውጣት አለመቻል ነው፡፡

በጣም ለብዙ ጊዜያት ንግግር የሚያደርጉ ሰዎችን በመሃከል እያስቆምኩ «እንደሰብኣዊ ፍጡር ተናገሩ» እያልኩ መምራት ነበረብኝ፡፡ ይህም ይህም በጣም በአካል ደቅቄና በአእምሮዬ አድካሚና አሰልቺ ከመሆኑ የተነሳ ማታ እቤት ስገባ ዝዬ ነበር፡፡ እመኑኝ እንደሚታየው ቀላል የሆነ ነገር አይደለም፡፡ እናም ውስጥ ከተገኛችሁ ቆም በማለት «ሃይ በንግግራችሁ ጊዜ በጣም የተምታታ ሁኔታ ውስጥ ከተገኛችሁ ቆም በማለት «ሃይ ነቃ በል! ችግሩ ምንድነው? እራስህን ሁን እንጂ» ብላችሁ መንገር አለባችሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ከአድማጫችሁ ውስጥ ፈዘዝ ብሎ ከወደኋላ የተቀመጠውን ሰው እያያችሁ ልክ ለእሱ ብቻ እንደምትናገሩ ቆጥራችሁ ለሌላው ሰው ትኩረት ሳትሰጡ መቀጠል ትችላላችሁ፡፡ በዚህ ሂደትም ከእሱ የተጠየቃችሁት ጥያቄ እንዳለና ለዚያም መልስ እየሰጣችሁ እንደገና ሲጠይቃችሁም መልስ እንደሚሰጥ ሰው ሆናችሁ በጥሩ ሁኔታ ንግግራችሁን ጭውውት ማስመሰል እንዲያውም ከዚህ ሁሉ ገፋ አድርጋችሁ በመሄድ ጥያቄዎችን ለራሳችሁ እያቀረባችሁ መልስ በመስጠት ዘና ብላችሁ ያለችግር መናገር ትችላላችሁ፡፡ ለምሳሌ በንግግራችሁ መሃል «አሁን ላነሳሁላችሁ ነገር ምን ማስረጃ አለህ? ብላችሁ ብትጠይቁ . . .በቂ የሆነ ማስረጃዬ ይኸውላችሁ . . . » በማለት ጥያቄዎችን በማቅረብ መልስ እየሰጣችሁ መቀጠል ይቻላል፡፡ ይህ አይነቱ የንግግር አቀራረብ ዘዴ አንድ ዓይነት ቃና ብቻ ያለው ንግግር ይዘን እንዳንቀጥል በማድረግ አስደሳች የሆነ የውይይት መንፈስ በመፍጠር ለማዋዛት ይረዳናል፡፡

በጥልቅ ስሜት ትህትናን ተላብሰን መናገርም ጠቃሚ ነጥብ ነው ምክንያቱም አንድ ሰው በእነዚህ ስሜቶች ተፅዕኖ ስር ሲሆን እውነተኛ ማንነቱ ጎልቶ እንዲወጣ ያስችለዋል፡፡ የውስጣዊ ስሜት ግለቱም ማንኛውንም ጋሬጣ የሆነ ነገር በማስወገድ እንደልቡ እናዲናገር ያደርገዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ ተፈጥሮአዊ ማንነቱን አገኘ ማለት ይቻላል፡፡ ይህን ጉዳይ በዚህ ስንዘጋው አንድ ነገር ታዲያ ተመልሶ ይመጣል፡፡ ይህም ከዚህ በፊት ደጋግመን ያየነው «ስትናገር ከልብህ ሆነህ ተናገር» የሚለው ነው፡፡

በያሌ መንፈሳዊ ዩንቨርስቲ ስለ ስብከት ያስተምር የነበረው ዲን ብራውን ሲናገር «አንድ ጊዜ ለንደን ለአገልግሎት በሄድኩበት ወቅት የሰማሁትን በዓይነቱ አገላለፅ መቼም ቢሆን አልረሳውም» ይላል በወቅቱ ያስተምር የነበረው ሰባኪ ጆርጅ ማክደናልድ ነበር፡፡ በሂብሩ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውን አስራ አንደኛውን ምዕራፍ ይጠቅሳል፡፡ ከዚህ በኋላ የፀሎት ስነ-ስርዓቱ ሲቀጥል «እስካሁን እንግዲህ የብዙ ዕምነት አባቶችን ታሪክ ሰምታችኋል! እኔ ስለ እምነት ትርጓሜ ላስተምራችሁ አልሞክርም፡፡ ይህን ከእኔ በተሻለ መልኩ በሃይማኖት ላይ ጥናት የሚያደርጉ ፕሮፌሰሮች ሊሰሩት ይችላሉ፡፡ እኔ የመጣሁት እንድታምኑ ላደርጋችሁ ነው» ካለ በኋላ የእራሱን እምነት በእነዚህ ሊታዩ በማይችሉ እውነታዎች ላይ አድርጎ በአድማጮቹ ላይ ለማስረፅ ምትሃታዊ በሆኑና ከልቡ

በሚመነጩ ዓረፍተ ነገሮች ማስተማር ቀጠሉ:: ይህ ሰው ንግግሩ ውጤታማ ሊሆንለት የቻለው ልቡ ከሚሰራው ስራ ጋር አብሮ ስላለና ከውስጡ ባለ እውነተኛ ማንነቱ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው:: «ልቡ ከሚሰራው ስራ ጋር አብሮ ነበር» ሚስጥሩም ይኸው ነው:: ይህም ቢሆን እንዲህ አይነት ምክሮች ብዙ ፈላጊ እንደሌላቸው አውቃለሁ ተማሪዎች ህጎችን መመሪያዎችንና ተጨባጭ የሆኑ ነገሮችን ይፈልጋሉ:: እነዚህን ለማስተማርም ቀላል ነው:: ነገር ግን አንድ ችግር አለባቸው ይኸውም ምንም ፋይዳ የሌላቸው መሆናቸው ነው:: ምክንያቱም በውስጣችሁ ያላችሁን ተፈጥሮአዊና ግብዓታዊ የሆነውን የንግግር ችሎታችሁን ጨምቀው በማውጣት ስለሚስውሩባችሁ ነው:: እኔም በወጣትነቴ እነዚህን ህጎች ለመተግበር ብዙ ሃይል ስላባከንኩኝ በደንብ አውቃቸዋለሁ:: ለዚህም ስል ነው በዚህ መፅሐፍ የማላካታቸው:: ጆሽ ቢሊንግ በአጭር ዓረፍተ ነገር እንደገለፀውም «የማይጠቀሙት ብዙ ነገሮችን ማወቅ ፋይዳ ቢስ ነው::»

## አንደኛ:- በህዝብ ፊት ስትናገሩ እነዚህን ነገሮች ታደርጋላችሁ?

በዚህ ርዕስ ስር ስለተፈጥሮአዊ የንግግር ችሎታ አንዳንድ ባህሪያት ለመነጋገር በመጣር ግልፅና የጠራ ግንዛቤ እንድታገኙ አደርጋለሁ ይህን ሃሳብ ላለመግለፅ ፈልጌ ነበር ምክንያቱም «አሃ! በቃ ቸአሁን እነዚህን ነገሮች ለማድረግ እራሴን ካስገደድኩት በጣም ስኬታማ እሆናለሁ» የሚል ሰው ይኖራልና ነው:: ለዚህ ደግሞ መልሴ አይሆንም የሚል ነው:: ምክንያቱም እራስህን በማስገደድ ልትተገብረው ብትሞክር ንግግርህ ራሱ እንጨት እንጨት የሚልና በማሽን ጉልበት የምትንቀሳቀስ አይነት ሰው ትሆናለህ::

እነዚህን መመሪያ የመሰሉ ነገሮች ሳታስበው ትናንት በንግግርህ ወይም እራት ላይ በጨዋታህ ተጠቅመህባቸው ይሆናል:: ማድረግም ያለብህ ብቸኛው መንገድ ይህ ነው:: እናም ግዴታ ውስጥ እራስህን ሳታስገባ በመለማመድ ንግግርህን ለማብቃት መቻልህ አይቀርም:: አንደኛው ወሳኝ ወይም ጠቃሚ ለሆኑ ቃላት ትኩረት መስጠት እንዲሁም ብዙም ጠቃሚ ያልሆኑትን ለይቶ ማውጣት::

አንዳንድ ጊዜ የተወሰኑ ፊደላትን ጠበቅ እያደረግን ሌሎችን ግን ልክ አንድ መኪና በመደዳ ጎዳና ላይ የተኙ ተዳዳሪዎችን በፍጥነት ሽው ብሎ እንደሚያልፍ አድረገን እናነባቸዋለን:: ለምሳሌ ማሳለ(ቹ)ሴትስ፣ አት (ራክ) ቲቭ፣ ኢን (ቫይ) ሮንሜንት (በቅንፍ ያሉትን ጠበቅ አድረገን የምንጠራቸው ፊደላት ናቸው:: ይህ አዲስ እና እንግዳ ነገር አይደለም እናንተም ትናንት ከመቶ ጊዜ በላይ አድርጋችሁ ይሆናል:: ወይም ደግሞ በቀጣዩ ቀን ታደርጉት ይሆናል:: እስቲ ቀጥሎ ባሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በጉልህ የተፃፉትን ፊደላት ጫን ብላችሁ በፍጥነት አንብቧቸው ሌሎችን ግን እንደወትሮአችሁ አንብቧቸው:: ያለውን ልዩነት ወይም ውጤት ምንድነው?

«ባከናወንኳቸው ማንኛውም ነገሮች ሁሉ ውጤታማ ሆኛለሁ ምክንያቱም ከልቤ ስለፈለኳቸው ነው ከሌሎች ሰዎች የሚላቶፕን አጋጣሚዎች ላለመጠቀም ፍፁም አመንትቼ አላውቅም::» ናፖሊዮን

እንደዚህ ያሉ ዓረፍተ ነገሮችን የማንበቢያ አማራጩ ይህ ብቻ አይደለም። ሌላ ሰው ደግሞ በተለያየ መልኩ ሊያነባቸው ይችላል ስለዚህ ተፅዕኖ እየሰጡ ለማንበብ ምንም ከልካይ የሆነ ህግ የለውም:: እስቲ ቀጣዩን ፅሁፍ ከልብ ሆናችሁ ጮክ እያላችሁ ለማንበብ ሙከራ አድርጉ እናም ጠንካራና ጠጣር ለሆኑት ቃላቶች እንዴት ሳታስቡ ተፅዕኖ ለመስጠት እንደምትገደዱ ተመልከቱ:: «የማጠላወልና ፅኑ የሆነ ውሳኔ ማሳለፍን የመሰለ እጅግ ጠቃሚ የሆነ የህይወት መርህ ያለ አይመስለኝም:: አንድ ወደፊት ትልቅ ሰው ለመሆን የፈለገን ታዳጊ ወይም ህይወቱን ካለፈ በኋላ ስሙን የሚያስጠራ ሥራ ሰርቶ ለማለፍ የፈለገ ሰው አዕምሮውን ማዘጋጀት ያለበት ለሚያጋጥሙት አንድ ሺህ መሰናክሎች ብቻ ሳይሆን ከአንድ ሺህ መሰናክሎች፣ መገፋቶችና ውድቀቶች በኋላ ማሸነፍ እንዳለ በማመን ነው::»

ቴዎዶር ሩዝቬልት

## ሁለተኛው:- የድምፅ ፊንጅህን መቀየር

በምናገርበት ጊዜ ድምፃችን ከፍ ይላል ዝቅ ይላል ወይም ይወጣል ይወርዳል:: ነገር ግን አይቆምም ልክ የባህር ጠለል እንደሚያንቀሳቅሰው ሁሉ ድምፅም እንደዚያው ይሆናል:: ለምን? ማንም ምክንያቱን አያውቀውም፤ ለማወቅም አይጨነቅም:: ምክንያቱም ያለው ውጤት አስደሳችና ተፈጥሯዊ በመሆኑ ነው:: ይህ ነገር በትምህርት የምናገኘው ሳይሆን ልጅ እያለን ጀምሮ አብሮን ሳንፈልገውና ሳንገነዘበው የሚያድግ ነው:: ይኸውም ሆኖ ግን አድማጭ ፊት ለንግግር ስንቀርብ ድምፃችን ቅዝቅዝ ያለ የሚሰለችና አንድ አይነት የመሆን ዕድሉ ሰፊ ነው:: በዚህን ጊዜ ታዲያ እንደተለመደው ቆም ብላችሁ ራሳችሁ «እንዴት ነው የተናገርከው? ሰው ምስል እንጂ! ተፈጥሮህን ተጠቀም» በሉት:: የድምፅህን መውጣትና መውረድ በመጠቀምም የፈለከውን ቃል ልክ ከወንዝ ዳር እንደበቀለ ዛፍ ከሌሎች አጉልተህ ማውጣትና ማሳየት ትችላለህ:: ይህን መንገድ ዝነኛና ታዋቂ የሆኑት እንደ ዶ/ር ፓረክስ፣ ሰር ኦሊቨር ሎጅ፣ ሩዝቬልትና ብሪያንን የመሳሰሉ ሰዎች ተጠቅመውበታል::

ቀጥሎ ያሉትን ከስር የተሰመረባቸውን ቃላት ከሌሎች በተለየ መንገድ ዝግ ብለህ እያነበብክ ጥራቸው! ውጤቱ ምንድነው?

«የትምህርት ታላቁ አላማው እውነት ሳይሆን ተግባር ነው»

ኸርበርት ስፔንሰር

«ለሰማንያ ስድስት ዓመታት በህይወት ስቆይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወንዶች ወደ ስኬት ጫፍ ሲወጡ አይቻለሁ፡ እናም ለስኬት ሊበቁ ከቻሉባቸው ብዙ ነገሮች ውስጥ እጅግ በጣም ጠቃሚው ታማኝነት ነው::»

\- ካርዲናል ጊብንስ

«ችሎታዬ አንድና አንድ ብቻ ነው ይኸውም ፍፁም ተስፋ ያለመቁረጥ ነው»

ማርሻል ፎክ

**ሦስተኛ፡- የንግግርህን ፍጥነት ቀያይረው**

አንድ ትንሽ ልጅ ሲናገር ስትሰሙትም ሆነ እናንተ ራሳችሁ ሳትጨነቁ ዘና በማለት ስትጨዋወቱ የንግግራችሁ ፍጥነት ወይ ይጨምራል ወይም ደግሞ ይቀንሳል:: ይህ ንግግር የሚያሳምር ተፈጥሮአዊ ነገር ነው:: ከእኛ ግንዛቤ ውጭ ነው፣ እንዲሁም ንግግራችን ጎልቶ እንዲወጣ በማድረጉም የፈለግነውን ሃሳብ በተለየ ሁኔታ ለማስገንዘብ የሚረዳ ዘዴ ነው:: ዋልተር ቢ ስቲቨንስ በሊንከን ዙርያ በዓፈውና ለሚዞር የታሪክ ማህበር በሰጠው ሪፖርት ላይ ይህ ዘዴ ሊንከን በጣም የሚመርጠው እንደነበር ገልጿል:: በንግግሩ ብዙ ቃላቶችን በፍጥነት ሲናገር ይቆይና አፅንኦት ሰጥቶ ማስረዳት የሚፈልገው ቃል ወይም ሃረግ ላይ ሲደርስ ድምጹን ጎተት አድርጎና ጫን ብሎ ይጠራዋል:: ከዚያ ወደ መደምደሚያው በፍጥነት ይገባል:: በዚያው ልክ ግን ብዙም ጠቃሚ ያልሆኑትን ቃላቶች ጊዜ ሳይሰጥ ያልፋቸዋል::

ይህን በምሳሌ እንመለከተው «30 ሚሊዮን ዶላር» ሚለውን በፍጥነት ልክ ምንም እርባና የሌለው ነገር አድርጋችሁ ጥሩት:: ቀጥሎ ደግሞ ዝግ ብላችሁ ስሜት በሚሰጥ መልኩ ልክ በገንዘቡ ብዛት እንደተደነቃችሁ በማድረግ «30 ሺህ ዶላር» ብላችሁ ጥሩ:: ታዲያ በዚህ መልኩ 30 ሺህ ዶላር ከ30 ሚሊዮኑ እንዲበልጥ አላረጋችሁትም?

**አራተኛ፡- ጠቃሚ የሆነውን ሃሳብ ቢትጀምሩ ስትሉ እንዲሁም ገለፃችሁ ስታበቁ ቆም በሉ**

ሊንከን አዘውትሮ በንግግሩ መካከል ልክ አድማጩ ልብ ውስጥ ጠልቆ እንዲገባ የሚፈልገውን ሃሳብ ላይ ሲደርስ ወደፊት ዘንበል ብሎ አይን አይናቸውን ትክ ብሎ እያየ የተወሰነ ጊዜ ዝም ብሎ ይቆያል ይህ ድንገተኛ ፀጥታውም ከድንገተኛ ጩኸት ያልተናነሰ ተፅዕኖ ነበረው:: የሰውን ትኩረትም እጅግ ይስባል:: ሁሉም አድማጭ በጉጉት፣ በንቃትና በትኩረት ቀጥሎ የሚናገረውን ነገር እንዲጠብቅ ያደርገዋል:: ለምሳሌ ከዳግላስ ጋር ለምርጫ ባደረገው ክርክር ሁሉም ነገር ወደ ፍፃሜው ሲቃረብና ሁሉም ምልክቶች እሱ መሸነፉን እያሳዩ ሲመጡ በክፉኛ ድብርት ተዋጠ ከድሮ ጀምሮ ያለበት የሃዘን ድባብ አጠላበት:: ልክ ወደ ማጠቃለያው ሲደርስ ድንገት ቆም አለ:: በፀጥታ በዙሪያው የተሰበሰቡ ከፊል የወዳጅነት መንፈስ ያላቸው ከፊሉ ደግሞ ምንም ዓይነት ስሜት የማታይባቸውን ሰዎች በጎድጓዳና የሃዘን ስሜት እንዲሁም እንባ ያዘሉ በሚመስሉት ዓይኖቹ እያየ ዝም አለ:: ከዚያ እጆቹን በዚህ ዋጋ የለሽ ትግል እንደተሸነፉ ሁሉ እጥፍጥፍ አድርጎ ለየት ያለ ቃና ባለው ድምፅ እንዲህ አለ፡-

«ወዳጆች የእኔም ሆነ የዳኛ ዳግላስ ለፕሬዝዳንትነት መመረጥ ያን ያህል የጎላ ልዩነት የለውም:: በመሃከላችንም ያለው እጅግ ጠባብ የሆነች የሃሣብ አለመስማማት ነች:: ነገር ግን ዛሬ ለእናንተ የምንነግራችሁ የሁለታችንም አጀንዳ ከግል ፍላጎቶቻችንና ፖለቲካዊ ድል ከማግኘት በላይ የሆነና እጅግ ውድ ዋጋ ያለው ነጥብ ነው:: እናም ክቡራን. . . .»» ካለ በኋላ ጸጥ አለ:: አድማጩም በጉጉት እያንዳንዷን ቃል እየተከታተለ እንደሆነ አስተዋለ:: ከዚያ «« ይህ አጀንዳችን የእኔና የዳግላስ ደካማ፣ የሚንተባተቡና ምስኪን የሆኑ ምላሶች



Scanned with CamScanner

በዝምታ ተሸብበው ወደ መቃብር ከወረዱ በኋላ እንኳን የሚያብብና ዘላለም ኗሪ ነው በማለት ጨረሰ፡፡

የእሱን ታሪክ ከጻፉት ሰዎች መካከል አንዱ እንደገለጸው «እነዚህን ቀላል የሆኑ ቃላት የተናገረበት ልዩ የሆነ ዘይቤ የእያንዳንዱን ሰው ልብ ዘለቀው እንደገቡና እንዲቀመጡ አስችሎታል» ብሏል፡፡

ሰር አለቪር ሎጅም አፅንኦት ሲሰጣቸው የሚፈልጋቸው ሃሳቦች ላይ ሲደርስንና ተናግሮም ሲጨርስ የተወሰነ ጊዜን በዝምታ ማሳለፍን ያዘወትር ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንዳውም በአንድ ዓረፍተ ነገር ላይ ለሶስትና ለአራት ጊዜያት ያህል ቆም ይል፡፡ ነበር ይህን ነገር ግን ሆን ብሎ የሚከታተለው ሰው ካልሆነ በስተቀር ማንም አያውቅበትም ነበር፡፡

ኪፕሊንግ፡- «በዝምታ ውስጥ ያለ ንግግር» ብሎ ይጠራው ነበር ዝምታን በንግግራችን ውስጥ አስፈላጊ በሆነው ቦታ ላይ ስንጠቀምበት እውነትም ወርቅ ይሆናል፡፡ ታዲያ ይህ ዝምታ ታላቅ ሃይል ያለው የንግግር መሳሪያ መሆኑን ልንዘነጋው የማይገባ ነጥብ ቢሆንም ብዙ ጀማሪ ተናጋሪዎች ልብ አይሉትም፡፡

ቀጥሎ ያለውን የሆልማን ንግግር የወሰድኩት በንግግራችን ወቅት ምን አይነት ቦታ ላይ በዝምታ ቆም ልንል እንደምንችል ለማሳየት ቢሆንም ያለው አማራጭ ይሄ ብቻ ነው ለማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የት ቦታ ላይ መቆም እንዳለብን በህግ ልንመራ ስለማይገባ ነው፡፡

ይሄ በቀላሉ የስሜትን ትርጉም አውጥቶ የማሳያ መንገድ ነው፡፡ ዛሬ በንግግራችን ላይ ዝም ያልንበትን ቦታ ነገ በምናደርገው ተመሳሳይ የሆነ ንግግር ላይ መቀየር እንችላለን፡፡ ቀጥሎ ያለውን ፅሁፍ ያለምንም ማቋረጥና ዝምታ ጮክ ብላችሁ አንብቡት፡፡ ከዚያ ደግሞ በምልክቶቹ በመመራት ቆም ማለት ሲያስፈልግ እንደዚያው እያደረጋችሁ አንብቡት፡፡

በዝምታ ቆም እያደረጋችሁ ስታነቡት ምን ውጤት አገኛችሁ?

««እቃዎችን ማሻሻጥ ማለት ጦርነት ማለት ነው፡፡ (ቆም ብላችሁ ጦርነት የሚለው ቃል እንዲታወስ አድርጉ) «ጦረኞች የሆኑት ብቻ የሚያሸንፉበትም አውድማ ነው፡፡ (ቆም በሉ) «ይህን አይነቱን ሂደት ለመቀየርም ሆነ ለማስተካከል አንችልም፡፡ (ቆም) «ወደዚህ የሽያጭ ውጊያ ስትገቡ ጀግንነታችሁ አብሯችሁ መሆን ይኖርበታል፡፡» (ቆም) «ካልሆነ ግን» (ቆም እዚህጋ ረዘም ይበል) «በስነዘራችሁት እያንዳንዱ ጥቃት የምታገኙት ውጤት ከዚያ እንቁላል የማይሻል ይሆናል፡፡» (ቆም) «በቤዝ ቦል ጨዋታ ኳሷን የሚቀበለው ሰው ወይም ተጫዋች የሚወረውረውን ሰው የሚፈራ ከሆነ» (ቆም) «መቼም አያሸንፍም፤ ይህን ነገርም በደንብ አስታውሱ፡፡» (ቆም) «በድፍረት ኳሷን በማጓን ከአጥሩ ውጭ የሚያወጣት ግን የጨዋታውን ህግ በመጠቀም ሜዳውን ሁሉ በማካለል ወደፍጻሜው» (እዚህ ጋር ስለ ጎበዙ ተጫዋች በደንብ እንዲያስቡ ረዘም ያለ ጊዜ ቆዩ) «ምህረት በሌለው ድፍረትና ውሣኔ በሙሉ ልቡ ሆኖ ይገባል፡፡»

የሚከተሉትን ጥቅሶች ጮክ እያላችሁ በማንበብና ድምጽ በመስጠት እየጠራችሁ የት ቦታ ላይ ዝም እንደምትሉ ለማወቅ ሞክሩ፡፡

- ትልቁ የአሜሪካን በረሃ የሚገኘው በኢንዳሆ:- በኒውሜክሲኮ ወይም አሪዞና አይደለም:: በመካከለኛ ዕድሜ ላይ በሚገኙ ወንዶች ኮፍያ ስር እንጂ! ይህ ታላቅ የሆነ የአሜሪካን በረሃ የጭንቅላት በረሃማነት እንጂ ቁስ አካላዊው በረሃ አይደለም::

ጄ . ኤስ. ኖክስ

- ለሰው ልጅ ጠቅላላ ችግር መፍትሄ የሚሆን አንድም ነገር የለም:: ለመፍትሄው ቅርብ የሆነው ነገር ቢኖር በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይፋ ማድረግ ብቻ ነው::

ፕሮፌሰር ፎክስዌል

- ሁለት በጣም ደስታ የሚሰጡኝ ነገሮች ጋር ፊልድና ጠፈር ናቸው:: ከጋር ፊልድ ጋር እዚህ ምድር ላይ በደንብ መኖር አለብኝ:: ከፈጣሪዬ ጋር ደግሞ በዚያኛው ህይወቴ ላይ አገኘዋለሁ::

ጀምስ . ኤ. . ጋር ፊልድ

ማንኛውም ንግግር የሚያደርግ ሰው እነዚህን መመሪያዎች ተጠቅሞ እንኳን ለስህተት ሊጋለጥ ይችላል:: ድምጹ የማያስደስት፣ ሰዋሰውን ያልጠበቀ፣ ጉጉት ያለና በንዴት የሚናገር ሰው ሊመስልም ይችላል:: የአንድ ሰው ተፈጥሮዊ የንግግር ዘይቤው ብዙ ማሻሻያዎች ሊያስፈልገው ይችላል:: እናም ይህን ተፈጥሮአዊ የሆነ የንግግር ዘይቤ ከሰዎች ጋር በመጫወት ካዳበርነው በኋላ ወደ መድረክ ይዘን ብንወጣ ተጠቃሚ ያደርገናል::

# ክፍል ሰባት

## የመድረክ ስቀራረብና የግል ስብዕና

የካርኒጌ ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ተቋም በአንድ ወቅት መቶ ለሚሆኑ በንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ወንዶች የዕውቀት ደረጃቸውን የሚፈትሽ መጠይቅ አድርጎ ነበር:: ይህ አይነቱ መጠይቅ በጦርነት ወቅት ሰጦር አባሎች ከሚሰጠው ጋር ተመሳሳይ ነው:: እናም ተቋሙ ባወጣው ውጤት መሰረት የግል ስብዕናችን ከከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ በተሻለ መልኩ ለስራችን ስኬት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ደርሶበታል::

ይህ መረጃ ለንግድ ማህበረሰቡ በጣም ወሳኝ እንደሆነ ሁሉ በማስተማር ስራ ለተሰማሩ፣ ሙያ ነክ ሥራ ለሚሰሩ እንዲሁም ንግግር ለሚያደርጉ ሰዎች እጅግ ወሳኝ የሆነ ነጥብ ነው:: እንዲያውም ቅድመ ዝግጅት ከማድረግ በስተቀር ሌላ እጅግ ወሳኝ የሆነ ነገር ቢኖር የግል ስብዕና ነው:: ኸርበረት ኩባርድ እንዳለው እንደበተ ርቱዕ ሆነን በምንናገር ጊዜ አሸናፊ የሚያደርጉን ቃላቶቹ እንዳሰው እንደበተ ርቱዕ ሆነን በምንናገር ጊዜ አሸናፊ የሚያደርጉን ቃላቶቹ

ወይም ሃሳብ ጥሩ ውጤት ያመጣልናል ነገር ግን ባህርይ ስንል በጣም ሰፊ እንዲሁም ውስብስብ የሆነ ነገር ነው:: ይህ የአንድ ሰው አካላዊ፣ መንፈሳዊ፣ አእምሮዊ፣ የሚኖረን ፀባይ፣ ያደረግነው ልምምድ፣ የአስተሳሰባችን አድማስ፣ የህይወት ልምዳችን ስልጠና እንዲሁም አጠቃላይ የህይወት ተሞክሮአችንን አጠቃሎ የያዘ ነገር ነው:: ልክ የአንስታይንን የአንፃራዊነት ንድፈ ሃሳብ የመሰለ ነገር ሲሆን ለመገንዘብ የምንበቃው ትንሹን ክፍል ብቻ ነው::

የግል ባህሪ በተፈጥሮ የምናገኘው እንዲሁም በዙሪያችን ባሉ ነገሮች የሚወሰን በመሆኑ ለመለወጥና ለማሻሻል እጅግ አስቸጋሪ ነው:: ይሁን እንጂ ጠለቅ ያለ ትምህርት በመውሰድ ልናዳብረውና የተሻለ ኃይል ያለው ሰውን እንዲሁም የሚስብ ማድረግ እንደሚቻል መዘንጋት የለብንም::

ይህን ተፈጥሮ የለገሰችንን አስገራሚ የሆነ ስጦታ ምርጥ የሆነውን ነገር አውጥተን ለመጠቀም በማንኛውም መልኩ መጣር ይገባናል:: ይህ ርዕስ በጣም ጠቃሚ በመሆኑ ለመሻሻል ያለን ዕድልም ለውይይትና ለምርምር በሚጋብዝ መልኩ ውስን የሆነ ነው::

የግል ብቃትህን አውጥተህ ለመጠቀም እንድትችል በድካም ስሜት ውስጥ ሆነህ ወደ ህዝብ አትውጣ:: ምክንያቱም የድካም ስሜት ያለው ተናገሪ መስህብ ያለውና ማራኪ ሊሆን አይችልምና ነው:: ዝግጅትህንና ዕቅድ ማውጣትን ብዙ ሰዎች ባለማወቅም ሆነ በቸልታ እንደሚያደርጉት ሁሉ አንተም ቀኑ ሲቃረብ በጥድፊያና በችኮላ አታድርገው:: ይህን ማድረግህ በአካልና በአእምሮህ ላይ ከባድ የሆነ ድካምና መዛል በማስከተል አእምሮህን በመመረዝ፣ ጎታታ እንድትሆን በማድረግና ወኔህን በመስለብ ደካማ እንድትሆን ያደርግሃል:: ስለዚህ በተለይ ወሳኝ የሆነ ንግግር በ10 ሰዓት ገደማ የምታደርግ ከሆነ ቀለል ያለ ምሳ ተመግበህ ከተቻለ ደግሞ ትንሽ በማሸለብ ለአካልህም ሆነ ለአእምሮህ አስፈላጊ የሆነውን

አረፍት መውሰድ ይገባሃል:: ንግግር በምታደርግበት ወቅት የረሃብ ስሜት እንዳይኖርህ ብቻ በመጠኑ ልክ እንደባህታዊ ተመገብ::

ሄነሪ ዋርድ ቤከር ለክሰዓት ትምህርቱ እንዲመቸው ጠዋት ወደ አምስት ሰዓት ላይ ወተትና ደረቅ ብስኩት ብቻ ይመገብ ነበር:: ማዳም ሜልባ የተባለችው ድምፃዊት ደግሞ «ምሽት ላይ የሙዚቃ ትርዒት ሲኖርብኝ ወደ አስራ አንድ ሰዓት ገደማ የዓሣ፣ የዶሮ ሾርባ እጠጣለሁ ወይም ጣፋጭ ዳቦ በትንሹ ብቻ እመገባለሁ:: ማታ ከትርዒቱ በኋላ እቤት ስደርስ በጣም ተርቤ ነው» ትላለች::

ይህንን ንግግር ተናግሬ ባበቃሁበት ሰዓት በምሽት ፕሮግራም ለማቀርበው ንግግር እራቴን በብዛት ተመግቤ ችግር ሳይገጥመኝ በፊት አልገነዘበውም ነበር:: በዚያን ዕለት የሥጋ ጥብስ፣ ሰላጣ፣ አትክልት፣ ድንች፣ ጥብስ ከዚያም በላዩ ላይ ክሬም ኬክ አክዬበት ለንግግር መቅረቤ ለያዝኩት አጀንዳም ሆነ ለሰውነቴ ጠቃሚ የሆነ ነገር እንደሆነልኝ ሊያስገነዝበኝ ችሏል:: ምክንያቱም ወደ አእምሮዬ መሄድ የነበረበት ከየደም ዑደቴ ጋር ያንን የድንችና የሥጋ ጥብስ እንዲፈጭ ለማገዝ በትግል ላይ ነበርና ነው::

አንድ ተናጋሪ ከሌላው በተለየ መልኩ ለምን ትኩረት ያገኛል? ያለህን የንግግር አቅም የሚጨቁኑ ማናቸውንም ነገሮች ከማድረግ ተቆጠብ:: ይህ አቅም መስህብ ያለው፣ ታላቅ ጥቅም የሚሰጥህ፣ በህይወት የተሞላና ሃሳብህን በጥሩ ሁኔታ እንድትገልጽ የሚያደርግህ ነው:: እኔም የንግግር ተማሪዎችንና አስተማሪዎችን በምመለምላቸው ጊዜ እንደ ዋነኛ መስፈርት የማስቀምጥላቸው ነገር ነው:: ብዙ ሰዎችም በእንዲህ አይነቱ ኃይል የተሞላ ተናጋሪ ዙሪያ ልክ በመኸር ወቅት በተሰበሰበ ስንዴ ዙሪያ እንደሚከማቹ ዝዬዎች የሚሰበሰቡበት ምክንያትም ይህ ነው::

ይህ ነገር እውነት መሆኑን ለንደን በሚገኘው ሃይድ ፓርክ በሚባለው ቦታ ላይ አይቻለሁ:: እዚህ ሃይድ ፓርክ ማንኛውም መናገር የፈለገ ሰው ንግግር ሊያደርግ የሚችልበት ቦታ ነው:: ከእምነ በረድ በታነፀው የመግቢያ በር ፊት ለፊት ዘርና ቀለም ሳይለይ ማንም ሊናገርበት የሚችል መድረክ ተገንብቷል:: እሁድ ከሰዓት ላይ በሚደረገው በዚህ ንግግር ላይ የካቶሊክ ፓፑ የሚሰጠው ትምህርትና መመሪያ እንከን የለሽና ድንቅ መሆኑን ከሚናገር ሰው ጀምሮ፣ የካርል ማርክስን የኢኮኖሚ ንድፈ ሃሳብ ደግፎ፣ እስከሚናገረው ሶሻሊስት፣ እንዲሁም የነብዩ መሃመድ ተከታይ የሆነ ሰው ከአንድ ሚስት በላይ ማግባቱ ለምን አስፈላጊና ተገቢ እንደሆነ ከሚናገር ፓኪስታናዊ ድረስ ልዩ ልዩ ሃሳቦችን መርጠን ማዳመጥ እንችላለን::

ታዲያ በዚህን ወቅት አንዱ ተናጋሪ እጅግ ብዙ አድማጭ ሲያገኝ ከጎኑ የሚናገረው ሌላ ሰው ግን መቶ የማይሞላ ሰው ብቻ ለምን ሊያዳምጠው ቻለ? የመረጡት ርዕስ በመሃከላቸው ያለውን አድማጭ የመሳብ ልዩነት ሊፈጥር ስለቻለ ነው? አይደለም! ይህን ልዩነት ያመጣው ነገር ያው በራሱ በተናጋሪው ውስጥ የሚገኝ ነው:: ለሚናገረው ነገር በጣም ፍላጎት ካለው በዚያው ልክ አድማጩም እንዲከታተለው ያደርገዋል:: ህይወት ባለው መንፈስ መናገሩ ወኔውንና ሞራሉን በማነቃቃት በከፍተኛ ኃይል ተሞልቶ እንዲናገር ስለሚያደርገው እንድናዳምጠው ያስገድደናል::

## አለባበስ እንዴት ተፅዕኖ ያደርግብናል?

ከአንድ የስነ ልቦና ባለሙያ የሆነ የዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ስለሰዎች የአለባበስ ሁኔታና ምን አይነት ተፅዕኖ እንደሚፈጥርባቸው በርከት ላሉ ሰዎች በደንብ ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸው ነበር:: ሁሉም ባንድ ድምፅ የመሰከሩት ነገር ሲገልፁት የማይችሉት ስሜት ሽክ ብለውና አምረው በወጡ ጊዜ የሆነ ብቻ ግልፅና የሚያነቁቃቸው እንደሚሰማቸውና ያንንም ስሜት በመገንዘባቸው መተማመናቸው ስለሚጨምርም መንፈስ እንደሚያላብሳቸው ገልጸዋል:: በራስ ይላል:: አክብሮትም እንዲኖራቸው ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከፍ ያስችላቸዋል::

ይህ አለባበሳቸውም የተሳካለት ሰው አይነት ያደረጋቸው ሲሆን አስተሳሰባቸውንም ለስኬት የቀረበ እንዲሆን ያደርገናል ብለዋል:: ይህ አለባበስ በራሱ በለባሹ ሰው ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ይገልጽልናል::

## በአድማጩ ዘንድ አለባበሳችን የሚኖረው ተፅዕኖ

ብዙ ጊዜ እንዳስተዋልኩት ተናጋሪው ሰው የለበሰው ሰፊ ሱሪ ኮት እንዲሁም ጫማው የሰፋው ከሆነ፣ የገነፈለ ብዕርና እርሳስ ከደረት ኪሱ የሚታይበት፣ ጋዜጣ ወይም የሲጋራ ፓኮ በጎን ኪሱ ተሸጉጦ የሚታይ፣ ተናጋሪዋ ሴት ከሆነችም በጣም ትልቅ መልኩ ደስ የማይል ቦርሳ አንጠልጥላ፣ የቀሚሷ ቅድ ከፊት ሰውነቷን አጋልጦ የሚያሳያት ከሆነ ለእንደዚህ ዓይነቱ ነገሮች አድማጩ ትኩረት ስለሚሰጥ ለሰዎቹም የሚኖረው ክብር በጣም አናሳ እንዲሆን ያደርጉታል:: እንዲህ አይነት ነገር በቀጥታ አስተሳሰባችንንም ሆነ ንግግራችንን ልክ እንዳልተበጠረው ፀጉራችን፣ እንደሰፊውና እንዳልተወለወለው ጫማችን፣ እንደ አስጠሊታው ቦርሳችን ሁሉ በዘፈቀደ ሳንዘጋጅና ሳንጠነቀቅ ለማቅረብ የመጣን ያስመስልብናል::

## የግራንት ፀፀት

ጄኔራል ሊ ወደ አፓማቶክስ ፍ/ቤት ሰራዊቱን ለማስረከብ ሲመጣ በአዲስ ዩኒፎርም ተውቦ፣ ከጎኑ ደግሞ ውድ የሆነውን ሻምላ ሻጥ አድርጎ ነበር:: ግራንት ግን ከላይ ኮት ለመደረብም ሆነ ሻምላ ለመያዝ ሳይጨነቅ በተራ ወታደር ሸሚዝ ነበር የቀረበው:: በማስታወሻዉ ላይ እንደጻፈውም «ስድስት ጫማ የሚረዝም በማራኪ ሁኔታ ከለበሰና ሻምላ ከታጠቀ ሰው አጠገብ መቆሜ በተገራሪ ሁኔታ ለመቅረብ የፈለኩ አስመስሎብኝ ነበር»:: በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ ላይ ሙሉ ተገቢ በሆነ ሁኔታ አለባበሱን አሳምሮ አለመገኘቱ ግራንትን በህይወቱ በቁጭት እንዲንገበገብ አድርጎታል::

ዋሽንግተን የሚገኘው የግብርና ቢሮ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የንብ ቀፎዎችን በምርምር ጣቢያው ውስጥ ያገኛል:: እያንዳንዱ ቀፎ አጉልቶ የሚያሳይ መስታወት የተገጠመለት ሲሆን ውስጡን በደንብ ለማየት የሚያስችል መብራት አለው:: ስለዚህ በቀንም ሆነ በማታ ንቦቹን በደንብ ለማየትና የሚያደርጉትን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ይቻላል::

አንድ ንግግር አቅራቢም እንደዚሁ አጉልቶ በሚያሳይ መስታወት ስር ነው፤ በመብራት ውስጥም ሆኖ ሁሉም አይኖች ያዩታል:: በአለባበሱ ላይ ያለች ትንሽ እንከንም በተራራ ላይ እንዳለች ነጭ በረዶ ጎልቶ ይወጣበታል::

ንግግር ሳንጀምር እንኳን ለትችትም ሆነ ለድጋፍ የተጋለጥን ነን:: ከብዙ ዓመታት በፊት በኒውዮርክ ስለሚኖር አንድ የባንክ ሰራተኛ የህይወት ታሪክ ለአንድ መፅሔት እፅፍ ነበር:: ጥቂት ጓደኞቹንም የስኬታማነቱን ሚስጥር እንዲነግሩኝ እጠይቃቸው በነበረ ጊዜ አንዱ ጓደኛው ለዚህ ስኬቱ የጎላውን ድርሻ የሚወስደው ፈገግታ የተላበሰ አቀራረቡ መሆኑን ሳያመነታ ነገረኝ:: በመጀመሪያ ላይ የተጋነነ አስተያየት አድርጌ ወስጄው ነበር:: በኋላ ላይ ግን ብዙዎቹ ይህን ነገር ስላረጋገጡልኝ ለማመን ተገድጀያለሁ:: ሌሎች በርከት ያሉት የስራ ባልደረቦቹ ከእሱ የተሻለ የሥራ ልምድና ስለገንዘብ ዝውውር እውቀቱ ቢኖራቸውም እሱ በተጨማሪነት ያለው ይህ ማራኪ ብቃቱ ግን አልነበራቸውም:: ሞቅ ባለ ፈገግታ ተሞልቶ ደንበኞቹን መቀበሉም የማንኛውንም ሠው አመኔታ በቶሎ እንዲያገኝና ስራውን እንዲያስፈጽም ይረዳው ነበር:: እሺታንም ወዲያው ነበር የሚያገኘው:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው ለስኬት ሲበቃ ማየት ሁላችንም የምንፈልገው ነገር ይመስለኛል::

ቻይናዎች ሲተርቱ «ፈገግታ የሌለው ሰው ሱቅ አይክፈት» ይላሉ ታዲያ ፈገግታ ለአንድ የሽያጭ ሰራተኛ የሚያስፈልገውን ያህል ንግግር ለማድረግ ወደ አድማጭ ዘንድ ስንቀርብስ አያስፈልግም ትላለህ? ይህ አንድ ነገርን አስታወሰኝ:: የብሮክሊን ንግድ ምክር ቤት ህዝብ ፊት መናገርን በተመለከተ በሰጠው አንድ ኮርስ ላይ ተሳታፊ ነበርኩ:: በዚህ ትምህርት ላይ አንድ ለየት ያለ ወጣት ነበር:: ሁል ጊዜም አድማጭ ፊት የሚቀርበው እዚያ በመሆኑ ብቻ እጅግ ደስተኛ እንደሆነ በሚገልፅ ስሜት ነበር:: ሁልጊዜም ፈገግታ የማይለየው በመሆኑና ዘወትር እኛን በማየቱ ደስ የሚል ስሜት እንደተሰማው በሚያሳይ ስሜት ውስጥ በመሆኑ አድማጮቹ ያለምንም ማንገራገር ነበር ወዲያውኑ ሞቅ ያለ አቀባበል የሚያደርጉለት::

በሌላ መልኩ ደግሞ ቅዝቅዝ ባለና የማይስማማውን ሥራ የግብር ይውጣ እንደሚሰራ ሰው ሆኖ የሚቀርብና ተናግሮ ሲጨርስም አምላኩን የሚያመሰግን ተናጋሪም አጋጥሞኛል:: የዚህ አይነቱ ተናጋሪ ሰው መንፈስ ወደ እኛ (አድማጮቹም ላይ ስለሚጋባ እሱ ተናግሮ ሲጨርስ እኛም ማመስገናችን አይቀርም:: ፕሮፌሰር ኦቨር «የሰዎች ባህሪ ላይ ተፅዕኖ ስለመፍጠር» በሚል ፅሁፋቸው እንደገለጹት «ማንም የተመኘውን ያገኛል:: እኛ አድማጮቻችንን ከወደድናቸው እነሱም እኛን እንዲወዱን ለማድረግ ያለን ዕድል እጅግ ከፍተኛ ነው:: በዝናው አንፃርም ግንባራችንን አጨፍግገን ወደ አድማጭ አቅርበን በአድማጩ ዘንድ በግልፅ የሚታይም ሆነ የማይታይ ተመሳሳይ ስሜት እንዲፈጠር የማድረግ እድላችን ሰፊ ነው:: በድንጋጤና ግራ በተጋባ ሁኔታም ለንግግር ስንቀርብ አድማጫችን በእኛ እምነት እንዲያጣ እናደርገዋለን:: ከዚህ በተለየ ደግሞ በጣም አይን አውጣ ሆነንና ለአድማጩ ክብር ሳንሰጥ ስንቀርብም አድማጩ እራሱን ከማስነዘር በሚመነጭ ስሜት ምላሽ እንዲሰጠን እናስገድደዋለን::

# አለባበስ እንዴት ተፅዕኖ ያደርግብናል?

ከአንድ የስነ ልቦና ባለሙያ የሆነ የዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ስለሰዎች የአለባበስ ሁኔታና ምን አይነት ተፅዕኖ እንደሚፈጥርባቸው በርከት ላሉ ሰዎች ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸው ነበር፡፡ ሁሉም ባንድ ድምፅ የመሰከሩት ነገር በደንብ ሽክ ብለውና አምረው በወጡ ጊዜ የሆነ ሊገልፁት የማይችሉት ስሜት እንደሚሰማቸውና ያንንም ስሜት በመገንዘባቸው ብቻ ግልፅና የሚያነቁቃቸው መንፈስ እንደሚያላብሳቸው ገልጸዋል፡፡ በራስ መተማመናቸው ስለሚጨምርም ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከፍ ይላል፡፡ አክብሮትም እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል፡፡

ይህ አለባበሳቸውም የተሳካለት ሰው አይነት ያደረጋቸው ሲሆን አስተሳሰባቸውንም ለስኬት የቀረበ እንዲሆን ያደርገናል ብለዋል፡፡ ይህ አለባበስ በራሱ በለባሹ ሰው ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ይገልጽልናል፡፡

## በአድማጩ ዘንድ አለባበሳችን የሚኖረው ተፅዕኖ

ብዙ ጊዜ እንዳስተዋልኩት ተናጋሪው ሰው የለበሰው ሰፊ ሱሪ ኮት እንዲሁም ጫማው የሰፋው ከሆነ፣ የገነፈለ ብዕርና እርሳስ ከደረት ኪሱ የሚታይ፣ የሚታይበት፣ ጋዜጣ ወይም የሲጋራ ፓኮ በጎን ኪሱ ተሸጉጦ የሚታይበት፣ ተናጋሪዋ ሴት ከሆነችም በጣም ትልቅ መልኩ ደስ የማይል ቦርሳ አንጠልጥላ፣ የቀሚሷ ቅድ ከፊት ሰውነቷን አጋልጦ የሚያሳያት ከሆነ ለእንደዚህ ዓይነቱ ነገሮች አድማጩ ትኩረት ስለሚሰጥ ለሰዎቹም የሚኖረው ክብር በጣም አናሳ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡ እንዲህ አይነት ነገር በቀጥታ አስተሳሰባችንንም ሆነ ንግግራችንን ልክ እንዳልተበጠረው ፀጉራችን፣ እንደሰፊውና እንዳልተወለወለው ጫማችን፣ እንደ አስጠሊታው ቦርሳችን ሁሉ በዘፈቀደ ሳንዘጋጅና ሳንጠነቀቅ ለማቅረብ የመጣን ያስመስልብናል፡፡

## የግራንት ፀፀት

ጄኔራል ሊ ወደ አፖማቶክስ ፍ/ቤት ሰራዊቱን ለማስረከብ ሲመጣ በአዲስ ዩኒፎርም ተውቦ፣ ከጎኑ ደግሞ ውድ የሆነውን ሻሞላ ሻጥ አድርጎ ነበር፡፡ ግራንት ግን ከላይ ኮት ለመደረብም ሆነ ሻሞላ ለመያዝ ሳይጨነቅ በተራ ወታደር ሸሚዝ ነበር የቀረበው፡፡ በማስታወሻዉ ላይ እንደጻፈውም «ስድስት ጫማ የሚረዝም በማራኪ ሁኔታ ከለበሰና ሻሞላ ከታጠቀ ሰው አጠገብ መቆሜ በተፃራሪ ሁኔታ ለመቅረብ የፈለኩ አስመስሎብኝ ነበር»፡፡ በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ ላይ ተገቢ በሆነ ሁኔታ አለባበሱን አሳምሮ አለመገኘቱ ግራንትን በህይወቱ ሙሉ በቁጭት እንዲንገበገብ አድርጎታል፡፡

ዋሽንግተን የሚገኘው የግብርና ቢሮ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የንብ ቀፎዎችን በምርምር ጣቢያው ውስጥ ያገኛል፡፡ እያንዳንዱ ቀፎ አጉልቶ የሚያሳይ መስታወት የተገጠመለት ሲሆን ውስጡን በደንብ ለማየት የሚያስችል መብራት አለው፡፡ ስለዚህ በቀንም ሆነ በማታ ንቦቹን በደንብ ለማየትና የሚያደርጉትን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ይቻላል፡፡

አንድ ንግግር አቅራቢም እንደዚሁ አጉልቶ በሚያሳይ መስታወት ስር ነው፤ በመብራት ውስጥም ሆኖ ሁሉም አይኖች ያዩታል:: በአለባበሱ ላይ ያለች ትንሽ እንከንም በተራራ ላይ እንዳለች ነጭ በሬዶ ጎልቶ ይወጣበታል::

ንግግር ሳንጀምር እንኳን ለትችትም ሆነ ለድጋፍ የተጋለጥን ነን:: ከብዙ ዓመታት በፊት በኒውዮርክ ስለሚኖር አንድ የባንክ ሰራተኛ የህይወት ታሪክ ለአንድ መፅሔት እፅፍ ነበር:: ጥቂት ጓደኞቹንም የስኬታማነቱን ሚስጥር እንዲነግሩኝ እጠይቃቸው በነበረ ጊዜ አንዱ ጓደኛው ለዚህ ስኬቱ የጎላውን ድርሻ የሚወስደው ፈገግታ የተላበሰ አቀራረቡ መሆኑን ሳያመነታ ነገረኝ:: በመጀመሪያ ላይ የተጋነነ አስተያየት አድርጌ ወስጄው ነበር:: በኋላ ላይ ግን ብዙዎቹ ይህን ነገር ስላረጋገጡልኝ ለማመን ተገድጃያለሁ:: ሌሎች በርከት ያሉት የስራ ባልደረቦቹ ከእሱ የተሻለ የሥራ ልምድና ስለገንዘብ ዝውውር እውቀቱ ቢኖራቸውም እሱ በተጨማሪነት ያለው ይህ ማራኪ ብቃቱ ግን አልነበራቸውም:: ሞቅ ባለ ፈገግታ ተሞልቶ ደንበኞቹን መቀበሉም የማንኛውንም ሠው እምኔታ በቶሎ እንዲያገኝና ስራውን እንዲያስፈጽም ይረዳው ነበር:: እሺታንም ወዲያው ነበር የሚያገኘው:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው ለስኬት ሲበቃ ማየት ሁላችንም የምንፈልገው ነገር ይመስለኛል::

ቻይናዎች ሲተርቱ «ፈገግታ የሌለው ሰው ሱቅ አይክፈት» ይላሉ ታዲያ ፈገግታ ለአንድ የሽያጭ ሰራተኛ የሚያስፈልገውን ያህል ንግግር ለማድረግ ወደ አድማጭ ዘንድ ስንቀርብስ አያስፈልግም ትላለህ? ይህ አንድ ነገርን አስታወሰኝ:: የብሮክሊን ንግድ ምክር ቤት ህዝብ ፊት መናገርን በተመለከተ በሰጠው አንድ ኮርስ ላይ ተሳታፊ ነበርኩ:: በዚህ ትምህርት ላይ አንድ ለየት ያለ ወጣት ነበር:: ሁል ጊዜም አድማጭ ፊት የሚቀርበው እዚያ በመሆኑ ብቻ እጅግ ደስተኛ እንደሆነ በሚገልፅ ስሜት ነበር:: ሁልጊዜም ፈገግታ የማይለየው በመሆኑና ዘወትር እኛን በማየቱ ደስ የሚል ስሜት እንደተሰማው በሚያሳይ ስሜት ውስጥ በመሆኑ አድማጮቹ ያለምንም ማንገራገር ነበር ወዲያውኑ ሞቅ ያለ አቀባበል የሚያደርጉለት::

በሌላ መልኩ ደግሞ ቅዝቅዝ ባለና የማይስማማውን ሥራ የግብር ይውጣ እንደሚሰራ ሰው ሆኖ የሚቀርብና ተናግሮ ሲጨርስም አምላኩን የሚያመሰግን ተናጋሪም አጋጥሞኛል:: የዚህ አይነቱ ተናጋሪ ሰው መንፈስ ወደ እኛ (አድማጮቹም ላይ ስለሚጋባ እሱ ተናግሮ ሲጨርስ እኛም ማመስገናችን አይቀርም:: ፕሮፌሰር ኦቨር «የሰዎች ባህሪ ላይ ተፅዕኖ ስለመፍጠር» በሚል ፅሁፋቸው እንደገለጹት «ማንም የተመኘውን ያገኛል:: እኛ አድማጮቻችንን ከወደድናቸው እነሱም እኛን እንዲወዱን ለማድረግ ያለን ዕድል እጅግ ከፍተኛ ነው:: በዝናው አንፃርም ግንባራችንን አጨፍግገን ወደ አድማጭ አቅርበን በአድማጩ ዘንድ በግልፅ የሚታይም ሆነ የማይታይ ተመሳሳይ ስሜት እንዲፈጠር የማድረግ እድላችን ሰፊ ነው:: በድንጋጤና ግራ በተጋባ ሁኔታም ለንግግር ስንቀርብ አድማጫችን በእኛ እምነት እንዲያጣ እናደርገዋለን:: ከዚህ በተለየ ደግሞ በጣም አይን አውጣ ሆነንና ለአድማጩ ክብር ሳንሰጥ ስንቀርብም አድማጩ እራሱን ከማስከበር በሚመነጭ ስሜት ምላሽ እንዲሰጠን እናስገድደዋለን::

ስለዚህም ነው ገና ንግግር ሳንጀምር እናኳን ለነቀፌታና ለድጋፍ ቀደም ብለን የምንጋለጠው በንግግር ወቅት የሚኖረንን ባህሪና አመለካከት ከአድማጭ ዘንድ የሞቀ ድጋፍና ተቀባይነትን በሚያስገኝልን መልኩ እርግጠኛ ሆነንበት መቅረብ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው።

## አድማጮችህ ሰብሰብ ብለው እንዲቀመጡ አድርግ

ንግግር በማቅረብ ብዙ ስለቆየሁ ከልምዴ እንዳስተዋልኩት አዘውትሬ ከሰዓት በኋላ ላይ በማደርገው ንግግር ብዙ የማይባሉ ሰዎች ለዚያውም ተበታት ነው በመቀመጥ ሰምተውኛል። በማታው የንግግር ፕሮግራሜ ላይ ግን በርካታ አድማጮች ተጠጋግተውና ሰብሰብ ብለው በመቀመጥ ያዳምጡኝ ነበር። ታዲያ የከሰዓት አድማጮችን በጥቂቱ እንኳን ፈገግ የማያደርጋቸው ነገር የምሽቱ አድማጮቼን ተመሳሳዩ ነገር ከልብ እንዲስቁ ሲያደርጋቸው ተመልክቻለሁ። ለምን ይመስላችኋል? አንደኛው ነጥብ አድሜያቸው የገፉ ሰዎችና ህፃናቶች በከሰዓቱ ፕሮግራሜ ላይ በርከት ብለው ስለሚገኙና ብዙም ተሳትፎ ያለው እንቅስቃሴ ስለማያድርጉ ነው። ነገር ግን ይሄ በከፊል ብቻ ነው ሁኔታውን የሚገልጸው። እውነተኛው ምክንያት ግን ማንኛውም አድማጭ ተራርቆ የተቀመጠ ከሆነ የሚናገረው ሰው በሚለው ነገር በቀላሉ ሊሳብ አለመቻሉ ነው። በአድማጭ መካከል ብዙ ሰው ያልተቀመጠባቸው ወንበሮች መኖሩ በከፍተኛ ጉጉት ተናጋሪውን የመከታተል ስሜትን በጣም ያጠፋዋል።

ሄነር ጎርድ ቤከር በንግግር ላይ የተመረኮዘ ትምህርቱን በአያሌ ዩኒቨርስቲዎች በሚሰጥበት ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበር። «ብዙ ጊዜ ሠዎች እንዲህ ብለው ይጠይቃሉ። ለብዙ አድማጭ ንግግር ማድረግ ትንሽ አድማጭ ብቻ ለሚገኝበት ቦታ ከመናገር ይልቅ ሊያነቃቃን አይችልም። ወይ? እኔ ግን በሺህ ለሚቆጠሩ ሰዎችም ይሁን ለአስራ ሁለት ሰዎች የማደርገው ንግግር ተሰብስበው በዙሪያዬ እጅበውኝ እስከተቀመጡ ድረስ ምንም ለውጥ አያመጣም እላችኋለሁ። ነገር ግን ለአንድ ሺህ ሰዎች ብናገር በመሃከላቸው ባሉት ሁለት ሰዎች መካከል ያለውን ክስተት ከሁለት ሜትር በላይ ከተቀመጠ ባዶ ለሆነ አዳራሽ ከመናገር አይተናነስም. . . አድማጮችህን ግን ስብሰብ ብለው እንዲቀመጡ በማድረግ ብቻ ያለብዙ ልፋት ትኩረትን ልታገኝና ልትስባቸው ትችላለህ።

በብዙ ሰዎች መካከል ንግግር የሚያደርግ ሰው ብቻውን ቆሞ የሚናገር ያህል ሊሰማው አይችልም። ምክንያቱም እራሱን የስብስቡ አንድ አካል አድርጎ በመቁጠር ለያይቶ ከማየት በበለጠ ልባቸውን ለማግኘት ይረዳዋል። ለምሳሌ ወደ ጦር ግንባር የሚዘምቱ ወንዶች አንዱ ከአንዱ ሳይባል ሁሉም እጅግ አደጋ ሊያመጣ በሚችልና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ እጅብ ብለው መቀመጥ ያዘወትራሉ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የጀርመን ወታደሮች እጃቸውን እርስ በርስ በማቆላለፍ ወደ ጦር አውድማ በማምራት ይታወቃሉ።

የሰው ስብስብ! የሰው ስብስብ! የሰው ስብስብ! ይህ ማለት በእርግጥም አንድ ነገር ለመስማት፣ ለማየት፣ ለመታደም ለመሳሰሉት ሁሉ ከፍተኛ የሆነ ጉጉት ያላቸው ማለት ነው። ታላቅ የሆኑ የህዝብ ንቅናቄዎችና ለለውጥ የተደረጉ

Scanned with CamScanner

ትግሎች የተቃኙት ከብዙ ሰዎች አስተሳሰብ በፈለቁ እርዳታዎችና አመለካከቶች ነው፡፡

ትንሽ ለሆኑ ሰዎች የምንናገር ከሆነ አነስ ያለ ክፍል መምረጥ ይገባናል፡፡ በትልቅ አዳራሽ ውስጥ ሰዎች ተበታትነው እንዲቀመጡ ከማድረግ ይልቅ በትንሽ ክፍል ውስጥ ሰብስብ አድርጎ በማስቀመጥ ህይወት ያለው መንፈስ ለመዝራትና ውጤት ለማግኘት ይረዳናል፡፡ አድማጮችህ ተበታትነው የተቀመጡ ከሆነ ወደፊት ጠጋ ብለው በአካባቢህ እንዲቀመጡ አጥብቀህ ሳትጠይቃቸው በፊት ወደ ንግግርህ አትግባ! በተጨማሪም ብዙ አድማጭ ከሌለህ በስተቀርና ሙሉ ለሙሉ ለማየት የማትችል ካልሆነ መድረክ ላይ ሆኖ መናገሩ ምንም ጥቅም አይሰጥህም ከዚህ ይልቅ ወርደህ ከእነሱ ፊት ለፊት ቆመህ ተናገር፡፡ ህጎችንና ሥነ-ስርዓቶችን ለጊዜው ችላ በላቸው፡፡

## ሻለቃ ፓንድ መስታወቶችን ለምን ነበር የሚሰብረው?

በንግግርህ ቦታ ምንጊዜም አየሩ ንፁህ እንዲሆን አድርገው፡፡ በምትናገርበት ጊዜ ኦክስጅን በጉሮሮህ እያለፈ ወደሳንባህ በመግባት ህይወት እንደሚሰጥህ ሁሉ ብዙ ሰው በተሰበሰበበት ቦታም በበቂ ሁኔታ የንፁህ አየር ዝውውር መኖሩ ለንግግሩ ሂደት መቀላጠፍ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የሲሲሪዮ አንደበተ ርቱዕነት ወይም በሙዚቃ አዳራሽ እየተወዛወዙ ዳንስ የሚያሳዩ ሴቶች ህዝቡ ተነቃቅቶ ደስ እያለው እንዲከታተላቸው ለማድረግ በአካባቢውስ የሚገኘው አየር ያልተበከለና ንፁህ መሆን አለበት፡፡ እኔ ንግግር በማቀርብበት ቦታ ላይ ከእኔ በፊት ብዙ ተናጋሪዎች ካሉ ተራዬ ደርሶ ከመናገሬ በፊት ለሁለት ደቂቃዎች ያህል እረፍት እንዲያደርጉ በትህትና እጠይቅ ነበር፡፡ ከዚያ መስኮቶቹን በመክፈት አየር እንዲገባ አደርጋለሁ፡፡

ለአስራ አራት አመታት ያህል የዝነኛው ሰባኪ ሄነሪ ዋርድ ቤከር ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የሠራ ሻለቃ ጀምስ ፓንድ የተባለ ሰው ነበር፡፡ ታዲያ ህዝብ ወደ ስብሰባ ቦታ ሳይመጣ ቀድሞ በመገኘት ቦታዎቹን ይጎበኝ ነበር፡፡ ቦታው ያለውን የብርሃን መጠን፣ የወንበሮችን አቀማመጥ፣ እንዲሁም ንፁህ አየር በደንቡ መግባት አለመግባቱን ይቆጣጠራል፡፡ ፓንድ ጡረታ የወጣ የድሮ ሻለቃ በመሆኑ ያለውን ስልጣን ለማሳየት እየጮኸ ትዕዛዞች እንዲፈፀሙለት ማድረግ ያስደስተው ነበር፡፡ ስለዚህም ቦታው ሞቃታማ አየር ካለው እንዲሁም በቂ ኦክስጅን የማያገኝ ሲሆን መስኮቶቹን ለመክፈትና አየር ለማስገባት ይሞክራል፡፡ የማይከፈት መስታወት ካጋጠመው ትልልቅ መፅሐፎችን እየወረወረ ይሰብራቸው ነበር፡፡ የሱ እምነት ስተርጅን እንደተባለው ሰባኪ ሁሉ «ከአምላክ በረከት ለመቀበል አንድ ሰባኪ የሚያስፈልገው ምርጡ ነገር ኦክስጅን ነው» የሚለው ነበር፡፡

## በፊትህ ላይ ብርሃን ሲንፀባረቅ ይገባል

ከተወሰኑ ሰዎች ጋር መንፈሳዊ ሥነ-ሥርዓቶችን ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር ክፍሉ ሙሉ በሙሉ በብርሃን እንዲጥለቀለቅ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከፊል ብርሃን ባለው ክፍል ውስጥ በመናገር ሰዎችን በጥልቀት እንዲከታተሉንና እንዲመሰጡ ከማድረግ ይልቅ ብዙ ጅግራዎችን ሰብስቦ ማላመድ ይቀላል፡፡

ዴቪድ ቤሊሾን ስለመድረክ አቀራረብ የፃፋቸውን መጣጥፎች ያነበበ ሰው ብዙ የመድረክ ተናጋሪዎች በሚናገሩበት ቦታ መኖር ስለሚገባው በቂ የሆነ ብርሃን ያላቸው ግንዛቤ እዚህ ግባ የማይባል መሆኑን ይረዳል:: በቂ በሆነ ብርሃን ሲንፀባረቅና ሲታይ ይገባል:: ምክንያቱም በንግግርህ ጊዜ ፊትህ ላይ የሚኖረውን የገፅታ መለዋወጥ ከምትናገራቸው ሃሳቦች ጋር በቀጥታ የተገናኙና እንደ አንዱ የማንነትህ መገለጫዎችህ ስለሆኑ ነው:: እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ ከምትናገርበት ትይዩ ከአናትህ ላይ መብራት የሚበራ ከሆነ ፊትህ ላይ ጥላ ስለሚያጠላበት ላይታይ ይችላል:: ነገር ግን ከፊት ለፊትህ በቀጥታ ወደአንተ የሚበራ ከሆነ በትክክል ልትታይ ትችላለህ ስለዚህም እንዲህ አይነቱን ቦታ መምረጥ ብልህነት አይመስልህም?

## • በመድረክህ ላይ አላስፈላጊ ዕቃዎች አትደርድር

ንግግር ከምታደርግበት ጠረጴዛ ጀርባ አትደበቅ:: ምክንያቱም አድማጩ ንግግር የሚያቀርብለትን ሰው ሙሉ አካል ማየት ይፈልጋልና ነው:: አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም ወደመተላለፊያው ብቅ ብለው ለማየት ጥረት ያደርጋሉ የንግግሩ አዘጋጆች ጠረጴዛው ላይ ውሃ የያዘ ብርጭቆና ኮዳ ያስቀምጡላችኋል::

በንግግራችሁ ጊዜ ጉሮሮአችሁ ቶሎ ቶሎ የሚደርቅ ከሆነ ትንሽ ጨው ወይም የሎሚ ጭማቂ አፋችሁ ማድረግ ከውሃው በበለጠ ሁኔታ የምራቅ እጢዎቻችሁ እንዲሰሩ ያግዛቸዋል:: ስለዚህ የውሃ ጆግ በሆነ የእንጆሪ ጭማቂ አያስፈልግህም? መድረክህን የተለየ አስቀያሚ ገፅታ የሚያላብሱትና የተጨናነቁ መንፈስ የሚፈጥሩ ነገሮችም ጥቅም የላቸውም በብሮድዌይ የሚገኙትና የተለያዩ መኪና አምራቾች ለሽያጭ የሚያቀርቧቸውን ተሽከርካሪዎች የሚያሳዩበት ሱቆች ለአይን የሚስቡና እጅግ ማራኪ ናቸው:: እንደዛው ሁሉ በፓሪስ የሚገኙት የሽቶና የጌጣጌጥ መሸጫ ሱቆች ስነ ውበትን የሚያንጸባርቁ በቅንጡ መልኩ የታነፁ ናቸው ለምን? ምክንያቱም ለስራቸው አስፈላጊ በመሆናቸውና ደንበኞቻቸውንም በዚህ አይነቱ ሁኔታ ለመማረክና ለመሳብ ይረዳቸዋል:: ደንበኞችም በእነዚህ አይነት ውብ በሆኑ አቀማመጦችና በሱቆቹ ውበት ከፍተኛ አድናቆት እንደሚያድርባቸውና አክብሮት እንደሚሰጧቸው ስለሚያውቁ ነው::

በተመሳሳይ መልኩ አንድ ተናጋሪ በሚቀርብበት መድረክ ጀርባ አስደሳችና ማራኪ መሆን አለበት:: እኔ እጅግ አድርጌ የማምንበት ነገር ከተናጋሪው ሰው ጀርባ ምንም አይነት ቁሳቁስና ትኩረትን ሊስብ የሚችል ነገር ባይቀመጥ እመርጣለሁ:: እንድ መኖር ያለበት ነገር ቢኖር ጥቁር ሰማያዊ መጋረጃ ብቻ ነው ግን በተለምዶ ሲደረግ የምናየው . . . የተለያዩ የዓለም ካርታዎች፣ ምልክቶች፣ ወንበሮች እርስ በርስ ተነባብረውና በአስቀያሚ ሁኔታ ተደርድረው ነው:: እናም ውጤቱ ምንድን ነው? በእዚያ ቦታ መኖር የሚገባውን ድባብ በመረበሽ በምትኩ የተዘበራረቁና ትርምስምሱ የወጣ ትዕይንት እንደፈጠረ አድርጎ ያበላሸዋል::

ሄነር ቤከር አዘውትሮ እንደሚገልጸውም «በሕዝብ ፊት ለመናገር እጅግ አስፈላጊው ነገር ሰውዬው ነው» ስለዚህም ተናጋሪው በስዊዘርላንድ እንደሚገኘው ጆንግፍራ ህንፃ ኮራ ብሎ ሊቆምናሰ ሊናገር ይገባል::

# በመድረክህ ላይ እንግዶች አታስቀምጥ!

አንድ ጊዜ በለንደን አንታሪዮ ተገኝቼ የካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር ንግግር ሲያደርጉ አዳምጬ ነበር በመሃል ግን የፅዳት ሰራተኛው ረጅም ዘንግ ይዞ ወዲህ ወዲያ እያለ መስኮቶቹን ለመክፈትና ብርሃን እንዲገባ ለማድረግ ጥረት ያደርግ ጀመር:: ከዚያ ምን ሆነ መሰላችሁ:- አድማጩ በሙሉ ማለት ይቻላል ለተወሰነ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በመርሳት የፅዳት ሰራተኛውን ልክ የሆነ የአስማት ትርዒት እንደሚያሳይ ሰው ሲያስተውል ቆየ::

አንደኛ:-

አድማጭ ብዙ ጊዜ እንደዚህ አይነት ነገሮችን ችላ ብሎ ማለፍ ወይም ዳግም ትኩረቱን እንዳይሰርቁት እራሱን ለመቆጣጠር ሲቸገር ይታያል:: ተናጋሪውም ሆነ አድማጩም ይህን እውነታ ከተገነዘበ ካላስፈላጊ መረበሽና ችግር እራሱን ማዳን ይችል ነበር:: በመጀመሪያም የእጁን ጣቶች እያፍተተ ከመጫወት፣ ልብሱን ከመነካካትና ከመረበሽ የሚመጡ ድርጊቶችን ከማከናወን መቆጠብ አለበት::

አንድ ወቅት በኒውዮርክ ንግግር የሚያደርግን ታዋቂ ሰው በእጁ የጠረጴዛውን መሸፈኛ ጨርቅ እየነካካ የሚያደርገውን ጨዋታ ለግማሽ ሰዓታት ያህል ትክ ብለው ሲመለከቱ የነበሩ አድማጮችም አጋጥመውኛል::

ሁለተኛ:-

ማንኛውም ተናጋሪ በተቻለው አቅም ሁሉ ቀድመው የገቡ አድማጮችን ከፊት ለፊት እንዲቀመጡ አድርጎ ዘግይተው የሚመጡትን እንደአገባባቸው አስተካክሎ በማስቀመጥ ቀድመው ቦታ የያዙት በኋላ ላይ በሚገቡት ሰዎች እንዳይረበሹ ማድረግ ይቻላል::

ሦስተኛ:-

አንድ ሰው እሚናገርበት መድረክ ላይ ምንም ዓይነት እንግዳ የሆነ ሰው እንዲቀመጥ መፍቀድ የለበትም:: ከጥቂት ዓመታት በፊት ሬይመንድ ሮቢንስ በብሩክሊን ተከታታይ የሆኑ ንግግሮችን ያቀርብ ነበር :: ታዲያ በአንደኛው ቀን ንግግር ላይ ከሌሎች ተጋባዥ እንግዶች ጋር በመድረኩ ላይ እንድቀመጥ ተጋብዤ ነበር:: ይህ ነገር ለንግግር አድራጊው ሰው ጥሩ እንዳልሆነ ምክንያቶችን በመጥቀስ ግብዣውን ሳልቀበል ቀረሁ:: ምክንያቱም ከዚያ በፊት ባደረገው ንግግሩ ላይ እዚያ የጋበዛቸው እንግዶች አንዱ እግሩን ሲያጣምር፣ ሌላው ሲያወርድና ወዲህና ወዲያ ሲያዘነብሉ በእነዚህ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ አድማጩ እብሮ አይኑን ከአንዱ ወደ አንዱ ሲያንቀዋልል ተመልክቼ ስለነበር ነው:: ለሮቢንስ ይህን ችግር አንስቼ ስለነገርኩትም የተፈጠረውን መዘበራረቅ በመረዳቱ በሚቀጥለው ጊዜ ባለው ንግግሩ ታዲያ በብልሃት መድረኩን ለብቻው ሊቆጣጠረው ችሏል::

ዴቪድ ቤሊሽ በሚናገርበት መድረክ ላይ አበባ እንዲቀመጥ አይፈቅድም ነበር፤ ምክንያቱም የአብዛኛውን አድማጭ ትኩረት ይስባልና ነው፡፡ ታዲያ አንድ ተናጋሪስ የሚንቀሳቀሰውንና የሚቁነጠነጠውን የሰው ፍጡር መድረኩ ላይ እንዲቀመጥ የሚፈቅደው ለምንድነው? እንዲህ የሚያደርግ ንግግር አቅራቢ ስህተቱን ተረድቶ በብልሃት ማረም ይጠበቅበታል፡፡

## የአቀማመጥ ጥበብ

አንድ ተናጋሪ ንግግሩን ከመጀመሩ በፊት ባሉት ጊዜያቶች አድማጩ ፊት ባይቀመጥ ጥሩ አይመስላችሁም? እንደተናፈቀና እንደተጠበቀ ሆኖ በድንገት ብቅ ብሎ ንግግሩን መጀመርስ ተመራጭ አይሆንምን? ይህ ሲሆን አይችልም ናላችሁኛና ቀደም ብላችሁ መቀመጥ ከፈለጋችሁ እንዴት ልትቀመጡ እንደምትችሉ ተጠንቅቃችሁና አስባችሁ መሆን አለበት፡፡ ብዙ ጊዜ ተናጋሪው ሰው ወንበር በመፈለግ ልክ ቀበሮ በምሽት አካባቢ ለአደን እንደሚያደባው ቀበሮ አይነት እንቅስቃሴ ሲያደርግ ሳትመለከቱ አትቀሩም፡፡ ወንበር ያለበትን ቦታ ከተገኘ በኋላ ደግሞ ልክ አሸዋ እንደተሞላ ጆንያ ዘፍ ብሎ ሲቀመጥ ማየት ያስቀይማል፡፡ አንድ በቀላሉ ወንበሩ የት እንደሚገኝ ለማወቅ የሚረዳ ዘዴ በእግሩ ጀርባ በመታከክና በማወቅ እንዲሁም አንገቱን ወደላይ ቀና በማድረግ ቀስ ብሎና ሰውነቱን ተቆጣጥሮ በዝግታ መቀመጥ ይችላል፡፡

## አቋቋም

ከዚህ በፊት ባሉት ክፍሎች ከልብሳችን ከጌጣጌጦቻችንና ከእጃችን ጣቶች ጋር መጫወት የሰዎችን አትኩሮት ስለሚሰርቅ ለንግግር ጥሩ እንደማይሆን አይተናል፡፡ ሌላ ተመሳሳይ ነገር ደግሞ ይቀረናል፡፡ ይኸውም እራስን ተቆጣጥሮና አስተካክሎ ያለመቆም ድክመት ነው፡፡ ማንኛውም እኛ ልንቆጣጠረው የማንችለው እንቅስቃሴያችን እንደ ድክመት ሊታይብን ይችላል፡፡ ስለዚህም ቀጥ ብለን በመቆምና ሰውነታችንን በሙሉ በመቆጣጠር አዕምሯችን ሰውነታችንን ማዘዝ እንደሚቻል በማሳየት አቋቋማችንን ለንግግራችን ታላቅ እገዛ እንዲያደርግ አሳምረን ለመጠቀም እንችላለን፡፡ ተነስተን አድማጭ ፊት ከቆምንም በኋላ ንግግር ለመጀመር የጥድፊያ ምልክት ማሳየት የለብንም፡፡ ይህ ጅምር ተናጋሪዎች የሚያደርጉት ነገር ሲሆን አንተንም እንደዚያው ያስቆጥርሃል፡፡ ከዚህ ይልቅ አየር በጥልቀት ከሳብክ በኋላ ለተወሰኑ ሰኮንዶች ያህል አድማጮችህን ሙሉ በሙሉ ለማየት ጥረት በማድረግ አሳልፍ፡፡ የሚረብሹ ድምፆች ወይም ጩኸት ካለ እስከሚረግብና ፀጥ እስከሚል ድረስ ንግግርህን አትጀምር፡፡ ሌላው ደረትህን ወደፊት ገፋ አድርገህ መቆምህ ነው፡፡ ይህን ነገር አድማጭ ፊት ንግግር ለማድረግ ስትዘጋጅ ብቻ ለምን ታደርገዋለህ? በግልህ ኮራ ብለህ መቆም በመለማመድ ልታሳካው ትችላለህ፡፡ ከዚህ በኋላ እንደ ልማድ ይሆናል፡፡ ሳታስበው በንግግርህ ጊዜም ወደታች አዘቅዝቀህ እንዳትታይ ያደርግሃል፡፡

ሉተር ጉሊክ «እንከን የለሹ ህይወት» በተባለው መፅሐፍ እንደገለፀው ማራኪ የሆነ አቋቋም «ከአስር ወንዶች መካከል እራሱን ቀና በማድረግ እንዲኖረው ጥረት የሚያደርገው አንድ ብቻ ቢሆን ነው» ብሏል፡፡ ምን ማድረግ እንደሚገባን ሲመክርም «አየር ወደ ሳንባችን በዝግታና በጥልቀት እየሳብን

በማስገባት ደረታችንን ከፍና ዝቅ እያደረግን በተመሳሳይ ሰዓትም ጭንቅላታችንን ወደኋላ በማዘንበል መቆየት፣ እዚህ ላይ እንዳለን ትንሽ መቆየት ይገባል:: ይህን እንቅስቃሴ በፍጥነት ማድረግ አስፈላጊ አይደለም:: ምክንያቱም ዋና ዓላማው በሁለቱ ትከሻዎቻችን መካከል የሚገኘውን ክፍል በማጠንከር ደረታችን ወደፊት እንዲሰጠጥ ማድረግ ነው»

እጆችህንስ እንዴት ልታደርጋቸው ታስባለህ? እጆችህ ተፈጥሯዊ አወራረዳቸውን በመጠበቅ በእንዲህ ትይዩ እስከዋሉ ድረስ መጨነቅ አይገባህም:: ነገር ግን እንደሙዝ ዝንጣፊ ክርፍፍ እያሉ ካስቸገሩህ ግን ማንም ልብ ብሎ ሊያስተውልና ሊከታተላቸው አይችልም ብለህ አትዘናጋ:: ምክንያቱም ዘና ባለ ሁኔታ ከንግግርህ ጋር አብረው የሚንቀሳቀሱ ሲሆኑ ብቻ የማንንም ትኩረት የማይስቡና በጣም ተቺ የሆኑ ሠዎች ፊት ብትቀርብ እንኳን ምንም አቃቂር ሊያወጡላቸው ስለማይችሉ ነው::

መጨነቅና መረበሽ በሚኖርብህ ጊዜ እጆችህን ወደ ጀርባህ እያዞርክ በማቆላለፍ፣ ኪስህ ውስጥ እያስገባህ ማውጣት፣ ጠረጴዛው ላይ መዘርጋት ምናልባትም ለዓይናፋርነትህ ጊዜያዊ መፍትሄ ሊሰጥህ ይችላል:: ነገር ግን ዘላቂ መፍትሄ ይሆነኛል ትላለህ? ይህ ብዙ ማሰብ የሚጠይቅ ነገር አይደለም:: ብዙ ታዋቂና ዘመናዊ ተናጋሪዎች ሁሉም ማለት ባይቻልም አብዛኞዎቹ ግን በንግግር ወቅት እጃቸውን ወደኪሳቸው መክተት ያዘወትራሉ:: ለምሳሌ ለመጥቀስ ብርያን ቻውንሲ፣ ሩዝቬልትን የመሳሰሉት ይህን ድርጊት ያዘወትሩ ነበር:: የሚገርመው ግን ፈጣንና ቅብጥብጥ የሚባለው ዴዚሬ እንኳን ሲያደርገው መታየቱ ነው:: ይህን ነገር ማድረግ ማለት ሰማይ ተደፋብን ማለት አይደለም:: የአየር ትንበያውን በደንብ ሰምቼ ከሆነ ነገ ብሩህ ቀን ስለሚሆን ፀሃይም ትወጣልናለች:: አንድ ተናጋሪም ሚዛን የሚደፋ ሃሳብ ይዞ ወደ መድረክ እስኪወጣ እንዲሁም ከልቡና በስሜት ሆኖ መግለጽ እስከቻለ ድረስ በእርግጥም እጅና እግሩ የሚሰሩት ነበርና ብዙም አዋኪ ሊሆኑበት አይችሉም:: እነዚህ ነገሮች በሁለተኛ ደረጃነት የሚታዩ እንደመሆናቸው በእራሳቸው ጊዜ ቀስ ብለው እንደሚስተካከሉ እርግጠኛ መሆን እንችላለን:: ዞሮ ዞሮ በንግግራችን ላይ ወሳኝና እጅግ ጠቃሚ የሆነው ነገር ስነልቦናዊ ዝግጅታችን እንጂ አቋቋማችንም ሆነ የእጅና፣ የእግራችን አቀማመጥ አይደለም::

## በንግግር ወቅት እራስን ለመግለፅ በሚል ስም ግራ የሚያጋቡና ሰው ለመማረክ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች

## ትምህርት ይሰጥባቸዋል

ይህ ነጥብ ግራ ወደሚያጋባውና በንግግራችን ወቅት መደረግ ያለበት እንቅስቃሴ ምንድነው? ወደሚል ጥያቄ ይመራናል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝብ ፊት መናገርን የተማርኩት በአንድ የኮሌጅ ፕሬዝዳንት በነበረ አስተማሪዬ ነበር:: በደንብ እስከማስታውሰው ድረስ ትምህርቱ በአብዛኛው ትኩረት ይሰጥ የነበረው በንግግር ወቅት ስለምናደርገው እንቅስቃሴ ነበር:: ይህ ነገር ዋጋ የለሽ ከመሆኑም በላይ ተማሪውን ትክክል ወደ አልሆነ አቅጣጫ የሚመራና ባላሰብነው መልኩም ለንግግራችን ጎጂ ነበር::

እጃችንን ወደታች በማድረግ ላላ አድርገን እንድንለቃቸው፣ የውስጥ መዳፋችን ወደፊት እንዲታይ አድርገን እንዲሁም ጣቶች ሙሉ በሙሉ ሳይገጥሙ በአውራ ጣታችን ታፋችንን እንድንነካ ስንማር ቆይተናል:: ቀኝ እጄን ግርማ ሞገስ በተላበሠ መልኩ ግማሽ ክብ በመስራት ብድግ እንዳደርግና ስመልሰውም በመጀመሪያ አመልካች ጣቴን ቀጥዬ ሁለተኛውንና ሶስተኛውን ጣቴን እያጠፍኩ መመለስ እንዳለብኝ ስለማመድ ነበር:: እነዚህን ሁሉ ድራማዊ እንቅስቃሴዎች ካደረኩ በኋላ እጄን መልሼ በታፋዬ ትክክል ማስቀመጥ እንዳለብኝ ተነግሮኛል:: ይህ ሁሉ ድርጊት ምንም ጥቅም የሌለውና እንጨት እንጨት የሚል ሆኖብኝ ነበር::

በዚህ ሁሉ ልምምድ የእራሴን አቋቋም እንድጠቀም ምንም ሙከራ እንኳን አልተደረገልኝም:: ስለዚህም አጠቃላይ የሆነ እራሴን የመግለጫ እንቅስቃሴዎች ተብለው የተማርኳቸው ነገሮች ምንም ስሜት የማይሰጡ፣ በድን የሆኑና ህይወት ሰጥተው ሊያንቀሳቅሱ የማይችሉ ነበሩ:: አንድ ሰው ሳድርገው ብሎ በመለማመድ ብቻ ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ለማድረግ አይችልም:: ይህ ከእኛ ቁጥጥር በላይ የሆነና ፍፁም ተፈጥሯዊ ይዘት ያለው ነገር ነው:: በድንገት ከውስጣችን ሳናስበው የሚመነጭና የእራሳችን ልናደርገው የምንችል እንቅስቃሴ ነው::

ይህ እኔ የተማርኩት አስቂኝ የሆነ የሰውነት እንቅስቃሴ በዚህ ዘመን ላስተምር ቢሉት የሚገርም ነው የሚሆነው:: ይሁን እንጂ ከጥቂት ዓመታት በፊት በንግግራችን ጊዜ ስለምናደርገው እንቅስቃሴ የሚተነትን መፅሐፍ ታትሞ ነበር:: የመፅሀፍ ይዘት የሚያወራው የትኛውን አይነት እንቅስቃሴ ለየትኛው ዓረፍተነገራችን መጠቀም እንዳለብንና በየትኛው አረፍተ ነገር አንድ እጃችንን እንደምናነሳ፣ ለየትኛው ደግሞ ሁለት እጃችንን ማንሳት እንዳለብን፣ መቼ ዝቅ እንደምናደርገው፣ ጣታችንን የትኛውን መጀመሪያ እንደምናጥፈው፣ መቼ እንደምንጨብጥና የመሳሰሉትን ነገሮች የያዘ ነበር::

በአንድ ወቅት የንግግር ትምህርት ይማሩ ከነበሩት ተማሪዎች መካከል ሃያ የሚሆኑት ከሌሎቹ ተማሪዎች ፊት በመቆም ከመፅሐፉ የተወሰነ ክፍል በመውሰድ ያንን እንቅስቃሴ አንድ አይነት ቃላት እየተናገሩ እንዲለማመዱ ሲደረጉ አይቻለሁ:: ይህ ሰውን እንደማሽን እንዲሰራ የሚያደርግ፣ጊዜያቸውን ያለአግባብ የሚያቃጥልና ምንም የእራሴ የምንለው ነገር እንዲፈጥር የማያደርግ ስለሆነ አጠቃላይ ንግግርን ለመማር የሚፈልጉ ሰዎች ትምህርቱን በጥርጣሬ እንዲያዩት አድርጓቸዋል::

አንድ በማሳቹሴትስ የሚገኝ ትልቅ ኮሌጅ ዲን በተለይ እንድንገልፀው በንግግር ላይ የሚሰጠውን ኮርስ ማንም በተግባር ሲያውላቸው እንዳልተመለከተ በመግለፅ በእሱ ትምህርት ቤት ከእንግዲህ እንደማይሰጥ አሳውቋል:: እኔ ግን በዲኑ ችግሩ ያለው በትምህርቱ ላይ ሳይሆን በአሰጣጡ ላይ መሆኑን ስለማውቅ ንግግር አዝኛለሁ::

በንግግር ወቅት መደረግ ስላለበት እንቅስቃሴ ከሚገልጹ መጽሐፎች ውስጥ ከአስሩ ዘጠኝ ያህሉ ትክክል ያልሆኑና ትርፋቸው ሌላ ጠቃሚ ነገር ሊፃፍባቸው የሚችሉትን ውድ ወረቀትና ቀለም ማባከን ብቻ ነው :: ይህን ነገር የምናገኝበት ብቸኛው ቦታ ውስጣችን ያለ ነው:: ከልባችን ከአስተሳሰባችን፣ ለምንናገረው ርዕሰ

ካለን ጥልቅ ፍላጎት የሚመነጭ ነው:: በዚህ ጊዜ አንድን ሃሳብ አድማጩ እንዲረዳን ካለን ስሜት የተነሳ ከውስጣችን ያለውን ነገር ለመግለፅ አካሎቻችን ይንቀሳቀሳሉ:: ይህ ከራስ የመነጨ እንቅስቃሴ ታዲያ 1-2-3 በማለትና ህግ ወጥቶላቸው ከምንማራቸው ነገሮች እጅግ የላቀና የበለጠ ነው::

የንግግር እንቅስቃሴ ለአለቱ ግብዣ የመረጥነውን ልብስ ብድግ አድርገን እንደምንለብሰው ሁሉ በእኛ ምርጫ የምናገኘው ነገር አይደለም::

ይህ በውስጣችን ያለንን ስሜት ወደ ውጭ አውጥተን ለማሳየትና ለመግለፅ የሚረዳ መንገድ ሲሆን ከሳቅ፣ ከህመም፣ ከመሳሳም ... ከመሳሰሉት ነገሮች ጋር አንድ አይነት የሆነ ነገር ነው ::

አንድ ሰው በንግግር ጊዜ የሚያሳየው እንቅስቃሴም ልክ እንደጥርስ ቡሩሽ ሁሉ የግሉ የሆነ ነገር ነው:: ስለዚህም የሰው ልጅ ሁሉ አንድ አይነት ስላልሆነ ከውስጣችን የሚመነጨው ይህ እንቅስቃሴም በተፈጥሮ የምናገኘው እስከሆነ ድረስ ፍፁም አንድ አይነት ሊሆኑ አይችሉም! ሁለት ሰዎችንም አንድ ዓይነት እንቅስቃሴ እያደረጉ እንዲስማሙ ማድረግ የዋህነት ነው:: እስቲ አስቡት:: ቀስ ብሎ፣ እያሰበና በዝግታ የሚናገረውን ሊንከንን ፈጣን ተናጋሪ፣ ቅብጥብጥ ከሆነው ዳግላስ ጋር በእንቅስቃሴያቸው እንዲመሳሰሉ ለማድረግ መሞከር ማለት ቂልነት ነው::

ከሊንከን ጋር በህግ ትምህርት ቤት አብሮ የተማረውና በኋላም የህይወት ታሪኩን የጻፈው ሃራንዲን ሲናገር «ሊንከን በንግግሩ ጊዜ ከእጆቹ እንቅስቃሴ ይልቅ አዘውትሮ በጭንቅላቱ ንቅናቄ ነበር የሚጠቀመው:: አንድ ጊዜ ጭንቅላቱን ወደ ግራና ቀኝ እያደረገ ይናገራል:: ሌላ ጊዜ ደግሞ አንገቱን ወደፊት አስግጎ እራሱን በማስጠጋት ሃሳቡን ይገልፃል» አንድ አጠንክሮ የሚናገረው ነገር ካለው ይህን እንቅስቃሴውን በጉልህ ለማየት ይቻል ነበር:: በተረፈ ግን እንደ ኤሌክትሪክ ብልጭታ ፈጣንና ቶሎ የሚጠፋ በመሆኑ ለማስተዋል አይቻልም:: እሱ እንደሌሎች ተናጋሪዎች መሬቱን በእግሩ እየደበደበና በእጁ አየሩን እየቀዘፈ ተናግሮ አያውቅም:: እንዲሁም ለመድረክ ንግግር ብሎ እንቅስቃሴዎችን አያጠናም. . . ንግግሩ እየገፋ ሲመጣ በጣም ነፃ ይሆንና እንቅስቃሴው እጅግ ቀልል ያለ ይሆናል:: ይህ የጠነከረ ስብዕና ያለው ፍፁም ተፈጥሮአዊና በጣም ግርማ ሞገስ የተላበሰ ነገር ነበር::

በዚያው መጠን ልታይ ልታይ ማለትን፣ የውሸት ፈገግ ማለትን እንዲሁም ለንግግሩ ደንቦች እንዲቀመጡለት የማይወድ ሰው ነበር:: ጠንካራና ረጃጅም በሆኑት ጣቶቹ ጠረጴዛው ላይ የነጥብ ምልክት እያሳየ የሚናገረው ነገር ትርጉም እንዲያገኝለትና በአድማጩ ዘንድ እንዲሰማለት ያደርግ ነበር:: አንዳንድ ጊዜ የሃዘን ወይም የደስታ ስሜትን ለመግለፅ ሁለቱንም እጆቹና በሞት የተለያየውና የሚወደውን መንፈስ እንደሚያቅፍ ሁሉ በሃምሳ ዲግሪ ወደላይ ከፍ ያደርጋቸዋል:: የጥላቻ ስሜቱን ለመግለፅ . . . ባርነትን ለማውገዝ ሁለቱንም እጆቹን ካነሣ በኋላ እንደቦክስ ጨብጦ ወደታች ይወረውራቸዋል:: ይህ እንቅስቃሴው እጅግ የሚታወቅበትና ይህ እጅግ አምርሮ የሚጠላውን ባርነትን እስከ መጨረሻው ወደ መቃብሩ ወርዶ አፈር እንዲሆን ለማድረግ የበቃበትና ውጤታማ የሆነበት ነበር:: ሁል ጊዜ ሲናገር ቀጥ ብሎ በመቆም የእግሮቹ



Scanned with CamScanner

ጫፎች ትይዩ እንዲሆኑ አድርጎ ሲሆን ይህም አንደኛው እግሩ ከሌለው ወደፊት እንዲወጣ ፍፁም አያደርገውም ነበር:: በአራት ማዕዘን ቅርፅ እንደቆመ ሁሉ ምንም እንቅስቃሴ አያደርግም ወይም ምንም ነገር ላይ ለመደገፍ አይሞክርም እስከ ንግግሩ ማብቂያ ድረስ ጥቂት የአቋቋም ለውጥ ብቻ ነበር የሚያደርገው:: እጁን ዘና ለማድረግ ሲፈልግ የግራ እጁን አውራ ጣት ወደላይ አድርጎ የኮቱ ቀበቶ ማሰሪያ ውስጥ በመክተት ቀኝ እጁን ወደታች ዘና አድርጎ ይለቀዋል:: በቺካጎ በሊንከን መናፈሻ ያለውን የእራሱን ምስል በዚህ አይነት ሁኔታ ላይ እያለ ጋውደንስ በተባለ ሃውልት ቀራፂ የታነፀለት ነው::

ይህ የሊንከን መንገድ ነበር:: ቴዎደር ሩዝቬልት ደግሞ በጣም ጎልቶ የሚታይ በኃይል የተሞላ፣ፈጣን፣ ፊቱ ህይወት ባለው መንፈስ እየታየበት፣ እጁን እንደቦክስ ጨብጦና ጠቅላላ የሰውነት አካሉን ለንግግሩ በሚረዳ መልኩ እንደመሳሪያ ተጠቅሞ ነበር የሚናገረው:: ብራያን ደግሞ መዳፉን ወደላይ አድርጎ ሁለቱንም እጆቹን መዘርጋት ያዘወትር ነበር:: ግላድስቶን ጠረጴዛውን በቡጢ ወይም በመዳፉ ይደበድባል አሊያም በእግሩ እንዲሰማ አድርጎ መሬቱን ይመታ ነበር::

አዎን ይህ ሁሉ ነገር የሚያሳየው መጀመሪያውኑ በተናገሪዎቹ መንፈስ ውስጥ ያንን ኃይል እንዲጠቀሙ ወይም የተለየ ድርጊት እንዲያሳዩ የገፋፋቸው ስሜት እንደነበር ነው:: ስለዚህም ነው እንቅስቃሴያቸው በግብዓታዊነት የተደረገና ጠንካራ መልዕክት የሚያሣይ ሊሆን የቻለው:: ሰር አርቪንግ አንድ እግሩ አንክስ ስለሚል የራሱ የሆነ ልዩ እንቅስቃሴ መፍጠር ሊሆንለት አልቻለም ነበር:: በካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ ግራንትና ፐርኔልም ተመሳሳይ ነገር ገጥሟቸዋል:: በካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ ስለፓርላሜንታዊ ንግግር አቀራረብ ያስተምር የነበረው ሎረድ ኩርዘን «ታዋቂ ተናጋሪዎች የራሳቸው የሆነና ሃሳባቸውን ሲገልፁለት የሚያስችል እንቅስቃሴ ነበራቸው:: አንዳንድ በቃላት ንግግራቸው ብቻ የተካኑት ደግሞ በአስተማሪ እርዳታ የራሳቸው ያልሆነና የተቀባባ ግርማ ሞገሳዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ይሞክራሉ:: ይህ አይነቱ ጥረታቸው ታዲያ ውጤቱ ለተመልካች አስጠሊታና ደስ የማይል ይሆናል» ብሏል::

ከብዙ ዓመታት በፊት ጂፕሲ ስሚዝ የሚባል ሰባኪ ሲያስተምር እከታተል ነበር:: እናም በዚህ ሰው እንደበተ ርቱዕነት ብቻ ሳይሆን በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎቹ ሁሉ በጣም እማረክ ነበር:: የሰውነት አካሉቹን አብዝቶ የሚጠቀም ቢሆንም ለእራሱ ግን እንደሚተነፍሰው አየር ሁሉ አይታወቀውም ነበር::

እናንተም ታዲያ እራሳችሁን መሆን ያለባችሁ እንደዚሁ ነው:: ልምምድ ስታደርጉም በንግግራችሁ ወቅት እንደ መመሪያ እስገብታችሁ ለመጠቀም መሞከሩ ውጤት አይኖረውም:: ለንግግራችሁ የሚሆን እንቅስቃሴን እንደ መመሪያና ህግ አልሰጣችሁም፣ ምክንያቱም ሁሉም ነገር የሚወሰነው በተናጋሪው ሰው የግል ባህሪ፣ በሚገኝበት ቦታ ያለው ወቅታዊ ሁኔታ ስሜቱ የግል ስብዕናው፣ በሚናገርበት ርዕስና በአድማጭ መንፈስ ላይ ስለሆነ ነው::

# ምናልባት ሲገዱ የሚችሉ አስተያየቶች

በዚህ ርዕስ ላይ ምናልባት አንዳንድ ጊዜ ሊጠቅሟችሁ የሚችሉ የተወሰኑ አስተያየቶች ልስጣችሁ:: ደጋግማችሁ አንድ አይነት እንቅስቃሴዎችን ብቻ በንግግራችሁ ወቅት አትጠቀሙ፣ እጃችሁን ከተጠቀማችሁም ከትከሻችሁ ጀምሮ ያለው ክፍል በሙሉ መሆን ይኖርበታል:: ከክርናችን ጀምሮ ያለውን ክፍል ብቻ ነጥሎ ማንቀሳቀስ ጠቃሚ አይደለም:: አመልካች ጣታችሁን ከተጠቀማችሁ ደግሞ ያነሳችሁትን ሃሳብ የያዘው ዓረፍተ ነገር እስኪጠናቀቅ ድረስ አትመልሱት:: ምክንያቱም ተፅዕኖ ልትሰጡት የፈለጋችሁት ነጥብ ምንም እንዳልሆነ ያስመስልባችኋል:: በአድማጭ ፊት ቀርባችሁ ንግግር ስታደርጉ ደግሞ ተፈጥሮአዊውንና እውነተኛ የሆነውን በራሱ ጊዜ የሚመጣላችሁን እንቅስቃሴ ብቻ አድርጉ:: በንግግር ጊዜ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚረዳ መፅሐፍ የምታነቡ ከሆነም አሁኑኑ እንድታቆሙ እመክራችኋለሁ፣ ምክንያቱም በንግግር ጊዜ የራሳችሁ ስሁት የፈጠረውን እንቅስቃሴ ማመን በአስተማሪ የተሰጣችሁን እንቅስቃሴዎች ከመቀበል በብዙ እጥፍ ይሻላል:: እስካሁን ድረስ የተነጋገርነውን ከረሳችሁት እንኳን ይህን አስታውሱ:: አንድ ሰው ምን መናገር እንዳለበት በማሰብ አብዝቶ ከተጨነቀ መልዕክቱንም ለሚያደርሰው አካል ለማቅረብ ካለው ጉጉት የተነሳ በመዘንጋቱ በደመነፍሱ መመራትና መንቀሳቀስ ቢጀምር የንግግሩ አቀራረብም ሆነ የሚያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች እጅግ የተዋጣለት ባይሆን እንኳን ማንም ግን ሊተቸው የማይችል ይሆናል::

ቀጥሎ ያሉትን አስራ አንድ ቃላት በንግግር አቀራረብ ላይ ካነበብኳቸው ሁሉ እጅግ ጠቃሚ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ::

**በርሜሉን እስካፍጢሙ ሙላው**

**ከዚያ ክዳኑን ክፈትና መሬት ጣለው**

**ተፈጥሮም አንድትበርቅ ፍቀድላት!**

# ክፍል ስምንት

## የንግግር መክፈቻችንን እንዴት ማድረግ እንደምንችል

የኖርዝ ዌስተርን ዩኒቨርስቲ የቀድሞ ፕሬዝዳት የነበረውን ዶርሲን ሃሮልድን ለብዙ ጊዜያት ያህል ንግግር ከማድረጉ የተነሳ ከልምዱ የተማረው እጅግ ጠቃሚው ነገር ምን እንደሆነ ስጠይቀው ለትንሽ ጊዜያት ያህል ሲያወጣና ሲያወርድ ቆየ:: ከዚያም «በንግግር መክፈቻዬ ስሜት የሚጭርና የአድማጭን አትኩሮት ወዲያውኑ መሳብ የሚችል ነገር ማግኘት» ነው ሲል መለሰልኝ:: በእርግጥም እሱ ከዚህ በላይ ሁሉ ሄዶ መዝጊያና የመክፈቻ ቃላቶችን ፊልጎና አቅዶ ማዘጋጀት ይጠቀምባቸው ነበር:: ጆን ብራይት፣ ግላድስቶን፣ ዌብስተርና ሊንከንን የመሳሰሉ ሰዎችም በልምድና በተሞክሮ ይህን ነገር ይጠቀሙበት ነበር::

ጀማሪ ተናጋሪዎችስ እንደዚህ ያደርጋሉ? አልፎ አልፎ ያደርጋሉ ነገር ግን አቅዶና በደንብ አስቦ ለመተግበር አድካሚና ሙሉ ኃይልን መጠቀም ስለሚጠይቅ ይከብዳቸዋል:: በጥልቀት ማሰብና መመራመር ለህመም የሚዳርግ ሂደት ነው:: ቶማስ ኤድሰን ቀጥ ያለውን የሰር ጆሹዋ ሬይኖልድስን ንግግር ጠቅሶ በምርምር ጣቢያው ግድግዳ ላይ ሰቅሎ ነበር::

«የሰው ልጅ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በሚተጋ ጊዜ እጅግ በጥልቀት ከማሰብና ከመመርመር የሚያድነው ልዩ የሆነ መላ የለም»

ቀዳማዊው ሎርድ ኖዝክሊፍ ከተራ የሳምንት ደሞዝተኛነት ተነስቶ በመላው የእንግሊዝ ግዛት ታዋቂ የሆነ የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ባለቤትና እጅግ ሃብታም ለመሆን የቻለ ሰው ነበርና ለስኬቱ ያበቃውን ነገር ሲገልፅ ካነበባቸው ብዙ ነገሮች ይልቅ የፓስካል አንድ ዓረፍተ ነገር ህይወቱን ሲቀይረው እንደቻለ አምኗል:: ይኸውም:-

«የወደፊቱን ማየት መቻል ገዥ መሆን ማለት ነው»

ይህን አባባል እናንተም ንግግር በምታዘጋጁ ጊዜ ጠረጴዛችሁ ላይ ብታኖሩት ጠቃሚ ነው ንግግራችሁን እንዴት እንደምትጀምሩ ለማስተዋል ብትሞክሩ፣ እያንዳንዱ የምትሏትን ቃላት አእምሮችሁ እንዴት እንደሚይዘው ብታውቁ፤ እንዲሁም በንግግራችሁ መጨረሻ በአድማጮችሁ ላይ ምን አይነት ስሜት ስሜት መፍጠር እንደቻላችሁ ብታውቁ ከዚህ በኋላም እንደናንተ አይነት ስሜት ሲፈጥር የቻለ አለመኖሩን ብትረዱ እና የመሳሰሉት ሁሉ እያሰባችሁ ለእራሳችሁ መነቃቃትን መፍጠር ትችላላችሁ::

ከአርስቶትል መፈጠር በኋላ ባሉት ጊዜያት ውስጥ በዚህ ርዕስ ላይ የተፃፉ መፃህፍት አንድን የንግግር አይነት ሶስት ቦታ ላይ ከፋፍለውታል ይኸውም የንግግሩ መግቢያ፣ ዋናው ሃሳብ እና ማጠቃለያ ነው:: በንፅፅር ሲታይ እስከ ቅርብ አመታት ለሚባል ጊዜ የመግቢያ ሃሳብ የሚባለውን ነገር በዘፈቀደ በተናጋሪው ፍላጎት የሚደረግ ቀልድ አዘል ነገር ብቻ ነበር:: በዚያን ወቅት አንድ ለህዝብ የሚናገር ሰው እንደ ዜና አብሳሪና ሰዎችን የሚያዝናና ተደርጎ ይወሰድ

ነበር። ከብዙ መቶ አመታት በፊት ደግሞ ዛሬ ጋዜጦች ፣ሬድዮን፣ ቴሌቪዥንን፣ ፊልምና ቲያትሮች የተረኳቸውን ማህበረሰባዊ ፍላጎቶችን እነዚህ ተናጋሪዎች ለብቻቸው ይሰሩት ነበር።

አሁን ግን ሁኔታዎች ሁሉ ተቀያይረዋል፣ አለም እንደገና ተፈጥራለች ልዩ ልዩ ግኝቶችና ፈጠራዎች ህይወት እንዲፈጥን በማድረግ ከቤልሻዛርና ነቡከደነፆር በኋላ ባሉት ጊዜያት ሙሉ ለሙሉ እንዲቀየር አድርገውታል። ተሽከርካሪዎች፣ አውሮፕላኖች፣ ቴሌቪዥንና ሬድዮኖች ፣ የመሳሰሉት ሁሉ የህይወትን ግስጋሴ ፈጣን ስላደረጉት አንድ ተናጋሪም ከጊዜው መሻሻል ጋር እራሱን አጣጥሞ ሊሄድ ግድ ይለዋል። በዚህ ጊዜ ታዲያ የመግቢያ ንግግራችን ልክ እንደግድግዳ ማስታወቂያ አጠር ያለ ሊሆን ይገባል። «ምንድነው! የምትናገረው ነገር የለህም እንዴ?» ወይም« ቶሎ የምትለውን በልና ቁጭ በል» መባልን ሊያመጣ ይችላልና ነው።

ፕሬዝዳንት ዊድኖው ዊልሰን በሰርጓጅ መርከቦቻቸው ላይ በውጭ ኃይሎች ስለተሰነዘረባቸው ዛቻና ማስፈራሪያ ለኮንግረሱ ባሳወቀበት ወቅት ስለሚናገረው ነገር ምንነት ከገለፀ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ጉዳዩ የገባው ከተወሰኑ ቃላቶች በኋላ ነበር። ይህም «ሃገራችን ከሌሎች ሃገራት ጋር ባላት ግንኙነት ላይ አደጋ ሊያመጣ የሚችል ጉዳይ ተከስቷል። ይህንንም ለእናንተ የማሳወቅ ግዴታ አለብኝ» በማለት። ቻርልስ ዌብ በኒውዮርክ ለሚኖሩ የፔንስልቫኒያ ማህበረሰቦች ንግግር ሲያደርግ በነበረበት ወቅት ልክ ሁለተኛ ዓረፍተ ነገሩ ላይ ሲደርስ ወደ ዋናው ጉዳዩ ገብቶ ነበር።

የገንዘብ መቀበያ ማሽን አምራች ኩባንያ የሽያጭ ሰራተኛ የሆነው ግለሰብ በተመሳሳይ ሥራ ለተሰማሩ ባልደረቦቹ ገለፃ ሲያደርግ ለመግቢያ ያህል የተጠቀማቸው ሶስት ዓረፍተ ነገርን ብቻ ነበር። እነሱም ሊሰሟቸው የማይከብዱና ቀላል ነበሩ።

የተመረቱ ዕቃዎቹ እንዲሸጡ ገበያ አፈላልገው የሚያመጡ እንደናንተ ያሉ ሰዎች በምርት ጊዜ ከፋብሪካዎች የሚወጣው ጭስ እንዳይቋረጥ ማድረግ ይችላሉ። ካለፉት ሁለት ወራት ወዲህ ግን ከእኛ ፋብሪካ የሚወጣው ጭስ እጅግ ቀንሷል። ያ ሁኔታ ይህን ጊዜ አሁን ስላበቃና የንግድ እንቅቃሴውም መነቃቃት እየታየበት ስለሆነ ላሳስባችሁና ልጠይቃችሁ የምፈልገው አጭር የሆነ ጉዳይ ብዙ ጭስ ማየት እንደምንፈልግ ነው ።

ብዙ ልምድ የሌላቸው ተናጋሪዎች ግን እንደዚህ ቀላልና ግልፅ በሆነ መንገድ የመክፈቻ ቃላቶችን በመጠቀም ሊሳካላቸው ይችላል ትላላችሁ? አብላጫውን ቁጥር የሚይዙት ልምድ አልባና ያልሰለጠኑ ተናጋሪዎች የሚጀምሩበት አንድ ወይም ሁለት መንገድ አላቸው። ነገር ግን እንዳቸውም ጥሩዎች አይደሉም። እስቲ ቀጥሎ እንያቸው:-

## አስቂኝ ታሪኮችን በመናገር አትጀምሩ

እዚህ ግባ በማይባል ምክንያት ለመጀመሪያ ጊዜ ንግግር የሚያደርግ ሰው ሁሉ ግድ ማሳቅ መቻል ያለበት ይመስለዋል። እስቲ አስቡት ይህ ሰው እኮ



Scanned with CamScanner

የምሰራው ነበር:: ምክንያቱም አስመስለው ከሚሰሩ፣ ከነፍስ ገዳዮች፣ ከገንዘብ አጭበርባሪዎችና ከመሳሰሉት ድርጅቶች ውስጥ ከሚሰሩ አትሌቶች ጋር ያስተዋውቀኝ ስለነበር ነው (ሳቅ) አንድ በነፍስ ማጥፋት እድሜ ልክ የተፈረደበት ሰው አውቅ ነበር:: በጣም ብልህ የሆነና ሲናገር ደስ የሚል ልጅ እግር ቢጤ ነበር እናም የህይወት ታሪኬ የሚለውንና እንዴት ወደ ነፍስ ማጥፋት ወንጀል እንደገባ እንዲህ ሲል አጫወተኝ «ከእኔ ተሞክሮ ማየት እንደምትችለው አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ህገወጥ የሆነና የማጭበርበር ነገር ውስጥ ከገባ ይህ ነገር ወደ ሌላ ወንጀል ይመራዋል:: ቀጣዩ ነገር እንዲሁ በተራው ወደ ሌላ ወንጀል እየተላለፈ ይቀጥልና በመጨረሻ ላይ እራሱን ነፃ አውጥቶ ወደ ትክክለኛ ሰውነተ መመለስ የሚችልበት አማራጭ አንድ ብቻ ይሆናል:: ይኸውም ይህን እንቅፋት እየሆነ ያስቸገረውን ነገር በማስወገድ መሆኑን ይገነዘባል» (ሳቅ) እና የዚህ ሰው ሁኔታ በትክክል የሚገልፀው አሁን ያሉትን የካቢኔ አባሎች ነው :: (ሳቅ)

በዚህ አይነት መንገድ ሣቅ የሚያጭር ንግግር ካደረጉት መካከል የሚትሮፖሊታን የህይወት መድህን ኩባንያ የበላይ ጠባቂ ዊልያም ሃዋርድ ነበር::

ውድ ፕሬዝዳንት ክቡራን እና ክቡራት የህይወት መድህን ኩባንያ ሠራተኞች ከዘጠኝ ወራት በፊት ከድሮ አካባቢዬ ሄጄ አንድ ሰው ከእራት በኋላ በተደረገ ሥነ-ሥርዓት ላይ ንግግር ሲያደርግ አድምጬ ነበር:: እናም በንግግሩ ባለመተማመን ባደረበት ፍርሃት ለዚህ ንግግሩ ሲል በዚህ ዓይነቱ ግብዣ ላይ መናገር እጅግ ብዙ ልምድ ያካበተ አንድ ጓደኛውን አማክሮ እንደመጣ ገለፀ:: እንደ ጓደኛው ምክር ከሆነ ምርጥ የሆኑት በእራት ግብዣ ላይ የሚታደሙት አድማጭ ብልሆች፣ የተማሩና ከጭንቀትም ሆነ ድብርት ዘና ብለው የሚከታተሉት ናቸው:: እኔም ዛሬ የምላችሁ ነገር ልክ እንደሱ ሁሉ የዛሬ ምሽቱ አድማጮች ብልሆች፣ የተማሩና ከጭንቀትም ሆነ ድብርት ዘና ብለው የሚከታተሉ ናቸው:: የዛሬ ምሽት አድማ= ጩ እጅግ ምርጥ ከሆኑት መካከል የምትመደቡ መሆናችሁን አረጋግጣችኋለሁ:: አንድ የሆነ መንፈስ ግን ይህን ድብርት አስወግዶ ዘና እንድትሉ የረዳችሁ ይመስለኛል:: ይህውም የሚትሮፖሊታን የህይወት መድህን ድርጅት መንፈስ ነው:: (ጭብጨባና ሳቅ)

## ንግግርህን በይቅርታ ስትጀምር

ሁለተኛው እጅግ መጥፎ የሆነና ጀማሪ ተናጋሪ በፍፁም ሲጠቀምበት የማይገባ ነገር ይቅርታ በመጠየቅ ንግግርን መጀመር ነው:: «እኔ በእርግጥ ተናግሬ ባላውቅም . . . ለመናገር ዝግጅት ስላላደረኩ. . . . ምንም የምናገረው ነገር የለም . . . .» አትበሉ! አትበሉ! አንድ ኪፕሊንግ የፃፈው የግጥም ስንኝ እንዲህ ይላል «ሳልጨርስ ጀመርኩ! ሳልጀምረው ጨረስኩ» እናም አድማጩ በትክክል ከዚህ በኋላ የምትናገሩትን ነገር መቀበል አይፈልግም:: ለማንኛውም ለንግግራችሁ ያልተዘጋጃችሁ ቢሆን እንኳን ለሚያውቁ ሰዎች ባትናገሯቸውም እንኳን ይደርሱበታል:: ነገር ግን የማያውቁትን ሰዎች ምንም ትኩረት እንዲያደርጉ ታሳስቧቸዋላችሁ? አድማጮቻችሁንስ ለእናንተ ብዬ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም በሚል ስሜት ለምን እንደስድብ የሚቆጠር

ነገር ትናገራላችሁ? እነርሱ እዚያ ቦታ ላይ የተገኙበት ምክንያት እየተደሰቱ
መረጃ ለማግኘት ነው። ይህን ነገር በደንብ ማስታወስ ያስፈልጋል።

በመጀመሪያ ላይ ንግግርህን ለማቅረብ አድማጭ ፊት ስትቀርብ የሁሉንም ትኩረት ማግኘትህ አይቀርም። ለሚቀጥሉት አንድ አምስት ሰከንዶችም ይህ ትኩረታቸው አብሮህ ይቆያል። ችግሩ ያለው ለሚቀጥሉት አምስት ደቂቃዎች ይህን ጠብቆ በማቆየቱ ላይ ነው። አንድ ጊዜ ካጣኸው ደግሞ መልሶ ለማግኘት እጅግ አስቸጋሪና ከባድ ነው። ስለዚህ ምንጊዜም ቢሆን የመጀመሪያ አረፍተ ነገርህ ደስ የሚልና የሚስብ ሊሆን ይገባል። አስታውስ! ሁለተኛውና ሶስተኛው ነገርህ ደስ የሚልና የሚስብ ሊሆን ይገባል። አስታውስ! ሁለተኛውና ሶስተኛው
ሳይሆን የ.መ.ጀ.መ.ሪ.ያ.ው ዓረፍተ ነገርህ እንዴት? በማለት መጠየቃችሁ አይቀርም። እጅግም ሰፊ የሆነ ነገር ነው። እናም ምን አይነት መረጃዎችን በማቅረብ ማሟላት ይቻላል እያላችሁ ስዚህም ዋናውና ወሳኝ የሆነው ነገር የሚወሰነው በእናንተ ምርጫ፣ በአድማጩ፣ በርዕሰ ጉዳዩ፣ በያዛችሁት መረጃ፣ ንግግር በምታደርጉበት ምክንያት እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ይሆናል። ይህም ሆኖ ንግግር በምታደርጉበት ምክንያት እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ይሆናል። ይህም ሆኖ
ግን ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሃሳቦች በተለዋጭነት ሊያገለግሏችሁ ይችላሉ።

## የሰውን ጉጉት ጨምር

ሐዌል ሃሊ በፊላደልፊያ ውስጥ ለሚገኝ ፔን አትላንቲክ ክበብ ለተባለ ድርጅት ባቀረበው ንግግር ላይ የተጠቀመበት የመክፈቻ ንግግር ይኸውላችሁ፡-

ከ82 ዓመታት በፊት ልክ በዚህ ወር ላይ ህያው ልትሆን የበቃች አንዲት አጭር ታሪክ የያዘች መፅሐፍ ታትማ ነበር። እናም ብዙ ሰዎች ይህችን መፅሐፍ «የዓለም ታላቋ ግን ትንሽዋ መፅሐፍ» ብለው ይጠሩታል። ለመጀመሪያ ጊዜ «የዓለም ታላቋ ግን ትንሽዋ መፅሐፍ» ብለው ይጠሩታል። «አዲሱን መፅሐፍ ለገበያ የቀረበ አካባቢ እርስ በርሳቸው የሚገናኙ ጓደኛሞች «አዲሱን መፅሐፍ አንብባችኋል?» እየተባባሉ ያወሩ ነበር። እና መልሱ ሁል ጊዜ «እንዴታ! ብቻ እሱን እግዚአብሄር ይባርከው» የሚል ነበር።

ይህ መፅሐፍ በታተመበት ቀን ብቻ በሺዎች የሚቆጠሩ ቅጂዎች ሲሸጡለት አስራ አምስት ቀን ሳይሞላ ግን ይህ የቀን ሽያጭ ወደ ሃምሳ ሺህ ሊያሻቅብ ችሏል። ከዚያ በኋላ ላይ ባሉት ጊዜያት ደግሞ ለቁጥር በሚያታክት ሁኔታ ብዙ ጊዜያት ተደጋግሞ እየታተመ ተቸብችቧል። ከሰማይ በታች ባሉ ቋንቋዎች ሁሉ ተተርጉሞ በተለያዩ የዓለም ክፍል የሚኖሩ ሰዎች እንዲያነቡት ተደርጓል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ጄ.ፒ. ሞርጋን የተባለ ሰው ዋናውን የመፅሐፍ ቅጂ እጅግ ውድ በሆነ ዋጋ በመግዛት የእኔ ቤተ መጻህፍት ለሚለው የኒውዮርክ ስነ-ጥበባት ማዕከል ውስጥ ከሌሎች ዋጋ ሊወጣላቸው ከማይችሉ ስብስቦች ጋር እንዲቀመጥ አድርጎታል። ታዲያ ይህ በመላው ዓለም ሁሉ ዝነኛ ሊሆን የበቃ መፅሐፍ የትኛው ይመስላችኋል?

የቻርልስ ዲክንስ ክሪስማስ ካሮል . . . . .

ይህን የመግቢያ ንግግር እንዴት አያችሁት? ስኬታማ ሊባል የሚችል ይመስላችኋል? ጉጉት ኖሯችሁ እንድትከታተሉትስ አላደረጋችሁም? ንግግሩ እየቀጠለ ሲሄድስ የእናንተም የማወቅ ጉጉት በዛው ልክ አልጨመረም? ለምን?



Scanned with CamScanner

ምክንያቱ እንድትነቃቁና ቀጥሎ ምን እንደሆነ ለማወቅ በጉጉት እንድትወጠሩ ስላደረጋችሁ አይደለምን? ለምንም ነገር ጉጉት የለኝም የሚልስ ማን ይኖራል?

አልፕስ ተራራ ላይ ያለ አንድ አዳኝ ሰውነቱን በአንሶላ ጨርቅ በመሸፈንና በደረቱ እየተሳበ ብዙ ወፎች ወዳሉበት ቦታ በመጠጋት የእነሱን ትኩረት ያገኘ እንደሆነ ለማወቅ ጥረት ሲያደርግ ተመልክቻለሁ:: ውሻዎች፣ ድመቶች፣ በአጠቃላይ ሁሉም የእንስሳት ዘር ብልህ የሆነውን የሰው ልጅ ጨምሮ ጉጉት የሚያድሩባቸው ነገሮች አሏቸው:: ስለዚህ እናንተም የአድማጫችሁን ጉጉት ሊጨምር በሚችል ዓረፍተ ነገር ንግግራችሁን ብትጀምሩ ለቀጣይ ንግግራችሁ ሙሉ በሙሉ ትኩረታቸውን ታገኛላችሁ::

የዚህ መፅሐፍ ደራሲ ኮሎኔል ቶማስ ሎውራንስ በምዕራቡ ዓለም ያደረገውን የቅኝት ጉዞ አስመልክቶ ገለፃ ሲያደርግ ይህን መንገድ ተጠቅሞበታል ይኸውም:- ሊዮድ ጆርጅ ስለ ኮሎኔል ሎውረንስ ሲናገር እጅግ በጣም ሰው አፍቃሪና ካለበት ቦታ ጋር በቀላሉ የሚመሳሰል ዘመናዊ ሰው ነው ይለዋል::

ይህ የንግግር መክፈቻ ሁለት ጥቅም ዓለው:: አንደኛው የታዋቂ ሰውን ንግግር ጠቅሶ በመናገር የማንኛውንም ሰው ትኩረት ለመሳብ ይረዳል:: ሁለተኛው ደግሞ «ለምን አፍቃሪ አለው?» እና «ካለበት ቦታ ጋር እንዴት ነው የሚስማማው?» የሚሉ ጥያቄዎችን በአድማጭ አዕምሮ እንዲመላለስ በማድረግ ጉጉት እንዲኖር ማድረግ ስለሚቻል ነበር:: «ስለዚህ ሰው ሰምቼ አላውቅም:: ምን የሰራ ሰው ይሆን?» ብለን ለማዳመጥ ዝግጁ እንሆናለን::

ሎዌል ቶማስም ስለ ኮሎኔል ሎውረንስ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ በእየሩሳሌም የክርስቲያን ጎዳና ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ ወደታች እየወረድኩ ሳለሁ አንድ እንደሩቅ ምስራቅ ሰዎች ያለ ግልድም የለበሰና ከጎኑ ላይ ደግሞም የነብዩ መሃመድ፣ ተከታዮች የሚታጠቁትን ዓይነት ቆልማማ የወርቅ ጎራዴ የታጠቀ ልጅ እግር አጋጠመኝ:: ይህን ሰው ታዲያ ልብ ብዬ ስመለከተው ምንም ዓረብ ሊመስለኝ አልቻለም:: ምክንያቱም የዐይን ቀለሙ ሰማያዊ በመሆኑ ሲሆን የአረቦቹ ግን ሁልጊዜም ጥቁር ወይንም ቡናማ ብቻ ነበር::

ይህ ንግግር በሰማችሁት ነገር ብቻ ረክታችሁ እንድትቆሙ አያደርጋችሁም? ማነው? ለምን እንደአረቦች ለበሰ? ምን ሰራ? ምንስ ያጋጥመው ይሆን? በማለት ተጨማሪ ለማወቅ የምትፈልጓቸው ነገሮች እንዲኖሩ ያደርጋችኋል::

አንድ ተማሪ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ በማቅረብ ንግግሩን ጀምሮ ነበር:: አስራ ሰባት በሚሆኑ የዓለማችን ሐገራት ውስጥ ባርነት እስካሁን እንዳለ ታውቃላችሁ?

ይህ ጥያቄ ጉጉት ማሳደር ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም «ባርነት? በዚህ ዘመን? ለዛውም በ17 ሐገራት? እነማን ይሆኑ?» በማለት አድማጩን በድንጋይ መንፈስ እንዲዋጥ አድርጓል::

አንድ ሰው ንግግሩን ከመደምደሚያው በመጀመር አድማጩ ይህ ነገር በምን ምክንያት ሊከሰት እንደቻለ ለማወቅ እንዲጓጓ ማድረግ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ተማሪ በዚህ መልኩ ስሜት በመጫር ንግግሩን ጀምሯል፡፡

በህግ አውጪው አካል ውስጥ አባል የሆነ አንድ ሰው ይኸው የህግ አውጪ ምክር ቤት በስብሰባ ላይ እንዳለ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ዙሪያ በሁለት ማይል ርቀት የሚገኙ ታድፖሎች ወደ እንቁራሪትነት ሳይለወጡ በፊት እንዲወገዱ የሚጠይቅ ረቂቅ ህግ አቅርቦ ነበር፡፡ የሚያስቅ ነገር ነው አይደል? ተናጋሪው እየቀለደ ይሆን? እንዴት ግራ የገባው ነገር ነው? ይህ ነገር እውነትም ተደርጎ ይሆን እንዴት? ... አዎን! በማለት ተናጋሪው ንግግሩን ቀጥሏል፡፡

በሳተርዴይ ኢቨኒንግ ጋዜጣ ላይ የወጣ አንድ ርዕስ «የአሸባሪ ቡድኖች» የሚል ነበር፡፡ እነዚህ የአሸባሪ ቡድኖች የተደራጁ ይሆኑ? እንደ ስያሜያቸው የተደራጁ ቢሆኑ ነው፣ ግን እንዴት?

በእነዚህ በጣት በሚቆጠሩ ቃላት ቀጥሎ ለሚዘረዝርልን ነገር ምንነት ጥቂት ነገሮች ጠቅሶልን ሲያበቃ እንዴት ሊደራጁ እንደቻሉ ለማወቅ ጉጉት እንዲያድርብን ያደርገናል፡፡ እያንዳንዱ ሕዝብ ፊት የሚናገር ሰው እነኚህን የጋዜጣና የመፅሔት ፀሃፊዎች የሚጠቀሙባቸውንና የአንባቢውን ስሜትና ጉጉት እንዲጨምር የሚያደርጉ የቃላት አጠቃቀም ዘዴዎችን ለማወቅ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ በእርግጥም የታተሙ የንግግር ስብስቦችን ከማጥናት ይልቅ እነዚህ ፀሃፊዎች የሚጠቀሙባቸውን ቴክኒካዊ ዘዴዎች ማጥናት ለንግግር መክፈቻችሁ ብዙ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## ንግግርህን ስምን በትረካ ለትጀምርም

ሁላችንም ቢሆን አንድን ከእራሱ ልምድ በመነሳት ልክ እንደየትረካ አድርጎ የሚናገርን ሰው ማዳመጥ እንወዳለን፡፡ ሩሴል ኮንዌል «የአልማዝ ሄክታሮች» የሚለውን ገለፃውን ከስድስት ሺህ ጊዜ  በላይ በማስተማር በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ሊያገኝበት ችሏል፡፡ ይህ እጅግ ድንቅ የሆነ ገለፃ እንዴት ይሆን የሚጀምረው?

በ1970 የጢግሮስን ወንዝ ተከትለን ቁልቁል ወደታች ወረድን ባግዳድ ውስጥ በነበርን ጊዜም ፔርሲግሊስን፣ አንቪንና ባቢሎንን እያስጎበኘ መንገድ የሚመራንን ሰው ቀጥረን ስለነበር . . .እያለ በታሪኩ ይዞን ይሄዳል፡፡ ይህ አጀማመር በጣም ልብ አንጠልጣይ በመሆኑ ያጓጓል፡ እንዲህ ዓይነቱ የመክፈቻ ንግግር ሊሰናከል አይችልም፣ ይቀጥላል፣ ይነጉዳል፡፡ እኛም ቀጥሎ ምን ይከሰት ይሆን እያልን አብረን ተከትለነው እንነጉዳለን፡፡ እኔም በዚህ መፅሐፍ (ክፍል አራት) ላይ ይህን ተጠቅሜዋለሁ፡፡ ቀጥሎ የማቀርበው የሳተርዴይ ኢቭኒንግ ጋዜጣ ካተመው ዜና ላይ የተቀነጨቡ ሁለት ታሪኮች ናቸው፡፡

1. የሪቮልቨር ሽጉጥ የመቀባበል ድምፅ ፀጥታውን አደፈረሰው
2. ይህ ድርጊት በራሱ ብቻውን ጉዳት የሚያስከትል ባይሆንም ሊያደርስ ከሚችለው ጉዳት አንፃር ሲታይ እንዲሁም በሞንትቪው ሆቴል ውስጥ በሃምሌ መጀመሪያ ሳምንት ከደረሰው ነገር ወዲህ ግን የማይረባ ነገር ነው ልንለው አንችልም፡፡ ይህም ድርጊት የመኖሪያ ቤቶቹ አስተዳዳሪ የሆነውን የጎቤልን ቀልብ በመሳቡ ለሞንትቪው

ሆቴልና ብዙ የፍራዳይ ሆቴሎች ባለቤት ለሆነው ስቲቭ ፍራዳይ የሥራ ጉብኝት በማድረግ ላይ እንዳለ ስለ ጉዳዩ አሳስቦ ሲገልፅለትና ሲያመለክት በቅቷል::

እነዚህ የመክፈቻ ሀሳቦች በድርጊት የተሞሉ መሆናቸውን አስታውሱ:: በከፍተኛ ሁኔታ ጉጉት የሚጨምሩ በመሆናቸውም ብዙ ገፍተን እንድናነብ ያደርጉናል፡ ጉዳዩ ስለምን እንደሚያወራ እስክናውቅ ድረስም አናቋርጥም::

አንድ ምንም ልምምድ ያልነበረውና ጀማሪ ተናጋሪ እንኳን እነዚህን ተራ የሆኑ ዘዴዎች ከተጠቀመና ጉጉታችሁን ለመጨመር ከቻለ የተሳካ የንግግር መክፈቻ ሊያደርግ ይችላል::

## በምሳሌ ከተብራራው ሃሳብ ንግግርህን ጀምር

በአብዛኛው አድማጭ ዘንድ ድፍንፍን ያሉ ንግግሮች አሰልቺና ለብዙ ሰዓት ለማዳመጥ የማይመቹ ናቸው:: በምሳሌ የተብራሩ ከሆነ ግን ለማድመጥ እጅግ ቀላልና ምቹ ይሆናሉ:: ስለዚህ ለምን በዚህ መልክ ለመናገር አትሞክሩም? ይህን ነገር በእርግጥም ተናጋሪዎች በተግባር እንዲያውሉ ለማድረግ ከባድ ነው:: ምክንያቱም እኔ ለማስተማር ሙከራ በማደርግበት ጊዜ እንደማውቀው ብዙ ተናጋሪዎች ንግግራቸውን መጀመር ያለባቸው የግድ ካጠቃላይ ሃሳብ በመነሳት ይመስላቸዋል:: ይህ ልክ አይደለም:: በምሣሌ ከተብራሩት ነጥቦችህ በመጀመር የሰዎችን የማድመጥ ፍላጎት ለማነሳሳት ትችላለህ:: ከዚያ በኋላ ጠቅለል ያለውን መደምደሚያ ሃሳብ ለማቅረብ ትችላለህ:: (ይህን ዘዴ ለማለት ክፍል ስድስትን ተመልከቱ) አሁን እያነበባችሁ ያለውን ክፍል ለመጀመር ምን አይነት ዘዴ ተጠቀምን?

## ዕቃዎችን እንደማሳያ ተጠቀም

ምናልባትም በዓለማት ላይ ካሉ የሰውን ቀልብ በቀላሉ ከሚስቡ ነገሮች ሁሉ እጅግ ቀላል የሆነው አንድን ዕቃ ከፍ አድርጎ ለሰዎች ማሳየት ሳይሆን አይቀርም:: አውሬዎች፣ የዝግመት ችግር ያለባቸው ሰዎች፣ ህፃናቶች፣ በአጥር ውስጥ ያሉ ጦጣዎች በመንገድ ላይ ያሉ ውሻዎች እንኳን በዚህ ድርጊት በጣም ይሳባሉ:: በተለይ ይህ ዘዴ እጅግ በምታከብራቸው አድማጮችህ ፊት ሲሆን እጅግ ውጤታማ ነው::

ለምሳሌ:- የፊላደልፊያው ተወላጅ ሚስተር ኤስ ኤስ ኢሊስ በአንድ ንግግሩ ላይ በአውራ ጣቱና አመልካች ጣቱ መካከል አንዲት ሳንቲም በመያዝ እጁን ከፍ አድርጎ በማንሳት ንግግሩን ጀበሯል:: ይሄን ድርጊት በመጀመርያ ላይ ዝም ብለው ሲመለከቱት «እንደዚህች አይነት ሳንቲም ከመሬት ወድቆ ያገኘ ሰው እዚህ ይኖራል? ሲል ጠየቀ:: እከሌ የተባለው የቤቶች ሥራ ድርጅት ላገኘው ሰው የነፃ መሬት በመስጠት ቤት ሊሰራላችሁ ዝግጁ እንደሆነ እያወጀ ነውና ሳንቲሙን ያገኘ ሰው ማድረግ ያለበት ስልክ በመደወል ይህን ሳንቲም ማስረከብ ብቻ ነው . . .» እያለ ገለፃውን ከቀጠለ በኋላ ግን ድርጅቱ ገበያ ለማግኘት ብሎ የተከተለውን መንገድ አሳሳችና ምግባረ ብልሹ የሆነ አሰራር በመንቀፍና በመተቸት ንግግሩን አጠቃሏል::

## ጥያቄ ጠይቅ!

የሚስተር አሊስ በንግግሩ መክፈቻ ሌላ ጠቃሚ የሆነ ነጥብም አካቷል፡፡ ይኸውም ጥያቄ በመጠየቅ መጀመርና አድማጩ መልሱ ምን ይሆን እያለ በመመራመር አብሮ እንዲጓዝ ማድረግ ነው፡፡ የሳተርዴይ ኢቨኒንግ ጋዜጣም በመጀመሪያው ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ላይ ሁለት ጥቄዎችን በመጠየቅ ጀምሯል «አሽባሪዎቹ በእርግጥ የተደራጁ ናቸውን? እንዴት?» የጥያቄ ዋና ጥቅሙ የአድማጭን አእምሮ ከፍቶ ለመግባት እጅግ ቀላልና አስተማማኝ የሆነ ዘዴ መሆኑ ነው፡፡ ያሉንን መሳሪያዎች ሁሉ ተጠቅመን ውጤት ካላገኘን ይህን ዘዴ ተጠቅመንበት በቀላሉ ከችግር መውጣት እንችላለን፡፡

## ዝነኛ የሆነ ሰው ያነሳውን ጥያቄ ተጠቅመህ ለምን ንግግርህን አትከፍትም?

ታዋቂና ዝነኛ ሰዎች የተናገሯቸው ቃላቶች ሁልጊዜም ትኩረት የመሳብ ከፍተኛ ኃይል አላቸው፡፡ ስለዚህም የእነዚህን ሰዎች ንግግር በመጥቀስ ትኩረት የሚስብና ኃይል ያለውን ንግግር ለማድረግ መሞከር ምርጥ የሆነው ዘዴ ነው፡፡ እስቲ ቀጥሎ ያለውን ለስራ ስኬታማ ስለመሆን የሚያነሳውን የውይይት መክፈቻ ይስማማህ እንደሆነ ሞክረው፡፡

ኤልቨርት ሁባር እንደገለጸው «ዓለም ታላቅ ገፀ-በረከቷን በገንዘብና በክብር ሽልማት ታንበሸብሽናለች፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ደግሞ ይቀራል ይህም ተነሳሽነትን ነው፡፡ ተነሳሽነት ምን ማለት ነው?»

ይህ እንደንግግር መጀመሪያ ሲታይ በርካታ ጠቀሜታ ያለው ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያው ዓረፍተነገር ጉጉት እንዲያድርብን ያደርገናል ወደፊት የሚሆነውን እያሰብንም እንድናዳምጥ ያደርገናል፡፡ ተናጋሪው የታዋቂውን ሰው ስም ኤልበርት ሁባርድ ብሎ ከጠቀሰ በኋላ ትንሽ ቆም ማለት ቢችል ደግሞ ስሜታችንን ቀፍድዶ መያዝ ይችል ነበር፡፡ ዓላማችን ታላቅ የሆነውን ገፀ-በረከቷን የምትሰጠን ለምንድ ነው? ብለን እንጠይቃለን፡፡

«ፍጠን! ንገረን እንጂ!» ምናልባት በምትለው ነገር ላንስማማ ብንችልም እንስማው እስቲ . . . . ከዚያ በሁለተኛው ዓረፍተ ነገሩ ደግሞ የጉዳዩን ፍሬ ነገር ዱብ ያደርገዋል፡፡ በሶስተኛው ዓረፍተ ነገሩ ደግሞ አድማጩን በጥያቄ ወጥሮ የውይይቱ ተሳታፊ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ትንሽ እንድናስብ በማድረግም ሥራ ይሰጠናል፡፡ አድማጭ ደግሞ እንዲህ ዓይቱን ነገር ሲሰጠው በፍቅር ይሰራዋል፡፡ አራተኛው ዓረፍተ ነገሩ የተነሳሽነትን ምንነት ያብራራል፡፡ ከዚህ የመክፈቻ ንግግሩ በኋላ የሰውን ትኩረት ስለሚያገኝ የፈለገውን ታሪክ ጥርት አድርጎ እየገለጸ መሄድ ይችላል፡፡ የንግግሩ አደረጃጀትን በተመለከተ ግን ሚዛን ሲደፋ የሚችለው የአድማጭን ስሜትና ፍላጎት የማጠብቅ ሲሆን ነው፡፡

## የንግግርህን ርዕስ በአድማጭህ ፍላጎት ላይ አድርግ

እዚህ ላይ ንግግርህን ስትጀምር አድማጭህን በግሉ ደስ ሊያሰኝ ይችላል ብለህ በምታስበው ነገር ላይ በቀጥታ ገብተህ ተናገር፡፡ ይህ ከምርጥ የንግግር

መክፈቻ መንገዶች አንዱ ነው። ያለጥርጥርም ትኩረትን ለማግኘት የሚያስችል ነው። ማንኛችንም በግል የሚመለከተንና የሚነካንን ጉዳይ መከታታል እንወዳለን።

ለምሳሌ ያህልም አንድ ተናጋሪ በየጊዜው ተከታታይ የሆነ የጤና ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ሲናገር ከሰማሁት ላካፍላችሁ። እንዴት የጀመረ ይመስላችኋል? አንድ እድሜን ለማራዘም የሚረዳ ምርምር ስለሚያደርግ ተቋም አመሰራረት የተመለከተ ታሪክ በማውራት ይሆን? እንዲህ ከሆነ ግራ የተጋባ መክፈቻ ነው የሚሆነው። አድማጭም አንድ ካምፓኒ እንዴት እንደተቋቋመና ምን ለመስራት እንደሚንቀሳቀስ ለማድመጥ ያለውን ፍላጎት ስለእራሱ የሚነገርን ነገር ከማድመጥ ጋር ሲነፃፀር እጅግ አናሳ ነው። ከዚህ ይልቅ ይህ ኩባንያ ለእነሱ ሊሰጥ የሚችለውን ጠቀሜታ በመግለፅ ለምን አትጀምሩም እንደዚህ ብትሉስ?

«እንደ የህይወት መድህን ድርጅቶች መግለጫ ከሆነ ምን ያህል ዕድሜ ለመኖር እንደምትችሉ ታውቃላችሁ? የመድህን ድርጅት ስታስቲክስ ሰራተኞች እንደሚሉት በህይወት የምትቆዩበት ቀሪ ዕድሜያችሁ አሁን ባላችሁ ዕድሜና በሰማንያ ዓመት መካከል ያለውን ዕድሜ ልዩነት ሁለት ሶስተኛ የሚሆነውን ነው ለምሳሌ አሁን ዕድሜው 35 ዓመት የሞላው ሰው አሁን ባለው ዕድሜውና በሰማንያ ዓመታት መካከል ያለውን ልዩነት 45 ዓመት ነው እናም ከዚያ ውስጥ ሁለት ሶስተኛውን በመውሰድ 35 ዓመት ላይ ስትደምሩት ቀሪ ዕድሜያችሁን ልታውቁ ትችላላችሁ ማለት ነው። ነገር ግን ይሄ ዕድሜ ብቻ ይበቃናል ትላላችሁ? በፍፁም አትሉም። ሁላችንም ይበልጥ ብዙ ለመኖር እንጓጓለን። ቢሆንም ግን ይህ መረጃ ሊደረስበት የቻለው በብዙ ሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ጥናት ተደርጎና ውጤቶቹም ከተሰበሰቡ በኋላ ነበር። ስለዚህም እኔና አንተ ይህን ወሰን ጥሰን ለማለፍ ጥረት ማድረግ መጀመር ይኖርብናል። የመጀመሪያው እርምጃችን ደግሞ አጠቃላይ የሆነ የጤና ምርመራ ማድረግ ነው።»

በዚህ ዘዴ ተከታታይ የሆነ የጤና ምርመራ ስለ ማድረግ አስፈላጊነት ከገለፅን በኋላ አንድ የሆነ ኩባንያ ደግሞ ይህን አገልግሎት እንዴት ሊሰጠን እንደተዘጋጀና እንደተቋቋመ ብንገልፅ አድማጩ በትኩረት ሊከታተለን ይችላል ማለት ነው። ነገር ግን በቀጥታ ስለኩባንያው አመሰራረት መናገሩ ጥፋት የሚያስከትልና ንግግራችንን ሁሉ የሚገድል ነው። ሌላ ምሳሌ ልስጣችሁ፣ አንድ ተማሪ ደኖቻችንን መንከባከብ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑን በመግለፅ ንግግሩን ሲያደርግ አድምጫለሁ።

«እኛ አሜሪካውያን ባለን የተፈጥሮ ሐብት ልንኮራ ይገባናል። ከዚህ የመክፈቻ ንግግሩ በኋላ ግን ይህ የደን ሃብት ያፈራውን የጣውላ ምርት ያለርህራሄ ሊተካ በማይቻል ፍጥነት እያባከነው እንደሆነ ማሳየት ይቻላል ነገር ግን የመክፈቻው ዓረፍተ ነገር በጣም ጥቅል የሆነ ሃሳብ የያዘ፣ ግልፅ የሆነና መጥፎ የማይባል አይነት ነበር። በአድማጩ መካከል በህትመት ሥራ የተሰማሩ ወይም ከእንጨት የሚሰሩ ነገሮችን የሚያመርቱ ይኖራሉ፤ እነዚህ ሰዎች ቀጥታ ችግሩ ይመለከታቸዋል። ይህ ማለት ደግሞ የሀገሪቷን ምጣኔ ሀብት ስለሚጎዳ የባንክ ሰራተኛውም ይመለከተዋል ማለት ነው። ስለዚህ እንዲህ ብሎ ቢጀምርስ «አሁን የሚነሳው ጉዳይ የአቶ እገሌን ስራ የሚጎዳ እንዲሁም የወ/ሮ እከሊትን

Scanned with CamScanner

ሥራ የሚመለከትና በአጠቃላይ በምግብ ዋጋችን በቤት ኪራይ ላይ ጭማሪ የሚያስከትል በበጎ አድራጎትና በዕድገታችን ላይ ደግሞ ከፍተኛ ጉዳትን ስለሚያስከትል ነገር ነው»

ይህ የደን ሀብት መንከባከብን አስመልክቶ ያለውን ጥቅም እጅግ አጋኖ ይናገራል ትላለህ? እኔ አይመስለኝም ከዚያ ይልቅ የኤልበርት ሀባርድን ንግግር ተጠቅሞ ያቀረበው ይመስለኛል:: ይኸውም:- «ስዕልህን በትልቁ ከሳልከው በኋላ ነጥብህን ትኩረት እንዲሰጠው አድርገህ በውስጡ አስቀምጠው::» የሚለውን

## አስደንጋጭ እውነታዎች ያላቸው ሰውን

## የመሳብ ኃይል

ኤስ.ኤስ ማክሴር የተባለ የፔሬዲካል ጋዜጣ መስራች ሲናገር «ጥሩ የመፅሔት አዘጋጅ ማለት አስደንጋጭ የሆኑ ርዕሶችን የያዘው ነው» ይላል እንደዚህ ያሉ ርዕሶች ትኩረታችንን እንድንሰጣቸው በማስገደድ ስሜታችንን ጨምድደው በመያዝ ካለንበት የቀን ቅዠት ጎትተው የሚያወጡን ናቸው::

ለምሳሌ:- የባልቲሞሩ ሚስተር ኤን.ኢ.ባለንቲን የሬድዮ ታዕምራት በተሰኘው ንግግሩ ላይ ለመክፈቻነት የተጠቀመውን ንግግር እንመልከት:-

አንዲት ኒውዮርክ ውስጥ ከመስታወት ላይ እየተጋጨች ጥዝ.ዝ የሚል ድምፅ የምትፈጥር ዝንብ ብትኖር ይህን ድምፅ በሬዲዮ አማካኝነት በመካከለኛው አፍሪካ ውስጥ ልክ እንደ ኒጋራ ፏፏቴ ጎልቶ እንዲሰማ ማድረግ እንደሚቻል ታውቃላችሁ? ሚስተር ሃራ.ሂ.ጀንስ በኒውርክ ያለው የሃራ.ጂ.ንስ ኩባንያ ፕሬዝዳንት ሲሆን በወንጀለኝነት ጉዳይ ላይ ንግግር ሲያደርግ እንዲህ ብሏል:: የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበረው ዊልያም ሃዋርድ አስረግጦ ሲናገር «የምንተዳደርበት የወንጀለኛ መቅጫ ህጋችን ለስልጣኔ ማፈሪያ የሆነ ነው» ብሏል:: ይህ መክፈቻ ንግግር ሁለት ጥቅም አላመጣም ለምን ቢባል አስደንጋጭ ሆኖ መጀመሩና በጉዳዩ ላይ ደግሞ እጅግ ተስሚነት ያለውን ሰው መጥቀሱ ነው::

ሚስተር ፓል ጊቦንስ የፊላደልፊያ ተስፋ ክበብ ፕሬዘዳንት ሲሆን በወንጀል ጉዳይ ላይ አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ በመናገር መግለጫ ሰጥቶ ነበር:: አሜሪካኖች በአለም ላይ ካሉት እጅግ አደገኛ ወንጀለኞች ሁሉ የከፉት ናቸው:: ይህ አገላለፅ ባይዋጥላችሁም እውነታው ግን ይኸው ነው በክሊቭላንድ እሃቶ የሚፈጸመው የግድያ ወንጀል በለንደን ከሚፈጸመው ጋር ሲነጻጸር በስድስት እጥፍ የበለጠ ነው:: ለንደን ካላት የህዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸርም ሃዩ የሚፈጸመው የዘረፋ ወንጀል በ170 እጥፍ የበለጠ ነው በየአመቱም መላው እንግሊዝ፣ ዌልስና ስኮትላንድ በጋራ ሆነው ከሚደርስባቸው በላይ ብዙ ሰዎች ይዘረፋሉ፣ ለጥቃት ይጋለጣሉ ወይም ይደበደባሉ:: በሴንት ሉዊስ ደግሞ በመላው እንግሊዝና ዌልስ ከሚፈጸመው በላይ የነፍስ ግድያ ይፈጸማል:: በኒው ዮርክ ብቻ የሚፈጸመው የነፍስ ግድያ ወንጀል በፈረንሳይ፣ በጀርመን ወይም በጣያልያን ከሚፈጸመው ሁሉ የበለጠ ነው:: አሳዛኙ ነገር ታዲያ ወንጀለኞቹ ሳይቀጡ መቅረታቸው ነው በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ህይወትህን በቅጣት ልታጣ የምትችልበት እድል ከመቶ አንድ ብቻ ነው:: ከዚህ ይልቅ አንድ ሰላማዊ የሆነ ዜጋ አንድን ሰው በጥይት

በካንሰር በሽታ ተሰቃይቶ ገድሎ ነፍሱን በቅጣት ከመንጠቅ በአስር እጥፍ ለመሞት ያለው ዕድል ይበልጣል::

ሚስተር ጊቦንስ ቃላቶቹን በሚገባና ትህትናን በተላበሰ መልኩ እያዋቀረ ስለተጠቀመባቸው የንግግሩ መክፈቻ ስኬታማ ሊሆን በቅቷል:: እስትንፋስና ህይወት ያላቸው ቃላት ነበሩ:: በተመሳሳይ የወንጀል ርዕስ ላይ ንግግራቸውን የጀመሩ ሌሎች ተማሪዎች ያጋጠሙኝ ቢሆንም የመክፈቻ ንግግሮቻቸው እዚህ ግባ የማይባሉ ነበሩ:: ለምን? ብትሉ መልሱ ቃላቶች፣ ቃላቶች፣ ቃላቶች፣ የሚለው ይሆናል:: ምክንያቱም ንግግራቸውን ያደራጁበት መንገድ ጥሩ ሆኖ እያለ የተጠቀሙባቸው ቃላቶች ግን ባዶና ህይወት አልባ ስለነበሩ ነው:: ይህ የንግግር ዘይቤያቸውን ሁሉ በማመንመን ሲናገሩት የፈለጉትን ሃሳብ እንዲበላሽባቸው አድርጎታል::

## በአጋጣሚ የተገኘ በሚመስል ሃሳብ መጀመር ያለው ጥቅም

በአጋጣሚ የተገኘ በሚመስል ሃሳብ መጀመር ያለው ጥቅም

ቀጥሎ የቀረበውን የንግግር መክፈቻ እንዴት ተመለከታችሁት? ለምን? ሳራ ራችምንድ የተባለች ሴት በአመታዊው የኒውዮርክ ሴት መራጮች ሊግ ላይ ተገኝታ ያደረገችው ንግግር ይህ ነበር::

«ትናንትና ከዚህ ብዙም የማይርቅ ከተማን በፈጣን ባቡር ተሳፍሬ እያቋረጥኩ በነበርኩበት ጊዜ ልክ በዚያ ሰዓት እዚያው ከተማ ውስጥ ከጥቂት ዓመታት በፊት የተፈጸመ ጋብቻን እንዳስታውስ አድርጎኝ ነበር:: ምክንያቱም በዚህ ሃገር እየተፈጸሙ ያሉ ብዙ ጋብቻዎች ልክ እንደ ባቡሩ ሁሉ በጥድፊያ የሚካሄዱና በጥፋት የሚደመደሙ ነበሩ:: ስለዚህም ነው ከዚህ በግሌ ካጋጠመኝ ሁኔታ በመነሳት ዛሬ ልናገር የምፈልገውን ነገር የምቀጥለው::

ቀኑ ታህሳስ 12 ነበር አንዲት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን የጨረሰች የ15 ዓመት ልጃገረድ በዚያው ከተማ ባለ ኮሌጅ ውስጥ ትምህርቱን ገና ከጀመረ ወጣት ጋር ትተዋወቃለች:: ከሶስት ዓመት በኋላም ማለትም ታህሳስ 15 ቀን ልጅቷ ዕድሜዋ 18 ዓመት እንደሞላት በመሐላ አረጋግጠው የጋብቻ ፍቃድ በማግኘት ሌላ የወላጅ ፈቃድ ሳያስፈልግ ለመጋባት የሚችሉበትን አጋጣሚ አመቻቹ:: ይህን ፍቃድ ይዘው አንድ የካቶሊክ ቄስ ዘንድ በመሄድ እንዲያጋባቸው ጥያቄ ያቀርባሉ:: ቄሱ ግን ተገቢ የሆነ ምክንያቱን በመግለፅ እንደማያጋባቸው ገለጸላቸው:: የልጅቷ እናት በቄሱ አማካኝነት ልጇ ያደረገችውን የጋብቻ ሙከራ ዜና ሰማች:: ነገር ግን ልጇን ከማግኘቷ አስቀድሞ የማህበራዊ ፍርድቤቱ ጥንዶቹን አጋብቷቸው ነበር::

ከዚህ በኋላ ሙሽራው ሙሽሪትን በአንድ ሆቴል ውስጥ ይዟት ይገባና ለሁለት ቀንና ለሊት አብሯት ካሳለፈ በኋላ ጥሏት ይጠፋል፤ ከዚያ ወዲህም በፍጹም አብሯት አልታየም:: እኔ በግሌ ይህን የመክፈቻ ንግግር ወድጄዋለሁ:: ከመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ጀምሮ ያሉት ቃላት ጥሩ ናቸው ያለፈውን ነገር በትዝታ መልክ እያመጣልን የወደፊቱን ለመተንበይ የሚሞክር ንግግር ነበር:: ሰውን ሊማርክ የሚችል ንግግር ደግሞ ማንም ተረጋግቶ በመቀመጥ እንዲያዳምጥ የማድረግ ኃይል አለው:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ንግግሩ የተጠና እና ሥነ-ሥርዓታዊ በሆነ መልኩ የቀረበ ሳይሆን ተፈጥሯዊ የሆነ ነበር ...

«ትናንትና ከዚህ ብዙም የማይርቅ ከተማን በፈጣን ባቡር ውስጥ ሆኜ እያቋረጥኩ ነበር እናም ልክ በዚያ ሰዓት እዛው ከተማ ውስጥ ከጥቂት ዓመታት በፊት የተፈጸመ ጋብቻን እንዳስታውስ አድርጎኝ ነበር»

ይህ ንግግር በእርግጥም የፈጠራ ያልሆነ በግብታዊነት የተነገረና ፍፁም ተፈጥሯዊ የሆነ ነው። አንድን ደስ የሚል ታሪክ ከሌላኛው ጋር እያዛመደ እንደሚነግረን ሰው አይነት ጣዕም አለው። አድማጭም በጣም ወዶታል። ነገር ግን ይህ ታሪክ እጅግ በተብራራ ባማረ መልኩ ቢቀርብ ብዙ ዝግጅት ከተደረገለት የአድማጭን የቀናት ስሜን ባዘለ ሁኔታ የተነገረ ቢሆን አድማጩን በማስደንገጥ ለጉዳዩ የሚሰጠውን ትኩረት ችላ እንዳይለው ያደርገዋል።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ንግግራችንን እንዴት መጨረስ አለብን?

በምታደርጉት ንግግር ውስጥ የትኞቹ የተናገራችኋቸው ነገሮች ልምድ፣ እውቀትና፣ ችሎታ የሌላቸው መሆኑን አሲያም ያላችሁን የአስተሳሰብ ደረጃና ምጥቀት እንዲሁም ግንዛቤ የሚገልፁ ወይም የሚያሳውቁ መሆናቸውን የማወቅ ፍላጐቱ አላችሁ? በቲያትር ዓለም ውስጥ የሚነገርና የተለመደ አንድ የቆየ አባባል አለ፡፡“ በመድረክ ላይ የተውኔት ባለሙያዎችን ችሎታ ለማወቅ አጀማመራቸውንና አጨራረሳቸውን ብቻ መመልከት በቂ ነው፡፡

አጀማመርና አጨራረስ! እነዚህ ሁለት ነገሮች በጣም አስቸጋሪ የሆኑና የምንሠራቸውን ማንኛቸውንም ዓይነት ስራዎች በብልሃት ለመምራትና ለማከናወን የማያስችሉን ናቸው፡፡ ለምሣሌ ማህበራዊ ነክ በሆኑ ጉዳዩች ላይ የምናደርገውን ንግግር በሚስብ ባማረ፣ በሚማርክና፣ በሚያሣምን ሁኔታ በመጠቅለል መጨረስ መቻል ወይም አለመቻላችን እንዲፈፀሙልን ለምንፈልጋቸው ተግባሮች ወይም እንዲከናወኑልን ለምንፈልጋቸው ስራዎች መፈፀም ቁልፍ የሆኑትን መልእክታችንን ለአድማጮቻችን ለመንገር ወሳኝና አስፈላጊ አይደለምን? በንግድ ስራ መስክ ውስጥም በምናደርጋቸው ንግግሮች. . . በጣም ከባዱና አስቸጋሪው ነገር ሠዎችን በማግባባትና በማሣመን በንግድ ልውውጡ አሸናፊ የሚያደርገንን ንግግር መናገር መጀመርና በዚያው መልኩ መጨረስ አይደለም፡፡

የንግግር የማጠቃለያው ወይም የመጨረሻው ክፍል ሠዎች በሚያደርጓቸው ማንኛውም ዓይነት ንግግሮች ውስጥ በጣም ወሳኙና ቁልፍ የሆነው ክፍል ነው፡፡ አንድ ሠው በንግግሩ ማጠቃለያ ላይ የሚጠቀማቸው ቃላቶች ከጆሮ የማይጠፉና ለረጅም ጊዜ የሚታወሡ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ ንግግር አድራጊዎች የንግግራቸውን ማጠቃለያ የማይረሣ ወይም ሁሌም የሚታወስ እንዲሆን ማድረግ ያለውን ትልቅ ጠቀሜታ አይረዱትም፡፡ ስለሆነም ንግግራቸውን የማያጠቃልሉበት ሁኔታ «መልዕክታቸውን በትክክል በሚገልፅ በሚስብና በሚማርክ ሁኔታ መናገር የሚችሉ ንግግር አድራጊዎች» ተብለው ተመራጭ ለመሆን አያበቃቸውም፡፡ ጀማሪዎች በተደጋጋሚ በንግግራቸው መጀመሪያና መጨረሻ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምንድን ናቸው? እስቲ ስለነዚህ ችግሮች ትንሽ እንወያይና ስህተቶቹን ለማስተካከል የማያስችሉ መፍትሄዎችን እናስቀምጥ፡፡

የመጀመሪያዎቹ ጀማሪ ተናጋሪዎች ንግግራቸውን በሚያጠቃልሉበት ጊዜ “በጉዳዩ ዙሪያ ልለው የምችለው ነገር በሙሉ ይኸው በመሆኑ እዚህ ላይ አቆማለሁኝ ” ብለው የሚናገሩ ናቸው፡፡ ይህ ተገቢና ትክክለኛ የሆነ የንግግር

አጨራረስ መንገድ አይደለም፡፡ ፍፁም ስህተት የሆነ ነው፡፡ ጀማሪነትን የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁን ተብሎ እንኳን በዝምታ የሚታለፍ ዓይነት ስህተት ብቻም አይደለም፡፡ አንድ ንግግር አድራጊ ሲናገረው የሚችለውን በሙሉ ያለ ከሆነ መናገር የምችለው ይኸው ስለሆነ እዚህ ላይ አቆማለሁ ብሎ ከመናገሩ በፊት ንግግሩን ማቆም ይችላል፡፡ እስቲ ይኸን አድርግና ምናልባትም አድማጩ በጥሩ ሁኔታ ንግግርህን በማቅረብ መልዕክትህን እንዳስተላለፍክ አድርጐ የሚወስድበትን ስሜት ልትፈጥር የምትችል ከሆነ ማለትህን ሞክር፡፡

ሁለተኛዎቹ ተናጋሪዎች ወይም ንግግር አቅራቢዎች ደግሞ "ብዙ እንደተናገሩና ንግግራቸውን እንዴት ማቆም እንደሚችሉ እንኳን እንደማያውቁና ለማቆም እንደሚቸግራቸው" በመግለፅ ንግግራቸውን የማያጠናቅቁ ናቸው፡፡ ጆሽ ቢሊንግ ለሠዎች ምክር ሲለግስ ሁሌም ይናገራቸው ከነበሩት ነገሮች ውስጥ አንዱ " የኮርማ በሬውን ቀንዱን ሣይሆን ጅራቱን ያዝ፡፡ መልቀቅ ሲያስፈልግህ ለመልቀቅ በጣም ቀላል ስለሆነ" የሚለው ይገኝበታል፡፡ የዚህ ዓይነቱም ንግግር አቅራቢ ኮርማ በሬውን ከፊት ለፊቱ ተጋፍጦ ቀንዱን በመያዝ የተወሠነ ርቀት ድረስ አብሮት እንዲጓዝ ለማድረግ ያለውን ሃይል ሁሉ በመጠቀም የሚፍጨረጨርና ኮርማ በሬውን ከሚፈልግበት ቦታ ለማድረስ ወይም አንድ ቦታ ላይ ለማሠር የማይችልና የሚሣነው ይሆናል፡፡ ስለዚህ የዚህ ዓይነቱ ተናጋሪ በአንድ ሃሣብ ዙሪያ ብቻ በመሽከርከር እየደጋገመ በሚሠለች አኳኋን የሚያወራና የአድማጮቹን ትኩረት ለማግኘት የሚቸገርና ትዝብት ላይ የሚወድቅ ነው፡፡

ለዚህ መፍትሄው ምንድን ነው? አንዳንዴ ንግግራችንን የምንጨርስበትን ሁኔታ አስቀድሞ በማቀድና በማጥናት ዝግጅት አድርገን ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡ አይመስላችሁም?. . . . . ንግግራችንን ለመጨረስ የምንጠቀምበት መንገድ እንዲሁም የምንጠቀምባቸውን ቃላት እዛው መድረክ ላይ በአድማጮቻችን ፊት ሆነን ንግግር እያደረግን ሃሣቡንና ቃላቶቹን የማመንጨትና የመናገር አቅሙ፣ ብቃቱና፣ ችሎታው ያለን ከሆነ የአስተሣሠባችን ምጥቀትና የልበ ሙሉነታችን መገለጫ ይሆናል፡፡

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ንግግር ስናደርግ ለየት ያለ የጭንቀትና የፍርሃት ስሜት ሲገጥመን የሚችልበትን ሁኔታ ሲፈጠርና ለንግግራችን መጨረሻ የሚሆኑ ሃሣቦችንና ቃላቶችን፣ በመናገር ላይ እያለን እንኳን ማሠብና መዘጋጀት አይከብደንም፡፡

ይቻላል? ወይስ ስሜትህ የንግግርህን ማጠቃለያ በፊት አስቀድመህ ንግግር ከማድረግህ በፊት በተደጋጋሚ ሁኔታ ሳትጨነቅ፣ እንድታስብበት፣ እንድትዘጋጅና፣ እንድትለማመድ ነው የሚገፋፋህ?

እዚህ ላይ ልናውቀውና ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ጀማሪና ልምድ የሌለን ንግግር አቅራቢዎች ሆነን ቀርቶ አይደለም እጅግ የተዋጣላቸውና እንደበተ ርቱዕ ተናጋሪዎች ናቸው፣ ሃሣባቸውን ውሃ በሚቋጥር ሁኔታ ቀስ ባለ

አነጋገርና ማራኪ በሆነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አቀላጥፈው በመናገር መግለፅ የሚችሉ ናቸው ተብለው ከፍተኛ የሆነ ክብርና አድናቆት የተቸራቸው ሰዎች ችግር ያለባቸው ናቸው። እንደነ ዊልበርፎርስ፣ ቤል ይድ፣ ግላድስቶን፣ የመሳሰሉት ታዋቂ ሰዎች ንግግራቸውን ለመጨረስ ይጠቀሙባቸው የነበሩትን ዘዴዎችና ቃላቶች አስቀድመው በማጥናትና በተገቢው በመምረጥ ብቻው ደጋግመው በመለማመድ እንደሆነ [illegible] እንዲሁ በመጠቀም ንግግራቸውን ለመጨረስ [illegible] የሚጠቀሙበት ነበር።

ታዋቂ የሚሉ ንግግር አቅራቢ የሆነ ሰው የነዚህን ሰዎች ልምድና የንግግር አጨራረስ ሥነ-ዘዴ በመማርና በመረዳት በትክክል ግድብነት ብቻ ንግግሩን ለመጨረስ ቢሞክር [illegible] ንግግሩን የሚጨርስበት ሁኔታ የሚያስቸግረው [illegible] የሚጠቀምበት ሁኔታ [illegible] ንግግሩን [illegible] ግድብነት [illegible] ለመጨረስ እንዳለበት [illegible] [illegible] [illegible] የሚጨርስበትን ሁኔታ [illegible] አለበት።

እንዳንድ ጊዜ ንግግር [illegible] [illegible] [illegible] ንግግራቸው [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] ንግግራቸውን ለመጨረስ [illegible] [illegible] [illegible] ይህ ግድብነት [illegible] [illegible] ንግግራቸውን ለመጨረስ [illegible] የሚችሉ [illegible] የንግግር አጨራረስ [illegible] [illegible] [illegible] ለንግግራቸው [illegible] [illegible] [illegible]

[illegible] የንግግር [illegible] ንግግራቸውን ለመጨረስ የሚያቅታቸው [illegible] [illegible] ንግግራቸው [illegible] [illegible] ንግግራቸውን [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] ንግግራቸውን [illegible] [illegible] ግድብነት ንግግር [illegible] ንግግር [illegible] [illegible] [illegible] ንግግራቸውን [illegible] [illegible] ንግግራቸውን ለመጨረስ [illegible] [illegible] ንግግራቸው [illegible] [illegible] ንግግራቸው [illegible] [illegible] [illegible] ይህ ግድብነት [illegible] [illegible] ንግግር ምን ያህል የሚያስፈልግና ንግግር [illegible] [illegible] ልምድ የሌለው ሰውን [illegible] [illegible] [illegible] ንግግሩን

ግፍጨርስ አቋርጦ ቢሄድ ሲፈጠር የሚችለውን የንዴትና የብስጭት ስሜት ዓይነት የሚፈጥር ሁኔታ ነው የሚሆነው።

እንደዚህ ያለውን ስህተት አብረሃም ሊንከን የአሜሪካን ኘሬዝዳንት ሆኖ መመረጡን አስመልክቶ ለመጀመሪያ ጊዜ በበዓሉ ላይ ሲያደርገው አዘጋጅቶት የነበረውን ንግግር የመጀመሪያው የዕሁፍ ረቂቅ ላይ ከሠራቸው ቃላትና የሃሣብ አጠራረድ ስህተቶች በላይ ስህተት የሠራ ተናጋሪ አልነበረም። ሊንከን ያንን ንግግር ያደረገው አሜሪካ ከፍተኛ የሆነ ውጥረት ውስጥና የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ በገባችበት ወቅት ላይ ነበር። በአገሪቱ ላይ የእርስ በርስ ጥላቻና የጠላትነት መንፈስ ጥቁር ደመና ያጠላበትና ጥቂት ቆይቶም በአገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ውድመት የደረሰበትና የደም ጐርፍ የፈሠሠበት ጊዜ ነበር። በዚህ ወቅት ላይ ነው አብረሃም ሊንከን የመጀመሪያውን የኘሬዝዳንትነት ንግግሩን ፅሁፍ ከዚህ በታች በተቀመጠው የንግግር አጨራረስ መንገድ ለአሜሪካ የደቡብ ግዛት ነዋሪዎች ለሚያደርገው ንግግር የፃፈው።

> ይህ በአገራችን የተከሠተው የእርስ በእርስ ጦርነት መነሻ ምክንያት፣ ያስከተለው ጥፋትና ውድመት፣ እንዲሁም መፍትሄው እጅግ በምታሣዝኑኝ በእናንተ በአገሬ ልጆች እጅ ውስጥ ያለ እንጅ በእኔ እጅ ውስጥ ያለ አይደለም። መንግስት እናንተን እንደጠላት አያያችሁም። እናንተም መንግስትን ጠላት አድርጋችሁ እስካላያችሁና ብጥብጥ፣ ግጭትና፣ ጦርነት ውስጥ ለመግባት እስካልወሠናችሁ ድረስ ምንም ዓይነት የግጭት፣ የብጥብጥና የጦርነት ሁኔታ አይከሠትም። መንግስትም በምንም ዓይነት እንደጠላት አያያችሁም። እናንተ እኮ ይህችን አገራችንን ለማውደምና ለማፈራረስ ቃለ መሃላ የፈፀማችሁና ግዴታ ያለባችሁ አይደላችሁም። እኔ ግን የአገሬን ሠላምና ደህንነት ለማረጋገጥና ወራሪን ለመከላከል ቃለ መሃላ የፈፀምኩና ሃላፊነትም ግዴታም ያለብኝ ነኝ። እናንተ ከዚህ ዓይነቱ የጥፋትና የብጥብጥ መንገድ እራሳችሁን ብታወጡ ቅር ሊላችሁ አይችልም። እኔ የአገሬን ሠላምና ደህንነት ከማረጋገጥ ወደ ኋላ የምልበት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖረኝም። "ሠላም ወይስ ጦርነት" ምርጫው በእናንተ እንጂ በእኔ እጅ የሚገኝ ምርጫ አይደለም።

ሊንከን ለመናገር አስቦት የነበረውን ይህን ንግግር ፅፎ ሲያበቃ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሲዋርድ ነበር እንዲያይለት የሠጠው። ሲዋርድ ግን ወዲያውኑ በንግግሩ መጨረሻ ወይም መደምደሚያ ሃሣብና ቃላቱ የሚያበሳጩ፣ እልህ የሚያጋቡና፣ ግጭትን የሚያባብሱ እንደሆኑ ለሊንከን ይገልፅለታል። በመቀጠልም የንግግር ዕሁፍን መጨረሻ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ፅፎ በማዘጋጀት ሊንከን ይበልጥ የሚስማማውን በመምረጥ ለንግግሩ መጨረሻ እንዲጠቀምበት ሠጠው። ሊንከንም አንዱን ከመረጠ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ላደረገው ንግግር መቋጫ ተጠቅሞበታል። የአሜሪካ የኘሬዝዳንትነት በዓሉ ላይ ያደረገው የመጀመሪያ ንግግሩም ወዳጅነትን፣ ፍቅርንና፣ ከፍተኛ የሆነ ትብብርን

በሚያበረታታና በሚያጎላ መንገድ ከዚህ በታች በተቀመጠው መልኩ ማድረግ ቻለ፡፡

«በንግግሬ መጨረሻ ላይ መናገር የምፈልገው አንድ ነገር አለ፡፡ እኛ እንዳችን ለአንዳችን ጠላቶች ሳንሆን ወዳጆች ነን፡፡ ጠላት መሆንም የለብንም፡፡ አንዳችን ለአንዳችን ያለን የወዳጅነት መንፈስና ስሜት የተሟላና ያልተሸራረፈ ባይሆንም እንኳ ከዚህ በፊት የነበረንን ጠንካራ የሆነ የፍቅር፣ የወዳጅነትና፣ የመተሳሰብ ጠንካራ ትስስር ፈፅሞ የሚሸረሽረውና የሚያጠፋው አይሆንም፡፡ ሁሌም በየሄድንበትና በረገጥነው ቅንጣት የአገራችን መሬት ላይ ይህችን አገራችንን ለማፅናትና ለማቆም የፈሠሠው የአባቶቻችን ደም፣ ለአገራችን ሉዓላዊነትና ደህንነት ከፍተኛ የሆነ ፍልሚያ በተካሄደባቸው የጦር ሜዳዎች ላይ የወደቁ ጀግኖች አባቶቻችን ይህችን አገር ለማፅናት፣ ከወራሪ ለመከላከልና፣ ለኛ ለማቆየት መስዕዋት የሆኑበት የአንድነት መንፈስ ስሜት፣ ሁሌም በሁላችን ውስጥ ያለውንና ነገም ለልጅ ልጆቻችን የምናወርሠውን የአባቶቻችንን የመስዕትነት ታሪክ እና የአንድነት ስሜት የሚጭርብን ነው፡፡ ይሄ ከበፊትም ያለ የማንነታችን መገለጫ ታሪክና የጋራ ስሜታችን ሁሌም አብሮን የሚኖር የእኛ በጐ ገፅታ ነው፡፡»

አንድ ጀማሪ ንግግር አቅራቢ እንዴት ትክክለኛ በሆነ መንገድ ንግግሩን ለመጨረስ የሚችልበትን መንገድ ሊማርና ሊያዳብር ይችላል? የዚህን ዓይነት ስሜት እንዴት ሊፈጥር ይችላል? መሠረታዊ የሆኑ የንግግር አጨራረስ ስልቶችንና መመሪያዎችን ብቻ በማወቅና በመማር? አይደለም! ልክ እንደ አንድ ባህል ለማወቅ ውስብስብ ነው የሚሆነው፡፡ እኛ ያለብን በውስጣችን ትክክለኛ በሆነ መንገድ እንዴት ንግግራችን መጨረስ እንችላለን? የሚለውን ስሜት መፍጠርና ማጎልበት ነው፡፡

አንድ ሠው የሌሎችን ምርጥ የንግግር አጨራረስ መንገዶች በመመልከትና በመማር የእራሱን ችሎታና ስሜት ለማዳበርና ለመፍጠር ሊጠቅመው በሚችልበት ሁኔታ እስካልተጠቀመበት ድረስ በሌላ ምንም ዓይነት መንገድ ንግግሩን በትክክለኛው መንገድ ሊጨርስበት የሚችለውን እውቀትና ችሎታ ሊማር አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ስሜት ማዳበር ይቻላል፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ ንግግራችንን በራስ የመተማመን ስሜት ለመጨረስ የምንችልበትን መንገድ ከሌሎች ልምድ በመውሠድና በማጥናት አዳብረን ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡

የቀድሞው የዌልስ ልዑል ለቶሮንቶ የንጉሣዊያን ቤተሠቦችና አጋሮቻቸው ንግግር በሚያደርግበት ወቅት የተጠቀመበትን የንግግር አጨራረስ መንገድ እስቲ ለዚህ ለማሣያነት እንጠቀምበት፡፡ ክቡራትና ክቡራን ዛሬ ከልክ በላይ በሚባል ዓይነት ብዙ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን ስለራሴ በመናገሬ ከፍተኛ የሆነ የፍርሃት ስሜት ነው የፈጠረብኝ፡፡ ዛሬ ግን እዚህ ካናዳ ውስጥ ብዙ ታላላቅ ሠዎች

የማህበረሰብ ንግግር የማድረግ እድሉን ማግኘቱ የተገኘውበትን ቦታ ከፍተኛውን ለማስከበርና ክብር ዋላፊነት እንዲጠይቅብኝ ነው የደረገኝ። ዛሬ እኔ የማገኛችሁ የምፈልገው ነገር ሁሌም በሆነ የመጣችሁኝን ታላቅ ኃላፊነት የሚገኝ ዋንቃቅ እንደምወጣና ለሚላችሁብኝ እምነት ታማኝ እንደምሆን ነው።

ዶዩን የልቡሱን ንግግር ያዳመጠው አይነስውር የሆነ ሠው እሄን ቢሆን ንግግሩ እንደተጠናቀቀ በደም ብ ያውቃል። ንግግሩ ልክ በአየር ላይ ተንጠልጥሎ ድንገ ወዲያና ወዲህ እንደሚወዛወዝ የረዝብ ገመድ የሆነ አይደለም። የተጠቀሰለ ነው። ያለቀ የተቋጨ ነው።

እውቀ ዶክተር ሃሪ ኤመርሰን ፎስዲክ በጄኔቭ በቅዱስ ፒየር ካቴድራል በስድስተኛው የሊግ ኦፍ ኔሽን ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንዲህ የሚል ንግግር አድርጉ ነበር። ለንግግሩ የመረጠውም ርዕስ " ሁሌም ጉራዴን መፍትጊ አድርገው የሚወስዱና የሚመርጡ ሁሉ መጥፊያቸው ጉራዴ ነው" የሚል ነበር። ዶር ሃሪ ንግግሩን የማዳመጥ ፍላጎትን በሚጭርና ጠንክር ባለ ሁኔታ መልእክቱን ለማስተላለፍ በሚያስችል መንገድ ጨርሶ የተጠቀመበትን ዘዴ ቀጥሎ እንመልከት።

ቀጥሎ ያቀረበው ንግግርም "የእየሱስ ክርስቶስን ጦርነትን ለማስማማት ፍፁም የማይቻል ነገር ነው የሚል ይዘት ነበረው። " ያ ነው ዛሬ ክርስትና ለአለም ከፍተኛ የሆነ ፈተና የሆነበት። ጦርነት የሠው ልጅ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥፋትን እያደረሠ ያለ ማህበራዊ ሃጢያት ነው። ጦርነት በምንም መልኩ ክርስቲያናዊ ያልሆነ ተግባር ነው። ጠቅለል ባለ መልኩም ጦርነትን መቀስቀስም ሆነ ማካሄድ የእየሱስ ክርስቶስ ተግባርም ሆነ ትምህርት ያልሆነና ድጋፍ የሌለው ነው። ጦርነትን ማድረግ ማለት ጭፍን በሆነ ሁኔታ የክርስትና እምነት ስለፈጣሪና የሰው ልጆች ያስቀመጣቸውን መመሪያዎችም ሆነ መርሆዎች ፍፁም መካድና ሃይማኖት የለሽነትን በዓለም ላይ እንዲሠፍን መፍቀድ ነው። ይህንን ለመለወጥ ስራን ቤተክርስቲያን ወስዳ በማስተማርና ሠፊ ግንዛቤ እንዲፈጠር ኃላፊነቷን መወጣት መቻል አለባት። አሁን በኛ ጊዜ ቤተክርስቲያን ይህን የህሊና ዳኝነት ተቀብላ በማራመድ መወጣት መቻሏ ልክ ጥንት ቤተክርስቲያን ይዛቸው በበረውና ታራምዳቸው ከነበሩት አቋሞች ሃይማኖት የለሽችን የመቃወም፣ ጦርነትን የሚቀሠቅሱና የሚያካሂዱ አገራትን የሚቃወምና የሚያወግዙ አቋሞቿ ማለትም ቤተክርስቲያንን ሰማያዊውን መንግስት ከአገሮቹ ሉዓላዊነት በላይ ያደረሰች ለአለም ሰላም መስፈን ታላቅ ጥሪ ያቀረበች ያደረጋት አልነበረምን? ያ . . . እኮ . . . . በቤተክርስቲያንና የክርስትናን እምነትን አገር ወዳድነትንና ጀግንነትን የመካድ ጉዳይ ማይሆን የህሊና ዳኝነት ጉዳይ ነው።

ዛሬ ልክ እንደ አንድ አሜሪካዊ በዚህ ታላቅ በሆነና እንግዳ ተቀባይ በሆነ አገር ውስጥ መናገር የምፈልገው ለራሴ መንግስት ብቻ አይደለም። ግን ልክ እንደ አንድ ክርስቲያን ወገኖቼ ሁላችንም የምናምንበትንና ቀላል ነው የምንለውን

ሴት ተቀንም ሀሉት የምናደርግበትን የሠላም ጥያቄ ምንም ባለማድረግ ሃላፊነታችንን ያልተወጣን እንደሆነ ከሚደርስብን ሀሀት ለመዳን እንደሚሻን ለመናገር ነው የምፈልገው:: ሁላችንም በየአቅጣጫው በተለያዩ ሁኔታዎች የምንሠራው ለአንድ መጨረሻ ነው" ለሠላም መስፈን . . . ዓለም በሞላ ለሠላም በአንድነት እንዲቆም:: ከዚህ ባለፈ ሁኔታ ያለው አማራጭ የሠው ልጅ እስከ ዛሬ ድረስ ካያቸው ወይም ካጋጠሙት ጥፋቶች የባሠው ነው:: በተጨባጩ ዓለም ውስጥ እንዳለው የደንብ መለዋወጥ የፈጣሪ ሕግ ከፍትህና ከህሊና ፍርድ አኳያ ለማንም ሠው ወይም ለማንም አገር ሲባል የሚቀስበስ ወይም የሚቀየር አይደለም::

"እነኚያ ጎራዴን የሚያነሱ ሁሉ መጥፊያቸው ጎራዴ ነው"

ነገር ግን እነዚህ በሙሉ የአንድ ንግግር ማጠናቀቂያ ሃሳቦችና ንግግሮች አስገራሚ፣ አስደናቂ፣ አስደማሚ፣ በሆኑ የንግግር ቅላጼዎችና ድምፆች የታጀቡና የቀረቡ እስካልሆኑ ድረስ የተሟሉ አይሆኑም:: ልክ በበአለ ሲመቱ ቀን እንዳቀረበው የሁለተኛው የንግግር ፅሑፍ፣ መልዕክትና ንግግርን ያቀረበበት የአነጋገር ዘይቤ ደስ እንደሚል ሙዚቃ ማራኪ የሆነ ንግግር ድምፅና ቅላጼ አይነት ማለታችን ነው:: የኬድልስተን ከተማ ነዋሪ የነበረውና አሁን በህይወት የሌለው የቀድሞ የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ኦርል ከርዞን ያማረ የንግግር መጨረሻ መምረጥና በሚማርክና በሚስብ ሁኔታ ንግግር የማቅረብ ችሎታ «የሠው ልጅ ካሉት ዝናዎችና ኃብቶች አንዱና . . . ወርቃማ የሆኑ የሠው ልጆች ብቃት ... ነው›› በማለት አሳውቆ ነበር::

ያለፉትን ጦርነቶች ጠባሳና ሰቆቃ በቶሎ እንድንረሳቸውና ከህሊናችን እንዲርቁ ተስፋ በማድረግ በተደጋጋሚ እንፀልያለን:: ይሁንና እግዚአብሔር እስኪፈቅድ ድረስና ባለፉት ሁለት መቶ ሃምሳ አመታት በጦርነት ያወደምናቸው ንብረቶች እስኪተኩ ያፈሰሥነው ደም እስኪደርቅ እንኳን በተጨማሪ ጥፋትና ጦርነት አላስፈላጊ ደም ማፍሠሳችንና ንብረት ማውደማችን አይቀርም:: የቀድሞውን የጦርነት ውጤት ጠባሳ ከማዳን ይልቅ ተጨማሪ ደም ከማፍሰስና የንብረት ውድመት ከማምጣት የምንታቀብ አልሆንም:: ከሦስት ሺህ አመታት በፊት የተባለውን የፈጣሪያችን ፍርድ ሁሌም እውነተኛውና ትክክለኛው ነው›› ዛሬም ድረስ ልንቀበለውና ልንተገብረው የሚገባ ነው::

ለማንም ጥላቻ ሳይኖረንና ለሁሉም በጎና ሲጋስ በመሆን ለእውነትና ለትክክለኛው ነገር በመቆም ልክ ፈጣሪ አምላካችን ትክክለኛውን ነገር እንድናይ እንዳደረገን ባለንበት ወቅት የሚጠበቅብንን ስራዎች ለመስራትና ለማጠናቀቅ ዝግጁ ሆነን መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል:: አገሮች በጦርነት የደረሰባቸውን ጉዳትና ቁስል ለማከም እንድንችል፣ በጦርነት ውስጥ ለተወለዱ ሰዎች አስፈላጊውን እንክብካቤ ለማድረግ እንድንችል፣ በጦርነት ምክንያት ባሎቻቸውን ላጡ፣ እናትና አባቶቻቸውን አጥተው ያለቤተሰብ የቀሩ ልጆችን እንድንከባከብ በመካከላችንና

በአገሮች መካከል ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ሰፍኖ ለማየት ማድረግ ያለብንንና ልንሰራቸው የሚገቡንን ስራዎች መወጣት መቻል አለብን።

እንደኔ አስተሳሰብ እስከዛሬ ድረስ ከሰው ልጅ አንደበት የወጣው በጣም ምርጡ የንግግር ማጠቃለያ ወይም የንግግር መጨረሻ ነው ብዬ የምለውን ያነበባችሁት ይመስለኛል።. . .በኔ ግምት ትስማማላችሁ? እስከዛሬ ድረስ ምርጥ የሆኑ ንግግሮች ናቸው ተብለው በተለያዩ መድብሎች ውስጥ ተጽፈው በምታገኙዋቸው ስነ-ጽሁፎች ውስጥ ለሰው ልጅ ደህንነት አሳሳቢነትንና ተቆርቋሪነትን ታገኙባቸዋላችሁ፣ የሰዎች እውነተኛ የሆነ ፍቅርንስ? አዛኝነትንስ? ልክ እንደ ጌትስበርገ መልእክት" ዊሊያም ኢ. ባርተርን የአብረሃም ሊንከን የህይወት ታሪክ በሚለው ፅሁፍ ላይ በፃፈው የአብርሃም ሊንከንን የንግግር መቋጫ ሃሳብና ንግግር በተመለከተ እንደገለፀው. . . ሳቅ ያለና ከፍተኛ የሆነ የስብዕና ደረጃ ላይ መድረስ ነው. . .ይሄ አብረሐም ሊንከን ከተናገራቸውና ካስተላለፋቸው መልእክቶች ሁሉ ከፍተኛ የሆነውንና ሊንከን ያለውን የህሊናና የመንፈስ ኃይል ከፍተኛነት አጉልቶ በማውጣት ከፍ ያለ ቦታ ላይ እንዲሰፍር ያደረገው ነው።

‹‹ይህ ልክ እንደሚመለክ ግጥም ነው›› በማለት ካርል ሽሩዝ ፅፎታል። ማንም የአሜሪካን ፕሬዚዳንት እስከዛሬ ድረስ እንደዚህ አይነት ንግግር ለአሜሪካን ህዝቦች አድርጎ አያውቅም" እስከ ዛሬ ድረስ አሜሪካ እንደዚህ ያለ ከልብ የመነጨ ንግግር ያደረገ ፕሬዝዳንት ኖሯት አያውቅም" ግን አንተ እንደዚህ አይነት ሳቅ ያለና ከሰው ልጅ ከምንጠብቀው በላይ የሆኑ አይነት ንግግሮችን ልክ እንደ ዋሽንግተኑ ፕሬዝዳንት ወይንም የኦቶዋው ወይም የካንቤራው ጠቅላይ ሚኒስቴር ልታቀርብ አትችልም። ችግርህ ምናልባትም በጥቂትና በተወሰኑ ሰራተኞች ወይም በድኖች ፊት የምታደርገውን ቀላል ንግግር እንዴት ማጠናቀቅ እንዳለብህ አለማወቅ ሊሆን ይችላል። ለዚህ እንዴት መዘጋጀት ትችላለህ? እስቲ ለዚህ መንገድ እንፈልግ። ንግግርን ለማጠናቀቅ የሚረዱ የተወሰኑ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን እንመልከት።

አንድ ተናጋሪ ሲላው ቀርቶ በጣም አጭር በሆነና ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ ብቻ የሚፈጅ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ እንኳን ሃሳቡን ለመግለጽና ለማስረዳት በንግግሩ ውስጥ ብዙ ነገሮችን ማንሳቱና መጥቀሱ የማይቀር ነው። በመሆኑም አድማጮቹ በስተመጨረሻ ላይ ዋናው ነጥቡን ለመገንዘብና መልእክቱን ለመረዳት ሊሰላቹና ሊሳነፉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ጥቂት የሆኑ ተናጋሪዎች ብቻ ይህንን ይረዳሉ ወይም ይገነዘባሉ። ብዙዎች ተናጋሪዎች የሚናገሯቸው ነገሮችና መልእክቶች እነሱ የሚያውቋቸውና በደንብ የተረዷቸው ነገሮች መሆናቸውን በማሰብ ብቻ አድማጪቻቸውም ልክ እንደነሱ የሚናገሩትን ጉዳዮችና ነጥቦች ጠንቅቆ የሚያውቅ ስለሚመስላቸውና ወይም ያውቃል ብለው ስለሚገምቱ ከፍተኛ የሆነ ስህተት ላይ ይወድቃሉ። ሁልጊዜ ባይሆንም የዚህ አይነት ተናጋሪዎች በራሳቸው ኃሳቦችና በተረዷቸው ነገሮች ዙሪያ ብቻ

የዘመናዊው የእነስ የሃገሮች ለኢኮኖሚው አዲስ ናቸው፡፡ ቀላልና የሆኑ ግን ለኢኮኖሚው እንዲሁ ግፊ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ምናልባትም ጥቂቶች ሊገቡበት ሊሆኑ የቻሉት ሊጎለብቱ እነዚሁ ግራ መጋባትና መደናገር ውስጥ መውደቃቸው የማይቀር ነው፡፡ እንደዚህ ያለ ነገር አድማጮችን ከንግድ ዘርፉ በዙ ዘመናዊ ነገሮች እንዲያጠኑ ከማድረጉ እንደዚሁም ግልጽና ተጨባጭ የሆነ ግብ እንዲጨብጡና እንዲያስተውሉ የሚያደርግ ሁኔታን የሚፈጥር አይደለም፡፡

እንደ ስሙን የሚያደርጉት አድርጋችሁ ታላቁን ንግግር ማድረግ አስመልክቶ በዚህ ቀጥሎ የተጠቀሰውን አባባል እንጠቀማለን፡፡ ይናገሩ መቻል የለባችሁም እንዲሁ ንገሩ፡፡ ቀጥሉ ንገሩ፡፡ በመጨረሻም እንደነገርኳቸው ንገሯቸው፡፡ በእውነት በዚሁ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ የመነጋገር የሆነው እንደነገርኳቸው ንገሯቸው የሚለው ነው፡፡ በዝርዝር በአጭሩ ምክንያቱ ትኩረት የሚያገኙ መልእክቱን ንገሯቸው ማለት ነው፡፡

ለዚህ ማሳያ የሚሆን ጥሩ ምሳሌ ከዚህ በታች ታገኛለህ፡፡ ትኩረቱ በፍጥነት ከሚያድጉ የብድር ማህበራት መካከል የአንዱ ስራ አስኪያጅ ነው፡፡

የተከበራችሁ፡ አድማጮቻችን ከደርባችን የሚገኙ የራሳችን አካሉ አዲስን ቴክኖሎጂ እየተጠቀመ ነው፡፡ በሁሉም በምስራቅና በምዕራብ ቀበሌ ከብድር ደርጅቶችን ውስጥ ይህን አዲስ የሆነ ቴክኖሎጂ በመጠቀማችሁ የተሻለ መልእክቶችን ከምናው የመቀማጠሪያ ማሽን ወደ ተለያዩ ባንኮች በማስተላለፍ ከፍተኛ በሆነ መንገድ ስራን ማቀላጠፍ ተችሏል፡፡ አላስፈላጊ ወጭንና ጊዜን መቆጠብም ተችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ በአንድ አመት ውስጥ ይታጣ የነበረውን ከፍተኛ ጊዜ ለማዳን ተችሏል፡፡ ውጤቶቻችሁንም በከፍተኛ ሁኔታ መቀየስ ችለናል፡፡

ስለዚህ ሁላችሁም በአንድ ድምጽ ሆናችሁ ይህን አዲስ ቴክኖሎጂ በደብብ ክፍል የብድር ማኪያዎች ውስጥ እንዲተከሉ ድጋፋችሁን ስጡኝ፡፡ ስራ አስኪያጁ ምን እንዳደረገ ለማየት ችላችኋል? ይህን ንግግር በመስማት ብቻ ስራ አስኪያጁ ያስተላለፈውን መልእክት ልትረዱት ወይም ሊሰማችሁ ይችላል፡፡ እሱ ሁሉንም መልእክቶችን በጥቂት አረፍተ ነገሮች በቀላል አድርጎ በማስቀመጥ ነው የተናገረው፡፡ ዋናና መልእክቱን ለማስተላለፍ ስልሳ ሁለት ቃላትን መጠቀም ብቻ ነው ያስፈለገው፡፡

እንደዚህ ባለ አጭር ባለ ሁኔታ የንግግራችንን አንኳር ነጥቦች በቀላል አድርገን በንግግር ማጠቃለያችን ውስጥ ማቅረብ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ ተረድታችሁታል? ከሆነ ከእንግዲህ ወዲያ ይህንን ዘዴ በመለማመድና በማዳበር ልትጠቀሙበት ይገባል፡፡

## አንድ ድርጊት እንዲፈፀም መጠየቅ

ከላይ በምሳሌነት የተመለከትነው የንግግር ማጠቃለያ አንድ ድርጊት እንዲፈጸም ወይም እርምጃ እንዲወሰድ የሚጠይቅ ንግግርና የንግግር ማጠቃለያን ለማሳየት የሚረዳ በጣም ጥሩ ምሳሌ ነው። ተናጋሪው አንድ ነገር እንዲፈጸም ወይም እንዲደረግ ነው የፈለገው። የደቡብ የባቡር መስመር ስምሪትን ከአንድ ማዕከል ለመቆጣጠርና ለመምራት የሚያስችል አዲስ የግንኙነት ቴክኖሎጂ እንዲተከልና ሥራ እንዲጀምር ነው የፈለገው። የሃሳቡን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ለማሳመን የሞከረውም ይህን የግንኙነት መሳሪያ በመትከልና በመጠቀም ድርጅቱ በርካታ የሆነ ገንዘብ ከማውጣት እንደሚድንና ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት እንደሚችል በመዘርዘር ነው። ተናጋሪው እንዲከናወንለት የፈለገው ነገር ነበር። ያንንም አሳክቷል። በንግግሩም እንዲሰራ የፈለገውን ስራ ብቻ የመንገር አልነበረም። መልእክቱን የነገረው ወይም ያስተላለፈው ስራውን እንዲፈፅም መፍቀድ ለሚችሉ የደቡብ ክፍል የባቡር ጣቢያ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነበር። በመሆኑም የፈለገውን ዘመናዊ የሆነ የግንኙነት መሳሪያ በደቡባዊው ክፍል የባቡር ጣቢያዎች ውስጥ እንዲተከልና አገልግሎት መስጠቱን እንዲጀመር የጠየቀው ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረግ ችሏል።

## አስደሳች አስተያየት የሚያንፀባርቅ

ታላቋ የፔንሲልቫንያን ስቴት የነገው የእድገት ጎዳና መሪ ሆና መገኘት ይኖርባታል። ፔንሲልቫንያ ዋነኛዋ የብረትና የስቲል አምራች፣ በአለም ላይ የባቡር ሃዲድን በመዘርጋት በአንደኝነት የሚታወቀው ካምፓኒ የሚገኝባት፣ በእርሻ ምርት ከአሜሪካ ግዛቶች ሶስተኛዋ የሆነችው ፔንስዮኒያ የአገራችን ዋነኛዋ የንግድ እቅስቃሴ ቁልፍ ናት። ሆኖም ግን ይህ ታላቅነቷና ያላት ሐብት በተፈጥሮ ፀጋዋ ሊኖራት የሚገባትን ቦታ እንዲሁም የመሪነት ሚና እንድትጫወት ያደረጋት አልነበረም።

በእነዚህ ቃላቶች ቻርለስ ሸዋብ በኒውዮርክ ግዛት ለሚገኙት የፔንስልቫኒያ ነዋሪዎች ያደረገውን ንግግር አስደሳች በሆነ የንግግር አጨራረስ መንገድ አቅርቧል። በዚህ ንግግር አድማጮቹ ከፍተኛ የሆነ ደስታ እንዲሰማቸውና ብሩህ ተስፋ እንዲታያቸው ነው ያደረገው። ይህ በጣም የሚደነቅ የንግግር አጨራረስ መንገድ ነው። ግን ከዚህ በላይ ውጤታማ እንዲሆን ቃላቶቹ ከልብ የመነጩና እውነተኛ መሆን ይገባቸዋል። ዝም ብሎ የቃላት ጋጋታና ድርደራ በማቅረብ ማሞካሸት ብቻ መሆን የለበትም። በዚህ አይነት ሁኔታ ንግግርን መጨረስ እውነትን የማይደውል ከሆነ የሀሠተኝነትን ደወል ይደውላል። ውሸታምነትን በግልጽ ያሳያል ወይም ያሳውቃል። ልክ በሀሰት ለመለገስ ቃል እንደተገባ እርዳታ ለሰዎች ጠብ የሚል ምንም ነገር አይኖርም።

## አስቂኝ የሆነ የንግግር አጨራረስ

«ሁሌም እንዲስቁ አድርጋቸው፡፡» ይህን የተናገረው ጆርጅ ኮሰን ነው፡፡ «ደህና ሁኑ ብለህ ስትሰናበታቸው» የማድረግ ችሎታው ካለህ በተጨባጭ የምታውቀው የሚያስቅ ቀልድ ካለህ ቆንጆ አጨራረስ ይሆናል! ግን እንዴት ማድረግ ትችላለህ ያን. . . . ሐምሌት እንዳለው….. ዋነኛው ጥያቄ ነው፡፡ እያዳንዱ ሰው ይኼን በራሱ መንገድ ማድረግ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ማንም ሰው ሲሎይድ ጆርጅ ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራ ከተሰባሰቡ ወጣቶች የጆን ዌይስሊን የመቃብር ቦታ ንፅህና ስለመጠበቅና ስለማሳመር ጉዳይ በተናገረበት ወቅት ተሰብሳቢዎቹን በጣም በሚያሥቅና እጅግ በሳል በሆነ ሁኔታ እያዋዛና ንግግሩን እንዴት ጠቅለል አድርጎ እንዳቀረበው ልብ ብላችሁ አጢኑት፡፡

> ይህንን የመቃብር ቦታ ለማደስና ለማሳመር አስባችሁ በመነሳታችሁ ምን ያህል ደስታ እንደተሰማኝ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁኝ ክብር የሚገባው ሰው ነው፡፡ እሱኮ በተለየ ሁኔታ ንጽህና የሌለውንና ቆሻሻ የሆነ ቦታን የማይወድ ሰው ነበር፡፡ እንደማስታውሰው ‹ማንም ሰው ንፅህና የጎደለውና የቆሸሸ ነገርን ማየት የለበትም" ያለው እሱ ነበር፡፡ ለዚህ ነው ዛሬ አንድም የቆሻሻና ንጽህናው የተጓደለ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰራተኛ የማታዩት፡፡ (ሣቅ)፡፡ እናም ይህ ሰው የተቀበረበትን የመቃብር ቦታ ንጹህና ያማረ አለማድረግ ከአንዴም ሁለቴ ምንም አይነት ሩህሩህነትና አሳቢነት ለሱ የለንም ማለት ነው፡፡ እሱ በመንገድ ላይ እየሄደ ሳለ እየሮጠች መጥታ ጮክ ብላ "እግዚአብሔር ይባርክህ ሚ/ር ቄይስሊ ላለችው የደርቢሻየሯ ሴት ልጅ ምን ብሎ መልስ እንደሰጣት ታስታውሳላችሁ "አንቺ ልጅ የመረቅሽኝንና ፊትሽና ልብስሽ ንጹህ ሆኖ ቢሆን ኖር የተመኘሽልኝ የበለጠ የተሳካ ይሆን ነበር› በማለት ነበር የመለሰላት፡፡ (ሣቅ)፡፡ እሱ የገለፀላት ንጹህ ስላለመሆን ያለውን አመለካከትና ስሜት ነበር፡፡ በፍጹም የመካነ መቃብሩን ቆሻሻ ዝም ብላችሁ እንዳትተዉት፡፡ እሱ እንደዚያ ቆሻሻ ሆኖ ማየት ቢችል ከምንም በላይ ተጎጂ የሚሆነው እሱ ነው፡፡ ቦታውን ጠብቁት ተንከባከቡት የሱ መካነ መቃብር ቦታ ሁሌም የሚታወስና የተቀደሰ ነው፡፡ እምነታችሁም ነው፡፡ (ጭብጨባ)

## የግጥም ጥቅሶችን በመጥቀስ ንግግር መጨረስ

ሁሉም የተለያዩ የንግግር አጨራረስ አይነቶች ምንም እንኳን በጥሩ አኳኋን የቀረቡ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ በቀልድ ወይንም በግጥማዊ ዘይቤ አጨራረስ ከቀረቡ የንግግር መቋጫዎች ጋር ስናነጻጽራቸው የተሻሉ ተመራጭና ተቀባይ አይሆኑም፡፡ በእርግጠኝነት ትክክለኛውን ግጥም ለንግግርህ መጨረሻ መምረጥና መጠቀም ከቻልክ ለየት ያለና ደስ የሚያሰኝ ነው የሚሆነው፡፡ ለንግግርህ መጨረሻ ያማረ ጣእም ይሰጠዋል ግርማ ሞገስም ያጎናጽፈዋል፡፡ ቁንጅናን ያላብሰዋል፡፡

ሮታሪያዊያኑ ሰር ሐሪ ላውደር ለአሜሪካን ሮታሪያን ተወካዮች ኤድንብራው ኮንቬንሽን ላይ ንግግሩን ሲያቀርብ የተከተለው ይሄን አይነት የንግግር መዝጊያ ዘይቤ ነበር፡፡

እናም ወደ ቤታችሁ ስትመለሱ ከመሃላችሁ የተወሰናችሁት ፖስት ካርድ ላኩልኝ፡፡ እናንተ አንድ ፖስት ካርድ የማትልኩልኝ ከሆነ እኔ እልክላችኋለሁ፡፡በቀላሉም ካርዱ በእኔ እንደተላከላችሁ ታውቁታላችሁ፡፡ ምክንያቱም በፖስታው ላይ ምንም አይነት ማህተም ስለማታገኙ (ሳቅ)፡፡ ሆኖም ግን በፖስታው ላይ የሆነ ፅሁፍ መጻፌ አይቀርም፡፡ ያም የምጽፍላችሁ ነገር ይኼ ነው፡፡

ወቅቶች ይመጣሉ ይሄዳሉ ይፈራረቃሉ፤
ሁሉም ነገር በጊዜው ያልፋል
ታውቃላችሁ
ነገር ግን ሁሌም እንደ ጤዛ የማይጠፋ አንድ ነገር አለ
ያም ሁሌም ቢሆን ለእናንተ የሚኖረኝ ፍቅርና ውዴታ ነው

ይህ አጠር ያለ ግጥም ሐሪ ላውደር ላለው ስብዕናና ማንነት የሚመጥን ነው፡፡ ግጥሙ በተጨማሪም በዚያን ቀን ሳደረገው ንግግርም ተስማሚ የሆነና የሚመጥን ነው፡፡ ስለዚህም ግጥሙ እጅግ በጣም ጥሩ ነበር የሆነለት፡፡ ይህንን ግጥም አንድ ሌላ የሮታሪያን ክለብ አባል ቢሆን ኖሮ የተጠቀመበት ለንግግሩ መጨረሻ ምንም ጣእም የማይሰጠውና የማይገናኝ ነበር የሚሆነው፡፡

ለረጅም ጊዜ ስለ ህዝብ ንግግር እያስተማርኩ በመቆየቴ ስሄድ በግልጽ የተረዳሁት፣ ያየሁትና፣ የተሰማኝ ነገር ቢኖር ሁሌም ተቀባይነት ያለው አንድ ወጥ የሆነ የንግግር አደራረግ ህግ ለማውጣት የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይህ ነገር የሚወስነው ንግግር የምናቀርብበት ጉዳይ፣ ጊዜው፣ ቦታው እንዲሁም የራሱ የንግግር አድራጊው ሰው ተስጥኦ፤ ልክ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ‹‹ተናጋሪው እራሱን የላቀ ተናጋሪ ለማድረግ ያለው ብቃት ናቸው፡፡››

አንድ ጊዜ በአንድ እውቅ የኒው ዮርክ ባለሙያ መሞት ምክንያት በተዘጋጀ የቀብር መልስ የእራት ፕሮግራም ላይ እንግዳ ሆኜ ተገኝቼ ነበር፡፡ በምሽቱ ደርዘን የሚሞሉ ተናጋሪዎች በየተራ ለተለያቸው ወዳጃቸው ባደረጉት የስንብት ንግግር በሄደበት ቦታ መልካም ነገር እንዲገጥመውና እንዲሳካለት ተመኝተው ነበር፡፡

ሁሉም ንግግር ያደረጉ ቢሆንም የአንዱ የንግግር አጨራረሱ ግን ፍጹም የማይረሳ ነበር፡፡ ያ ሰው ንግግሩን የጨረሰው በግጥማዊ ዘይቤ ነበር፡፡ ተናጋሪው ወደተለየው ወዳጁ አስከሬን አቅጣጫ ዞሮ ስሜታዊ በሆነ ድምጽ እያስቀሰ "እንግዲህ አሁን ደህና ሁን ….. መልካም እድል ይግጠምህ፡፡ ወዳጄ ሆይ እኔ ጥሩ የሆነውንና አንተ ልትመኘው የምትችለውን እንድታገኝና እንዲሳካልህ

እመኛለሁ:: በማለት ጀምሮ ከዚህ በታች በተቀመጠው ግጥም የስንብት ንግግሩን ጨርሷል::

ልክ እንደ ምስራቃዊያኑ እኔም ልቤን እሠጥሃለሁ
የአላህ ሰላም ሁሌም ካንተ ይሁን እልሃለሁ
ከየትም ብትመጣ ወዴትም ብትሄድ
የአላህ ስጦታ የሆኑት የሚያምሩ የቴምር ዛፎች
ይብቀሉልህ ቀን ቀን በስራ በምሽቱ እረፍትም በረከት ይሁንህ
የአላህ ፍቅርም በረከት ይሁንህ
ልክ እንደምስራቃዊያን እኔም ልቤን ልስጥህ
የአላህ ሰላም ሁሌም ካንተ ይሁን

ሚር ጂ ኤ አቦት በብሩክሊን የሚገኘው የኤል ኤ ዲ ሞተርስ ኮርፖሬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት ለድርጅቱ ሰራተኞች ስለባቤትነትና ስለኮርፖሬሽን ንግግር ባደረገበት ወቅት ንግግሩን ለመጨረስ የተጠቀመበት የማይረሳ ግጥም ከኪፕሊንግ ሁለተኛው ‹ዳን› ከተባለው መጽሐፍ በመውሰድ ነበር::

እሁን ይህ የጫካው ህግ ነው:: ልክ እንደ ሠማይ የቆየ የነበረና ህያው ነው:: የሚጠብቁትና የሚንከባከቡት ተኩላዎች ይኑሩበት! ይሳካላቸው! ግን የሚያጠፉትና የሚያወድሙት ግን መሞት አለባቸው::

የደኑ ጥንካሬ ተኩላዎች እንደሆኑ ሁሉ የተኩላዎቹም ጥንካሬ ደኑ ነው::

በከተማው ወደሚገኘው የህዝብ ቤተመጻህፍት ሄደህ ለቤተመጻሕፍቱ ባለሞያ በአንድ ወይም በሌላ ጉዳይ ላይ ንግግር ለማድረግ እየተዘጋጀህ እንዳለህ ነግረሃት ለንግግርህ ሃሳብ ተስማሚ የሆነ የግጥም ጥቅስ እንድትጠቁምህ ብትጠይቃት ለንግግርህ ሃሳብ ተስማሚ የሆነ የግጥም ጥቅሶችን የያዘ የመጽሀፍት ማውጫ ዝርዝር እንደ ‹ባርትሊት የተለያዩ ግጥሞችን ዝርዝር የያዘ መጽሀፍትን የመሳሰሉትን በመስጠት ልትረዳህ ትችላለች::

## ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በመውሰድ ለንግግርህ መጨረሻ መጠቀም ያለው ኃይል

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅሶችን በመውሰድ ለንግግርህ ማጣቀሻ መጠቀም ከቻልክ በጣም ዕድለኛ ነህ:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅሶችን ወስዶ መጠቀም ከፍተኛ የሆነ ውጤት አለው:: ታዋቂው የባንክ ባለሙያ ፍራንክ ቫንደርሊፕ ለአሜሪካ የታወቁ የብድር ተቋማት ንግግር በሚያደርግበት ወቅት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማጣቀስ ንግግርን የመጨረስ መንገድ ተጠቅሞበታል::

«እቋማችን ያበደርነውን ገንዘብ በፍርድ ቤት ከሰን ማስመለስ ብቻ ከሆነ የምንፈልገውን መቼም አናገኘውም:: በራሥ ወዳድነትና በሥግብግብነት መንፈስና እቋም ብቻ የምንፀና ከሆነ ከፍተኛ የሆነ ጥላቻን ብቻ እንጂ

> ገንዘባችንን አናገኘውም፡፡ በሳልና ጠንቃቃ ችር ወይም ሰጋስ ከሆንን ግን፡፡ ያበደርነውን ገንዘብ በሙሉ ማግኘትና ማስመለስ እንችላለን፡፡ ለእነሱ የምናደርገው ማንኛውም ጥሩ ነገር ለእኛ ከፍተኛ የሆነ ጥቅምን በሌላ አካሄድ በመሄድ ከምናገኘውና ከምናረጋግጠው በላይ ያመጣልናል፡፡ ሕሱ የእራሱን ህይወት ብቻ ለማዳን የሚሯሯጥና የሚጥር ህይወቱን ያጣዋል፡፡ ግን እሱ ለእኔና ለቃሌ ሲል የራሱን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥልና የሚመጣ ህይወቱን ያዳን ይሆናል፡፡»

## ከፍተኛ ማጋነን

ንግግር በከፍተኛ ሁኔታ በማጋነንና በመስቀል መጨረስ እጅግ የተለመደ የዕውቀት መንገድ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ይህን አይነት የንግግር መንገድ ንግግሩን ተቆጣጥሮ ሳይሰሩ ከጭብጡ ሳይወጣ ለማጠናቀቅ እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን በአግባቡ የምንጠቀምበት ከሆነ እጅግ በጣም ምርጥ የሆነ የንግግር አጨራረስ መንገድ ነው፡፡ ደረጃ በደረጃ ስሜት ቀስቃሽና በአረፍተ ነገሩ ስሜትን የሚቆሰቅስ ንግግራችንን ልንደመድምበት የሚያስችለን መንገድ ነው፡፡

እንደዚህ ያለ ስሜትን በከፍተኛ ደረጃ የሚቀሰቅስና በሚያናድድ ሁኔታ ንግግርን መጨረስ በምዕራፍ ሦስት ውስጥ እንደተመለከትነው በፊላደልፊያው የሽልማት ስነ-ስርዓት ላይ በቀረበው ንግግር ውስጥ መመልከት እንችላለን፡፡

በተመሣሣይ መልኩም የአብርሃም ሊንከን ከፍተኛ ስሜት በሚቀሰቅስ መልኩ ንግግርን መጨረስ በኒጋራ ፏፏቴዎች ባስተማረበት ወቅት ላዘጋጃቸው ንግግሮች ተጠቅሟል፡፡

እስኪ በዚህ በሊንከን ንግግር ውስጥ እያንዳንዱን ለንጽጽር የተጠቀመባቸውን ዓረፍተ ነገሮች ተከትሎ ከመጣው ከዋናው የንግግሩ መልእክት ጋር ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠርና ከፍተኛ የሆነ ስሜትን ለመቀስቀስ እንደተጠቀመበት ተመልከቱ፡፡ አብርሃም ሊንከን የእሱን ዘመንና ጊዜ ከኮሎምቦስ፣ እየሱስ፣ ከሙሴ፣ ከአዳም እንዲሁም ከሌሎች ጋር በማነጻጸር ለንግግሩ ማጠቃለያ ከፍ ያለ ውጤትና ጥቅም ለማግኘት ተጠቅሞበታል፡፡

> የኋላው ታሪካችን ተዳስሶ የማያልቅ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቶፎር ኮሎምቦስ ይህን አህጉር ሲፈልግ፣ እየሱስ ክርስቶስ ስቃይን ተቀብሎ በመስቀል ላይ ሲሰቀል፣ ሙሴ እስራኤላውያንን ቀይ ባህርን ለሁለት ከፍሎ ሲያሻግራቸው፣ ሌላው ቀርቶ አዳም በፈጣሪው እጅ ወደዚህ አለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ እንደ አሁኑ የኒጋራ ፏፏቴ ያኔም እዚሁ ቦታ ላይ ያጓራ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት ላይ ከምድረገጽ የጠፉውና አመጽ ቅሪቶች የአሜሪካን ምድር የሞሉት የዳይኖሰር አይኖች ሁሌም እኛ ዛሬ እንደምናየው ወደ ኒጋሪ ፏፏቴዎች ያማትሩና ይመለከቱ ነበር፡፡ ከመጀመሪያው የሰው ዘርም ሆነ ከጥንታዊው የሰው ልጅ እድሜ በላይ የሆነው ኒጋራ ከዛሬ አስር ሺህ አመት በፊት እንደነበረው ዛሬም ጠንካራና አዲስ ነው፡፡ ከብዙ ጊዚያት በፊት ከምድር ላይ የጠፉት እጅግ ግዙፍ የሆኑት አውሬዎች እንኳን ከኒጋራ ውሃ ይጠጡና በአካባቢው ይገኙ

እንደነበር በየቦታው የተገኙት ትላልቅ አጽመ ቅሪቶች ይመሰክራሉ:: በዚያ በረጅም ጊዜ ውስጥ ቢሆንም የጊዜው ርዝመት ኒጋራን አላደበዘዘውም፣ ውሃውን አላደረቀውም፣ በፍጹም አላቀዘቀዘውም፣ ፀጥ ብሎና እርፎ እንዲተኛ አላደረገውም::

ዌንደል ፊሊፕስም ይህ አይነቱን ስልት ለቶው ሴይንት ሊአቨርቸር ባደረገው ንግግር ላይ ተጠቅሞበታል:: የንግግሩን የማጠቃለያ ክፍል ከዚህ በታች ተጠቅሷል:: ይህ የዌንደል የንግግሩ የመጨረሻ ክፍል የተለያዩ ህዝባዊ ንግግሮች ተሰባስበው በታተሙበት መጽሃፍ ውስጥ የሚገኝ ነው:: የንግግሩ መጨረሻ የአነሳሽነት ኃይል አለው:: በዚህ አይነቱ የንግግሩ መጨረሻ ምንም እንኳን ከአሁኑ ዘመን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ልናጣጥመው ባንችልም እንኳን አጨራረሳችንን ከፍ ባለ መልኩ በማጋነን የሚያሳምር ከሆነ በጣም አስደሳች ነው:: ይህ ንግግር የተጻፈው ከግማሽ ምዕተ አመት በፊት ነበር:: በንግግሩ ውስጥም ዌንደል ፊሊፕስ በጠላትነት ስሜትና መንፈስ የተነሳ ምን ያህል ስህተት ውስጥ ወድቆ እንደነበር መመልከት አስደሳች ነው::

ጆን ብራውንና ቶው ሴይንት ለአቨርቸር አስቀድመው በመመልከትና በማየት መጥፎና ትክክል ያልሆኑ ድርጊቶችን በማውገዝና በመናገር በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ የሆነውን ቦታ የያዙ ናቸው:: ‹ከሃምሳ አመት በኋላ ሲሆንና እውነታው ሲገለጥ› ደግሞ እንደነሱ በታሪክ ሂደት ውስጥ አንድ ነገር ይናሆል ብሎ ለመናገር መድፈር ልክ የሚቀጥለው ዓመት ገበያ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ አስቀድሞ እንደመናገር ከባድ እንደሆነ ይታወቃል::

እኔ ናፖሊዮን ብዬ እጠራዋለሁ ግን ናፖሊዮን በታጠፈ ቃልና መሃላ በክህደት ውስጥ የደም ባህርን በፈጠረ ጦርነት ታላቅ ግዛትን ለመፍጠር ነበር የሞከረው:: ይህ ሰው ቃሉን የለወጠ ወይም የካደ አልነበረም:: «ማፈግፈግ የለም! የህይወቱ መመሪያና መሪ ቃል ነበር:: በመጨረሻው ሰዓት ፈረንሳይ ውስጥ ለወንድ ልጁ የነገረው ይህን ነበር «ልጄ አንተ አንድ ቀን ወደ ሳንቶ ዶሚኒጎ ትመለሳለህ፣ አገርህ ፈረንሳይ አባትህን እንደ ገደለችብህ እርሳው::» እኔ ሮምዌል ብዬ እጠራዋለሁ:: ግን ሮምዌል ወታደር ብቻ ነው የነበረው:: የመሰረታት አገሩም ከሱ ሞት ጋር አብራ ወደ መቃብሩ ነው የገባችው:: ዋሽንግተን ብዬም እጠራዋለሁ ግን ይህም ታላቅ ቨርጂኒያዎ ባሮች ነበሩት:: ይህ ሰው የአሜሪካን ግዛት አደጋ ላይ ከመጣል ይልቅ በቆንጆዋ በራሱ ግዛት ይጧጧፍ የነበረውን የባሪያ ንግድ የከለከለና ያገደ ሰው ነው:: እናንተ ታሪክን ከሁሉም ጎን የተፃፈውን እውነት በመመልከት፣ በማንበብና፣ በመስማት ማወቅና መረዳት ሳይሆን እናንተ የምትፈልጉትንና የምትወዱትን ብሎም የምታነቡትንና የምታውቁትን ብቻ ከሆነ መስማት የምትፈልጉት ዛሬ ማታ እንደ እብድ አድርጋችሁ ልትቆጥሩኝ ትችላላችሁ::

ግን ልክ ከሃምሳ አመታት በኋላ እውነታው ሲከሰትና ሲገለጥ የጣትክ ማሕደር ፎሲዮንን ለግሪኮች፣ ብሩተስን ለሮማውያን፣ ሐምፐዳንን ለእንግሊዞች፣ ላፋይቴን

ለፈረንሳዮች፣ጂርጅ ዋሽንግተንን ብልህና የቀደመው ዘላቂ የሆነው ስልጣኔያችን አበባ፣ ጃን ብራውንን የቀትር ብስል ፍሬ አድርጎ ታሪክ እንደመዘገባቸውና እንዳሰፈራቸው ሁሉ ከሁሉም በላይ በሆነ መልኩ የወታደሮች፣ የአገር ገርዎች፣ የጀግኖች እንዲሁም የቶው ሲይንት ለአቨርቸር ሥምን ታሪክ ከፍ አድርጎ በሠማያዊ ሰማይ መዝገብ ላይ በወርቃማው የፀሀይ ቀለም በማጣቀስ የሚመዘግበው ነው።

## ወደ መሬት ሲወርድ

በጣም ጥሩና ቆንጆ የሆነ የንግግር አጀማመርና አጨራረስ ልምድ እስከታዳብርና እስክትለምድ ድረስ የሚስማማህን መንገድ ለማወቅና ለመካን ጥረት ማድረግ፣ ማደን፣ መፈለግ አለብህ። ካገኘሽውና ካወቅከው በኋላ ተዋህደው፣ አጣጥመው፣ ቅረበው፣ ምርጥ ሁንበት። የአድማጩን ስሜትና ሞቅታ በመመልከትና በመከተል ብቻ ንግግሩን ገታ ሳያደርግ ያለማቋረጥ በፍጥነት የሚናገር ተናጋሪ ብዙውን ጊዜ ተስማሚና ተመራጭ ተናጋሪ አይደለም። አንዳንዴም ንግግሩ አወንታዊ የሆነ ያለመወደድ ሁኔታ ይደርስበታል።

ከዚህ አንጻር እንደ ታርሳሱ ቅዱስ ሳዑል ከፍተኛ የሆነ ውግዘት የደረሰበትና ሀጢያተኛ የተደረገ ሰው የለም። ቅዱስ ጳኡል ረጅም ሰዓት የደረሰበትና ሀጢያተኛ የተደረገ ሰው የለም። ቅዱስ ጳኡል ረጅም ሰዓት በቤተመቅደሱ ውስጥ ሲሰብክ በስብከቱ አሰልቺነት የተነሳ "አንድ ያለማቋረጥ በቤተመቅደሱ ውስጥ ሲሰብክ በስብከቱ አሰልቺነት የተነሳ "አንድ ኢትቺየስ" የሚባል ወጣት እንቅልፍ ጥሎት ከቤተክርስቲያኑ የላኛው ፎቅ በመስኮት ወድቆ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት አንገቱ ይሰበራል። ሆኖም ከዚህ በኋላም እንኳን ቅዱሱ ንግግሩን አላቆመም ነበር። ማን ያውቃል? በማለት ነበር ስብከቱን የቀጠለው። እኔም አንድ እንዲህ ያለ የማይቋርጥ ንግግር በብሩክሊን ዩኒቨርሲቲ ክለብ በተዘጋጀ የእራት ግብዣ ላይ ያደረገ ዶክተር ትዝ ይለኛል። የእራት ግብዣው ፕሮግራም ረዥም ነበር። ብዙ ሰዎች በየተራ ንግግር አድርገው ከጨረሱ በኋላ ሌሊቱ ተጋምሶ ወደ መንጋቱ ላይ ነበር። በወቅቱ የአብዛኞቻችን ግምት የነበረው የመጨረሻውን ንግግር እንዲያደርግ ተራ የደረሰው አንድ ሰድስት አረፍተ ነገሮችን የያዘ አጭር ንግግር አድርጎ በቶሎ ወደ ቤት እንሄዳለን የሚል ነበር። ግን ያን ያደረገ ይመስላችኋልን አልነበረም። ዶክተሩ ለአርባ አምስት ደቂቃ ያለማቋረጥ አሰልች በሆነ መንገድ ንግግር አድርጎ የንግግሩን ግማሽ ለመሸፈን እንኳ ብዙ ያቀርበው ነበር። በዚህን ጊዜ ግን በግብዣው ላይ የተገኘው እንግዳ በሙሉ ዶክተሩ ልክ እንደ "አትቺየስ" ከሆነ ነገር ላይ ወድቆ አንዱ አካሉ ተጎድቶ ወይም ብቻ የሆነ ነገር ሆኖ አፉን እንዲዘጋ ብቻ ነበር የሚመኘው።

ሚር ሎሪሚየር የቅዳሜ ምሽት ፖስት ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በነበረበት ወቅት በጋዜጣ ላይ ይጻፉና ይወጡ የነበሩ የተለያዩ ጽሁፎች በጣም ተወዳጅ ሆነው ብዙ አንባቢ አግኝተው ከፍተኛ የሆነ ደረጃ ላይ ከደረሱ በኋላ እንዳይወጡ ያስቆም እንደነበር ነግሮኛል። ለምን ነበር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ

የሚያስቀምጠው? ሁሌስ ለምን ያደርገዋል? "ምክንያቱም". . . ይላል ሚር ሎሪሚየር "ከፍተኛ" ደረጃ ላይ ከደረስክና ከፍተኛ ተቀባይነት ካገኘህ በኋላ የሚቀጥለው ነገር ከሚፈልጉትና ከበቂ በላይ በሆነ አኳኋን መስጠት ወደም ማቅረብ ነው። ስለዚህ ልክ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ማቆም አለብህ። አለበለዚያ ከከፍተኛ የተፈላጊነት እና የተወዳጅነት ደረጃ በኋላ የሚከተለው ወደታች ማሽቆልቆል ነው? ያለመፈለግ ነው? መሰልቸት ነው? በዚህ ዓይነት ሁኔታ አንድን ተቀባይነትና ተወዳጅነት ያገኘ ነገር ከመሰልቸቱና ተወዳጅነቱ ከማሽቆልቆሉ በፊት እንደተወደደ ማቆም የመቻል አቅም ትክክለኛና ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኝ ምክንያታዊ ውሳኔ ነው። በመሆኑም ንግግር በምናደርግበት ጊዜም ልንጠቀምበት የሚገባ ነው። አድማጭህ ገና ብዙ ለመስማት በሚጓጓበት ሰዓት ላይ ንግግርህን ጨርሰው። እየሱስ ክርስቶስ አድርጓቸው ከነበሩት ንግግሮች ሁሉ የላቀውና ማንም ሰው በአምስት ደቂቃዎች ውስጥ ደግሞ ሊናገረው የሚችለው ስለእናትና የሀሊና ሚዛን በተራራዎቹ ላይ የተናገረውና ያስተማረው ነው። በጌትስበርግ አብርሃም ሊንከን መልእክቱን በንግግር ለማስተላለፍ የተጠቀመው አስር አረፍተ ነገሮችን ብቻ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለምድር አፈጣጠር የተጻፈውን ለማንበብ የሚወስደው ጊዜ በአንድ እለታዊ የጠዋት ጋዜጣ ላይ የሚወጣውን ተከታታይ የግድያ ታሪክ ለማንበብ ከሚወስደው ጊዜ ያነሰ ነው።

ዶክተር ጆንሰን የናያሳ አንጀሊካን ቤተክርስቲያን ጳጳስ ከመሆኑ በፊት በአፍሪካ ከሚገኙ ኋላቀር ህዝቦች ጋር ለአርባ ዘጠኝ አመት አብሮ በመኖር ሰፊ የሆነ ጥናት በማድረግ መጽሐፍ ጽፎ ነበር። በመጽሐፉ በአፍሪካ በቆየበት ጊዜ በመንደሮች በሚደረጉ ስብሰባዎች ወይንም ‹ጉዋንጉዋራ› ላይ አንድ ተናጋሪ በጣም ረዥም የሆነ ንግግር በሚያደርግበት ወቅት አድማጩ "ኢሜቶሻል" "ኢሜቶሻል" . . . ወይንም "በቃህ" "በቃህ" እያለ በመጮህ ተናጋሪውን ንግሩን እንዲያቋርጥ ዝም እንዲል እንደሚያደርጉ በመጽሐፉ ጽፎታል።

በአንድ ሌላ ጎሣም አንድ ንግግር አድራጊ ሰው ንግግሩን በአንድ እግሩ ቆሞ እስካቀረበ ድረስ ብቻ ለመቀጠል እንደሚፈቀድለት ማየቱን ጽፏል። በአንድ እግር ቆሞ ንግግር የሚያቀርበው ሰው የተነሳው እግሩ መሬት ሲነካ . . .አበቃ. . . ጨርሷል ማለት ነው።

በአንድ ስብሰባ ላይ ከሚገኙ አድማጮች ግማሹ እንኳን ትዕግስተኞች ጨዋና ስሜታቸውን የሚቆጣጠሩ ሆነው የሚገኙ ቢሆንም እንኳን ረዥምና የተንዛዛ ንግግርን እጅግ በጣም ነው የሚጠሉት።

ስለዚህ እኔ ከሰማኋቸው እናንተ ከማታውቋቸው ከላይ ባየናቸው ጥሩ እና መጥፎ ንግግሮች እንዲሁም ንግግር አቅራቢዎች ድክመቶችና ጥንካሬዎች ከስህተቶቻቸው ጥንቃቄን፣ ከጠቃሚና ቆንጆ ዘዴዎቻቸው ደግሞ ትምህርትን ውሰዱና ንግግር ማድረግን ተማሩ።

# ምዕራፍ አስር

## ሃሳብህን እንዴት ግልጽ አድርገህ መናገር ትችላለህ?

በአንደኛው የአለም ጦርነት ወቅት ታዋቂው እንግሊዛዊ ጳጳስ በፍቃደኝነት ለዘመቱ የተወሰኑ የጦር ሰራዊቱ አባላት በካምፕ አፕተን ንግግር አድርጎ ነበር፡፡ በወቅቱ ወታደሮቹ ለመከላከያ ወደተቆፈረው የጉድጓድ ምሽግ እየተጓዙ ነበር፡፡ ነገር ግን ከመሃከላቸው ከጥቂቶች በስተቀር ለመዋጋት ወደጦር ግንባር ስለዘመቱበት ምክንያት በቂ የሆነ እውቀትና ግንዛቤ የነበራቸው አልነበሩም፡፡ እኔም ይህን አውቅ ስለነበር ጥያቄውን አቅርቤላቸው ነበር፡፡ ጳጳሱ ለዘማች ወታደሮቹ ስለ አገሮችና ስለ ህዝቦች አለምአቀፍ ወዳጅነት "እንዲሁም ስለ ሰርቢያውያን ከፀሀይ በታች የመኖሪያ አገር የማግኘት መብት በሚያወሩበት ወቅት ለምን ነበር ከመሃከላቸው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሰርቢያ ከተማ ይሁን ወይም የበሽታ አይነት ፍፁም የማያውቁት የነበረው? እርሱስ ጳጳሱስ ቢሆን የሚናገራቸው ነገሮች ለአብዛኞቹ ወታደሮች ግልፅ እና ሊረዷቸው የማይችሉ ሆነው ሳለ ለምንድን ነው በማያውቋቸው ነገሮች ዙሪያ ንግግር ማድረጉ? . . . ንግግሩ እኮ ከመለፍለፍ የበለጠ ምንም ነገር እንዲጨብጡ ያደረጋቸው አልነበረም፡፡ ጳጳሱ ስለንግግሩ ዓላማም ሆነ እንዴት ንግግሩን በተሳካ ሁኔታ ማድረግ እንደሚችሉ አስቀድሞ የሚያውቁት ምንም ነገር አልነበረም፡፡

የአንድ ንግግር ዓላማ ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህ ማለት ሁሉም ንግግር አድራጊ ሰው አወቀውም አላወቀውም ንግግር የሚያደርግበት ምክንያት ከአራት የንግግር ዋነኛ አላማዎች አንዱ ነው፡፡

እነዚህ አራቱ የንግግር ዋና ዓላማዎች ምንድን ናቸው?

1. አንድን ነገር ግልጽ ለማድረግ
2. አድናቆትን ለመፍጠር እና ለማሳመን
3. ድርጊት ለማስፈፀም
4. ለማዝናናት

1.እስቲ እነዚህን የንግግር ዓላማዎች ተከታታይ በሆኑ ጠንካራ ምሳሌዎች በማስደገፍ እንመልከት፡፡ አብርሃም ሊንከን ሁሌም ስለ ሜካኒክስ የማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት የነበረው ሰው ነበር፡፡ አንድ ጊዜም የራሱ ፈጠራ የሆኑ ጀልባዎችን ከአሸዋ ዳርቻ ላይ ወይም ከሌሎች ቦታዎች ላይ በከፍታ በማንሳት ወደተፈለገው ነገር ላይ አውጥቶ ለመጫን የሚረዳን ማንሻ መሳሪያ ሰርቶ ነበር፡፡ በቢሮው አቅራቢያ በሚገኝ አንድ ጋራዥ ውስጥም የሰራው ይህ የጀልባ ማንሻ ምንም እንኳን የተዋጣ ሆኖለት አገልግሎት ላይ የዋለ ባይሆንም፡፡ አንድ ቀን ተቀባይነት አግኝቶ ጥቅም ሊሰጥ ይችላል ብሎ ከፍተኛ እምነት ነበረው፡፡ በመሆኑም ሁሌም ጓደኞቹና ሌሎች ሰዎች ወደ ቢሮ በሚመጡበት ጊዜ ስለፈጠረው የጀልባ ማንሻ ሊፍት ያለምንም መሰልቸት በተደጋጋሚ ማብራሪያ

በመስጠት ያስረዳ ነበር። የእነዚህ ተደጋጋሚ ንግግሮቹ ዋነኛ አላማ ስለፈጠረው መላሪያ ምንነት ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነበር።

ሊንከን ሁሌም ቢሆን የሚታወሰውንና ሰው ሁሉ የማይረሳውን የጌትስበረ ንግግሩን ሲያደርግ፣ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን በዓለ ሲመቱን ንግግር ሲያደግ በዜንጎ ክፋይ የቀብር ስነስርዓት ላይ የመታሰቢያ ንግግሩ ሲያደርግ፣ የነዚህ ንግሮች ሁሉ ዋነኛ ዓላማ አድናቆትንና እርግጠኝነትን ለመፍጠር ነበር። እዚህ ላይ ሊንከን ንግግሩ አሳማኝ ከመሆኑ በፊት ግልጽ መሆን እንዳለበት ምንም ጥርጥር የለውም። ይሁን እንጂ በእነዚህ ንግግሮች ውስጥ በማብራራትና በማስረዳት ግልጽ ግንዛቤን መፍጠር ዋነኛው ጉዳይ አልነበረም።

ሊንከን በፍርድ ቤት ከዳኞቹ ፊት ቆሞ በሚያደርጋቸው ንግግሮች ብይን እንዲበየንለት ወይም የሚፈልገው ውሳኔ እንዲሰጠው ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። በሚያደርጋቸውም የፖለቲካ ንግግሮች ከፍተኛ የሆነ መራጭ ወይም ድምጽ ለማግኘት ይጥር ነበር። እናም የነዚህ ንግግሮቹ ዓላማ አንድ የሆነ ድርጊትን እንዲያከናውን ማድረግ ማስቻል ነበር።

ፕሬዚዳንት ሆኖ ከመመረጡ ሁለት ዓመት በፊት ሊንከን በፈጠራ ዙሪያ አንድ ትምህርታዊ ገለፃ አዘጋጅቶ ነበር። ዋነኛ ዓላማውም ማዝናናት ነበር። ቢያንስ ማዝናናትን አንዱ አላማው ሲያደርገው ይችላል፣ ነገር ግን ይህ ዝግጅት የተሳካና ተቀባይነት ያገኘ አልሆነለትም ነበር። ሊንከን በማስተማር ስራው እጅግ የተወደደ ቢሆንም በአንድ ከተማ በዚሁ በፈጠራ ዙሪያ ሲሰጥ የነበረው ትምህርት ምንም ሰው ያልተገኘለትና በህይወቱ በማስተማር ስራ ሳይሳካለት የቀረ ተብሎ የተወሰደ ብቸኛው ምሳሌ ነው።

ነገር ግን በዚህ ዕሁፍ በጠቀስኳቸው ሌሎች ንግግሮቹ በከፍተኛ ሁኔታ የተሳካለትና ታዋቂ ለመሆን የቻለባቸው ነበሩ። ለምን? ምክንያቱም በነዚህ ንግግሮቹ ንግግር የሚያደርግበትን ዓላማ ያውቅ ስለነበር እንዴት ማሳካት እንደሚችልም ተረድቶት ነበር። በንግግሮቹ ወዴት መሄድ እንደሚፈልግና የሚፈልግበት ቦታ እንዴት መድረስ እንደሚችልም ያውቅ ነበር። ይህን ጠንቅቆ ባለማወቅና ባለመረዳት ብዙ ተናጋሪዎች ለመናገር የሚፈልጉት ነገር የተምታታ የተዘበራረቀና ፍርሃት ላይ የሚጥል ይሆንባቸዋል።

ለምሳሌ አንድ ጊዜ አንድ የአሜሪካን ምክር ቤት አባል ከድሮው የኒው ዮርክ ሂፖድሮም የምክር ቤቱ መሰብሰቢያ መድረክ ከፍተኛ በሆነ የተቃውሞ ጩኸት ንግግሩን አቋርጦ ከመድረኩ ላይ እንዲወርድ መደረጉን አይቻለሁ። ምክንያቱም የምክር ቤት አባሉ ባለማስተዋልና እርግጠኛ በመሆን ነገር ግን ብልህነት በጎደለው ሁኔታ የንግግሩ ዋነኛ አላማ አድርጎ የወሰደው በማብራራትና በማስረዳት ግልፅ ማድረግን በመሆኑ ነበር። ይህን ንግግር ያደረገው በጦርነቱ ጊዜ ነበርና በንግግሩ አሜሪካን ለጦርነት እንዴት እንደተዘጋጀች ነበር የሚያወራው። ተሰብሳቢው ግን ትዕግዝን ወይም መመሪያውን ለመቀበል አልነበረም

የሚፈልገው:: በትዕግስትና በጨዋነት ለአስር ደቂቃዎች ያዳምጡት ነበር:: ከሩብ ሰዓት በኋላ ግን በቶሎና በአጭሩ ንግግሩን እንዲያጠናቅቅ ይመኙ ነበር:: ግን አልሆነም:: የምክር ቤት አባሉ ከአንዱ ወደ አንዱ እያለ ቀጠለ፣ ትዕግስ አለቀ፣ አድማጮቹ ከዚያ በላይ ማዳመጥ የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ:: በዚህ መሃል አንድ ሰው ከፍተኛ የሆነ የተቃውሞ ጩኸት አሰማ ወዲያው ሌሎችም ቀጠሉ:: በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ በምክር ቤቱ የተገኙ አንድ ሺህ ሰዎች የፉጨትና የጩኸት ድምፅ ማሰማት ጀምረው ነበር::

ተናጋሪው የአድማጮቹን ስሜት በደንብ አድርጎ ሲያጤንና ሲረዳ ባለመቻሉ በተቃውሞና በጩኸት ንግግሩን እንዲያቋርጥ ሲገደድ ችሏል::

አድማጮቹ ያንን እንዲያደርጉ የገፋፋቸው እሱ የአድማጮቹን ስሜት መረዳት ያለመቻሉ ነው:: በንግግር አድራጊውና በአድማጮቹ መካከል ግን ያለመግባባት ነበር:: ይህም ትዕግስታቸውን ጨርሰው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲናገሩና እንዲጮሁ ያደርጋቸዋል አድርጓቸዋል:: ንግግሩን በማቋረጥ ዝም እንዲልላቸው ነው የተነሣሡት:: የተቃውሞ ድምፃቸው እየጨመረና ከፍ እያለ ነው የመጣው:: በስተመጨረሻ ከከፍተኛ ንዴትና ብስጭት ውስጥ የወጣው ከፍተኛ ጩኸት የንግግር አድራጊውን አንደበት እንዲዘጋ አድርጎታል:: ተናጋሪው በዛ እየጨመረ በመጣው የተቃውሞ ጩኸት ውስጥ ሃያ እርምጃ ላይ እንኳን ሊሠማ እንዳማይችል ያደረገው:: ስለዚህ ንግግሩን እንዲያቋርጥ ተገዷል:: ሽንፈትን በውርደትንም ተቀብሎ ከመድረኩ ላይ ንግግሩን አቋርጦ ለመውረድ ግዴታው ሆኗል::

ከዚህ ምሳሌ ልንማር የምንችለውና የምናገኘው ጥቅም ንግግር የምታደርግበትን ዋነኛ ግብ ጠንቅቆ መረዳትን ነው:: ልታደርገው ያሠብከውን ንግግር ከማዘጋጀትህ በፊት ግብህን በትክክል ማወቅ ወይም መምረጥ አለብህ:: እንዴት ልታሣካው እንደምትችልም መረዳትና ማወቅ አለብህ:: ከዚያም ዝግጅት በማድረግ በሣይንሳዊ የንግግር አቀራረብ መንገድ ንግግርህን ማቅረብ አለብህ::

## ግልፅ የሆነ ግንዛቤን ለመፍጠር ኃይልን መጠቀም

ግልፅ በሆነ ሁኔታ ማስረዳት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን እንዲሁም ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ልናውቅ ይገባል:: አንድ ጊዜ አንድ አየርላንዳዊ ገጣሚ በአንድ ምሽት ግጥሞቹን በሚያቀርብበት ጊዜ ከተሰበሰቡት አድማጮቹ ውስጥ አስር ከመቶው እንኳን ስለምን እንዳወራ እንኳን የሚያውቁ ነገር አልነበረም:: ብዙ ንግግር አቅራቢዎች በግል ህይወታቸውም ሆነ በመንግስት ስራ ውስጥ የሚያቀርቧቸው ንግግሮች የዚህ አይነት ናቸው::

ለአርባ አመታት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና የመንግስት ተቋማት በማስተማር ካሣለፈው ከሰር ኦሊቨር ሎጅ ጋር ስለ ህዝባዊ ንግግሮች ውይይት በሚደርግበት ወቅት ከሁሉም በላይ ህዝባዊ የሆኑ ንግግሮችን ለማድረግ በጣም

አስፈላጊ መሆናቸውን ልንረዳና ልናውቅ የሚገባን ሁለት ነገሮች መሆናቸውን መገንዘብ ችያለሁ። አንደኛው የንግግር አደራረግ ዕውቀትና ዝግጅት፣ ሁለተኛ የምናደርገው ንግግር ለአድማጮችን ግልፅ እንዲሆንና በቀላሉ መረዳት እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ናቸው።

ጄኔራል ቮን ሞልቴክ የፍራንኮ ፕራሽያን ጦርነት በተጀመረበት ወቅት ለጦር ሰራዊቱና ለበታች አመራሮች ይህንን ንግግር አድርጎ ነበር። «ክቡራንና አስታውሱ — ተገቢ በሆነ መንገድ ልንረዳው ያልቻልነው ወይም ያላወቅነው ማንኛውም ዓይነት ስርዓት ሁሉም አይታወቅም»

ናፖሊዮንም ይህን አደጋ ሁሉም ይገነዘበው ነበር። ሁልጊዜም ለረዳቱና ለሞና በሀሳቡ ደጋግሞ ያስገነዘበውና ይሰጠው የነበረው መመሪያ «ግልፅ አድርገው፣ ግልፅ አድርገው» የሚል ነበር።

እየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ ሁልጊዜም ለህዝቡ ትምህርትን ሲያስተምር ተጨባጭ የሆኑ ነገሮችን ለአስተምሮቱ በምሳሌነት እንደሚጠቀም በጠየቁት ወቅት «ምክንያቱም የሚያዩትን ነገር አያዩትም፣ የሚሰሙትን ነገር አይሰሙትም፣ የሚያዩትንም የሚሰሙትንም ልብ ብለው አያጤኑትም አይገነዘቡትም» በማለት ነበር የመለሰላቸው።

በአንድ ርዕስ ወይም ጉዳይ ላይ ቢል የሰመዶና ለአድማጭህ እንግዳ በሆነ መልኩ በምታወራበት ጊዜ ስለምታወራው ጉዳይ ግንዛቤና እውቀት ካላቸው ሰዎች በስተቀር ሌሎች አድማጮቹ የምታወራውን ነገር ይረዱታል ወይም እየገባቸው ነው ብለህ ተስፋ ታደርጋለህ? ይከብዳል። ስለዚህ እንደዚህ አይነትን ሁኔታ ምን ልናደርግ እንችላለን? አንድ ሰው እንደዚህ አይነት ተመሣሣይ ሁኔታ ሲያጋጥመው ምን ሊያደርግ ይችላል? ሊታሰብና ሊሆን የሚችለው በጣም ቀላሉና የተሻለው ተፈጥሯዊ መንገድ ችግሩን መቅረፍ ብቻ ነው የሚቻለው። ለዚህም ሰዎች የሚያውቋቸውን ነገሮች በማብራራትና ግልፅ በማድረግ ጀምረን የማያውቋቸውን ነገሮች በማስከተል ማብራራት ነው ያለብን።

ሠማያዊ መንግስት ...... ምን ይመስላል? እንዴት ይህንን እነዚያ ያልተማሩ የፍልስጤም ገበሬዎች እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? ስለዚህ እየሱስ ክርስቶስ ሰማያዊው መንግስት ምን እንደሚመስል ለፍልስጤም ያልተማሩ ገበሬዎች ለማስረዳት በየቀኑ የሚያደርጓቸውን ተግባሮችና የሚያውቋቸውን እቃዎች በመጠቀም ተጨባጭ በሆኑ ምሳሌዎች ሰማያዊው መንግስት ምን እንደሚመስል ያስተምር ነበር።

ሰማያዊው መንግስት ልክ እንደ እርሾ ነው። አንዲት ሴት ትንሽ የሆነች ሊጥ ውስጥ እርሾ ጨምራ ኩፍ እንደሚያደርገው ወይም እንደሚያተልቀው ሰማያዊ መንግስትም እንቁ እንደሚፈልግ ነጋዴ ነው። አሁን ሰማያዊው መንግስት በባህር ላይ አሳ ለማጥመድ እንደተጣለ ትልቅ መረብ ነው ሁሉ ይህን አይነት አገላለጽ ቀላል ነበር። እነሱ በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት ነው። ከአድማጮቹ መሃል የገበሬት የቤት እመቤቶች እርሾን በየሳምንቱ ዳቦ ለማዘጋጀት

የሚጠቀሙበት ነው፡፡ አሳ አጥማጆችም በየቀኑ መረባቸውን ወደ ባህሩ ይዘው በመሄድ አሳ ለማጥመድ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ነጋዴዎችም ሁሌም ነው እንቁን በመሸጥና በመግዛት ሂደት ውስጥ የሚጠቀሙበት፡፡ ንጉሱ ዳዊት እንዴት ባለ አኳኋን ነበር የፈጣሪውን ጠባቂነት እሩህሩህነትና የሰው ልጅን ወዳድነት ግልጽ አድርጎ ያስረዳው?

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የምፈልገውንም ያደርግልኛል፡፡

በአረንጓዴውም ለምለም መስክ ላይ ያስቀምጠኛል፡፡ ለዘለዓለም ኮለል ብለው ከሚወርዱት ንጹሳ ምንጮች እንድጠጣ ያደርገኛል፡፡

ፍጹም በረሃና ምድረ በዳ በሆነ በዚያ ሃገር ለምለምና አረንጓዴ የሆኑ መስኮች ተራሮችና ሸለቆች . . . ምንም ውሃ በሌለበት ኮለል ብለው የሚወርዱ ምንጮች ሁሌም ሰዎችና እንስሳቶች የሚጠጧቸው...የፈጣሪውን አዛኝነት፣ ቸርነት፣ ደግነት በግልጽ ለማስረዳት ሲጠቀምባቸው እነዚህ አርብቶ አደር ህዝቦች በቀላሉ ለመረዳት ችለዋል፡፡

ከዚህ የሚከተለው ደግሞ በጣም አስገራሚና በተወሰነ መልኩ አስቂኝ የሆነ ተመሳሳይ ሃሳብን ወይም ንግግርን ግልጽ አድርጎ ማስረዳትን የሚያሳይ ምሳሌ ነው፡፡ ጥቂት ሚሽነሪዎች ከኢኳቶሪያል አፍሪካ አጠገብ ለሚገኝ አንድ ጎሳ መጽሀፍ ቅዱስ ወደ ጎሳው ቋንቋ እየተረጎሙ ነበር፡፡ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የተቀመጠ አንድ ግጥም «ሃጢያታችን እንደ ቀይ አበባ ምድሩን ያለበሰ ቢሆንም እንኳ እንደ በረዶ የነጣ ይሆናል» የሚለው ጋር ሲደርሱ ጥቅሱን እንዴት አድርገው ይተርጉሙት? ቃል በቃል ይተርጉሙት? ይህ ደግሞ ምንም አይነት ትርጉም የሚሰጥ አይሆንም፡፡ ፍጹም የማታይሰብ ነው!

እነዚያ ጎሳዎች በፍጹም በአንድ የየካቲት ወር በሰፊ ሜዳ ላይ እንደተነጠፈ ቀይ ምንጣፍ መሬቱን የሸፈነ ቀይ አበባ አይተው አያውቁም፡፡ በረዶን አይተው አይደለም ቃሉን እንኳን ሰምተው አያውቁም፡፡ በበረዶና በከሰል መካከል ያለውን ልዩነት እንኳን ለይተው ለመናገር የማይችሉ ነበሩ፡፡ ነገር ግን እነሱ ብዙ ጊዜ የኮኮናት ዛፎች ላይ በመውጣትና ቅርንጫፎቹን በመነቅነቅ የኮኮናትን ፍሬዎች ለምግብነት የሚጠቀሙ ነበሩ፡፡ ስለዚህ ሚሽነሪዎቹ በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በምሳሌነት የተቀመጡትን ነገር ግን በዚህ ጎሳ የማይታወቁትን ነገሮች በማውጣት እነሱ በሚያውቋቸውን ነገሮች በመቀየር የመጽሐፍ ቅዱሱን ጥቅስ ወደ እነሱ ቋንቋ ተረጎሙት፡፡ የተረጎሙት ጥቅስ እንዲህ ይነበባል «ሃጢያታችሁ እንደኮኮና የውጭ ሽፋን የቀላ ቢሆንም እንደኮኮናቱ የውስጠኛ ክፍል የነጣ ይሆናል» በመጀመሪያው አይነት ሁኔታ ትርጉማቸውን የጎሳው ሰዎች ወደሚያውቁት ነገር በማጣጣም ለመተርጎም ባይሞክሩ ኖሮ ሊሳካላቸው አይችልም ነበር፡፡ በምን ዘዴ መተርጎም ይችሉ ነበር?

በዋረንስበርግ ሚዩዙዩሪ በሚገኝ አንድ የመንግስት የግብርና ማስልጠኛ ተቋም ውስጥ አንድ የአላስካ አስተማሪ ያደረገው ንግግር ልክ ወደ አፍሪካ እንደሄዱት ሚሺነሪዎች ሃሳቡን ወይም ንግግሩን አድማጮቹ ወደሚያውቋቸው ነገሮች በማምጣትና በመመለስ ማጣጣም ባለመቻሉ ምክንያት ንግግሩ ሁለንተናዊ

በሆነ መልኩ ሳይሳካ እንደቀረ ማለትም ግልፅም ሆነ ማራኪና የሚስብ ሳይሆን እንደቀረ ሰምቼ ነበር::

እሱ ለምሳሌ አላስካ 590,804 ስኩዌር ማይል የቆዳ ስፋትና 64,356 ህዝብ እንዳላት ተናግሮ ነበር:: ግማሽ ሚሊዮን ስኩዌር ማይል . . . ብዙም ሰፋ ያለ እውቀት ለሌለው ሰው ይህ ምን ማለት ነው? የሚረዳው አይሆንም:: ብዙውን ጊዜ በሚያደርጓቸውና በሚሰሩቸው ነገሮች ስኩዌር ማይልን ሲጠቀሙ የኖሩ አይደሉም:: በአእምሮአቸው ውስጥ ካለውና ከሚያውቁት መለኪያ ጋር የሚቀናጅና የሚሄድ አይደለም:: አስተማሪው ግማሽ ሚሊዮን ስኩዌር ማይል ከቴክሳስ ወይንም ከሜይን ግዛቶች ስፋት ጋር ተቀራራቢና እኩል እንደሆነና እንዳልሆነ እንኳን ምንም የሚያውቀው ነገር የለም:: ሆኖም ተናጋሪው ለምሳሌ የአላስካ ግዛት የባህር ድንበር ርዝመት ከሌሎቹ የአሜሪካ ደረቅ ግዛቶችና ከለም መሬቶች ርዝመት የበለጠ እንደሆነና የአላስካ ጠቅላላ የቆዳ ስፋትም ከቬርሞንት፣ ኒውሀምፕሻየር፣ ሜይን፣ ማሳቹስተስ፣ ሮድ አይላንድ፣ ኮኔክቲከት፣ ኒው ዮርክ፣ ኒው ጀርሲ፣ ፔንሲልቬንያ፣ ዴልዋር፣ ሜሪላንድ፣ ዌስት ቨርጂኒያ፣ ኖርዝ ካሮላይና፣ ሳውዝ ካሮላይና፣ ጆርጂያ፣ ፍሎሪዳ፣ ሚሲሲፒና ቴኔሲ ግዛቶች ስፋት ድምር እንኳን የበለጠ እንደሆነ ማስቀመጥና መናገር ይችል ነበር:: እንዲህ አድርጎ ማስቀመጥ ወይም መናገር የአላስካ ግዛትን ጠቅላላ ርዝመትና የቆዳ ስፋት በተሳካና ግልፅ በሆነ መልኩ ለመረዳት አያስችልም?

እሱ የህዝብ ብዛቷ 64,356 ነው ብሎ ነበር የተናገረው:: ይህን የተናገረውን የህዝብ ብዛት ቁጥር ከአስር አድማጮቹ አንዱ እንኳን ከአንድ ወይም ከአምስት ደቂቃ በኋላ የሚያስተውልበት እድል በጣም ጠባብ ነው:: ለምን? ምክንያቱም ፈጠን ባለ ንግግር ውስጥ «ስልሳ አራት ሺህ ሶስት መቶ ሃምሳ ስድስት» ብሎ ሲናገር በማይረሳ መልኩ ለማስታወስ የሚያስችል ሁኔታ የሚፈጥር አይደለም::

ልክ በባህር ዳር አሸዋ ላይ እንደተፃፈ አይነት ቁጥር ካጭር ጊዜ በኋላ ሊቆይ የማይችል፣ ዘላቂ እና አስተማማኝ የማይሆን ስለሆነ በቀላሉ ከአእምሮ በማይጠፋና በማይረሳ መልኩ ተቀርጾ ወይም ተፅፎ ሊቀር በሚችል መልኩ ሃሳቡን በንግግሩ አለመግለፁን ነው የሚያሳየው:: ከዚህ በኋላ አድማጮቹ ትኩረት ሰጥተው የማዳመጥ ፍላጐታቸው እየቀነሰ ነው የሔደው::

የህዝብ ብዛት ቁጥሩን በሚገለጽበት መንገድ እነሱ በሚያውቁትና በተጨባጭ ሊረዱት ከሚችሉበት አንድ ተዛማጅ ነገር ወይም ሁኔታ ጋር በማያያዝና በማዛመድ ቢገልፀው ጥሩ አይሆንም ነበር? ለምሣሌ ሰይንት ጆሴፍ ከተማ አብዛኞቹ የስብሰባው ታዳሚዎች ንግግሩን ከማዳመጥ አቋርጠው ከወጡባት ከትንሸዋ የሚዩዙሪ ከተማ ብዙ የማትርቅ በአላስካ ግዛት የምትገኝ ከተማ ነች:: በእለቱ አድማጮቹ አብዛኞቹ ከዚህችኛዋ ትንሸዋ የሚዩዙሪ ከተማ የመጡ ነበሩ:: በወቅቱም አላስካ የነበራት የሕዝብ ብዛት ከሰይንት ጆሴፍ ከተማ በአሥር ሺህ ሕዝብ ያነሰ ነበር:: ስለሆነም ለምን ስለአላስካ ያደረኛን ንግግር በቅርብ ካለችውና አብዛኞቹ ታዳሚዎች ከመጡባት ትንሸዋ የሚዩዙሪ ከተማ አጠገብ ካለችው የአላስካ ከተማ ሴየንት ጆሴፍ ጋር በማነፃፃር ንግግሩን ያላደረገው? ይኽን ቢያደርግ የተሻለ ነበር? ንግግሩን ያቀረበው ነበር « የአላስካ ግዛት ስፋት የሚዮዙሪን ስምንት እጥፍ ነው:: የአላስካ ከተማ በሆነችው ሴንት ጆሴፍ እንኳን የሚኖረው ሕዝብ በሚዮዙሪ ግዛት ሚኖረውን ሕዝብ አሥራ

ስት እጥፍ ነው» በማለት ቢሆን ኖሮ ንግግሩን በጣም ግልፅና በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት አይነት ይሆን ነበር፡፡

ከዚህ በታች ባሉት ምሳሌዎች ውስጥ የተቀመጡት ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ማለትም ከ (ሀ) እና (ለ) የትኛው ዓረፍተ ነገር ነው ግልፅና በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት?

(ሀ) ለምድራችን እጅግ በጣም ቅርብ የሆነችው ኮከብ ሰላሳ አምስት ትሪሊዮን ማይልስ ብቻ ነው የምትርቀው

(ለ) በአንድ ደቂቃ አንድ ማይል የሚጓዝ አንድ ባቡር ለምድራችን በጣም ቅርብ ከሆነችው ኮከብ ጋር ለመድረስ አርባ ስምንት ሚሊዮን አመታት ይፈጅበታል፡፡ በዚያች ለምድራችን ቅርብ ናት የምትባል ኮከብ ላይ ዘፈን የሚዘፈን ቢሆንና የምናዳምጠው የምንችልበት ሁኔታ ቢኖር ዘፈኑን የምንሰማው ከሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ዓመታት በኋላ ነው ወደዚች ለመሬት ቅርብ የሆነች ኮከብ የሽረሪት ድርን እንደገመድ መዘርጋት ብንችል የሚያስፈልገን አምስት መቶ ቶን ክብደት ያለው ሸረሪት ድር ነው፡፡

(ሀ) የአለማችን ትልቁ ቤተክርስቲያን የሆነው የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተክርስቲያን ከፍታው ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ጫማ ሲሆን ወርዱ ደግሞ ሶስት መቶ ስልሣ አራት ክንድ ነው፡፡

(ለ) የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተክርስቲያን ሁለት የዋሽንግተኑ ካፒቶል ህንፃዎች አንዱን በአንዱ ላይ ብንደራርባቸው የሚኖራቸውን መጠን ያህል ነው ያለው፡፡

ሰር ኦሊቨር ሎጅ እንዲህ አይነት የንግግር አገላለፅ መንገድ ማራኪና አስደሳች በሆነ ሁኔታ ስለአቶሞች አፈጣጠርና መጠን እጅግ ታዋቂ ሰዎች ለነበሩት አድማጮቹ ማብራሪያ በሰጠበት ንግግሩ ላይ ተጠቅሞበት ነበር፡፡ እኔም አንድ ጊዜ በዚሁ ጉዳይ ላይ በሜዲትራኒያን ባህር ውስጥ በጣም ብዙ ጠብታ ውሃዎች እንዳሉ ሁሉ በአንድ ጠብታ ውሃ ውስጥም በጣም ብዙ የሆኑ አተሞች እንዳሉ ሲናገር ሰምቼው ነበር፡፡ እናም ይህን ንግግሩን አዳምጠው የነበሩ ብዙ ሰዎች ለሣምንት ከጅብራልታር እስከ ስዊዝ ካናል ባህሩን ሲያስሱ አሳልፈዋል፡፡ ንግግሩን መሬት የወረደና የበለጠ ግልፅ የሆነ ለማድረግም መሬት ላይ በቅሎ የሚገኘውን እጅግ ብዙ ሳሮች የሚያህል ብዛት ያለው አቶም በአንድ ጠብታ ውሃ ውስጥ ይገኛል በማለት ነበር የተናገረው፡፡

ሪቻርድ ሃርዲንግ ዴቪስ በኒዮርክ ተገኝተው ለነበሩት አድማጮቹ ስለ ሴይንት ሶፊያ መስጊድ ንግግር ሲያደርግ «በአምስተኛው መንገድ ላይ ያለውን የቲያትር አዳራሽ የሚያህል ስፋት አለው በማለት ነበር የተናገረው» ስለትልቋ መርከብ ብረዲስ ባደረገው ንግግርም «ከኋላ በኩል ስትመለከታት እረጅም የደሴት ከተማ ትመስላለች» ነበር ያለው፡፡

ከአሁን በኋላ እነዚህን ከላይ በተሰያዩ ምሣሌዎች ያያችኋቸውን በቀላሉ ሊረዷችሁ የሚችሏቸውን እና ግልፅ የሆኑ ንግግሮችን ለማድረግ የሚያስችሉዋችሁን መመሪያዎችን ንግግር በምታደርጉበት ጊዜ ተጠቀሙባቸው፡፡ ስለታላቁ ፒራሚድ ንግግር የምታደርጉ ከሆነ በመጀመሪያ ለአድማጮቻችሁ 451

ጫማ ከፍታ እንዳለው ንገሯቸው:: ከዚያም አንድ ሁልጊዜም ከሚያዩት ወይም ከሚያውቁት ህንፃ አንፃር ምን ያህል ከፍታ እንዳለው ንገሯቸው:: ስፋቱም በአንድ ከተማ ውስጥ ያሉ ቤቶችን ምን ያህል ሊጠቀልል ወይም ሊሸፍን እንደሚችል ግለፁላቸው:: ስለአንድ ፋሳሽ መጠን ስትናገሩም ዝም ብላችሁ ብቻ ምን ያህል ሺህ ጋሎኖች ወይም ብዙ መቶ ሺ በርሜሎች ብቻ መሆኑን ነግራችኋቸው ስታበቁ የዚያ ፋሳሽ መጠን ምን ያህል ክፍሎችን ለመሙላት እንደሚችል ሳትጠቅሱ በፍፁም መቅረት የለባችሁም:: ሃያ ጫማ ከፍታ ያለው ብሎ ከመናገር ይልቅ የዚህን ቤት ግድግዳ አንድ ከግማሽ በሚያህል ከፍታ የሚበልጥ በማለት የማንናገረው ለምንድን ነው? ርቀትን በመንገድ ወይም በማይል ከመግለፅና ከመናገር ይልቅ ከዚህ እስከ ዩኒዬን እስቴሽን ያለውን እርቀት ያህላል ብንላቸውስ? ብለን የማንናገረው? ይኸኛው በማይል ከማስቀመጥ የተሻለና ግልፅ አይደለም? ... ወይም ከዚህ መንገድ እስከ እዚያኛው መንገድ ብሎ ከመናገር በተሻለ ንግግራችንን ግልፅና በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት አይነት አያደርግልንምን?

## የሙያ ቃላትን ስትጠቀም!

አንድ የሙያ ቴክኒክን የሚጠይቅ ሥራ ባለሙያ ከሆንክ. . . ጠበቃ ከሆንክ፣ ሐኪም፣ ኢንጅነር ወይም የተለየና ወይም ልዩ ሙያ የሚጠይቅ የሥራ ባለሙያ ከሆንክ ... ካንተ ሙያ ውጭ ለሆኑ ሰዎች ሃሳብህን ሊረዱት በሚችሉበት አኳኋን ቀጥተኛ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሃሳብህን ግለፅ ኃሳብህን እንዲረዱት ለማድረግ ንግግር ስታደርግ ሙያዊ ወይንም ቴክኒካዊ ቃላትን ላለመጠቀም ከአንድም ሁለት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ መቻል አለብህ::

አንዴ ሳይሆን ሁለት ጊዜ ጥንቃቄ አድርግ ብዬ ያልኩት እኔም እራሴ እንደ አንድ ባለሙያ በመቶዎች የሚቆጠሩ የሰዎች ንግግሮችን በዚህ ምክንያት የተነፃ ለማሳካት እንዳልቻሉና ከፍተኛ የሆነ ንደትንና ተቃውሞን እንዳስነሱ ስለሰማሁና ስለማወቅ ነው:: የዚህ አይነት ንግግር አቅራቢዎች ሙያቸውን የተመለከቱና እነሱ ብቻ የሚረዱአቸውን ሙያዊ ወይንም ቴክኒካዊ ቃላቶችን አብዛኞቹ አድማጮቻቸው ፍፁም የማያውቋቸውና የማይረዷቸው መሆናቸውን የተረዱና ግንዛቤ ያላቸው አልነበሩም:: ስለዚህ ምን ተፈጠረ? ከአንዱ አሳብ ወደ ሌላው እየተሻገሩ ለራሳቸው ብቻ ተስማሚ የሆኑና እነሱ ብቻ ከሙያም ከልምድም ከእውቀትም አንፃር የሚያውቋቸውን ቃላቶች ቀላቅሎ በመጠቀም ሃሳባቸውን መናገር ነበር የቀጠሉት:: ግን ያደረጉት ንግግር ልክ የሚሲሲፒ ወንዝ ከሰኔ የዝናባማ ወራት በኋላ የአዮዋና የካንሳስን ታርሰው ለዘር የተዘጋጁ የበቆሎ የእርሻ ሜዳዎች በውሀ እንደሚያርሳቸው ሁሉ በሙያዊ ወይም በቴክኒካዊ ቃላት ጋጋታ የሚደረግ ንግግር እንደ ሚሲሲፒ ወንዝ ኮለል ብሎ ግልፅ በሆነ ሁኔታ በመፍሰስ አድማጮቹን የሚያርስና የሚያረካ አይሆንም:: ታዲያ እንዲህ ያለ ንግግር አድራጊ ምን ማድረግ አለበት? ከዚህ በታች የተቀመጠውን የቀድሞውን የኢንዲያና ሴኔተር በቬሪጅን ዕሁፍ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በጥሞና ማንበብና ሴኔተሩ ይህንን አይነት ስህተት ላለመድገም ያስችላሉ ብለው በተባሉ ብዕራቸው ያሰፈሩትን ምክር ልብ ማለት አለበት::

> ንግግር በምናደርግበት ጊዜ ካድማጮቻችን መሀል ስለምናወራው ጉዳይ ምንም አይነት እውቀት የሌለውን አንድ አድማጫችንን በመውሰድ በንግግራችን

እንዲሳብና ለማዳመጥ ፍላጎት እንዲያድርበት ማድረግ መልመድ በጣም ጥሩ የሆነ ልምድ ነው የሚሆነው:: ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ እውነታውን ግልጽ በሆነ ዐረፍተ ነገር እና ምክኒያታዊነት መናገር ስንችል ነው:: ለዚህም የተሸለው አካሄድና መንገድ የንግግርህን ማዕከል ከቤተሰቦቿ ጋር የመጣች ወይም የመጣ ትንሽ አድማጭ ልጅን ማድረግና ንግግርህን ሊረዱበት በሚችሉበት አኳኋን ማሰብና ማዘጋጀት ነው:: በውስጥህ ለራስህ የምትናገረውን. ከወደድከው ከፍ ባለ ድምፅ ጮክ ብለህ ለአድማጮችህ ተናገረው:: ይህ ከሆነ ንግግርህን በቀጥተኛና ግራ በማያጋባና ግልፅ በሆነ አነጋገር የምታቀርበው ከሆነና አድማጭህ የሆነው ትንሽ ልጅ እንኳን የምትዘረዝራቸውን ሀሳቦችና የምታነሳቸውን ጥያቄዎች በደንብ ተረድቶና አውቆት ሲያበቃ ስብሰባውና ንግግርህ ካበቃ በኋላ እንኳ ምን እንደተናገርክ በመድገም ሊነግርህ ይችላል::

በአንድ ወቅት አንድ የህክምና ባለሙያ በንግግሩ መሃል ላይ «ከታችኛው የሳንባችን አቃፊ ከሆድ እቃችን የላይኛው መሸፈኛ አካባቢ ባለው የውስጥ የሰውነታችን ክፍል ደጋግሞ አየርን እያስወጡና እያስገቡ መተንፈስ በጣም ለሚያሰቃየው የአንጀት ግድግዳ መበከልና መቁሰል በሽታ በአይነቱ ልዩ እና ፍቱን የሆነ መድሀኒት ነው» በማለት ተናግሮ እንደነበር አስታውሳለሁ::

ይሁንና የህክምና ባለሙያው ይህን ንግግሩን በአንዲት ዐረፍተ ነገር አስቀምጦ ወደ ሌላኛው ሃሳቡ በፍጥነት ከመሄዱ በፊት ግን አንድ አድማጭ በድንገት ያስቆመውና ከአድማጮቹ መሀል ስለዲአፍራማትሪክ አተነፋፈስ (በሳንባ አቃፊ አማካኝነት አየርን በማስገባት በማስወጣት መተንፈስ ማለት ነው) ምን ማለት እንደሆነ፣ ይህስ አይነትና አተነፋፈስ በሌሎቹ የመተንፈሻ አካሎቻችን ከመተንፈስ በምን እንደሚለይ፣ በተለይም ለምን ከአንጀት ህመምና ስቃይ ለመዳን እንደሚረዳ? እንዲሁም የውስጥ አካላችን ግድግዳ ጉዳት ምን ማለት እንደሆነ፣ ከአድማጮቹ መሀል የተረዱና የገባቸው ካሉ እጃቸውን ወደ ላይ በማንሳት እንዲገልፁ ጠየቀ:: የዚህ ጥያቄ መልስ ውጤት ግን ዶክተሩን በጣም እንዲደነቅ ነበር ያደረገው:: ስለዚህም ወደኋላ ተመልሶ ከዚህ በታች በተቀመጠው መልኩ ሰፋ ባለ ማብራሪያና ትንተና ግልፅ አድርጐ አስቀምጧል::

ዲያፍራም ማለት ስስ የሆነና የደረታችንን የላይኛውን ክፍል ከሆዳችን የታችኛው ክፍል ከውስጥ አካላት የሚለይ ስጋ ነው:: ይህ ስስ ስጋ የሳንባችን የላይኛው አቃፊ ሲሆን ለሆድ እቃችን ደግሞ የላይኛው ሽፋን የሚሆን ነው:: ይህ ክፍል በእንቅስቃሴ ላይ በማይሆንበት ጊዜና ከደረታችን አየር ወደ ውጭ በማስወጣት በምንተነፍስበት ወቅት ልክ አንድ ጉድጓዳ ሳህን ገልብጠን ብናስቀምጠው እንደሚኖረው ቅርፅ ወደላይ ከፍ ብሎ የሚነሳ ይሆናል:: ይህንን ክፍል በመጠቀም በደረታችን ስንተነፍስና አየር ወደ ውስጥ ስናስገባ በእያንዳንዱ የአተነፋፈስ ዙሪያ ወደ ውስጥ በማስገባት የምንተነፍሰው አየር በግማሽ ክብ ቅርፅ ወደ ላይ ተነስቶና ከፍ ብሎ የሚገኘውን የሳንባ የታችኛው አቃፊ ስስ ጡንቻን ወደታች እስከ እምብርታችን የውስጠኛው ክፍል ደጋግሞ ይገፋዋል:: በዚህ ጊዜ የታችኛው የሳንባችን አቃፊ ጡንቻ ደጋግሞ ከፍተኛ በሆነ ግፊት በሆድ እቃችን የላይኛው አካባቢ የሚገኙ አካሎቻችንን በማሸት መነቃቃት እንዲፈጠር ያደርጋል . . . ጨጓራ፣ጉበት፣ ሐሞት፣ ጣፊያ፣ እና በጨጓራችን የላይኛው ክፍል ያለውን የነርብ ሲስተም በሙሉ በማሸት መነቃቃትን

እንዲፈጥሩ ያደርጋቸዋል። እንደገና አየር ወደ ውጭ ከደረታችሁ ስታስወጡ ጨጓራችሁና እንጀታችሁ ከሳንባ አቃፊ ጡንቻ ተቃራኒ በሆነ መልኩ ወደ ላይ ከፍ ብለው ይነሁና ተጨማሪ በሆነ ሁኔታ ይፍታታሉ። እንደዚህ አይነቱ መተሻሸት በሰውነታችን የማይፈለጉ ነገሮችን የማስወገድ ሂደትን በጣም ቀላል በማድረግ ከፍተኛ የሆነ እርዳታ ያደርጋል።

አብዛኞዎቹ የጤና መጓደል ሁኔታዎች ምንጫቸው አንጀታችን ነው። የምግብ አለመፈጨት፣ሰገራ ያለመውጣት፣ የሆድ ቁርጠት አብዛኞቹ ችግሮች በትክክልና በተገቢው ሁኔታ በደረታችን በታችኛው የሳንባችን አቃፊ ጡንቻ ደጋግመን ጥልቅ በሆነ ሁኔታ በመተንፈስ ጨጓራችንንና አንጀታችንን እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ልምምድ የምናሰራ ከሆነ የሚወገዱ ወይም ፈጽሞ የሚድኑ ይሆናሉ።

## የሊንከን ንግግሮች ግልፅነት ሚስጥር

ሊንከን አንድ ሰው በንግግሮቹ ውስጥ የሚሰነዝራቸውን ሃሳቦች አስተያየቶች፣ ቃሎች ግልፅ አድርጎ ከመጀመሪያው ማቅረብ መቻሉ ሁሉም ሰው የሚናገረው ምን እንደሆነ እየገባውና እየተረዳው እንዲመጣ ያስችለዋል የሚል ከፍተኛ የሆነ እምነት የነበረው ሰው ነው።

ለአሜሪካን ኮንግረስ ካቀረበው የመጀመሪያው ንግግሩ ውስጥ «ሳዩ ማር የሆነ» የሚለውን ቃል ተጠቅም ነበር። እናም የህዝብ ንግግሮች መዝጋቢና የሊንከን የቅርብ ጓደኛ የሆነው ሚር ደፍሪስ በዚህ ይህን ንግግሩ ውስጥ የተጠቀመበትን ቃል እንዳለ በመውሰድ መመዝገብና በኤሊኖይስ በሚገኘው የምክር ቤቱ ንግግሮችና ቃለ-ጉባዔዎች ማስቀመጫ መዝገብ ቤት በመንግሥት ሰነድነት ለታሪክ ማስቀመጡ ጥሩ አይመስለኝም በማለት ያማከረዋል። «ደህና ደፍሪስ» ብሎ በመጀመር ነበር ሊንከን መልሱን የሰጠው «ስጋትህ ሰዎች ሳዩን ማር የተቀባ» የሚለውን ቃል ትርጉሙን የማይረዱበት ጊዜ ይመጣል ብለህ ከሆነ ለመቀየር ዝግጁ ነኝ። ያለበለዚያ ግን እንዳለ ይቀመጥልኛል ብዬ ነው የማስበው በማለት ነበር የመለሰለት።

በልጅነቴ ወቅት ማንም ሰው እኔ ፍፁም ልረዳውና ሊገባኝ በማይችል መንገድ ሲያናግረኝ ምን ያህል ግራ ያጋባኝ እና ያስጨንቀኝ እንደነበረ አሁን ድረስ የማልረሳው ነገር ነው። በዚያ ወቅት ከዚህ አይነት ሁኔታ ሌላ በጣም የሚያበሳጨኝ ምንም አይነት ነገር አልነበረም። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ውስጤን የሚረብሸኝ ነገር እሱ ነው። ለምሣሌ ከማስታውሳቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ አንድ ማታ ሳይ መኝታ ቤቴ ውስጥ ተኝቼ ሳለሁ ጎረቤቶቻችን ወደ እኛ ቤት መጥተው ከአባቴ ጋር ሲያወሩ እሰማቸው የነበሩ። ንግግሮችንና ቃላቶች ምንነትን ለመረዳትና ለማወቅ በመኝታ ቤቴ ውስጥ እጅግ ለብዙ ሰዓታት ወዲያና ወዲህ እየተንቆራጠጥኩኝ በማሰብ አዕምሮዬንና መንፈሴን አስጨንቅ ነበር። በዚያን ምሽት እነሱ ሲያወሩ የምሰማቸው ነገሮች ፍፁም የማልረዳቸው ነገሮች ነበሩ። ንግግራቸውን ከሰማሁ በኋላም ሌሊቱን እንቅልፍ በዓይኔ ሣይዞር በተደጋጋሚ ስለምን እንዳወሩ ምንስ ማለታቸው እንደሆነ ለመረዳትና ለማወቅ

የተለያዩ ነገሮችን በማዛመድ የተናገሯቸውን ነገሮች በትክክል ተረድቼአቸዋለሁ ብዬ እስከማምን ድረስ አሰላስል ነበር::

ሆኖም ግን ያወሩት ስለዚህ ጉዳይ ነው በማለት ያመንኩበት ሃሳብ ትንሽ ሳይቆይ ይሽረሽርና እንደገና የተለያዩ ነገሮችን ማሰብ እቀጥል ነበር:: በዚህ ሁኔታም ለአንድ ትንሽ ልጅ ሊገባው በሚችል ደረጃና መጠን ንግግራቸውን ማጠቃለል እስክችል ድረስ ማሰብና መጨነቄን አላቆምኩም ነበር:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በውስጤ የተፈጠረውን ይህን ልምድ እስከ አሁን ድረስ ግልፅ ያልሆነልኝ እና ያልተረዳሁት ንግግር' ወይም መልዕክት በሚገጥመኝ ወቅት ውስጤን የሚያስጨንቀኝና በተደጋጋሚ እንዳሰላስል የሚያደርገኝ ነገር ነው::

አንድ ወቅት ለኒው ሳሌም ትምህርት ቤት መምህር ለሆነው ግራሀም ለማወቅ ወይም ለመረዳት ሲናረኝ የሚገባው ስሜት ከላይ በጠቀስነው ደረጃ ሲሆን እንደሚገባው ሲገልፅ «እኔ አብርሃም ሊንከን ለብዙ ሰዓታት ሃሳብን እጅግ በጣም ምርጥ በሆነ አነጋገር ለመግለፅ የሚቻልባቸውን ሶስቱ መንገዶች ደጋግሞ ያጠና እንደነበር አውቃለሁ::»

ብዙ ጊዜም ሰዎች ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ ስለሚናገሩት ሃሳብ ሰፊ የሆነ ግንዛቤ እና ብስለት የሌላቸው ከሚያደርጓቸው የተለመዱ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ በንግግራቸው ሊገልፁት ወይም ሊያስተላልፉት የሚፈልጉት ነገር ለነሱ ለራሳቸው ግልፅ ያልሆነና ጠንቅቀው የማያውቁት መሆኑ ነው:: የተምታቱ ዓርፍተ ነገሮች፣ ግራ የሚያጋቡና ግልፅነት የሚጎላቸው ሃሳቦች የሚያስከትሉት ውጤት ነው:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ ንግግር የሚያደርጉ ሰዎች ልክ በድቅድቅ ጉም ውስጥ አንድ ካሜራ የሚያነሳው ምስል ያህል እንኳን የጠራ ሀሳብ በድቅድቁ ጉም የተሸፈነው ወይም የተዋጠው አዕምሮአቸው ማፍለቅ አይችልም::

እንደዚህ ያሉ ሰዎች ሁሌም አብርሃም ሊንከን እንደተሰማው አሻሚነትና አምታችነት ያላቸው ሀሳቦችና ንግግሮች ሊረብሽዋቸውና ሊያስጨንቋቸው ይገባል:: የሊንከንን መንገድ እንደመፍትሔ ሊጠቀሙበት ቢችሉ መልካም መሆኑን እመክራችኋለሁ::

## በዓይን በማሳየት መማረክና ማሳመን

በምዕራፍ አምስት ውስጥ እንዳየነው ዐይናችንን ከአንጎላችን የሚያገናኙት ነርቮች አንጎላችንን ከጆሮአችን ከሚያገናኙት ነርቮች እጅግ በጣም ብዙ በሆነ እጥፍ የሚበልጡ ናቸው:: ሳይንስ እንደሚነግረንም እኛ ጆሮዎቻችን ከሚያስተላልፉልን መልዕክት ሃያ አምስት እጥፍ በበለጠ ሁኔታ ዐይኖቻችን ለሚያስተላልፉልን መልዕክት ትልቅ የሆነ ትኩረት እንናጣለን::

«አንዴ ማሳየት» ይላል አንድ የቆየ ቻይናውያን አባባል፣

«አንድን ነገር መቶ ጊዜ እየደጋገሙ ከመንገር የተሻለ ነው»

ስለዚህ በምታደርገው ንግግር ግልፅ መሆን ከፈለግክ፣ ዋነኛ ነጥብህን ሳለው፣ የምትናገረውን ሃሳብ በእዝነ ህሊናህ ተመልከተው:: እጅግ ታዋቂ የሆነው የገንዘብ ስርጭትና ምዝገባ ብሔራዊ ድርጅት ፕሬዝዳንት የነበረውና አሁን

በህይወት የሌለው ጆን ኤች ፓተርሰን በደንብ ተዘጋጅቶ ይጠቀም የነበረው ይህንን ዘዴ ነበር፡፡ ለሲስተም መስሄት ፅፎት በነበረው አንድ ፅሁፍ ላይ ለስራ አጋሮቹና በንግድ ስራ ውስጥ ላሉ ሐይሎች ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ይጠቀምባቸው የነበሩትን መንገዶች በዝርዝር እንዲህ አስፍሯቸው ነበር፡፡

> እኔ በፍፁም አንድ ተናጋሪ ሰው በሚናገራቸው ነገሮች ብቻ አድማጮቹ ተረድተውኛል፣ ገብቷቸዋል ወይም ትኩረታቸውንና ስሜታቸውን ማግኘት ችያለሁ ብሎ መተማመንና እርግጠኛ መሆን የለበትም፡፡ ምክንያቱም ተጨማሪ ድራማዊ የሆኑ ነገሮች አስፈላጊ ናቸውና ነው፡፡ አንድ ንግግር አድራጊ ሰው በንግግሩ ውስጥ በተቻለ አቅም ጥሩውንም ሆነ መጥፎውንም ነገሮችን ለማሳየት እንዲቻለው ስዕላዊ የሆኑ መግለጫዎችን ለንግግሩ ማጣቀሻና ማሳያ መጠቀሙ በጣም ጠቃሚ ነው የሚሆነው፡፡ ስዕላዊ መግለጫዎችን መጠቀም ቁጥሮችን በቃላት እየጠቀሱ ከመናገር የበለጠ አሳማኝ ነው፡፡ ስዕሎችንና ፎቶዎችን መጠቀም ደግሞ ዲያግራሞችንና ስታስቲኮችን ከመጠቀም የበለጠ ንግግራችንን ተአማኒ ያደርጉታል፡፡ ሃሳባችንን በተዋረድ ቅደም ተከተሉን በጠበቀና ተያያዥነት ባለው መልኩ ከፋፍለን በአዝነ ህሊናችን ውስጥ በመሳል በቃላቶች አገናኝተን በመናገር መግለፅ መቻል አለብን፡፡ ቀደም ብዬ ከተረዳኋቸውና ካወቅኳቸው ነገሮች ደግሞ መካከል አንዱ ንግግር የምናደርገው ለወንዶች ከሆነ ስዕላዊ መግለጫዎችን መጠቀም ልንገልፅላችሁ ከምችለው በላይ ይጠቅማል፡፡

በዚህ ዓይነት ንግግርን በስዕላዊ ማሳያ በማስደገፍ ረገድ የግርቱስኩ ስዕሎች በሚገርም ሁኔታ ውጤታማ የሆኑ ነበሩ፡፡ በካርቱን ስዕሎች ወይም በተሳሉ ቻርቶች አማካይነት የተደገፉ ንግግሮችን ማድረግ የበለጠ መረዳትንና ግልፅነትን ለአድማጮቻችን መፍጠር እንችላለን፡፡ አንድ ክብ ከሳልን በኋላ ውስጡ የዶላር ምልክትን ማስቀመጥ በዛ ያለ ገንዘብን ያመለክትልናል፡፡ ጨረቃን የሰው ፊት ገፅታ በመስጠት መሳል በጣም በርካታ የሆኑ ጥሩ ነገሮችን ለመግለፅ ይረዳል፡፡ አንድ ክብ ሳሉ ቀጥሎም የተወሰኑ ሰረዞችን ወይም መስመሮችን ዓይን፣ አፍንጫ፣አፍ እንዲሁም ጆሮ እንዲሆኑ አስምሩ፡፡ እነዚህ ሰረዞች ባሉበት ቦታ ላይ ከጎን ያለውን አጠፍ ወይም ጎበጥ ብናደርጋቸው በደንብ ገላጭ ይሆናሉ፡፡ በፊት ጊዜ ይሳል የነበረው የሰው ፊትና አፍ በቁመት የተሳለ ሰረዝ ስለነበረ የአፋችን ቅርፅ ከላይ ወደታች የነበረ ነበር፡፡ በአሁን ጊዜ ካርቱኒስቶች የሚስሏቸው ደግሞ በአግድም ሰረዝ ከግራ ወደ ቀኝ ቅርፅ አለው፡፡ ብዙ ጊዜ በስዕላዊ መግለጫ መልዕክትን የሚያስተላልፉ ሰዎች ስራዎቻቸው በቤት ውስጥ የሚሰሩ ናቸው፡፡ አብዛኛውን ጊዜም እንደሚታየው በጣም የተዋጣላቸውና በስዕል መልዕክትን የሚያስተላልፉ ካርቱኒስቶች የሰሯቸው ስራዎች ወይም መልዕክት አስተላላፊ ስዕሎች በጣም ያማሩ ሆነው አይደለም፡፡ ነገር ግን ዋናው ቁም ነገር በስዕሎቻቸው ያንፀባረቁት ሃሳብና ያስተላለፉት መልዕክት ነው፡፡

ብዙ ገንዘብን ለማሳየትና ለማመልከት አሊያም ትንሽ ገንዘብ መኖርን ለማሣየትና ለመመልከት የምንጠቀምባቸው ስዕላዊ መግለጫዎች ሁለቱም አንድ ሃሳብን ጎን ለጎን ተቃራኒ በሆነ መልኩ ለማሳየት የምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡ አንደኛው ትልቁ ክብ የዶላር ምልክት ያለበት በዛ ያለ ገንዘብ መኖርን ያሳያል

ሁለተኛው ትንሽ ከብ ምልክት ያለበት ጥቂት ገንዘብ መኖርን ያመለክታል። እነዚህን ንግግር እያደረግህ ባለህበት ጊዜ በፍጥነት በቻርት ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ ብትስል በአድማጮችህ ላይ የምትፈጥርባቸው ምንም ዓይነት ብዥታ አይኖርም። ይልቁንም ንግግርህን እየተከታተሉ ከዚያ በኋላ የምታቀርበውን ሃሳብ ወይም ነጥብ ለማድመጥ ዝግጁ እንዲሆኑ ነው የሚያደርጋቸው። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የምናስቀምጣቸው ለየት ያሉ ስዕሎችን አድማጮችህ እንዲስቁና እንዲዝናኑ ያደርጓቸዋል።

እኔ ሁሌም አንድ የስዕል ባለሙያን በድርጅታችን የተለያዩ ሱቆች አብሮኝ በመሄድ እየዞርን በየሱቆቹ የምናያቸውንና የምንታዘባቸውን ትክክልና አግባብ ያልሆኑ ነገሮች ወደ ካርቶን ስዕሎች በመቀየር እንዲስላቸው አስደርግ ነበር። ከዚያም ሁሉንም በየሱቁ የሚሰሩ ሰዎች አንድ ላይ በመጥራት ስዕሎቹን እንዲመለከቷቸውና ምን እየሰሩ እንደነበሩ እንዲያውቁትና እንዲገነዘቡት አደርግ ነበር። በዚህ ሁኔታም እየቀጠልን እንዳለን ብዙዎቹ ለካርቶን ስዕሎቹ ትኩረት በመስጠት በደንብ እንደማይመለከቱ በተረዳሁ ጊዜ ወዲያውኑ አንድ ፕሮጀክተር በመግዛት በተሻለና ውጤታማ በሆነ መንገድ ስዕሎቹን በስክሪን ላይ እንደፊልም ማሳየት ጀመርን፤ ውጤቱም እጅግ በጣም ቆንጆ ነበር። ቀጥለንም ከዚህም በበለጠ ሁኔታ እያዘጋጀን ማሳየት ጀመርን። በዚህም ምክንያት ስራው አድጎና ሰፊ ሆኖ ድርጅታችን ሰፋ ባለ ሁኔታ ስራውን ለመስራት እንዲችል በማሰብ አንድ ራሱን የቻለ ጥናታዊ ፊልሞችን የሚያዘጋጅ ክፍል ተቋቁሞ ከ60 ሺህ በላይ የሆኑ ባለቀለም ተንቀሳቃሽ ፊልሞችን አዘጋጅቷል ይህም ግልፅ የሆኑና በቀላሉ መልዕክትን ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ጥናታዊ የፊልም መረጃዎችን በማግኘት የድርጅታችንን መልዕክቶች በተለያዩ ግንኙነቶችና ስብሰባዎች ላይ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ለማስተላለፍ ረድቶናል።

እዚህ ላይ ሁሉንም ሃሳቦችና መልዕክቶች ወይም ተግባሮች በስዕላዊ ተንቀሳቃሽ ፊልም፤ወይም በቻርት መልክ አዘጋጅተን ለምናደርጋቸው ንግግሮች ስዕላዊ መግለጫን ፤ፊልምን፤ ወይንም ሰንጠረዥን መጠቀም የምንችልበት ሁኔታ ከኖረና በአግባቡ ልንጠቀምበት ከቻልን በንግግራችን የምናስተላልፈውን ሃሳብ ወይም መልዕክት በሁለት እጥፍ ግልፅ በማድረግ የአድማጮቻችንን ትኩረት በመሳብና፤ የማዳመጥ ፍላጎታቸውን ከፍ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክትልናል።

## የሮክፌለር የሳንቲም ምሳሌዎች

ሚስተር ሮክፌለር በሲስተም መፅሄት ላይ የኮሎራዶ የነዳጅና የብረት ካምፓኒ ያሣዩትን የእድገት ደረጃ ትርፍና ኪሳራን ጨምሮ ያለውን እውነት ለባለድርሻዎቹ በዓይናቸው በማሳየት ግልፅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ በተወሰኑ የገንዘብ ሳንቲሞች እንዴት እንደተጠቀመ በዝርዝር ፅፎት ነበር።

ሠራተኞችን ወደጎን በመግፋትና የኮሎራዶ የነዳጅና የብረት አምራች ኩባንያ እጅግ በጣም ብዙ የሆነ ትርፍን በማጋበስ እንስተኛ ክፍያ በመክፈል ድርጅቱ መሆኑን ተረዳሁ። ብዙዎቹም ሰዎች በዚህ ላይ ነው የሚል እምነት እየተፈጠረ ከእውነታው ጋር የማይጣጣም ዓይነት ሁኔታ እየፈጠሩት ያለው አስተሳሰብ ቢኖር ይኸንኑ ሃሳብ በድጋሚ መሆኑን ይነግሯቸው ነበር። እኔም ያደረግኩት የኮሎራዶ የነዳጅና የብረታ ብረት በማጠናከር ማሳወቅ ነበር። ሆኖም እኔ ከጀመረበት ካለፉት አስራ አራት ማምረቻ ድርጅት በኮሎራዶ ግዛት መንቀሳቀስ በድርጅቱ ላይ የባለቤትነት ድርሻ ወይም ዓመታት ጀምሮ እስከዛች ቀን ድረስ እንኳን የትርፍ ድርሻ መስጠት አክሲዮን ላላቸው ባለሃብቶች አንድ ሳንቲም በአይናቸው እንዲያዩ ነበር ወይም መክፈል እንዳልቻለ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ያደረኩት።

በአንድ ስብሰባ ላይም የድርጅቱን የገንዘብ አቅምና ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ በሆነ ማሳያ በዓይናቸው አደረግኩ አደረግሁኝ። ይህን ለማድረግም በቅድሚያ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸውን የገንዘብ ሳንቲሞች ከፊት ለፊታቸው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጥኩ፤ ቀጥዬም የተወሰነውን ሳንቲም በመክፈል የድርጅቱ ሰራተኞች ቀዳሚ ጥያቄ ለሆነው ለደሞዝ የሚከፈል ድርሻ እንዲሆነ ገለፅኩላቸው። በተከታታይም ከመጀመሪያው በርከት ያሉ ሣንቲሞችን ከፈለኩ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ሐላፊዎች የሚከፈል ደመወዝ መሆኑን ገለፅኩ። በመጨረሻም የቀሩትን የተወሰ ሣንቲሞች የድርጅቱ ዳይሬክተሮች ደሞዝ እንደሆነ ገለፅኩ። ከዚህ ሁሉ በኂላ በድርጅቱ ላይ የባለቤትነት ድርሻ ወይም አክሲዮን ላላቸው ባለሃብቶች ገንዘባቸውን በድርጅቱ ላይ ኢንቨስት በማድረጋቸው ሊያገኙ ለሚገባው ዓመታዊ ትርፍ የሚከፈል ምንም የቀረ ሣንቲም ጠረጴዛው ላይ አልነበረም። በመሆኑም በመጨረሻ ላይ ሠዎች አራታችንም ዋነኛ ባለድርሻዎች በሆኑበት በዚህ ኮርፖሬሽን ትንሽም ይሁን ትልቅ ከኮርፖሬሽኑ አጋሮች ውስጥ ሦስቱ ብቻ ተጠቃሚ ይሁኑ። አራተኛው ባለድርሻ ግን ከድርጅቱ ምንም ዓይነት ጥቅምና ክፍያ አያግኝ ብሎ ማለት ፍትሃዊ ነው ትላላችሁ?" የሚል ጥያቄ ነበር የሰነዘርኩላቸው።

ዐይንህ የሚያሳይህ ነገሮች ግልፅና አሻሚነት የሌላቸው ነገሮች መሆናቸውን እርግጠኛ ሁን። ለምሣሌ ‹ውሻ› የሚለውን ቃል ስንሰማ አነሰም በዛ ግልፅ የሆነ የእንስሳ ስዕል በሀሊናችን ይታየናል። ምናልባት የተለያዩ የውሻ ዝርያዎችን ለምሣሌ እንደ ስኮች፣ ቤለር፣ ሴንበርናርድ፣ ወይም ዓመሬንያን የውሻ ዓይነቶችን ሊሆንና ሊለያይ ይችል ይሆናል። እስቲ እኔ ብዙም የማይታወቀውን ቡል ዶግ የሚባለውን የውሻ ዝርያ ብጠራልህ ምን ያህል ምስሉ በአእምሮህ ውስጥ ሊመጣልህ እንደሚችል ተመልከት። አስቸጋሪ ነው የሚሆንብህ። ምናልባትም የተለመዱትና የሚታወቁት ማንኛውም ዓይነት የውሻ ምስል ሊመሳለስብህ ይችል ይሆናል። ነገር ግን ወፍራምና የተዘበዘበ ፊትና ሰምቦጭ ያለው ውሻ ምስል አይመጣልህም። በአይንህ ቡልዶግ የሚባለውን ውሻ እስካላየኸው ድረስ በቃላት ብቻ በመንገር ግልፅ በሆነ መንገድ ላሣውቅህ አልችልም።

## የንግግርህን ዋነኛ ነጥብ በተለያዩ ቃላቶች ደጋግመህ ግለፅ

ናፖሊዮን አንድን ሃሣብ በመደጋገም መናገር ለአንድ ንግግር፣ መግለጫ፣ ስብከት፣ ወይም ጠቃሚ ውጤታማ መሆን ዋነኛውና ብቸኛው መመሪያ ነው በማለት ይናገር ነበር:: ይህን ሲል አንድ ሃሣብ ወይም ንግግር ለሱ ግልፅ ሆነለት ማለት ለሌሎች ሰዎች ወይም አድማጮች ግልፅ ስመሆኑ ማረጋገጫ እንደማይሆን ያውቅ ነበር:: በተጨማሪም ናፖሊዮን ሰዎች አንድ አዲስ የሆነ ሃሣብን ወይም ለውጥን ለመረዳት ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ የአድማጮችን መንፈስና አእምሮ በመሰብሰብ በሀሳቡ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ማድረግ መቻል አስፈላጊ መሆኑን ያውቅ ነበር::

ባጭሩ የንግግሩን ዋነኛ ነጥብ በመደጋገም መነገር እንዳለበት ያውቅ ነበር:: ይህ ማለት ግን በአንድ አይነት ቃላትና መንገድ ደጋግሞ መናገር ማለት አይደለም:: ይህ ከሆነ ግን ሰዎች በምንም ዓይነት የሚያዳምጡበት ሁኔታ አይኖርም:: ትክክልም ናቸው፣ ግን የመልዕክቱ ወይም የሃሣቡ ድግግሞሽ በአዳዲስና በተለያዩ ቃላቶች የሚደረግ ከሆነ . . . በተለያየ ሁኔታ ከሆነ ... አድማጭህ በጭራሽ ደግመህ መናገርህን ልብ አይለውም:: እስቲ አንድ ጥሩ የሆነ ምሣሌን እንይ:: አሁን በህይወት የሌለው ሚር ብርያን ይህን ንግግር አድርጎ ነበር::

> ስለ አንድ የትምህርት ዓይነት አንተ ዕውቀቱ ሣይኖርህ ሌሎች ሰዎችን እውቀቱ እንዲኖራቸው ልታደርግ አትችልም። የዚያ ትምህርት ከፍተኛ የሆነ እውቀት በኖረህ ቁጥር በዚያው መጠን በከፍተኛ ሁኔታ የትምህርቱንና ዕውቀቱን ሌሎች እንዲቀስሙት ማድረግ ይቻልሃል።

በዚህ ንግግር ውስጥ የተጠቀሰው የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር በመጀመሪያው የተጠቀሰው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ዋነኛ ነጥብ ተደግሞ የቀረበበት ነው። ነገር ግን እነዚህን ሁለት ዓረፍተ ነገሮች በምንናገራቸው ጊዜ አእምሮ እነዚህ ዓረፍተ ነገሮች አንድ ዓይነትና ተደጋጋሚ መሆናቸውን ለመለየትና ለማወቅ ጊዜ አይኖረውም፣ ሃሣቡ እንደተብራራና ግልፅ እንደሆነ ብቻ ነው የሚሰማው:: የተለያዩ ትምህርቶችን በማስተምርበት ጊዜ በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በዚህ ዓይነት ሃሳብን ደጋግሞ የመናገር መመሪያን ተናጋሪዎቹ ተጠቅመው ቢሆን በጣም ግልፅና አስደሳች መሆን የሚችሉ ከስድስት እስከ አስራ ሁለት የሚሆኑ ንግግሮችን ሣልሰማ ከክፍል ወጥቼ አላውቅም ነበር።

በአጠቃላይ ማሳያዎችንና ተጨባጭና ወደ መሬት የወረዱ ምሳሌዎችን መጠቀም ነጥቦችህን ግልፅ ለማድረግ ቀላልና አስተማማኝ ከሆኑት መንገዶች አንዱ የሆነው ነጥቦችህን ጠቅለል ባሉ ማሠሪያዎች ውስጥ በጠንካራ ምሳሌዎች በማስደገፍ ማቅረብ ነው:: በሁለቱ መሃል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? አንደኛው ቃሉ እራሱ እንደሚያሳየው አጠቃሳይ ነው ሌላኛው ተጨባጭ እና ተናጠል ነው:: እስቲ በሁለቱ መሃል ያለውን ልዩነት እና አጠቃቀማቸውን ቆንጆ በሆኑ

ምሳሌዎች እንያቸው። አስገራሚና አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ ክፍያ ተከፋይ የሆኑ ብዙ ወንድና ሴት ባለሙያዎች አሉ የሚሰጡን ዓረፍተ ነገር ብናይ።

ይህ ዓረፍተ ነገር በጣም ግልፅ የሆነ ነው። ተናጋሪው ምን ማለቱ እንደሆነ ወይም ምን ማለት እንደፈለገ ግልፅ በሆነና በማያሻማ አኳኋን ተረድታችሁታል? አልተረዳችሁትም አይደል! ተናጋሪው እራሱ እንኳን የዚህ ዓይነቱ ድምዳሜ ያለው ንግግር በሌሎች ሰዎች ወይም አድማጮች አእምሮ ውስጥ ስለሚፈጠረው ሁኔታ ምንነት እርግጠኛ ሊሆን አይችልም። በአሃርክ ተራራዎች ግዛት ውስጥ የሚኖር አንድ የህክምና ባለሙያ ዶክተር በአንድ ትንሽ ከተማ ውስጥ ለሚገኝ አንድ ቤተሰብ የግል ሐኪም በመሆን በወር እስከ አምስት ሺህ ዶላር ክፍያ ማግኘት እንደሚችል እንዲያስብ ያደርገዋል። አንድ ምርጥ የተፈጥሮ ማዕድን አውጪ ኢንጂነር ሌሎች የሙያ አጋሮቹ በዓመት መቶ ሺህ ዶላሮች ክፍያ እያገኙ እንደሆኑ እንዲያስብ ሊያደርገው ይችላል።

ዓረፍተ ነገሩ እንዳለ በጣም አሻሚና ብዥታን የሚፈጥር ነው። ስለዚህ መጠናከርና መስተካከል የሚያስፈልገው ዓረፍተ ነገር ነው። ተናጋሪው ስለምን ዓይነት ባለሙያዎች እየተናገረ እንደሆነ የሚያሳዩ የተወሰኑ ዝርዝር መግለጫዎች መካተት አለባቸው። በተጨማሪም በሚያስገርም ሆነ ብዙ ብሎ ሲናገር ምን ማለቱ እንደሆነ ሊያብራራቸው ይገባል። ለምሳሌ. . . ከአሜሪካ ፕሬዝዳንት በላይ የሆነ ገቢ ያላቸው፣ የኖቬል ተሸላሚዎች፣ የፊልም ስክሪፕት ፀሐፊዎች፣ ሰዓሊዎች ጠበቃዎች ተዋናዮች፣ ዘፋኞች አሉ።

አሁን ማንም ሰው የተናገረውን ሃሣብ ግልፅ በሆነ ሁኔታ መረዳትና ምን መናገር እንደፈለገ ማወቅ አይችልም? ይሁን እንጂ በተናጠል በግለሰብ ደረጃ ሊያሣይና ግልፅ ሊሆን በሚችል ሁኔታ አይደለም ያስቀመጠው። ጠቅለል ያሉ ማሣያዎችን ነው የተጠቀመው፤ወደ መሬት በወረደ መልኩ ሊያሣዩና ሊያስረዱ የሚችሉ ምንም ማሣያዎች የሉም። በደፈናው ዘፋኞች ብሎ ነው እንጂ ሮዛ ፖንስሊ፣ ክሪስቲን ፍላግስታድ፣ ወይም ሊሊ ፖንስ ብሎ አልተናገረም።

ስለዚህ አነሰም በዛም አሁንም ቢሆን ዓረፍተ ነገሩ በተወሰነ መጠን ግልፅነት የሌለው ነው። እኛም ብንሆን ይህን ዓረፍተ ነገር ግልፅ በሆነ መንገድ ለማስረዳት መሬት የወረዱ ምሣሌዎችን ማጣቀስ ይከብደናል። ተናጋሪውስ ይህን ሲያደርግልን አይገባም? ተናጋሪውስ ግልፅ የሆኑና የወረዱ ምሣሌዎችን ቢጠቀም ከዚህ በታች እንደተቀመጠው ንግግሩ የበለጠ ግልፅ አይሆንም ነበር?

> ከፍተኛ የሆነ እውቅና ያላቸው የግል ጠበቃዎች እንደነ ሣሙኤል አተርማየር እና ማክስ ስተወር በዓመት እስከ አንድ ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ገቢ ያገኛሉ። የጃክ ዲምፕሴይ አመታዊ ገቢም ከግማሽ ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደሆነም የሚታወቅ ነው። ምንም ዓይነት ትምህርት ያልተማረውና አድሜው በሃያዎቹ ውስጥ የሆነው ወጣቱ ጥቁር ጆ ሊዊስ ከግማሽ ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ አለው። የኧርቪንግ በርሊን ሙዚቃዎች በአመት ከግማሽ

ሚሊን ዶላር በላይ ገቢ እንደሚያስገኙለት የተዘገበ ጉዳይ ነው፡፡ ኪንግስ ሌይ ለ ሲድኒ በሚጫወትበት ክለብ የሚከፍለው ደሞዝ በሣምንት አስር ሺህ ዶላር ነው፡፡ ኤች ጂ ዌልስ በፃፈው በራሱ የህይወት ታሪክ መፅሐፍ ውስጥ ብዕሩ ሦስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዳስገኘለት አስፍሮታል፡፡ ዲያን ሪቬራ በስዕሉቹ ሽያጭ በአመት ከግማሽ ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ያገኛል፡፡ ካትሪን ኮርኔል በተደጋጋሚ በሣምንት የአምስት ሺህ ዶላር የፊልም ስራ ክፍያ ማግኘትን የሚያዘናጋ በቂ ያልሆነ ክፍያ በማለት ሳትቀበለው ቀርታለች፡፡

አሁንስ ማንም ሰው ተናጋሪው ለመግለፅና ለማስጨበጥ የፈለገውን ሃሳብ ፍንትው ባለ ግልፅና ትክክለኛ በሆነ ሁኔታ አይረዳውምን?

## እንደተራራ ፍየል እዚህም እዚያም

ፕሮፌሰር ዊሊያም ጀምስ ለመምህራኖች ባደረገው አንድ ንግግር ውስጥ ከፍተኛ አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባው ነገር እንደሆነ ያሰመረበት ማንም ሰው ትምህርት በሚያስተምርበት ጊዜ ሊያነሳ የሚገባው ነጥብ ከአንድ መብለጥ የሌለበት መሆኑን የተናገረ ሲሆን እሱ ራሱ ግን በዚያን ቀን ትምህርታዊ ገለፃው ብዙ ነጥቦችን ያነሳና ገለፃውንም ለማጠናቀቅ አንድ ሰዓት ወስዶ ቤት እንደነበር በቅርቡ ነው የሰማሁት፡፡ በሦስት ደቂቃዎች ውስጥ ብቻ ሃሣቡን እንዲገልፅ የተፈቀደለት አንድ ተናጋሪ ለአድማጮች በሚናገራቸው አስራ አንድ ነጥቦች ላይ ትኩረታቸውን እንዲያደርጉ በመጠየቅ ንግግሩን ጀምሮ እያንዳንዱን ነጥቦች በአስራ አንድ ነጥብ አምስት ሰከንዶች ውስጥ ንግግሩን አቅርቧል፡፡

ይህ ኀበዝ የሆነ ንግግር አድራጊ ሰው የማይቻሉና የማይሆኑ ነገሮች የተባሉትን ለማድረግ እንደማይሣነው ነበር ያሣየው፡፡ እዚህ ላይ እኔ የመጨረሻውን በትንሽ ጊዜ ውስጥ ሃሣብን በንግግር ለመግለፅ የተደረገ ጥረትን በመጥቀስ ለማሣየት ነው የሞከርኩት፡፡ ነገር ግን በዚህ ዓይነት አነስተኛ ጊዜ ከላይ እንዳየነው ተናግሬ ሃሣባችንን በንግግር እንደሱ በጣም በአነስተኛ ሰከንዶች ውስጥ ባይሆንም እንኳን በተወሰኑ ሰከንዶች ውስጥ ለመግለፅ መሞከር የምንናገረው ሃሣብ አርኪና ግልፅ ለማድረግ አያስችልም፡፡

ከላይ እንደጠቀስኩት ዓይነት ንግግር አድራጊ ሰው ማለት በፖሪስ ከተማ ውስጥ ያሉትን ምግብ ቤቶች በሙሉ በአንድ ቀን ውስጥ ለአንድ አገር ጎብኚ ለማሳየት እንደመሞከር ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው የአሜሪካን ብሔራዊ ሙዚየምን በሰላሳ ደቂቃ የእግር ጉዞ ላይ ላዩን ብቻ መጎብኘት እንደሚችለው ዓይነት ብቻ ከሆነ ነው፡፡ ሆኖም ግን የዚህ ዓይነቱ የጥድፊያ ጉብኝት በቂ በሆነ ሁኔታ መመልከትንም ሆነ እርካታና ደስታን አያስገኝም፡፡ ብዙ ንግግሮች ግልፅና ውሃ የሚቋጥሩ ሳይሆኑ በመቅረት ውድቅ የሚሆኑበት ምክንያት ብዙ ተናጋሪዎች በተመደበላቸው ሰዓት ውስጥ ሁሉንም ነጥቦቻቸውን ለመሰንዘርና ለመጨረስ በሚያደርጉት ሩጫ የተነሳ ነው፡፡

እጅግ ብዙ ንግግሮች አጭር መሆን ይገባቸዋል። በልክህ ልብስ ወይም በቁጥርህ መጠን ጫማ እንደምትገዛና እንደምትለብስ ማለት ነው። ለምሣሌ ንግግር የምታደርገው ለሰራተኛ ማህበሮች ቢሆን በሶስት ወይም በስድስት ደቂቃዎች ውስጥ የማህበሩ አባሎች ለምን በስብሰባው እንደተገኙ፣ ዓላማው ምን እንደሆነ፣ ማህበሩ ዓላማውንና ግቡን ለማሳካት ስለሚጠቀሙበት መንገድና ተሞክሮዎቻቸው፣ ስላጋጠሙ ችግሮችና ፈተናዎቻቸው፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ሰላም ስለሚረጋገጥበትና አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታዎችና መንገዶች ንግግር ማድረግ የለብህም። በፍፁም እንዲህ ያለን ንግግር በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ማድረግ የለብህም። ለማድረግ የምትሞክር ከሆነ ግን ስለምትናገረው ነገር ግልፅ የሆነ ግንዛቤ የሚኖረው አንድም ሰው አይኖርም። ሁሉም ነገሮች ድንግርግርና ብዥ ያሉ ይሆኑና የምትናገራቸው ነገሮች ከመፅሀፍ ማውጫ አርእስትነት የዘለለ ፋይዳ አይኖረውም።

# ምዕራፍ አስራ አንድ

## አድማጮችህ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማድረግ የምትችለው እንዴት ነው?

አሁን እየተመለከትከውና እያነበብከው ያለው የዚህ ገፅ ወረቀት አዲስ ያልሆነና የተለመደ ያው የምታውቀው ነው። አይደለም? ከዚህ በፊት በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ እንደዚህ ያሉ ወረቀቶችን ዐይንህ አይቷል። አሁን ይሄን ጥያቄ መጠየቅህ የሚያስገርምህና ምን ዓይነት ሞኝነት ነው ብለህ እንድትል የሚያደርግህ ነው። አይደል? ነገር ግን ስለዚህ ነገር የማታውቀው እውነታን ብነግርህ ያለምክንያት ጥያቄውን እንዳላነሳሁት ትረዳና በእርግጠኝነት ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት ያድርብህ ነበር። ታዲያ እስኪ ይህን እንመልከተው።

ይሄ ገፅ አንድ ጠጣር የሆነ ወረቀት ነገር ይመስልሃል! ነገር ግን እውነታው ከጠጣር ነገርነቱ ይልቅ በቀጫጭን ስስ ክሮች የተደራ የሸረሪት ድርን ነው የሚመስለው። የፊዚክስ ባለሙያዎች አቶሞች በውስጡ እንዳሉ ያውቃሉ፤ እናም አንድ አቶም ምን ያህል ትንሽ ነው? በምዕራፍ አስር ውስጥ በሜዲትራንያን ባሕር ውስጥ ያሉትን የውሃ ጠብታዎች ያህል ብዛት ያላቸው አቶሞች በአንድ ጠብታ ውሃ ውስጥ እንደሚገኙ አውቀናል። ልክ በዓለም ላይ ያለውን ሣር ብዛት የሚያህል አቶሞች በአንድ ጠብታ ውሃ ውስጥ አሉ እንዳልነው ማለት ነው። እናም የዚህን ወረቀት ቅርፅና ይዞታ የፈጠሩ አቶሞች የተሰሩትስ ከምንድን ነው? ከነሱ እጅግ በሚያንሱ ኤሌክትሮንስና ፕሮቶንስ በሚባሉ ጥቃቅን ንጥረ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ኤሌክትሮንስ የሚባሉት ጥቃቅን ነገሮች በአንድ አቶም የመሀከለኛ ክፍል ላይ የሚገኙትን ፕሮቶንስ በሚባሉት ነገሮች ዙሪያ እየተሽከረከሩ የሚገኙ ናቸው። ኤሌክትሮኖች በፕሩቶኖች ዙሪያ ሲሽከረከሩም ልክ በመሬትና በጨረቃ መካከል እንዳለው ርቀት የሚያህል ተፃራሪ የሆነ ርቀት በመሀከላቸው አለው።

በሚጢጢዋ የአንድ አቶም ትንሽ አለም ውስጥ የሚገኙት ኤሌክትሮኖች በፕሮቶኖች ዙሪያ በሰከንድ አስር ሺህ ማይል በሆነ ፍጥነት የሚሽከረከሩት የራሳቸውን ምህዋር በመጠበቅ ነው። ስለዚህ አሁን አንተ በእጅህ በያዝከው ወረቀት ውስጥ የሚገኙ ኤሌክትሮኖች ይሄን ዓረፍተ ነገር ማንበብ ከጀመርክበት ጊዜ ውስጥ ከኒውዮርክ እስከ ቶኪዮ ያለውን ርቀት ያህል ተሽከርክረዋል . . . እናም ከሁለት ደቂቃዎች በፊት ይሄ የወረቀት ገፅ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴዎች የሌሉበትና በድን እና የሞተ አድርገህ አስበኸው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ተጨባጩ እውነታ የሁሉም ነገሮች የእንቅስቃሴና ሀይል ምንጭ መሆኑን የሚያሣይና የሁሉም ነገር ፈጣሪ አምላክ ረቂቅነትን ማሣያ ነው። አሁን የማወቅ ፍላጎት ያደረብህ ከሆነ ያ የሆነው አዲስ እና እንግዳ የሆኑ እውነታዎችን በመስማትህና በመማርህ ምክንያት ነው። ሰዎች ፍላጎት

እንዲያድርባቸው ማድረግ ከሚቻልባቸው ሚስጥሮች አንዱን በዚህ ውስጥ ማየትና መገንዘብ እንችላለን። ያም ቁልፍ እውነታውን መረዳት ነው።

በእያንዳንዱ ቀን በሚኖረን ግንኙነት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ አዲስ ነገርን መገንዘብና የማወቅ ትርፍን ለማግኘት ጠቃሚ ነው። ሙሉ በሙሉ አዲስና የማይታወቅ ነገር የሚያጓጓ አይደለም። ሙሉ በሙሉ ቀደም ብለን የምናውቀው አሮጌ የሆነ ነገር በምንም ዓይነት የሚስበንና የሚማርከን አይሆንም። ነንዲነገረን እና እንድንሰማው የምንፈልገው ነገር በፊት ስለነበረውና በደንብ ስለምናውቀው ያረጀና ያፈጀ ወይም ፍፁም አዲስ ስለሆነ ጉዳይ አይደለም። ለምሣሌ ለአንድ የኤሲኖይስ ገበሬ ስለቦርጂያስ ካቴድራል ወይም ስለ ሞናሊዛ ንግግር ማድረግ ብታስረዳው ለሱ ሁሉቱም አዲስ የሆኑ ነገሮች ናቸው። ከድሮ ፍላጎቶቹ ወይም ከሚያውቃቸው ነገሮች ጋር ሊያገናኛቸውና ሊያስተሳስራቸው የሚያስችለው ምንም ዓይነት ነገር የለም።

ነገር ግን በሆላንድ የሚገኙ ገበሬዎች ከባህር ወለል በታች የሆነ መሬት እንደሚያርሱና የቦታ ወሰናቸውን ወይንም አጥራቸውን በመከለል የሚያጥሩት በዙሪያቸው በተቆፈረና በውሃ በተሞላ ጉድጓድ መሆኑንና እንደ መግቢያ የሚጠቀሙበትም ድልድይ እንደሆነ የሚገልጽ ከሆነ የምታወራው ነገር አንድን የኤሲኖይስ ገበሬ የማዳመጥ ፍላጎት ከፍ የሚያደርገውና የሚያነቃቃው ይሆናል። እንደውም የሆላንድ ገበሬዎች በክረምቱ የበረዶ ወራት ላሞቻቸውን እቤታቸው ውስጥ በማስገባት እንደሚያኖሯቸውና ምናልባትም ላሞቻቸው የተሰፋላቸውን የጥጥ ወይም የሐር ጨርቅ ልብስ ተሸፍነው ለአይኖቻቸው ብቻ በተቀደደ ክብ ቀዳዳ አሾልከው የሚወርደውን በረዶ ሲመለከቱ ማየት የተለመደ እንደሆነ በምታወራ ጊዜ የኤሲኖይሱ ገበሬ አፉን ከፍቶ በአድናቆትና በከፍተኛ ፍላጎት እንዲያዳምጥህ ታደርገዋለህ። እሱ እኮ ስለ ላሞችና አጥሮች በደንብ ያውቃል. . .አዲስ ነገሮችን ደግሞ..... አየህ.....በድሮዎቹ ወይንም በፊት በሚታወቁ ነገሮች ላይ ተጨማሪ ስትነግረው.......ከሐር ወይም ከጥጥ የተሰራ መሸፈኛ ልብስ ለላሞች....ድንቅ ነው የሚለው እናም የሰማውን ነገር እየዞረ ነው ለጓደኞቹ የሚያወራላቸው።

## በህይወትህ ውስጥ ሰልፈሪክ አሲድ ያለው ዘርፈ ብዙ ንክኪ

አብዛኞቹ ፈሳሽ የሆኑ ነገሮች የሚለኩት በፒንት፣ ኳርት፣ ጋሎን ወይም በበርሜል ነው። ሁሌም በተለመደ መልኩ ይህን ያህል ኳርት የወይን ጭማቂ፣ ጋሎን ወተት፣ እና በርሜል ሞላሰስ በማለት እናወራለን። አዲስ የነዳጅ ዘይት ማምረቻ ጉድጓዶች ካገኘን በኋላና ነዳጅን ለኃይል ምንጭነት መጠቀም ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ የየቀኑን ምርት ለመግለፅ በቀን ይህን ያል በርሜል ነዳጅ አመረትን ወይንም ሸጥን እያልን በመናገር የቆየነው። ሌላው አንድ ሌላ ፈሳሽ ደግሞ አለ ይሁን እንጂ የሚመረተውና ለጥቅም የሚውለው እጅግ በጣም

ከፍተኛ በሆነ መጠን በመሆኑ ይህን ፈሳሽ ለመለየት እንድንጠቀምበት መለኪያው "ቶን" እንዲሆን ሆኗል። ይህ ፈሳሽ ሰልፈሪክ አሲድ ነው።

ይህ ፈሳሽ በየቀኑ ህይወታችንን በተለያዩ መንገዶች የሚለካ ነው፡ ሰልፈሪክ አሲድ ባይኖር በቀጥታ መኪናህን ማሽከርከር ታቆም ነበር። በርካታ ሰልፈሪክ አሲድ የነዳጅ ዘይት ድፍድፉን ለማጣራት ተጠቅመን ቤንዚንና ናፍጣን ማምረት ባንችል ኖሮ ወደድሮው ተመልሰን በእንስሳት የሚጎተት ጋሪን መጠቀማችን አይቀርም ነበር። ቢሮህን ብርሃናማ የሚያደርግልህ የሌሌክትሪክ መብራት፣ እራትህን ለመብላት እንድትችል የምግብ ጠረጴዛህን በብርሃን የሚያደምቅልህ በኋላም ወደ አልጋህ ገብተህ እንድትተኛ የሚያስችልህ መብራት ያለሰልፈሪክ አሲድ ልታገኘው የምትችለው አይደለም።

ጠዋት ላይ ተነስተህ ገላህን ለመታጠብ የውሃ መክፈቻ ቧንቧውን ስትከፍት እየተጠቀምክበት ያለኸው ኒኬል የተለበጠ የውሃ ቧንቧ መክፈቻም ነው። ይህንን የውሃ ምርጫውን ረዘምያለ ቧንቧ መሣይ ቱቦ ለመስራትም ይኸው አሲድ አስፈላጊ ነው። የምትጠቀምበት የገላ ሣሙናም በዚሁ አሲድ አማካኝነት ከተመረቱ ዘይቶች፣ ወይም ቅባቶች የተመረተ ሊሆን ይችላል አንተ ገላህን ከምታደርቅበት ፎጣ ጋር ግንኙነት ሳይኖርህ የአንተ ፎጣ ቀድሞ ከሰልፈሪክ አሲድ ጋር ግንኙነት አለው። የፀጉር ማበጠሪያህም ላይ የሚገኙት ቀጫጭን ብረት መሣይ ጣቶችም ይህን አሲድ ይፈልጉታል። የፀጉር ማበጠሪያህም ያለ ሰልፈሪክ አሲድ ሊመረት አይችልም። የጺም መላጫህም እንዲሁ. . .ምንም ጥርጥር የሌለውም ምላጩ በሰልፈሪክ አሲድ አማካኝነት ተመርቶ ነው መላጫህ ላይ የተገጠመው። የውስጥ ሱሪህን ደግሞ እስቲ ተመልከተው። በውጭ በኩል ለሽንት መሽኛ ተከፋች የሆነውን እስቲ ቆልፈው ወይም ክፈተው፣ ሁሉም ዓይነት ሰውም ሆነ የውስጥ ሱሪ አምራች ድርጅቱ የዳይስ እና ዳየር ባለቤትም የሚጠቀመው ይህን የውስጥ ሱሪ ነው። ታዲያ የዚህ የውስጥ ሱሪን ቁልፍ አምራች ቁልፉን ሰርቶ ለማጠናቀቅ የሚችለው ይኸው ሰልፈሪክ አሲድ ሲኖረው ብቻ ነው።

ወርቅንም ሆነ ሌሎቹን የተፈጥሮ ማዕድናት ለማምረት የምንጠቀመውም ይህንኑ ሰልፈሪክ አሲድ ነው። ማንኪያህ፣ ቢላዋህ፣ ሹካህ በብር የተለበጡ እስከሆኑ ድረስ በሰልፈሪክ አሲድ መዘፍዘፋቸው የግድ ነው። በዳቦነት ተዘጋጅቶ የምትመገበው ስንዴ የተመረተው በፎስፌት ማዳበሪያ አማካኝነት ነው። ታዲያ የትኛውና የማን የማምረቻ ድርጅት ነው ይህን አሲድ የማይፈልገውና የማይጠቀምበት? በስንዴ ዱቄት የተጋገረ ኬክ ብንመገብ፣የተለያዩ መድሃኒትና ሽሮፖችን ብንወስድ....ሁሉም ይፈልጉታል።

በዚህ ዓይነት ቀኑን በሙሉ በምታደርጋቸው ነገሮችና እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሙሉ የዚህ አሲድ ሚና ህይወትህን ይነካዋል። እኛ የሰው ልጆች ያለ ሰልፈሪክ አሲድ ወደ ጦርነት መሄድም ሆነ በሠላም መኖር አንችልም። ታዲያ

ለሰው ልጅ ህይወት እጅግ አስፈላጊና ወሣኝ የሆነ አሲድ በአብዛኛው ሰው የማይታወቅ ነው ብሎ ለማሰብ የሚከብድ ሊመስለን ይችላል። ግን እውነታው ይኸ ነው. . . . አይታወቅም እንጂ።

## ሦስቱ በዓለም ላይ ያሉ እጅግ አስደሳች ነገሮች

በዓለም ላይ ያሉ ሦስቱ እጅግ አስደሳች ነገሮች ምን ምን ናቸው ትላላችሁ? ወሲብ፣ ንብረትና፣ ሃይማኖት ናቸው ። በመጀመሪያው ህይወትን እንፈጥራለን፣ በሁለተኛው ህይወታችንን እናቆያለን፣ በሦስተኛው ከዚህኛው ዓለም በኋላ በሚጠብቀን ዓለም ውስጥ ዘላለማዊ ህይወት ለመኖር ተስፋ እናደርጋለን።

ስለሆነም ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ የማዳመጥ ፍላጎት የሚያድርብን ወይም የሚቀሰቀስብን ስለወሲብ፣ ስለንብረትና፣ ስለሃይማኖት የሚደረጉ ንግግሮችን ለማዳመጥ ነው። ለነዚህ ሦስት ነገሮች መሟላት ያለን የውስጣዊ ስሜት ግፊት ሞቅ ያለ የማወቅና የማዳመጥ ፍላጎት እንደያድርብን ወይም በውስጣችን እንዲቀሰቀስ ያደርግልናል።

ይህ ማለት ግን በፒሩ ውስጥ ስላሉ ሰዎች የወሲብ ግንኙነት ለማዳመጥ ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት ላይኖረን ይችላል። ግን በመሃላችን ወይም በአቅራቢያችን ስለተፈጸመ ወይም ስለሚፈጸም የወሲብ ግንኙነትና ቅድመ ጥያቄ ለመስማት የሚኖረን ፍላጎት እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው የሚሆነው። በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ስለ ሂንዱ እምነት ማወቅ ካላስፈለገን በስተቀር ለማወቅ ፍላጎት የሚያድርብን አይሆንም። ነገር ግን ከህይወት በኋላ ባለው ህይወት ወይም ዓለም የዘላለም ደስታንና ህይወት እንጎናፀፋለን ብለን ስለምናምንበት ሃይማኖታችንን ለመስማት የሚኖረን ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ነው።

አሁን በህይወት የሌለው ሎርድ ኖርክሊፍ ሰዎች ምን የማዳመጥ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ያደርጋቸዋል ተብሎ በተጠየቀበት ጊዜ በአንዲት ቃል ብቻ ነበር መልስ የሰጠው. . .እናም ያ ቃል . . .‹እራሳቸው› የሚል ነበር። ሎርድ ኖርክሊፍ በታላቋ ብሪታንያ ውስጥ እጅግ ሃብታም የሆነ የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ባለቤት ነበር። ምን ዓይነት ሰው እንደሆንክ ማወቅ ትፈልጋለህ? አው. . አሁን እጅግ እስደሳች የሆነ እርዕስት ውስጥ ልንገባ ነው። አሁን የምንነጋገረው የአንተን ማንነት ልክ መስታወት ውስጥ እራስህን ሙሉ በሙሉ ግልፅ በሆነ መንገድ ልትመለከተውና ልትገልፀው የምትችልበትን መንገድ ነው። እናም በቀጣይ በዋናነት የምንነጋገረው አንተ ስለምታውቀው ልታየው ስለምትችለውና ስለምትገልፀው ማንነትህ ሳይሆን የሱ ፍፁም ተቃራኒ ስለሆነው ማንነትህ ነው። እስቲ. . . እንተም የአንተ ማንነት መገለጫዎች የሆኑትን ውሰድና ፍፁም ተቃራኒያቸውን ለመመልከት ሞክር። የአንተ ማንነት ፍፁም በሆነ ሁኔታ በተቃራኒ በሰወጥ ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህን እስቲ

ፕሮፌሰር ጀምስ ሀርቪይ ይመልሰው፡፡ መልሱን ከፕሮፌሰሩ በማይገኝ እን ዘ ሚኪንግ መፅሃፍ በመውሰድ ያጣቀስነው ነው፡፡

እኛ ሁሉም ገና ሙሉ ለሙሉ ከእንቅልፋችን እስክንነቃ በመንቃትና ባለመንቃት መሃል በምንቆይባቸውና በምናሣልፋቸው አጭር ደቂቃዎች ውስጥ አእምሮአችን ትክክለኛ በሆነ የማሰብ ሂደትና ተግባር ውስጥ እንዳለ አድርገን እንገነዘባለን፡፡ አብዛኞቻችንም በእንቅልፍ ውስጥ ሆነን እንደምናስብ አድርገን እንገነዘባለን፡፡ አብዛኞቻችንም በእንቅልፍ ውስጥ ሆነንም አእምሮአችን የማሰብ ሂደቱን የማያስተጓጉል ይመስለናል፡፡ በእንቅልፍ ውስጥም ሆነ በመንቃትና ባለመንቃት መሃል ሆነን በአእምሮአችን ውስጥ የምናገላባቸው ነገሮች ወደ ሆነ እንቅስቃሴ ወይም ድርጊት እስካለወጥናቸው ድረስ በማሰብ ላይ ሣንሆን በፍፁም ተቃራኒው ላይ ነን፡፡ በእንቅልፍ ላይም ሆነ በመንቃትና ባለመንቃት መሃል ባሉት ጊዜያቶች ሁሉ አእምሯችን እያሰበ አይደለም፡፡ እኛ ሁሌም ሃሣቦቻችን ተግባራዊ ወይም ተፈፃሚ እንዲሆኑ ፍፁም ፈቃደኞች ነን፡፡ ነገር ግን በአእምሮአችን ውስጥ ያሉ ሃሳቦቻችን ተፈፃሚ የሚሆኑበት ሂደት የሚወሰነው በእኛ ውስጥ በተስፋና ፍርሃት፣ ፍቅርና በጥላቻ፣ በመውደድና ባለመውደድ፣ በኩርፊያ እንደሁም ተቃውሞ የውስጥ ስሜቶች ግፊት መሃል አሸንፎ በመውጣት እያደገ በሚሄደው ስሜት በሚፈጥረው የፍላጎታችን መሳካትና ያለመሳካት፣ ስኬትና ውድቀት ስሜት ነው፡፡

ለራሳችን እንደራሳችን ዓይነት ከፍተኛ የሆነ ፍላጎትን ሊያሣድርብን የሚችል ምንም ዓይነት ነገር የለም፡፡ እነሰም በዛ ሃሣባችንን ሁብሰብ በማድረግ መቆጣጠርና አቅጣጫ ማስያዝ የማንችል ከሆነ ሁሌም ከኛ ፍላጎት ውጪ በሆነ ሁኔታ ማሰብና መመልከት እንዳንችል ያደርገንና በራሳችን ሃሣብ ዙሪያ ብቻ ታጥረን የራሳችን ፍላጎቶችና ሃሣቦች አምላኪነትንና ተገዢነትን እንድንጠናወት ያስገድደናል፡፡ ይህን ዓይነት ሁኔታ በራሳችንም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ መመልከትና ማስተዋል እጅግ አስገራሚ ነው፡፡ እኛ ሁሌም ታዛዥና ደግ በሆነ መልኩ የዚህን ዓይነት አስተሳሰብ ለመሸከምና ለመቋቋም ፍቃደኞች በመሆናችን እውነታውን ለማወቅና ለመረዳት እጅግ አዳጋች ይሆንብናል፡፡ ነገር ግን ለማሰብና ለመጠየቅ የምንደፍር ከሆነ ልክ እንደ ቀትር በኋላ ፀሐይ እየደከመ እየጠፋ የሚሄድ ይሆናል ፡፡

እውነተኛና ሊታይ የሚችለው የባህሪያች መገለጫዎች የሆኑ ዋነኛ ፀባዮቻችን፣ ፍፁም ተቃራኒ የሆኑ አምሣያ ፀባዮቻችን አዲስና በውስጣችን ያልነበሩ ባህሪዎች መገለጫዎች ወይም የተደበቁና የተረሱ የማንነታችን ነፀብራቆች ናቸው፡፡ የማንነታችን ወይም የፀባያችን ፍሁም ተቃራኒ የሆኑ የማንነት መገለጫዎች ያለምንም ጥርጥር እራሳችንን ከፍ በማድረግ የማገላትና የመደምደም ግምታችን ወይም አስተሳሰባችን ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሣርፉ ናቸው፡፡ ወይም የማንነታችን ተቃራኒ የሆነ ባህሪ ቀደም ብሎ በውስጣችን የነበረ መሆኑን የሚያሣይ ዋነኛ መገለጫ ነው፡፡

ስለዚህ ማስታወስ ያለብህ ሰዎችን ብዙም የእኛ ጉዳይ ነው፣ የእኛ ስራ ነው ብለው ብዙም ትኩረት ባልሠጡትና ፍላጎት በሌላቸው ጉዳዮች ዙሪያ ጊዜያቸውን መስዋት አስደርገህ ንግግር ልታደርግ ስትፈልግ ንግግርህ ማንነታቸውን የሚያጎላ መሆን የሚችልበትን መንገድ ልታስብበትና ልታዘጋጅ ይገባል፡፡

በአማካኝ አብዛኛው ሰው ለማዳመጥ ከፍተኛ የሆነ ትኩረትን የሚሰጠው ስለኢኮኖሚ ችግሩ እንጂ ጣሊያን ያለባትን የብድር ዕዳ ለአሜሪካ ስለመክፈሏ አይደለም፡፡ ስለ ደቡብ አሜሪካ አብዮት ከሚሰማ ይልቅ ስለ ፂም መላጫ አይነቶች መስማትን ይወዳሉ፡፡ የሚያሰቃይ የጥርስ ህመም ያለባት አንድ ሴት በእስያ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሠዎችን ህይወት ከቀጠፈው የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ በላይ ስለጥርስ ህመም መስማት ነው የምትፈልገው፡፡ ለአንድ ሴት ስለ አስሩ የአለም ታላላቅ ሰዎች ከምታደርገው ንግግር ይልቅ የሷን የተወሰኑ ጥሩ ነገሮች በመጥቀስ ለምታደርገው ንግግር ጆሮዋን ልትሰጥህና ልታዳምጥህ ትችላለች፡፡

## ጥሩ ተናጋሪ እንዴት ልትሆን ትችላለህ?

በጣም ብዙ የሆኑ ሰዎች ደካማ ንግግር አድራጊዎች የሚሆኑበት ምክንያት ሁሌም ለነሱ ስለሚያስደስታቸው ነገሮች ብቻ ንግግር ስለሚያደርጉ ነው፡፡ ይህን ማድረግ ደግሞ ለሌሎች ሰዎች ፍፁም አሰልቺና አታካች ይሆንባቸዋል፡፡ የዚህ አይነት ንግግር ፍፁም ተቃራኒ ደግሞ የምታወራውን ሰው ስለፍላጎቶቹ ስለስራው፣ ስለጎልፍ ጨዋታና ውጤቱ፣ ስለተሳኩለት ነገሮች . . . ወይም የልጆች እናት ከሆነች ስለልጆቿ እንድታወራልህ መምራትና መንገድ መክፈት ነው፡፡ ያን ካደረክ በኋላ ዝም ብለህ በጥሞና አዳምጥ፣ ደስታን ታገኛለህ፡፡ በዚህም ምንም እንኳን የአንተ ተሳትፎ በንግግሩ ውስጥ አነስተኛ ቢሆንም ጥሩ የሆነ የማዋራት ክህሎት ያለህ ተደርገህ ትወሰዳለህ፡፡

የፊላደልፊያው ሐርልድ ድዋይት ስለ ህዝብ ንግግሮች ሲሰጥ የነበረውን ስልጠና መጠናቀቅ አስመልክቶ በተዘጋጀ አንድ ግብዣ ላይ አፁብ ድንቅ በተባለ ሁኔታ የተሳካ ንግግር አድርጎ ነበር፡፡ ሐሮልድ ንግግሩን እንደጨረሰ በእለቱ የነበረው እያንዳንዱ ታዳሚ ሐርልድ ስልጠናውን ሲጀምር ምን ዓይነት ንግግር ያደርግ እንደነበርና በእለቱ ባደረገው ንግግር ውስጥ ሌሎች አባሎች የተናገሯቸውን ነገሮች በማካተት፣ ገለፃ ያደረጉባቸውን አርዕስቶች በማንሳት፣ የአንዳንዶቹንም የአነጋገር ዘይቤ በማስመሠል፣እንዲሁም አንዳንድ ተናጋሪዎች በንግግራቸው መሃል ያሳዩአቸውን እንግዳ የሆኑ የሰውነት እንቅስቃሴዎችንና ልምዶችን አጋኖ በመድገም ታዳሚውን በሙሉ ባሳቀና ባስደሰተ መንገድ እንዴት አድርጎ የንግግር ችሎታውን እንዳሻሻለው በማነፃፀር በየጠረጴዛው ላይ ያወሩ ነበር፡፡ በዚያን ሰዓት ከዚህ ንግግር ውጪ ከሠማያዊው ሰማይ ስር ባለ በየትኛውም ዓይነት ዓርዕስት ዙሪያ የሚደረግ ንግግር መስማት ታዳሚውን የሚያስደስተው አልነበረም፡፡ ሚር ድዋይት የሠው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባህሪን እንዴት አድርጎ መያዝ እንዳለበት አውቆት ነበር፡፡



Scanned with CamScanner

## ሁለት ሚሊዮን አንባቢያዎች ያፈሩ ሃሣብ

ከትንሽ ዓመታት በፊት አንድ ብዙም አንባቢ ያልነበረው መፅሄት በአሜሪካን የመፅሄት ስርጭትና ገበያ ውስጥ ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ የሽያጭ ድርሻን በመያዝ ትልቅ የእድገት ደረጃን መጎናፀፍና ማስመዝገብ ችሎ ነበር:: የዚህ መፅሄት ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ ስርጭት መጨመር ገበያውን መምራቱ በአብዛኞቹ የአሜሪካን የመፅሄት አሣታሚዎች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የግርምትና የአድናቆት ስሜትን ፈጥሮ ነበር:: የስርጭቱ መጨመር ሚስጥሩ አሁን በሕይወት የሌለው ጆን ኤም ሲዳል እና የሱ ሃሣብ ነበር:: ከሲዳል ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በተገናኘንበት ወቅት የዚህ መፅሄት አሣታሚ ድርጅት" ሠዎችን የሚማርኩና የሚያጓጉ ጉዳዮች" ዲፓርትመንት ሐላፊ ሆኖ ነበር:: በወቅቱ የተወሠኑ ሃሣቦችን ጽፌ አልክለት ነበር:: አንድ ቀን ግን ወደ ቢሮዬ በመምጣት አረፍ ብሎ ለረጅም ሠዓታት እንዲህ በማለት መፅሄቱን ተፈላጊና ተወዳጅ ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ አጫወተኝ ነበር::

«ሰዎች ራስ ወዳዶች ናቸው» ብሎ ነበር የጀመረው:: እነሱ! ሁሉም በዋናነት ጉጉታቸው ስለራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ብቻ ነው:: ለነሡ የባቡር አገልግሎት በመንግስት ባለቤትነት ስር የመሆኑና ያለመሆኑ ነገር ጉዳያቸው አይደለም:: ግን እንዴት ትልቅ ቦታ ላይ መድረስ እንደሚችሉ ማወቅን ይፈልጋሉ:: ከፍተኛ የሆነ ክፍያ ወይም ደሞዝ እንዴት ሊያገኙና ሊከፈላቸው እንደሚችል፤ እንዴት ጤናቸውን ሊጠብቁ እንደሚችሉ የመሣሠሉትን ማለት ነው:: "እኔ የዚህ መፅሄት ዋና አዘጋጅ ብሆን ኖሮ" በማለት ንግግሩን ቀጠለ" ለጥርሳቸው እንዴት እንክብካቤ ማድረግ እንደሚችሉ፣ የገላቸውን ቆዳ እንዴት ማሣመርና መንከባከብ እንደሚችሉ፣ በበጋው ሞቃታማ ወራቶች እንዴት ሙቀትንና ወበቅን መቋቋም እንደሚችሉ፣ እንዴት ከፍተኛ የሐላፊነት ቦታዎችን ማግኘት እንደሚችሉና እንዴት ተፅዕኖ መፍጠር የሚችል ግለሠብ መሆን እንደሚችሉ፣ ሠራተኞቻቸውን እንዴት ማሣመን፣ መምራትና መንከባከብ እንደሚችሉ፣ እንዴት ቤት መግዛት እንደሚችሉ እንዴት የተናገሯቸውን ስህተት የሆኑ ንግግሮች ማረም እንደሚችሉ የመሣሠሉትን እነግራቸው ነበር::

ሠዎች ሁሌም የሌሎችን ነገሮች ታሪኮች ለማወቅ ከፍተኛ የሆነ ጉጉትና ፍላጎት የሚያድርባቸው ናቸው:: ስለዚህ በቤት ግንባታ የስራ መስክ በመሠማራት በሚሊዬኖች የሚቆጠር ሃብት ያካበቱ ባለፀጎች እንዴት እዚህ ደረጃ እንደደረሡ አወራላቸው ነበር:: ታዋቂ የባንክ ሠዎችን እና የትላልቅ ኮርፓሬሽኖች ኘሬዝዳንቶችንና እዚህ የስልጣን ደረጃ እና ሐብት ላይ ለመድረስ ምን ዓይነት ፈታኝ ውጣ ውረዶችን እንዳሳለፉ እነግራቸው ነበር"

በአጭሩ ከዚህ ንግግር በኃላ ሲዳል የመፅሄቱ ዋና አዘጋጅ እንዲሆን ተደርጐ ነበር:: በወቅቱ መፅሄቱ የነበረው ዝቅተኛ ስርጭትና ሽያጭ በአንፃራዊነት ውድቀት ውስጥ ያለ ተደርጐ የሚወሰድ ነበር:: ታዲያ ሲዳል

ያደረገው "አደርገው ነበር" በማለት ይናገር የነበረውን ነገር ነው። ግብረ መልሱም? አጅግ የሚያስፈነጥዝ ነበር። የመፅሄቱ የስርጭት ሽፋን ወይም የገበያ ድርሻ ወደ ሁለት መቶ ሺህ . . . ሶስት . . . አራት . . . ግማሽ ሚሊዮን . . . ደረሰ።

ተከታታይ የሆነ የሽያጭ እድገት አሣየ። መፅሄቱ ያወጣቸው የነበሩ ጉዳዮች አብዛኛው ህዝብ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ነበር። ወዲያውኑም በወር አንድ ሚሊዮን ሠዎች መፅቱን ይገዙት ነበር። ከዚያም አንድ ሚሊዮን ከግማሽ በስተመጨረሻም ሁለት ሚሊዮኖች ደረሠ። በዚህ ብቻ ተወስኖ ሳይቀርም ለብዙ ዓመታት ስርጭቱ በተከታታይ እያደገ ይሄድ ነበር። ሲዳል በአንባቢዎቹ የራስ የመተማመን ስሜትና ከፍተኛ የሆነ ጉጉት መፅሄቱን ከፍተኛ ሽያጭ ያለው ተወዳጅና ተነባቢ መፅሄት ለማድረግ የመነዘረው።

## የአድማጮችን ትኩረት መሣብ በሚያስችሉ አርዕስቶች ዙሪያ ንግግርህን ቃኝ

ሁሉም ስለነገሮችና ሃሣቦች ብቻ የምታወራ ከሆነ ሠዎችን ልታሠለቻቸው ትችላለህ። ስለሠዎች በምታወራበት ጊዜ ትኩረታቸውን ለመሣብና ለመያዝ የሚያቅትህ አይሆንም። በነገው ዕለት ጠዋትና ማታ በአሜሪካን ውስጥ በሻይና በእራት ጠረጴዛዎች ዙሪያ የሚደረጉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወሬዎች ከየቤቶቹ አልፈው አጥር ተሻግረው አሜሪካንን ሲያጥለቀልቁ የሚችሉ ቢሆኑ የአብዛኞቹ ወሬዎች ቀዳሚውና ዋናው አርዕስት ምን የሚሆን ይመስላችኋል? የሠው ነገር። እሱ ይሄን አለ ወ/ሪት እከሌ እና እከሊት ያን አደረጉ። እኔ እሷ ይሄን ስታደርግ አይቻታለሁ . . . ያ እና ሌላው እሱ "ገዳይ" ፊልምን እየሠራ ነው። እና የመሣሠሉት ሠው ተኮር ወሬዎች ናቸው የሚሆኑት።

እኔ በአሜሪካና በካናዳ በርካታ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ተደጋጋሚ ንግግሮችን አድርጌአለሁ። እናም አሁን በቅርቡ ከልምድ ከተማርኩት ነገር አንዱ ሠዎች የማይደመጥ ጉጉት እንዲኖራቸው ለማድረግ ስለሠዎች ታሪክ ልንግራቸው እንደሚገባ ነው። አንድ ጊዜም አንድ የአሜሪካን ነጋዴዎች ቡድንን በፓሪስ ከተማ ውስጥ "እንዴት እንደተሳካላቸው" ንግግር እንዲያደርጉ ጠይቂአቸው ነበር። አብዛኛዎቹ ነጋዴዎችም በሀገራቸው በአሜሪካን ያለው እድልና የተመቻቸ ሁኔታ እዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ እንዳደረጋቸው ሠፋ ባለ ሁኔታ በዝርዝር አቀረቡ። እንደአጋጣሚ በቅርቡ አንድ በጣም የታወቀ የአሜሪካን ባለሀብት ልክ እንደዚሁ ዓይነት አስተያየት በአንድ የሬዲዮ ቃለ-ምልልስ ላይ ሲሠጥ ሠምቼው ነበር። ይህንን ሃሣብም ሌሎች ብዙ ከአሜሪካን ውጭ በማስተማር ላይ ያሉ ፕሮፌሠሮችና ነጋዴዎችም ይጋሩታል።

ስለዚህ እዚህ ላይ ውይይቱን እንዲህ በማለት «እኛ ይህን እንድታውሩልን አይደለም የምንፈልገው በዚህ ማናችንም የማዳመጥ» ፍላጎትና ጉጉት ሊያድርብን አይችልም። ልታስታውሱት የሚገባው ነገር የምትነግሩንን ማንኛውንም ነገር

ለማዳመጥ ትኩረት ልንሠጥ እንደማንችል ማወቅ አለባቸው፡፡ በዓለም ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የማደመጥ ፍላጎትን የሚፈጥረው ቆንጆ በሆነና በተጋነነ ሁኔታ ስለሰዎች የሚወራ ወሬ መሆኑን ልናውቅ ይገባናል፡፡ ስለዚህ እስቲ ስለምታውቋቸው ሁለት ሰዎች ታሪክ ንገሩን፡፡ አንዱ ለምን በንግዱ ውስጥ እንደተሳካለትና ሌላው ለምን እንዳልተሳካለትም ጨምራችሁ ንገሩን፡፡ ያንን በደስታ እዳምጣችኋለን፡፡ የምትነግሩን ታሪክ በደንብ የምታውቁትና አስተዋፅኦ በማድረግ በቀላሉ አሳማኝና ግልፅ ንግግር ማግኘት ውበት ከፍተኛ ችሎታ ባለቤት በመሆን ትጠቀማላችሁ፡፡ በተጨማሪም ለእናንተም በጣም ቀላልና ግልፅ በሆነ መልኩ እንዴት በንግድ ስራ ውስጥ እንደተሳካላችሁ ለማስረዳት በድፍኑ በአሜሪካ ካለፈው ትልቅ ዕድል የተነሳ ነው ብሎ ከመመለስ እጅግ በተሻለ መንገድ መናገርና ማስረዳት ያስችላችኋል፡፡

በዚያን እለት በዚህ ትምህርታዊ ውይይት ላይ ተገኝቶ የነበረና በሚያደርገው ንግግር የማንንም ቀልብና ልብ መሳብ ያልቻለ አንድ ተሳታፊ ወዲያው እድሉ እንዲሰጠው በመጠየቅ ካሁን በፊት በአንድ ኮሌጅ አብረውት ይማሩ ስለነበሩ ሁለት ጓደኞቹ ይህንን ታሪክ አወራልን፡፡ ከሁለቱ ጓደኞቹ አንደኛው ያስፈልገኛልና በቂ ነው የሚለውን ያህል ሸሚዞች በከተማው ውስጥ የሚገኙ የሸሚዝ መሸጫ ሱቆች ተዘዋውሮ አይቶና ዋጋ አወዳድሮ አንድ ጊዜ የሚገዛ ነበር፡፡ ሸሚዞቹንም ለረጅም ጊዜ ደጋግሞ በመልበስ በደንብ መቆሸሻቸው ካላስታወቀ በስተቀር የሚለብስና የተለያዩ የልብስ ንፅህና ቤቶችን ተዘዋውሮ አይቶና አወዳድሮ በሚከፍላት አንድ ዶላር እኩል ተመጣጣኝ የሆነ የልብስ ንፅህና አገልግሎት አገኝበታለሁ ብሎ ለሚያምንበት ላውንደሪ ቤት ብቻ ነበር የሚሰጠው፡፡ አስተሳሰቡ ሁሌም ከሳንቲም ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ ትምህርቱን አጠናቆ ሲመረቅ . . የምህንድስና ኮሌጅ ነበር. . . ለራሱ ከፍተኛ የሆነ ቦታን ይሰጥ የነበረ በመሆኑ ራሱን ከፍተኛ የሆነ ተፈላጊነት ያለው አድርጎ የሚመለከት ስለነበር እንደሌሎቹ ጓደኞቹ ወደታች ዝቅ ብሎ ለመስራት ምንም አይነት ፍላጎት የለውም ነበር፡፡ በአንዴ ትልቅ ትልቅ የሆነ ስራና ሃላፊነት ደረጃ ላይ ለመድረስ ብቻ ነበር የሚመኘው፡፡ ሌላው ቀርቶ በሶስተኛው የቀድሞ ተማሪዎች ዓመታዊ የግንኙነት ጊዜም ያው እንደቀድሞው ላውንደሪ ቤቶችን የማማረጥና አንድ ሸሚዝ ለረጅም ጊዜ መልበስ የመሳሰሉትን ልምዶችና ፀባዮች እንዳሉበት ያልተለወጡና በዚያን ጊዜም ቢሆን አንድ ቀን በሆነ ተዓምር ህይወቱ እንደሚቀየር የሚያስበውና የሚያልመው እንደሚሆን እርግጠኛ በመሆን ቀጥ ብሎ መጠበቁን ቀጥሎበት ነበር፡፡ ግን ያ ይበቃው የነበረው ተአምርም በጭራሽ አልመጣም፡፡ በዚህ ዓይነት ሃያ አምስት አመታትን ቢያሳልፍም አሁንም ዝቅተኛ በሆነ ቦታና ደረጃ ላይ ነው እየሰራ ያለው፡፡ በዚህ የተነሳም መራራ የሆነ ህይወትን እየገፋ ይገኛል፡፡

በመቀጠልም የዚህኛው ህይወቱ ስኬታማ ያልሆነለትን ጓደኛውን ታሪክ ከሌላኛው ህይወቱ እጅግ ከተዋጣለት ጓደኛው ታሪክ ጋር ለማነፃፀር በሚያስችል መልኩ መናገር ጀመረ፡፡ የዚህ ዓይነቱ የንግግር አቀራረቡንም ብዙዎቹ አድማጮቹ ወደውለት ነበር፡፡

ሁለተኛው ጓደኛዬ ደግሞ . . . በማለት ቀጠለ . . . ሁሉም ትልት ደረጃና ቦታ ላይ መድረስና ትላልቅ ስራዎችን መስራት የሚመኝ ቢሆንም ሀ ብሎ ስራ የጀመረው ግን ጀማሪ የግንባታ ንድፍ ሠራተኛ ሆኖ ነበር:: ነገር ግን ሁሌም የተሻሉ አማራጮችንና እድሎችን ማግኘት የሚችልበትን ሁኔታ የሚያስስ ሰው ነበር::

በአንድ ወቅት ላይም የፓን አሜሪካን የቴሌፎን ካምፓኒ በቡፋሎ የቴሌፎን አገልግሎት ለመስጠት ማቀዱን አሳውቆ ነበር:: ይህን በሚሰማበት ወቅትም ለስራው የኤሌክትሪካል ምህንድስና ሙያ ወሳኝና አስፈላጊ መሆኑን ያውቅ ስለነበረ የፊላደልፊያው ስራውን በመልቀቅ ወደ ቡፋሎ አመራ:: በዚያም ያለውን የመግባባት ችሎታ በመጠቀም አንድ በቡፋሎ ውስጥ ከፍተኛ ታማኝነትና ተሰሚነት ካለው ፓለቲከኛ ጋር በመግባባት ጓደኝነትን ፈጠረ:: ከዚያም የቴሌፎን ኮሚኒኬሽን ስራዎችን የሚሰራ አንድ አነስተኛ ድርጅት በጋራ አቋቋሙ:: ወዲያውም የፓን አሜሪካን የቴሌፎን ድርጅት በቡፋሎ ያጫረታቸውን የኮንትራት ስራዎች በጨረታ በማሸነፍ በከፍተኛ ሁኔታ ስራውን አጠናቀው ብዙ ትርፍ በማግኘት ውላቸውን ፈፀሙ:: የዚህን ልጅ ከፍተኛ የሆነ ችሎታ የተመለከተው የፓን አሜሪካን የቴሌፎን ካምፓኒም ከፍተኛ በሆነ ደመወዝ ቀጥረው:: በአሁኑ ወቅትም በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ባለቤትና ቂስተርን ዩኒየን የሐዋላ አገልግሎት ባለቤቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው በማለት ንግግሩን አጠቃለለ::

ንግግር አቅራቢው ያወራው ታሪክ ጠንቅቆ የሚያውቀውን እውነታ ስለነበር በጥሞና ፀጥ ብለን ነበር ስናዳምጠው የቆየነው:: እሱ ንግግሩን ያደርግ የነበረው እውነተኛ የሰዎች ታሪኮችን በሚተርክ አስደሳች አነጋገር ነበር:: . . . . . ከዚህ በፊት ለሶስት ደቂቃ እንኳን ማውራት ያቃተው ይህ ሰው ለሰላሳ ደቂቃዎች ንግግር ማድረጉን ሲያውቅ በቃላት ሊገልፀው የማይችለው አይነት አግራሞት ነበር የተፈጠረበት:: ያደረገው ንግግር እጅግ አስደሳችና የሚስብ ስለነበር ሁሉም አድማጮች አጭር የሆነ ንግግር ያደረገ ነበር የመሰላቸው:: ይህ ዕለት ሰውየው የመጀመሪያው የሆነውን አስደሳች የሆነ ንግግር ያደረገበት ቀን ነበር::

በዚህ አይነት የንግግር ስልጠና ለአብዛኞቹ ከፍተኛ የሆነ የንግግር ውበትን የተላበሰ ችሎታን ነበር የፈጠረላቸው:: የምናደርጋቸው ንግግሮች ብዙውን ጊዜ ስለሰዎች ታሪክ ከሆነ ከምንገምተው በላይ በሆነ መልኩ የሚማርክና ደስ የሚል ንግግር ነው የሚሆነው:: እንዲህ ያሉ ንግግሮችን ለማድረግ ንግግር አድራጊው አንድ የተወሰነ ነጥብ ወይም ሃሳብ በመሠንዘር ነጥቡን በማጉላት የሚያሳዩና ለመተንተንና ለማስረዳት በሚያስችሉ የሰዎች ታሪኮችን በምሳሌነት በማንሳት ወይም በመጥቀስ መናገር ነው ያለበት:: እንደዚህ ያሉ ንግግሮች ትኩረትን የማይሠጡበትና ተቀባይነትን የሚያጡበት ሁኔታ በፍፁም አይኖርም::

ከተቻለም ስለሰዎች በምናደርጋቸው ንግግሮች ባለቤቶቹ ስላደረጓቸው ጦርነቶችና ትግሎች ስላለፏቸው ፈተናዎች፣ እንዲሁም ስላገኟቸው ድሎችና ውጤቶች ማካተት ይኖርብናል:: አብዛኞቻችን ስለጦርነቶችና ውጊያዎች ለመስማት በጣም ከፍተኛ የሆነ ጉጉት አለን:: ዓለም በሙሉ የሚወደውን

የሚወድ ነው የሚል አንድ የቆየ አባባል አለ። ነገር ግን እውነታው ይህ አይደለም። ዓለም በሙሉ ከሚወደው የተለየ ነው ብለን በተፈጥሮአዊ የአነጋገር ጥበብን በጠበቀ መልኩ የምንላቸውን ዓይነት ወሬዎችን ስለሰዎች ታሪክ የመስማትን ነው የሚወደው። ዓለም እንዴት ቆንጆ ሴትን አፍቅረው እየተናነቁ ስላሉ ሁለት አፍቃሪ ወንዶች መስማትን ነው የሚፈልገው። ይህን ማረጋገጥ ከፈለጋችሁ እስቲ አብዛኞቹን የልቦለድ መፅሀፎች ስለምን እንደሚያወሩና በምን ጉዳይ ላይ እንደሚያጠነጥኑ ተመልከቱ። ዋናው ተዋንያን ሁሉንም ፈተናዎች አልፎ በድል አድራጊነት ሲወጣ ተመልካቹ በድል አድራጊነት ከመቀመጫው መነሳት ይጀምራል።

በአብዛኞቹ ፊልሞችና መፅሄቶች ላይ የሚታተሙና የሚፃፉ ታሪኮች በዚህ ዓይነት ስሌት ነው የሚታኙት። አንባቢው ጀግና ወይም እጅግ ደስተኛ እንዲሆን አድርገው በሚስው እሱን ወይም እሷን ልባቸው ለአንድ ነገር እንዲንጠለጠል አድርጋቸው ነው የሚለው። ያም ነገር ፍፁም ሊሆን የማይችል፣ ወይም ሊገኝ የማይችል ነገር እንዲሆን እንዲያስቡ አድርጋቸው በሚለው የጀግንነት ወይም ከፍተኛ የሆነ የእርካታ ስሜት በውስጣቸው እንዲፈጠር አድርግ በሚለውና በመሳሰሉ ስሌቶች ነው።

አንድ ሰው በሙያው ወይም በንግድ ስራው ውስጥ ስላጋጠሙት ፈተናዎችና ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች፤ ስላደረጋቸው ውጣውረዶች እንዲሁም እንዴት ባለድል ሆኖ እንደወጣ የሚያሳይ ታሪክ ሁሌም አንጊና አስደሳች ነው። በአንድ ወቅት አንድ የመፅሄት አዘጋጅ የማንም ሰው እውነተኛ የሆነ ታሪክ በጣም አዝናኝና ለማዳመጥ ስሜትን የሚጭር እንደሆነ ነግሮኝ ነበር። በጦርነት ላይ የዘመተና የተዋጋ አንድ ሰው . . . ታሪኩን ትክክለኛ በሆነ መንገድ መግለፅ ከተቻለ . . የሚስብና የሚማርክ ነው የሚሆነው። ለዚህ ምንም ጥርጥር የለውም።

## ንግግርህ ግልፅ ይሁን

የዚህ መፅሃፍ ፀሐፊ በአንድ ወቅት ላይ ስለ ህዝብ ንግግሮች ትምህርት በሚሰጥበት አንድ ክፍል ውስጥ አንድ የፊሊሶፊ ዶክተርና አንድ ከሰላሳ አመታት በፊት በእንግሊዝ ባሕር ሐይል ውስጥ የወጣትነት እድሜውን ያሳለፈ የመጣለትን ነገር እንደልቡ የሚናገር ስነ-ስርዓታዊነትን ለመጠበቅ የማይጨነቅ የሚባል ሰውን በአንድ ላይ አስተምሮአቸው ነበር። ሆላንዳዊው ምሁር የአንድ ዩኒቨርስቲ አስተማሪ ሲሆን ባህረኛው የክፍል ጓደኛው ደግሞ አንድ ሸቀጦችን በከተማ ውስጥ በሽፍን የጭነት መኪና የማመላለስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ባለቤት ነበር። በሚገርምና እንግዳ በሆነ መልኩ ግን ሸቀጥ አመላላሹ ባህረኛ ሰው ያደርጋቸው የነበሩት ንግግሮች ከኮሌጅ ፕሮፌሰሩ ንግግሮች እጅግ በሚያስንቅ ሁኔታ ከፍተኛ አድማጭ ወይም ሰሚ ነበራቸው። ለምን?

የኮሌጁ ሰው ንግገሩን ያደርግ የነበረው በቆንጆ እንግሊዝኛ፣ በጥንቃቄ ባህልንና ስነ-ስርዓታዊነትን በጠበቀ መልኩ፣ በጠራና ግልፅ በሆነ ሃሳብ፣ በጥሩ ቃላትና ሎጂክ ላይ በተንተራሰ ንግግር ነበር። ነገር ግን አንድ ወሳኝና አስፈላጊ



Scanned with CamScanner

የሆነ ነገር ይጎድለው ነበር። ግልፅነት ቀላልነትና ለመረዳት አሻሚነት የሌለውና፣ የማያጠራጥር በሆነ መልኩ መናገርና በዝግታ ንግግር ሃሳቡን አሻሚነት በሌለው ንግግር በእርግጠኝነት ማሳወቅ ባለመቻሉ ንግግሮቹን አጠቃላይ በሆነ ግልፅ እውነታዎች ውስጥ በማጣጣም በእርግጠኝነት ለማወቅና፣ ለመረዳት፣ የሚከብዱ ግራ የሚያጋቡ ነበሩ።

በሌላ መልኩ ግን የሸቀጥ አመላላሽ ድርጅት ባለቤቱ ወዲያው ስለ ንግድ ስራ አገልግሎቱ ማውራቱን ነበር የቀጠለው። እሱ ምንም አሻሚነት በሌለው መልኩ በቀላሉ ስለሚታወቁና እርግጠኝነትን ስለሚፈጥሩ ነገሮች ነበር ያነሳው። ከወንዳወንድነቱና ደፋርነቱ እንዲሁም የሚጠቀምባቸው አዳዲስ ቃላቶች ተደማምረው ንግግሩን ማራኪ፣ አዝናኝና፣ አስደሳች እንዲሆን አድርገውለታል።

ይህን እንደምሳሌ ሳነሳው የፈለግኩት ለኮሌጅ ሰዎች ወይም ለሸቀጥ አመላላሽ ድርጅት ባለቤቶች ልዩ የሆነና የማይታወቅ ነገር በመሆኑ ሳይሆን አንድ ሰው ሰዎች ንግግሩን የማዳመጥ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችለውን ኃይል እንዴት ሊያገኝ እንደሚችል ለማሳየት ነው...ከሁለቱ ማነው ለመረዳት በሚያስቸግርና በማያሻማ አገላለፅ ሃሳቡን በቀላሉ ለመገንዘብ የሚያስችልና እርግጠኛ ሁኔታን የሚፈጥር ንግግር የማድረግ ልምድ እንዳለው ያሳየው?

ይህ የንግግር መመሪያ ለአንድ ንግግር አድራጊ በጣም አስፈላጊው ነውና በደንብ እንድናውቀውና እንዲጣጣም ሌሎች ተጨማሪ ማሳያዎችን መመልከት አለብን። ከአሁን በኋላም በጭራሽ እንደማትረሱትና ፈፅሞም ችላ የማትሉት ነጥብ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን።

ለምሳሌ ማርቲን ሉተር ህፃን በነበረ ጊዜ «በጣም አስቸጋሪና በጥባጭ» ልጅ እንደነበረ ይታወቃል። ለመስማት አዲስ ትኩረትን የሚስብ የሚሆነው ወይስ የማርቲን ሉተር መምህር «ማርቲን በጠዋቱ በትምህርት ክፍለ ጊዜ ብቻ አስራ አምስት ጊዜ ያህል ይቀጣና ይገረፍ እንደነበረ ተናግሮ ነበር» ብሎ መናገሩ ነው የተሻለ የሚሆነው፡

«አስቸጋሪና በጥባጭን» የመሳሰሉ ቃላቶች ትኩረትን ለመሳብ ያላቸው ኃይል እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። እንዲሁም ስለቅጣቶቹና ግርፋቶቹ ብዛት ለማዳመጥ ቀላልና የሚስብም አይደለም?

በፊት ስለ አንድ ሰው የህይወት ታሪክ ይፃፍ የነበረው ጠቅለል ባለና ሁሉም በሚያውቋቸው ነገሮች ዙሪያ ባጠነጠነ መልኩ ነበር። አርስቶትል ይህን «የደካማ አዕምሮዎች መጠለያ» ብሎ ይጠራው እንደነበር ይታወሣል። ሆኖም አንድ ሰው የህይወት ታሪኩ በአዲሱ የአፃፃፍ መንገድ ግን ስለዚህ ሰው የሚያስረዱና ሚገልፁ ተጨባጭ ሃቆችን ቁልጭ አድርጎ በማሳየት መግለጽ ነው። የቀድሞውን የአፃፃፍ መንገድ ተከታይ የሆነ የህይወት ታሪክ ፀሐፊ ... ጆን ዶ «ደሃ ግን ታማኝ ከሆኑ ቤተሰቦች» ነበር የተወለደው ብሎ ይፅፋል። የአዲሱ ህይወት ታሪክ አፃፃፍ መንገድ ተከታይ ግን «የዶ አባት ለልጁ አዲስ ጫማ ለመግዛት የሚያስችል ምንም አቅም ስላልነበረው ጆ ቀዝቃዛው የበረዶ ወራት በሚጀምርበት ጊዜ በምትቀደደውና አሮጌ በሆነችው ጫማው ከሚገባው

በፍተኛ ቅዝቃዜ እግሩን ለመከላከል አሮጌ ጫማ ዙሪያውን በወፍራም ሸራ በመጠቅለል ለመጫማት ይገደድ ነበር፡፡ ነገር ግን የጆ አባት ያንን ያህል የነጣ ደሃ የነበረ ቢሆንም በጭራሽ ወተት ውስጥ ውሃ እየደባለቀ የሚሸጥ ያልነበረና ፈረሱንም ከሚችለው በላይ በመጫን ጥቅም ማግኘትን ፈፅሞ የማይቀበል ነበረ፡፡ ያ የሚያሳየው ቤተሰቦቹ «ደሃ ግን ሐቀኞች» እንደነበሩ ነው፡፡ አይደለም? . . . ታዲያ

ይህኛው የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መንገድ ከመጀመሪያው «ደካማ ግን ሃቀኛ ! ወይም ተጋኖ ያልቀረበ» የአፃፃፍ መንገድ የተሻለና አስደሳች አይደለምን?

ስለዚህ አዲሱ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ ለዘመናዊ የህይወት ታሪክ ፀሐፊዎች የሚሰራ ከሆነ ለዘመናዊ ንግግር አድራጊዎችም ይሰራል፡፡

ሌላ አንድ ተጨማሪ ማሳያ እንውሰድ፤ አንተ በአንድ ቀን ውስጥ በኒጋራ ፏፏቴ የሚገባውን ከፍተኛ የፈረስ ጉልበት ያለው ውሃ ጥቅም ላይ ቢውል ሊገኝ የሚችለውን ሃብት በመግለፅ በኒጋራ ወንዝ እየባከነ ያለውን ሐይል ምን ያህል ከፍተኛና አስደንጋጭ እንደሆነ ለመናገር ፈልገሃል እንበል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ንግግር እንደምታደርግ ገልፀሃል እንበልና ቀጥለህ ይህን የሚባክነውን ኃይል ጥቅም ላይ ማዋል ቢቻል የሚገኘው ትርፍ በህይወት ለመኖር ለሚያስፈልጉ መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች ቢውል የአሜሪካንን ህዝብ በሙሉ ማልበስና መመገብ ይቻል ነበር በማለት ብታክልበት ንግግርህ ትኩረትን የሚስብ፣ አስደንጋጭ፣ አስገራሚ፣ ስሜትን የሚነካና ቀስቃሽ የሆነ ንግግር መሆን ይችላል? አይደለም? . . . አይሆንም?

ይልቅ ከዚህ በታች ከዴይሊ ሳይንስ ቡሌቲን የወሰድነው የኤድዊን ኤሶ ስሎሶን በኒጋራ ፏፏቴ ስለሚባክነው ኃይል ያደረገው ንግግር እጅግ በተሻለና በላቀ ሁኔታ ትኩረትን የሚስብ፣ ስሜትን የሚነካ፣ በሚያስገርም ወይም በማስደንገጥ ስሜትን የሚቀሰቅስና የሚገፋፋ ንግግር ነው እንመልከተው፡፡

> በዚህ አገር ውስጥ በሚሊዮኖች ሚቆጠሩ ሰዎች በድህነት ውስጥ አንዳሉና በቂ በሆነ ሁኔታ እንኳን እራሳቸውን መመገብ እንደማይችሉ በቂ በሆነ ሁኔታ ተነግሮናል፡፡ ሆኖም እዚህ ከኒጋራ ወንዝ በአንድ ሰዓት ውስጥ ብቻ የ250,000 ዳቦዎች ዋጋ ያለው ኃይል ይባክናል፡፡ በ600,000 ትኩስ እንቁላሎች በመጋገር እጅግ በጣም ትልቅ የሆነ የእንቁላል ቂጣ በእያንዳንዷ ሰዓት ውስጥ እያጣን መሆኑን . . . እስቲ ምን ማለት እንደሆነ በህሊናችሁ ተመልከቱት፡፡ የካርኒጌ ቤተ መፅሀፍት ከዚህ ወንዝ ሊገኝ ከሚችለው ትርፍ ምርጥና ቆንጆ በሆኑ መፃሃፍቶች ለመሙላት ብናስብ በአንድ ወይም በሁለት ሰዓት ከወንዙ በሚገኝ ገቢ ሙሉ በሙሉ ማሟላት እንችላለን፡፡ ንግግሩ ሊገመት ከሚችለው በላይ እጅግ አስደናቂ፣ አስገራሚ፣ አስደንጋጭ እና ሐሳብንም የሚያስለውጥ ነው፡፡ ንግግሩ ለአብዛኛው ተሰብሳቢ የሚስብ፣ የሚያስደነግጥና የሚያስገርም እንደ ነበረ ሁሉ ወንዙን ለአገልግሎት ለመጠቀም ብዙ ወጪ ይፈልጋል በማለት ላለመጠቀም ችላ ብለው የነበሩ ሰዎችን ወጪው እንዳያሳስባቸው የሚያደርግ ንግግር ነው፡፡ ከወንዙ የሚገባውን ኃይል ለመጠቀም ወጪ ማውጣት ገንዘብ መጣል ነው ብለው ሽንጣቸውን ገትረው ይከራከሩ የነበሩ ሰዎችም ይህን ወንዝ አለመጠቀም ገንዘብ መጣል ነው በማለት እንዲገቱ የሚያደርግ ንግግር ነው፡፡

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## የቃላት ችሎታህን እና ክምችትህን አሳድግ

አንድ ምንም አይነት ስራ የሌለው እንዲሁም በባንክ ተቀማጭ የሆነ ገንዘብ የልነበረው እንግሊዛዊ ሰው ስራ ለመፈለግ በፊላደልፊያ ጎዳናዎች ላይ ወዲያና ወዲህ ይንከላወስ ነበር:: በድንገትም ስራ ማግኘትና መቀጠር ይችል እንደሆነ በማሰብ ለመጠየቅ ከገባባቸው ቢሮዎች መካከል አንዱ በከተማዋ ውስጥ ታዋቂ የንግድ ሰው ከሚባሉት አንዱ የሆነው የሚር ፖል ጊቦንስ ቢሮ ነበር:: በወቅቱ የእንግሊዛዊው አለባበስና ገፅታ ስራ ለመቀጠር ወይም ለመፈለግ የመጣ ሰው ነው ብሎ ለማሰብም ሆነ ለመገመት የሚያስቸግር ዓይነት ነበር:: ሚር ጊቦንስም ወደ ቢሮው ውስጥ የዘለቀውን የተጎሳቆለ እንግዳ ሰው በጥርጣሬ ነበር ያየው:: የለበሳቸው ልብሶችም ለብዙ ጊዜ የተበሱ በመሆናቸው የነተቡና የተቀዳደዱ ነበሩ:: ከሁሉም በላይ በሆነ ሁኔታ ግን የእንግሊዛዊው የተጎሳቆለ ሰውነትና የገረጣ ፊት ከፍተኛ በሆነ የኑሮ ችግር ውስጥ እንዳለ የሚያሳይ ነበር:: ሚስተር ጊቦንስም ሰውየው ስራ ለማግኘትና ለመቀጠር መምጣቱን ባወቀበት ጊዜ አንድም ለንስቋላው ሰው በማዘን አንድም በጥያቄው ከፍተኛ የሆነ ግርምት ተፈጥሮበት እስቲ ልየው በማለት ቃለመጠይቅ አደረገለት::

በመጀመሪያ ለጥቂት ሰከንዶች ብቻ ላናግረው ብሎ ነበር ያሰበው:: ግን ጥቂት ሰከንድ ጥቂት ደቂቃዎችን ስትወልድ ጥቂት ደቂቃዎች ደግሞ ወደ አንድ ሰዓት ሲያድጉ እንኳን የሚያደርጉትን ውይይት አላለቀም ነበር:: ንግግራቸው ያለቀው ሚር ጊቦንስ የፊላደልፊያው ዲይሎን ሪድ ኤንድ ካምፓኒ ስራ አስኪያጅ ለሆነው ለሚር ሮላንድ ቴይለር ስልክ ደውሎ ማናገር ሲጀምር ነበር:: እናም በዚያ ከተማ ከፍተኛ እውቅና ያለው የባንክ ሰው የሆነው ማር ቴይለር ወዲያውኑ ያንን እንግዳ የሆነ ሰው ምሳ በመጋበዝ የድርጅቱ ቋሚ ተቀጣሪ በመሆን ስራ ማግኘቱንና መቀጠሩን ነበር የገለፀለት::

ይሄ ሰው እንዴት በአጭር ጊዜ ውስጥ የገረጣና የተጎሳቆለ ገፅታ ይዞ የተቀዳደና የነተቡ ልብሶችን ለብሶ እንደዚያ ያለ ውጤት ያገኘበትን ግንኙነት ለመፍጠር ቻለ?

የዚህን ሚስጢር በአንድ አጭር አገላለጽ ውስጥ ልናገኘው እንችላለን። የእንግሊዝኛ ቋንቋ አነጋገር ችሎታው እና የቃላት አጠቃቀሙ!

እንግሊዛዊው ለሥራ ጉዳይ ወደ አሜሪካን መጥቶ ያላሰበው ችግር ውስጥ የገባና ያለምንም ገንዘብ፣ ረዳት እና ጓደኛ ብቻውን የቀረ የኦክስፎርድ ሰው ነበር። ነገር ግን የአፍ መፍቻ ቋንቋው በሆነው እንግሊዝኛ በሚገርሙ ቃላቶች ጣምና የአነጋገር ዘይቤ የሚያወራ ስለነበረ አድማጩ ሰው የተበጣጠሰና የነተበ ኮቱን፣ ያረጁና ተቀዳደዱ ጫማዎቹን፣ የገረጣ ፊቱን እና ያልተላጨው ፂሙ ላይ ትኩረት እንዳያደርግና ወዲያውኑም እንዲረሳው ነበር ያደረገው::

የሰውየው ታሪክ አስገራሚ ቢሆንም እንኳ አንድ ሊታለፍ የማይችል ሃቅንም የሚያሳይ እውነት በእያንዳንዱ ቀን በምንናገራቸው ነገሮች

እንደምንመዘንና እንደምንገመት ያሳየናል:: ከአፋችን የሚወጡት ቃላቶች የውስጣችንን ማንነት በመግለፅ የሚያሳዩ ናቸው:: ሲቀጥሩን ለሚፈልጉ ድርጅት ያለንን እውቀትና፣ ክህሎት፣ ተክለ ሰውነት፣ ስብዕናና ባህል ፍንትው አድርገው ሊያሳዩ የሚችሉ ቁልፍ መሳሪያዎች ናቸው::

እኛ በዚህ ዓለም ላይ ግንኙነት ለማድረግ የሚያስችሉን አራት ነገሮች ብቻ ናቸው ያሉን . . . እኔና አንተ በመመዘንና በመለካት መታወቅ የምንችለው በአራት ነገሮች ነው:: በምናደርጋቸው ነገሮች፣ በምንመስላቸው ነገሮች፣ በምንናገራቸው ነገሮችና፣ በአነጋገር ዘይቤያችን ወይንም ለዛችን ነው:: ይሁንና እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ ለነዚህ አራት ነገሮች ከፍተኛ የሆነ ትኩረትን ባለመስጠትና በግዴለሽነት ተደጋጋሚ የሆኑ ስህተቶችን ይፈጽማሉ:: ብዙ ሰዎችም በትምህርት ዓለም ባሉበት ወቅት ብዙ ቃላቶችን በማጥናትና በማወቅ በንግግራቸው ውስጥ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን ቃላቶች አገባብ፣ ትርጉም፣ እንዲሁም ትክክለኛነታቸውንና ተገቢነታቸውን መረዳትና ባለው ሁኔታ መናገር መቻል ተቀባይትን፣ ተሰሚነትን እና ታማኝነትን በቀላሉ በአድማጫቸው ዘንድ ማግኘት እንደሚችሉ አይገነዘቡትም::

ይህን ሃሳብ ለመግለፅ የሚረዳ አንድ የአገራችን አባባል አለ «ከአነጋገር ይፈረዳል ከአያያዝ ይቀደዳል» አነጋገራችን ምን ያህል የምንፈልገውን ጉዳይ ለማሳካት ወይም ለማግኘት ወሳኝ እንደሆነ የሚያሳይ አባባል ነው፡ እንግሊዛዊው ሰው የመጣው ለብዙ ጊዜ የቢሮ አነጋገርና ቃላትን ሁሉም ይጠቀምበት ከነበረው የሥራ ዓለም በመሆኑ የአነጋገር ዘይቤው ለየት የማይልና ለማንኛውም አይነት የስራ ግንኙነት ተስማሚና ተመራጭ የመሆኑ ጉዳይ ሲያስገርመን አይገባም:: እንደውም የቃላት አጠቃቀሙና እሰካኩ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የቃላት አጠቃቀምና አሰካክ እንዲሁም አለዋወጥ መሰረታዊ ህጎች በላይ የሳቀና የዳበረ ነበር::

ከዓመታት በፊት በአንድ ሰዓት ላይ በሮም በሚገኝ አንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ በሃሳብ ተውጬ ቆሜ አንድ የማላውቀው እንግሊዛዊ ኮሎኔል ወደ እኔ በመምጣት እራሱን ካስተዋወቀኝ በኋላ ስለ ፓሳዴና ከተማና በዛ በቆየበት ጊዜ ስላጋጠሙት ነገሮች እያወራን ሶስት ደቂቃዎች እንኳን ሳይሞሉ «አንተ ነበረ» «እኔ አደረገ» የንግግር ስህተቶችን ፈፅሞ ነበር::

እሱ እንዳጫወተኝ ከሆነ ሁሌም እንደሚያደርገው የዛን ዕለት ጧት ልክ ከእንቅልፉ እንደተነሳ ጫማውን ካፀዳ በኋላ በጫማው ላይ በቀላሉ ሊታይ የማይችል ነጭ ፕላስተር በዛን ዕለት ለሚያገኛቸውና ለሚተዋወቃቸው እንግዳ የሆኑ ሰዎች ማስታወሻነት ይለጥፍ ነበር:: ነገር ግን በንግግሮቹ ውስጥ ያሉትን የቃላትና የአነጋገር ግድፈቶች ለማረምና በትክክለኛው መንገድ ለማውራት ምንም ያደረገው ጥረትና ሙከራ አልነበረም::

ለምሳሌ ለሱ ከአንዲት ሴት ጋር በሚያወራበት ጊዜ ባርኔጣውን ያለማውለቅ እጅግ አሳፋሪ ተግባር ነው:: ነገር ግን የአነጋገርም ሆነ የቃላት ግድፈቶች ያሉበት ንግግር መናገሩ ምን ያህል ለአድማጭ ጆሮ ለቅጣጭ እንደሆነና እንደሚያሳፍር የተገነዘበውም ሆነ የተረዳው አይመስልም:: ዶ/ር ቻርለስ ደብሊው ኤሊኖት ለሶስተኛ ጊዜ የሃርቫርድ ፕሬዝዳንት ሆኖ ሲመረጥ

ሆኑ ሴቶች በትምህርታቸው ሊማሩና ሊያውቁት የተናገረው ነገር «ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በትምህርታቸው ሊማሩና ሊያውቁት የሚገባው ዋና አስፈላጊ የሆነ ነገር የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ጥርት አድርገው በደንብ ማወቅና መናገር መቻላቸውን እርግጠኛ መሆን መቻል እንዳለባቸው ነው» ቋንቋን የማዳበር አስፈላጊነትን ልንረዳው የሚገባንና በደንብ ትኩረት ሰጥተን ልናሻሽለው የሚገባን ነገር ነው::

ግን ቃላቶችን በደንብ አጥንቶ ለማወቅና በተገቢው አኳኋን አስፈላጊ በሆኑ ጊዜያቶች በንግግሬ ውስጥ ለመጠቀም ያለኝ ብቃት እንዴት ነው? ብለን የምንጠይቀውን ያህል ነው ቃላቶችን በትክክለኛው አግባብና ውበት ባለው አኳኋን በምንናገራቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ለማወቅ ሚስጥር የማይሆነው:: አብርሃም ሊንከን አስደናቂ የሆነ ስኬት ላይ ለመድረስ የተጠቀመበት ይህን እድል ነው:: ማንም አሜሪካዊ እንደ አብርሃም ሊንከን የተለያዩ ቃላቶቹን በሚናገረው ንግግር ውስጥ በተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በማድረግ ተወዳዳሪ በሌለው መልኩ ሙዚቃዊ ቃናን ትርጉሞችን እንዲሰጡ በማድረግ «ማንንም በማያስቀይምና ሁሉንም በሚያስደስት» ሁኔታ የተላበሰ ንግግር ሙሉ ሲሰራና ሲደክም ከሚውል አናጢ ንግግሩን ያደረገ ሰው ለምን ቀኑን ዘመናዊ ትምህርት ወይም ላቅ ያለ ልምድ ከሌላት እናቱ አባትና ምንም አይነት እጅግ አስገራሚ የሆነ የቃላት የተወለደው አብርሃም ሊንከን . . . የዚህ ዓይነት እጅግ አስገራሚ የሆነ የቃላት እውቀትና ላቅ ያለ አጠቃቀም ችሎታ በተፈጥሮ ያገኘው ደስታ ነው ማለት ይቻላልን? የተፈጥሮ ስጦታ ነው ብሎ ለማለት ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም::

ለአሜሪካን ኮንግረስ በተመረጠ ጊዜ ህጋዊ የትምህርት ማስረጃውን በዋሽንግተን ባቀረበበት ወቅት ከትምህርት ማስረጃው ላይ አንዱን ትምህርት በተመለከተ የተጻፈው «አላስፈላጊ» በሚል ነበር:: ሊንከን በህይወቱ የእንግሊዝኛን ቋንቋ የተማረው ለአስራ ሁለት ወራት እንኳን ለማይሆን ጊዜ ነበር:: እናም ቋንቋን ከየት ተማረው? የሚለው ጥያቄው የሊንከን አስተማሪ ማን ነው? ቋንቋን ከየት ተማረው? የሚለው ይሆናል:: በፎረስት ኦፍ ኬንተኪ ካሌብ ሃዜል እና ዘካርያ ቢርኔይ አዜል ዶርሴይ እና እንድሪው ክራወፎርድ በኢንዲያ ግዛት በምትገኘው ገጠራማዋ ፒገን ክሪክመንደር በሚገኝ አንድ ትምህርት ቤት የአበርሃም ሊንከን አስተማሪዎች የነበሩ ናቸው:: ሁሉም የሊንከን አስተማሪዎች ወደር በሌለው የንግግር ችሎታው የተለያዩ አስተዋፅዖዎችን ያበረከቱ ነበሩ::

ሊንከን በተለይም ለቋንቋና ስነ-ፅሁፉ መዳበር ምክንያት የሆኑትና ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነትና ፍላጎት እንዲያድርበት ያደረጉት እነዚህ አስተማሪዎችና የመኖሪያ መንደሩ በሆነው የኢሊኖይስ ስምንተኛው ጎዳና ይኖሩ ከነበሩ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ ጠበቆችና ተከሳሾች ጋር የነበረው የጠበቀ ግንኙነትና ጓደኝነት እንዲሁም ያደረጋቸው የነበሩ ውይይቶች ነበሩ:: በወቅቱ የመንደሯ ነዋሪዎች አስደናቂ የሆኑ ቃላትን እንዲሁም ንግግሮችን ያካበቱና የሚያደርጉ የነበሩ ባይሆንም ሊንከን ግን ከነሱ ጋር በነበረው ግንኙነት ምክንያት የኋላ ኋላ ላይ ከፍተኛ የሆነ የቃላት እውቀትና አጠቃቀም፣ የአረፍተ ነገር አመሰራረት፣ እንዲሁም የንግግር አደራረግ ችሎታን እንዲጎናፀፍ አስችሎታል:: . . . ሊንከን በእውቀት ከእሱ እኩል ከሆኑ ወይንም ከሚያንሱ ሰዎች ጋር ወዲያና ወዲህ በማለት ጊዜውን በጭራሽ በዋዛ ፈዛዛ የሚያጠፋ ሰው አልነበረም:: ብዙ ጊዜ

ጓደኝነትን የሚፈጥረው ወይም ትውውቅ የሚፈጥረው በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚገኙ ልሂቃን ጋር ነበር:: ከዘፋኞች፣ ከገዘኛ ገጣሚዎች፣ ከፀሐፊዎችና፣ ከመሳሰሉት ጋር ነበር::

በበርንስ ግጥሞች ላይ ለማስተማሪያ የሚሆን የጥናት ፅሁፍ ፅፏል:: የባይሮንስንም የግጥም መፅሐፍ በሁለት ኮፒ በማባዛት አንዱን በቢሮው አንዱን በቤቱ በማስቀመጥ ያነብ ነበር:: በተለይ በቢሮው ያስቀመጠውን መፅሐፍ ደጋግሞ ያነበው ስለነበረ ገፆቹ በጣም የተገነጣጠሉ በመሆናቸው መፅሐፉን ለማንሳት የማይመች ነበር:: የአሜሪካን ፕሬዝዳንት ሆኖ ኋይት ሐውስ ከገባ በኋላና በአሜሪካ የእርስበርስ ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ የሆነ የስራ ውጥረት ውስጥ በነበረበት ጊዜም ፊቱ ገርጥቶና ሰውነቱ ዝሎ ሁሉም ከመተኛቱ በፊት የግጥም መፅሐፍ ለማንበብ ጊዜ የሚሰጥ ሰው ነበር:: አንዳንዴም እኩለ ለሊት ላይ ተነስቶ መፅሀፉን በመግለጥ በጣም ያስደሰቱትንና ውስጡን ያረኩትን ጥቅሶች ደግሞ ደጋግሞ ያነብ ነበር:: የመዳከም ስሜት ሲሰማውም ከአልጋው በመነሳት በለሊት ልብስና በነጠላ ጫማው ወደታችኛው ምድር ቤት በመውረድ ፀሐፊውን እንድታነብለት ለማድረግ እየተዘዋወረ ይፈልጋት ነበር:: በኋይት ሐውስ ውስጥ ባሳለፏቸው ጊዜዎች ውስጥም የሼክስፔየርንም ረጃጅም ልብወለዶች ተዋናዮችን ለመተችትና የራሱንም የግል ትርጓሜ ለመተርጎም የሚያስችለውን ዘቲ ጊዜ በኋይት ሐውስ ቆይታው ለማግኘት ችሎ ነበር:: «እኔ የሼክስፒየርን ስራዎች ደጋግሜ አንብቤአቸዋለሁ» ብሎ ነበር ሊሃኬት በፃፈለት የግል አስተያየት ለምሳሌ ጆርጅ ሶስተኛው፣ ሄነሪ ስምንተኛው፣ ሃምሌት እና በተለይም ማክቤዝ ደጋግሜ ያነበብኳቸው የሼክስፒር ስራዎች ሲሆኑ ማክቤዝን የሚያህል ግን የለም::

ሊንከን ለጥቅሶች ከፍተኛ የሆነ ስሜትና ትኩረት ነበረው:: ጥቅሶችን ማስታወስ መቻልና ወይም ለሰዎች ደግሞ መናገር ብቻ ሳይሆን ወደ አጭር ስነ-ፅሁፎች ይለውጣቸው ነበር:: ሊንከን የፃፈውን አንድ ረጅም ግጥም በእህቱ ሰርግ ላይ አንብቦላቸው ነበር:: ሊንከን በጎልማሳ ሰው እድሜ ላይ በደረሰ ጊዜም የዕለት የማስታወሻ መፃፊያ ደብተሩ ሃሳቦች ሲመጡለት ወዲያው ይፅፋቸው በነበሩ የግጥምና የፅሁፍ ሃሳብ ረቂቆች ተሞልቶ ነበር:: ይሁንና ሊንከን በጣም ዓይናፋር ሰው ስለነበረ እነዚህን የፈጠራ ሃሳቦች የመጀመሪያ ፅሁፎች ሌላው ቀርቶ ለልብ ጓደኛው እንኳን እንዲያየው የሚፈቅድ አልነበረም::

«ይህ እራሱን በራሱ ያስተማረ ሰው» በማለት ነበር ሮቢንሰን የተባለ ሰው ሊንከንን የፊደል ሰው ብሎ ለመግለፅ የተጠቀመው «አእምሮውን አዲስ በሆኑ ባህሎችና እሴቶች ባዳበረ መጠን እውቀትና ችሎታ ሊያካብትና ሊያዳብር የቻለው . . ፕሮፌሰር ኤመርቶን ስለ ኤራስመስ እንዴትና በማን ቢማር ነው? እንዲህ ያለ እውቀትና ችሎታ ሊኖረው የቻለው ተብሎ ሲጠየቅ እንደተናገረው. . . » እሱ በትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርትን የተማረና እውቀትን የቀሰመ አልነበረም:: ነገር ግን አንዱና ብቸኛ ዘዴው ሁልጊዜም የሚሳካ በማይሆነው እራስን በራስ በማስተማር መንገድ ከፍተኛ ጥረትና ልፋት በሚጠይቅ ሁኔታ በማያቋርጥ ጥናትና ፋታ በሌለው ንባብ ነው የተማረው ብሎ ነበር:: ይህን እንደ ወዛደር የነበረ በፒንን ክሪክ እርሻ ቦታዎች በቆሎ በመፈልፈልና በስጋ ቤቶች ውስጥ የሸክም ስራ በመስራት በቀን 31 ሳንቲም ይከፈለው የነበረ ሰው እስከዛሬ ድረስ

በሰው ልጅ ከተደረጉ ንግግሮች ሁሉ የላቀውንና እጅግ በጣም ውብ የሆነውን ንግግር በጌትስብርግ አደረገ። በአሜሪካን የእርስ በርስ ጦርነቱ ሰባት ሺህ ሰዎችም ሞተዋል።

ቻርለስ ስምነር እንደተናገረውም «የጌትስበርግ የሊንከን ንግግር ሊንከን ከዚህ ዓለም ካለፈ ከረጅም ጊዜ በኋላም እንኳን የሊንከን ንግግር የሚኖርና የሚታወስ ሲሆን የዚህ አስከፊ የርስ በርስ ጦርነት ትዝታ ግን ከአጭር ጊዜ በኋላ ይጠፋል፣ ይረሳል። ወደፊትም አንድ ቀን ይህ የእርስ በርስ ጦርነት እንዲታወስ የሚያደርገው ምክንያት ቢኖር የሊንከን ንግግር ይሆናል» የዚህን ትንቢት መድረስ ወይም ትክክለኛ መሆን የሚጠራጠረው ማነው? ኤድዋርድ ኤቨርት በጌትስበርግ ለሁለት ሰዓታት ያህል ንግግር አድርጎ ነበር የተናገራቸውን ነገሮች ግን ማንም የሚያስታውሳቸው የለም። ከዚያች ጊዜ ጀምሮ ተረስተዋል! አብርሃም ሊንከን ግን የተናገረው ከሁለት ደቂቃ በታች በሆነ ጊዜ ውስጥ ነበር።

በወቅቱ አብርሃም ሊንከን ይህንን አጭር የሆነ ታሪካዊ ንግግር ባደረገበት ወቅት አንድ ፎቶግራፍ አንሺ ፎቶ ለማንሳት በጊዜው የነበረውን ቀርፋፋና ጓላቀሩን ካሜራ ገና በማዘጋጀት ላይ እንዳለ ሊንከን ታሪካዊውን የጌትስበርግ ንግግሩን በመጨረስ ሳይሳካለት ቀርቷል። ሊንከን ያደረገው ይህ ታሪካዊ ንግግር በብራና ላይ በመዳብ ተፅፎ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ምን መስራት እንደሚቻል የሚያሳይ ምሳሌ እንዲሆን በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ቤተመፅሐፍት በክብር ተቀምጧል። ንግግሩም ዘመን በማይሽረው ሁኔታ የህዝብ ንግግር አቀራረብ ትምህርት ተማሪዎች ሲታወስ የኖረና የሚኖር ነው።

> ከሰማንያ ሰባት ዓመታት በፊት አባቶቻችን በሁሉም ሰዎች የእኩልነት እና የነፃነት መብቶች መከበር ፅኑ መሰረት ላይ የተገነባች አገርን በዚህ አህጉር ውስጥ መስርተዋል። አሁን ግን እኛ ከፍተኛ በሆነ የእርስ በርስ ጦርነት በመታመስና በመተላለቅ ላይ ነን። ይሄ ጦርነት አባቶቻችን የዚህች አገር ህልውና ፅኑ መሰረት አድርገው ያቆሙት የሁሉም ሰዎች የእኩልነትና የነፃነት መብቶች የማስከበርና ያለማስከበር የማረጋገጥና ያለማረጋገጥ ጉዳይ ነው። በዚህ ምክንያትም በትልልቅ የውጊያ ሜዳዎች ላይ እርስ በርሳችን ተዋግተናል። በነዚህ የውጊያ አውድማዎች የተሰውትንና የዚህን አገር ቀጣይነት ለማረጋገጥ ዋጋ ለከፈሉ ጀግኖች የመጨረሻ ማረፊያ ቦታቸው ሆኖ በክብር የወደቁባቸውን መሬቶች መታሰቢያ ልናደርግላቸው ይገባል። ይህን ማድረጋችን ግን ትክክለኛና ተገቢ የሚሆነው ለነሱ ለሃገራችን ህልውናና ቀጣይነት የህይወት መስዋዕትነትን ለከፈሉ ጀግኖች ዛሬ ይህን ማድረጋችን እኛን ታላቅ የሆነ ተግባርን ያደረግን ለዚህች አገር የተቀደሰ ስራና ታላቅ ታሪክ የሰራን ሊያደርገን እንደማይችል እስከተገነዘብን ድረስ ብቻ ነው። ለዚህች አገር ህልውናና ቀጣይነት የታገሉና መስዋዕትነትን የከፈሉ ጀግኖች የተሰውትም ሆነ በህይወት ያሉት እኛ ልንጨምረው ወይም በማይቻለን ሁኔታ የተቀደሰ ታሪካዊ ስራን በዚህች ምድር ፈፅመዋል። እኛ/ አሁን የምንለውን ወደፊት ዓለም ብዙም የሚያውቀው አይሆንም። ከረጅም ግዜም በኋላ አያስታውሰውም። ነገር ግን እነዚህ ጀግኖች እዚህ ቦታ የሰሩትን ስራ ማንም ሠው በጭራሽ ሊረሳው አይችልም ጀግኖች ወገኖቻችን የተሰውበት ይህ ቦታ መታሰቢያነቱ ለነሱ ሳይሆን እነሱ መስዋዕትነተን ከፍለው የጀመሩትንና ያልተጠናቀቀውን የተቀደሰ ተግባራቸውን ወደፊት ማስቀጠል መቻል ላለብን ለኛ በህይወት ላለነው ሰዎች ነው። ከፊታችን

ትልቅ የሆነ ስራ ለሚጠብቀን ለኛ ነው መታሰቢያ ሊሆን የሚገባው:: እነሱ ዐበይ ጉዳይ እኛም ከፍተኛ የሆነ ክብርና ፍቅር ልንሰጥ ይገባናል:: ዛሬ እዚህ የመጨረሻውን የህይወት መስዋዕትነት በመክፈል የክብር ሞትን ለተቀበሉበት ቆመን እነሱ በህይወት መስዋዕትነትን የከፈሉት ያለምንም ምክንያት አለመሆኑን ማረጋገጥ አለብን:: ያው የኔ አገር ከእግዚአብሄር በታች አዲስ የሆነ የነፃነት መብት የሚከበርበት እና የህዝብ በህዝብ ለህዝብ የሆነ መንግስት ከዚህች ምድር ላይ ፈፅሞ የማይጠፋባት ለማድረግ ነው::

አብርሃም ሊንከን የዚህን የንግግሩን መዝጊያ ለረጅም ጊዜ በሚኖሩና ፍፁም በማይረሱ ቃላቶች ተናገረ ተብሎ ነው የሚወደሰው:: ወይም የሚታሰበው:: ግን የእሱ ስራ ነበር? የህግ ሙያ አጋሩ የነበረው ሄንድሮን ከብዙ ዓመታት በፊት የቴዎዶር ፓርከርን መፅሃፍ ከፒ አድርጎ ሠጥቶት:: ሊንከንም ይህን መፅሃፍ አንብቦ «የሚለው አረፍተ ነገር ላይ አስምሮበት ነበር ምናልባትም ቴዎዶር ፓርከርም ይህንን ሃሳብ ቁብስት ከአራት አመታት በፊት ለሐይን በሰጠው አስደናቂ መልስ ላይ ተናግሮት ከነበረው የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጀምስ ሞንሮውስ ንግግር «የህዝብ መንግስት፣ በህዝብ የተመሰረተ፣ ለህዝብ የተመሰረተ እና ተጠያቂነቱ ለህዝብ የሆነ» ከሚለው ተበድሮ ሊሆን ይችላል:: ጀምስ ሞንሮውስ ከማን ይሆን ይህን አገላለፅ የወሰደው? ሞንሮው ከመወለዱ ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ዋክሊፍ በተረጎመው መፅሃፍ ቅዱስ መቅድም ላይ «ይህ መፅሃፍ ቅዱስ የህዝብ በህዝብ ለህዝብ ለሆነ መንግስት ነው» የሚል ፅፎበት ነበር:: ዋክሊፍ ከመፈጠሩ እጅግ ረዥም ጊዜ በፊት ከእየሱስ ክርስቶስ ልደት አራት መቶ ዓመታት በፊት ክሊዮን ለአቴንስ ሰዎች ስለአንድ መሪ አድርጎ በነበረው ንግግር «የህዝብ፣ በህዝብ፣ ለህዝብ» የሆነ መሪ በማለት ቃሉንና አባባሉን ተጠቅሞበት ነበር:: እና ከየትኛው? ከምን አይነት? ጥንታዊ የሆነ መረጃ ክሊዮን ይህን አባባል የወሰደው? የሞላው ጥያቄ በጥንታዊው የኋላ ታሪካችን ጉምና ጨለማ የተዋጠ ነው:: ያለው አዲስ የሆነ ንግግር ምንም እንኳን በጣም ትንሽ ቢሆንም! ያችኑም ለማወቅ ምን ያህል ታላላቅ የሆኑ ንግግር አድራጊዎች እንኳን በመፅሃፍ ላይ ተጣብቀው በማንበብ እንደሚቃርሙ ማየት እንችላለን:: መፅሐፎች አንድ ሚስጢር ስላላቸው በየጊዜው አዳዲስ ቃላቶችን በማወቅ የቃላት እውቀቱን የሚያሰፋና የሚያካብት ሠው አእምሮውን ታላቅ የሆነ ስነፅሁፍን እንዲያበረክት በቃላት በማርጠብ እየሞረደው ነው:: «ይህ ሰው ልጅ ህይወት አጭር በመሆኑና ከፊት ለፊቴ የተደረደሩትን ብዙ ዘመናት የኋላ ታሪኮች በሙሉ ለማየትና ለመደሰት ተስፋ እንደሌለኝ ሳስበው የሚሰማኝ ስሜት ነው»

ብራይት በአስራ አምስት አመቱ ነበር ትምህርቱን በመተው በአንድ የጥጥ መዳመጫ ተቀጥሮ መስራት የጀመረው:: ከዛ በኋላ በድጋሚ ወደ ትምህርቱ ለመመለስ ምንም አይነት እድል አላገኘም ነበር:: ሆኖም እሱ ትውልድ አጅግ ጎበዝ ተናጋሪዎች ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ለመሆን የበቃ ነበር:: በተለይም የእንግሊዝኛ ቋንቋንና ቃላትን ወደር የለሽ በሆነ ሁኔታ በመቆጣጠርና ለፈለገው ሃሳብ መግለጫነት መጠቀም በመቻሉ ባለዝና ሆኖ ነበር:: እሱ ሚያነበውንና የሚያጠናውን በማስታወሻ መያዣ ደብተሩ ላይ በመፃፍ የሚያጠናና የባይሮንን እና ጎሚልተንን፣ የዎርድስዎርዝ እና የዊይትይን፣ እንዲሁም የሼክስፒርንና የሼሊን ረዣዥም የግጥም ፅሁፎች በቃሉ በማስታወስ ያነበንብ ነበር::

በተጨማሪም የቃላት ክምችቱን ለማሳደግም በአመት አንድ ጊዜ «መዝገበ ቃላትን» ደግሞ ያነብ ነበር::

ቻርለስ ጄምሶ ፎክስ የአነጋገር ዘይቤውን ለማሻሻል የሼክስፒየርን ጽሁፎች ድምፁን ከፍ አድርጎ ያነብ ነበር:: ግላድስቶን አጠናኑን «በገዳም ውስጥ ያለ ፀጥታና ሰላም» በማለት ይጠራው ነበር:: በዚህም ሁኔታ ውስጥ 15,000 መፅሐፎችን አንብቧል:: ለዚህም የሴይንት አውግስቲንን፣ የቢሾፕ በትለርን፣ የዳንቴን፣ የአሪስቶትልን፣ እና የሆሜርን መፅሐፍ ማንበቡ እጅግ እንደጠቀመው ገልፆ ነበር:: «ኤሊያድ» እና» «ኦዲሴይ» በውስጡ ከፍተኛ የሆነ ስሜት የሚፈጥሩ መፅሃፎች መሆናቸውን ተናግሯል:: በመሆኑም ስድስት መፅሃፎችን በሆሜራዊ ግጥሞች እና በሆሜራዊ ወቅቶች ላይ ፅፏል:: ግን አሁን ምርጥ ፀሐፊዎች ናቸው የተባሉትን በመጀመሪያ ላይ ሳናይ በመጨረሻ ልናነሳ ነው እነማን ናቸው?

ሰር ሄነሪ ኧርቪንግ ምርጥና መነበብ የሚገባቸው መፅሐፎች ናቸው የሚላቸውን መቶ መፅሃፎች እንዲጠቅስ በተጠየቀ ጊዜ እንዲህ የሚል መልስ ነበር የሰጠው፡- «ከመቶዎቹ መፅሃፎች በፊት የሁለቱን መፅሃፎች ይዘት ማንበብና ማወቅ ነው ድንቅ የሚሆነው . . . መፅሃፍ ቅዱስን እና ሼክስፒየርን» ሰር ሄነሪ ትክክል ነበር:: ከእነዚህ ከሁለቱ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፏፏቴ ምንጮች ጠጡ:: በተደጋጋሚ ለረጅም ጊዜ ጠጡ:: ማታ የምታነቡትን ጋዜጣ ወደዚያ ወርውሩና ይህን በሉ «ሼክስፒር በዚህ ምሽት ወደ እኔ ናና. . . ስለሮሚዎና ፍቅረኛው ጁሊየት አውራልኝ፣ ስለማክቤዝና ምኞቱም»

## ተፈፀመ



Scanned with CamScanner

# በቅርብ ቀን የወጡሲያነቧቸው የሚገቡ አጋዥ የሳይኮሎጂና ልቦለድ መጽሐፍት

- የፍቅር ትንሣኤ ስመጥር በሆነችው በዳንኤላ ስቲል ተጽፎ በአዳነ ቸኮል የተተረጎመ ምርጥ የፍቅር መጽሐፍ
- ወለላ ምርጥ ምርጥ አባባሎችና ጥቅሶች ከመሪዎች ፣ ከሙሁራን፣ ከፈላስፎች አንደበት ከአሰፋ ሽፈራው
- የመኖር ክህሎት በዴል ካርኔጊ ተጽፎ በፋንታሁን ኃይሌ የተተረጎመ ምርጥ የሳይኮሎጂ መጽሐፍ
- የንቃት ጥበብ Try It my way (እሾ) ትርጉም በዳዊት መሳኩ
- የአማልክትና የጀግኖች አፈ-ታሪክ (Mythology) በኢዲዝ ሃሚልተን ተጽፎ በአዳነ ቸኮል የተተረጎመ
- *Top Chemistry Grade 7-8* በቅርብ ቀን የወጣ ለማንኛው ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ተማሪ ላለ የሚጠቅም አጋዥ መጽሐፍ በሰይድ ይመር (MSc) የተዘጋጀ
- *Top Matmatics Grade 7-8* በቅርብ ቀን የወጣ ለማንኛው ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ላለ ተማሪ የሚጠቅም አጋዥ መጽሐፍ በሰይድ ይመር (MSc) የተዘጋጀ

# እንኳን ደህና መጡ!!

# ወደ ብሔረ መፃሕፍት ዘ-ኢትዮጵያ📚

# @ETHIO_PDF_BOOKS

አዳዲስ መፅሐፍትን በPDF
የሚያገኙበት ምርጥ የቴሌግራም ቻናል ነው፡

እናም ቤተሰብ ካልሆኑ ቤተሰብ ይሁኑ! ብዙ መፅሐፍት
እያመለጦ ነው ይፍጠኑ!





Scanned with CamScanner